ለቱንም ፡ ድሪዎች ፡ ጫፎች ፡ በሁለቱ ፡ ፈር
ጦች ፡ ውስጥ ፡ አግብተው ፡ በኤፉዱ ፡ ጫንቃ
፲፱ ዎች ፡ ላይ ፡ በፊታቸው ፡ አደረጉ ። ሁለቱንም ፡
የወርቅ ፡ ቀለበቶች ፡ ሠሩ ፡ እነርሱንም ፡ በኤ
ፉዱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በለው ፡ በደረቱ ፡ ኪስ ፡ በሁ
፳ ለት ፡ ጫፎቹ ፡ ላይ ፡ አደረጉአቸው ። ደግሞም ፡
ሁለት ፡ የወርቅ ፡ ቀለበቶች ፡ ሠሩ ፡ በኤፉዱም ፡
ፊት ፡ ከጫንቃዎች ፡ በታች ፡ በብልሃት ፡ ከተ
ጠለፈ ፡ ከኤፉዱ ፡ ቋድ ፡ በላይ ፡ በመያዣው ፡
፳፩ አጠገብ ፡ አደረጉአቸው ። የደረቱ ፡ ኪስ ፡ በብ
ልሃት ፡ ከተጠለፈው ፡ ከኤፉዱ ፡ ቋድ ፡ በላይ ፡
እንዲሆን ፡ ከኤፉዱም ፡ እንዳይለይ ፡ የደረቱን ፡
ኪስ ፡ ከቀለበቶቹ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ኤፉዱ ፡ ቀለበ
ቶች ፡ በሰማያዊ ፡ ፈትል ፡ አሰሩት ።
፳፪ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ የኤ
ፉዱን ፡ ቀሚስ ፡ ሞላውን ፡ በሸማኔ ፡ ሥራ ፡ ሰማ
፳፫ ያዊ ፡ አደረገው ። በቀሚሱም ፡ መካከል ፡ አን
ገትጌ ፡ ነበረ ፡ እንዳይቀደድም ፡ እንደ ፡ ጥሩር ፡
የተሠራ ፡ ጥልፍ ፡ በአንገትጌው ፡ ዙሪያ ፡ ነበረ ።
፳፬ በቀሚሱም ፡ ታችኛ ፡ ዘርፍ ፡ ከሰማያዊ ፡ ከሐ
ምራዊም ፡ ከቀይም ፡ ግምጃ ፡ ከተፈተለ ፡ በፍ
፳፭ ታም ፡ ሮማኖች ፡ አደረገ ። ከጥሩ ፡ ወርቅም ፡
ሻሹራዎችን ፡ ሠሩ ፡ ሻሹራዎቹንም ፡ ከሮማ
ኖች ፡ መካከል ፡ በቀሚሱ ፡ ዘርፍ ፡ ዙሪያ ፡ አደ
፳፮ ረጉ ። በቀሚሱ ፡ ዘርፍ ፡ ዙሪያ ፡ ሻሹራንና ፡
ሮማንን ፡ ሻሹራንና ፡ ሮማንን ፡ ለማገልገል ፡
አደረጉ ።
፳፯ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡
እንደ ፡ ሸማኔ ፡ ሥራ ፡ ከጥሩ ፡ በፍታ ፡ ለአሮንና ፡
፳፰ ለልጆቹ ፡ ሸሚዞችን ፡ ከጥሩ ፡ በፍታም ፡ መጠ
ምጠሚያውን ፡ ከጥሩ ፡ በፍታም ፡ መልካሞቹን ፡
ቆቦች ፡ ከተፈተለም ፡ ከጥሩ ፡ በፍታ ፡ የእግር ፡
፳፱ ሱሪዎችን ፡ ከተፈተለም ፡ ከጥሩ ፡ በፍታ ፡ ከሰ
ማያዊም ፡ ከሐምራዊም ፡ ከቀይም ፡ ግምጃ ፡ በጥ
ልፍ ፡ አሠራር ፡ የተሠራ ፡ መታጠቂያውን ፡ አደ
ረጉ ።
፴ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡
ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ የተቀደሰውን ፡ የአክሊል ፡ ምል
ክት ፡ ሠሩ ፡ በእርሱም ፡ እንደ ፡ ማኅተም ፡
ቅርጽ ፡ አድርገው ፡ — ቅድስና ፡ ለእግዚአብ
፴፩ ሔር ፡ የሚል ፡ ጻፉበት ። በመጠምጠሚያውም ፡
ላይ ፡ ያንጠለጥሉት ፡ ዘንድ ፡ ሰማያዊውን ፡
ፈትል ፡ አሰሩበት ።
፴፪ እንዲሁም ፡ የመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ የማደሪ
ያው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ተጨረሰ ። እግዚአብሔ
ርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ሁሉ ፡ የእስራኤል ፡
፴፫ ልጆች ፡ አደረጉ ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ። ማደሪ
ያውንም ፡ ድንኳኑንም ፡ ዕቃውንም ፡ ሁሉ ፡
ወደ ፡ ሙሴ ፡ አመጡ ፡ መያዣዎቹን ፡ ሰንጋቹን ፡
መወርወሪያዎቹን ፡ ምሰሶቹንም ፡ እግሮቹንም ፡
፴፬ ከቀይ ፡ ከአውራ ፡ በግ ፡ ቁርበትም ፡ የተሠራ ፡
መደረቢያ ፡ ከአቆስጣ ፡ ቁርበትም ፡ የተሠራ ፡
፴፭ መደረቢያ ፡ የሚሸፍነውንም ፡ መጋረጃ ፡ የምስ
ክሩንም ፡ ታቦት ፡ መሎጊያዎቹንም ፡ የስርየት ፡
መክደኛውንም ፡ ገበታውንም ፡ ዕቃውንም ፡ ፴፮
ሁሉ ፡ የገጹንም ፡ ኅብስት ፡ ጥሩውንም ፡ መቅ
ረዝ ፡ መብራቶቹንም ፡ በተራ ፡ የሚሆኑትንም ፡
ቀንዲሎች ፡ ዕቃውንም ፡ ሁሉ ፡ የመብራቱ
ንም ፡ ዘይት ፡ የወርቁንም ፡ መሠዊያ ፡ የቅብ ፴፯
ዓቱንም ፡ ዘይት ፡ ጣፋጩንም ፡ ዕጣን ፡ የድን
ኳኑንም ፡ ደጃፍ ፡ መጋረጃ ፡ የናሱንም ፡ መሠ ፴፱
ዊያ ፡ የናሱንም ፡ መክታ ፡ መሎጊያዎቹንም ፡
ዕቃውንም ፡ ሁሉ ፡ የመታጠቢያውን ፡ ሰንጋ ፡
መቀመጫውንም ፡ የአደባባዩንም ፡ መጋረጃዎች ፡ ፴፰
ምሰሶቹንም ፡ እግሮቹንም ፡ የአደባባዩንም ፡
ደጃፍ ፡ መጋረጃ ፡ አውታሮቹንም ፡ ካስማዎቹ
ንም ፡ ለመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ለማደሪያው ፡ ማገ
ልገያ ፡ የሚሆኑን ፡ ዕቃዎች ፡ ሁሉ ፡ በመቅደስ ፴፱
ውስጥ ፡ ለማገልገል ፡ በብልሃት ፡ የተሠሩትን ፡
ልብሶች ፡ በክህነትም ፡ ያገለግሉበት ፡ ዘንድ ፡
የተቀደሱትን ፡ የካህኑን ፡ የአሮንን ፡ ልብሶች ፡
የልጆቹንም ፡ ልብሶች ፡ አመጡ ። እግዚአብሔር ፡ ፴፱
ሙሴን ፡ እንዳዘዘ ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁ ፡ የእስራ
ኤል ፡ ልጆች ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ ሠሩ ። ሙሴም ፡
ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ አየ ፡ እነሆም ፡ አድርገውት ፡
ነበር ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ እንዲሁ ፡
አድርገውት ፡ ነበር ፤ ሙሴም ፡ ባረካቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፴ ።

፩ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡
ተናገረው ፡ — ከመጀመሪያው ፡ ወር ፡ በፊተኛው ፡
፪ ቀን ፡ የመገናኛውን ፡ ድንኳን ፡ ማደሪያ ፡ ትተክ
ላለህ ። በእርሱም ፡ ውስጥ ፡ የምስክሩን ፡ ታቦት ፡
፫ ታኖራለህ ፡ ታቦቱንም ፡ በመጋረጃ ፡ ትጋርዳ
ለህ ። ገበታውንም ፡ አግብተህ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡
፬ የሚኖረውን ፡ ዕቃ ፡ ታስገዳለህ ፡ መቅረዙንም ፡
አግብተህ ፡ ቀንዲሎቹን ፡ ትለኮሳለህ ። ለዕጣ ፡
፭ ንም ፡ የሚሆነውን ፡ የወርቅ ፡ መሠዊያ ፡ በምስ
ክሩ ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ ታኖራለህ ፡ በማደሪያውም ፡
ደጃፍ ፡ ፊት ፡ መጋረጃውን ፡ ትጋርዳለህ ። ለሚ
፮ ቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የሚሆነውንም ፡ መሠዊያ ፡
በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ በማደሪያው ፡ ደጅ ፡ ፊት ፡
ታኖረዋለህ ። የመታጠቢያውን ፡ ሰንጋ ፡ በመ
፯ ገናኛው ፡ ድንኳንና ፡ በመሠዊያው ፡ መካከል ፡
አኑረህ ፡ ውኃ ፡ ትጨምርበታለህ ። በዙሪያ
፰ ውም ፡ አደባባዩን ፡ ትተክላለህ ፡ የአደባባዩ
ንም ፡ ደጃፍ ፡ መጋረጃ ፡ ትዘረጋለህ ። የቅብዓ
፱ ቱንም ፡ ዘይት ፡ ወስደህ ፡ ማደሪያውን ፡ በእር
ሱም ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ትቀባለህ ፡ እርሱንም ፡
ዕቃውንም ፡ ሁሉ ፡ ትቀድሳለህ ፡ ቅዱስም ፡ ይሆ
ናል ። ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የሚሆነው
፱ ንም ፡ መሠዊያ ፡ ዕቃውንም ፡ ሁሉ ፡ ትቀባዋለህ ፡
መሠዊያውንም ፡ ትቀድሳለህ ፡ መሠዊያውም ፡
ቅድስት ፡ ቅዱሳን ፡ ይሆናል ። የመታጠቢያውን ፡ ፲፩
ሰንጋ ፡ መቀመጫውን ፡ ቀብተህ ፡ ትቀድሳለህ ።
፲፪ አሮንንና ፡ ልጆቹንም ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድን
ኳን ፡ ደጃፍ ፡ አቅርበህ ፡ በውኃ ፡ ታጥባቸዋለህ ።
፲፫ የተቀደሰውንም ፡ ልብስ ፡ አሮንን ፡ ታለብሰዋ

ለህ ፡ በክህነትም ፡ ያገለግለኝ ፡ ዘንድ ፡ ቀብተህ ፡
፲፬ ትቀድሰዋለህ ። ልጆቹንም ፡ አቅርበህ ፡ ሸሚ
ዞችን ፡ ታለብሳቸዋለህ ፡ በክህነትም ፡ ያገለግ
ሉኝ ፡ ዘንድ ፡ አባታቸውን ፡ እንደ ፡ ቀባህ ፡ ትቀ
ባቸዋለህ ፡ መቀባታቸውም ፡ ለልጅ ፡ ልጃቸው ፡
ለዘላለም ፡ ክህነት ፡ ይሆንላቸዋል ። ሙሴም ፡
፲፭ እንዲሁ ፡ አደረገ ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡
ሁሉ ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።
፲፮ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡ በፊ
ተኛው ፡ ወር ፡ በመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ ማደሪ
፲፯ ያው ፡ ተተከለ ። እግዚአብሔርም ፡ እንዳዘ
ዘው ፡ ሙሴ ፡ ማደሪያውን ፡ ተከለ ፡ እግሮቹንም ፡
አኖረ ፡ ሳንቆቹንም ፡ አቆመ ፡ መወርወሪያዎ
ቹንም ፡ አደረገባቸው ፡ ምሰሶቹንም ፡ አቆመ ።
፲፰ ድንኳኑንም ፡ በማደሪያው ፡ ላይ ፡ ዘረጋ ፡ የድን
ኳኑን ፡ መደረቢያ ፡ በላዩ ፡ አደረገበት ።
፲፱ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ጽላ
ቱን ፡ ወስዶ ፡ በታቦቱ ፡ ውስጥ ፡ አኖረው ፡ መሎ
ጊያዎቹን ፡ በታቦቱ ፡ ዘንድ ፡ አደረገ ፡ የስርየት ፡
መክደኛውንም ፡ በታቦቱ ፡ ላይ ፡ አኖረው ፡
ታቦቱን ፡ ወደ ፡ ማደሪያው ፡ አገባ ፡ የሚሸፍነ
ውንም ፡ መጋረጃ ፡ አድርጎ ፡ የምስክሩን ፡ ታቦት ፡
ሸፈነ ።
፳ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ገበ
ታውን ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ከመጋ
ረጃው ፡ ውጭ ፡ በማደሪያው ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡
፳፩ አኖረው ፡ እንጀራውን ፡ በላዩ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ አሰናዳ ።
፳፪ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ መቅ
ረዙን ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ በገበ
ታው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በማደሪያው ፡ በደቡብ ፡
በኩል ፡ አኖረ ፡ ቀንዲሎቹን ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ለኰሰ ።
፳፫ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ የወር

ዘሌዋውያን ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ እግዚአብሔርም ፡ ከመገናኛው ፡ ድንኳን ፡
ውስጥ ፡ ሙሴን ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተና
ገረው ፡ — ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡
፪ንገራቸው ፡ — ከእናንተ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡
ለእግዚአብሔር ፡ መባ ፡ ሲያቀርብ ፡ መባችሁን ፡
ከእንስሳ ፡ ወገን ፡ ከላሞች ፡ ወይም ፡ ከበጎች ፡
ታቀርባላችሁ ።
፫ መበውም ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ከላ
ሞች ፡ መንጋ ፡ ቢሆን ፡ ነውር ፡ የሌለበትን ፡
ተባቱን ፡ ያቀርባል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡
እንዲሠምር ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡
፬ ፊት ፡ ያቀርበዋል ። እጁንም ፡ በሚቃጠለው ፡
መሥዋዕት ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይጭናል ፤ ያስተሰርይ
ለትም ፡ ዘንድ ፡ የሠመረ ፡ ይሆንለታል ። በሬ
ውንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያርደዋል ፡ የአ
ሮንም ፡ ልጆች ፡ ካህናቱ ፡ ደሙን ፡ ያቀርባሉ ፡
ደሙንም ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ፊት ፡
ባለው ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ይረ
ጨታል ። የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡
፮ ይገፍፈዋል ፡ በየብልቱም ፡ ይቈርጠዋል ። የካ
፯ ህኑም ፡ የአሮን ፡ ልጆች ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡
እሳት ፡ ያነድዳሉ ፡ በእሳቱም ፡ ላይ ፡ እንጨት ፡
ይደረድራሉ ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ካህናቱ ፡
፰ የተቈረጠውን ፡ ብልቶች ፡ ራሱንም ፡ ስቡንም ፡
በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ በእሳቱ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡
በእንጨቱ ፡ ላይ ፡ ይረበርቡታል ። የሆድ ፡ ዕቃ
፱ ውንና ፡ እግሮቹን ፡ ግን ፡ በውኃ ፡ ያጥባል ፡
ካህኑም ፡ ሁሉን ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡

የእሳት ፡ ቍርባን ፡ አድርጎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲሆን ፡ በመሠዊ
ያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ።
፲ ቍርባኑም ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ከበ
ጎች ፡ ወይም ፡ ከፍየሎች ፡ ቢሆን ፥ ነውር ፡ የሌ
፲፩ ለበትን ፡ ተባቱን ፡ ያቀርበዋል ። በመሠዊያ
ውም ፡ አጠገብ ፡ በሰሜን ፡ ወገን ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ፊት ፡ ያርደዋል ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡
ካህናቱ ፡ ደሙን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ በዙ
፲፪ ሪያው ፡ ይረጨታል ። በየብልቱም ፡ ራሱ
ንም ፡ ስቡንም ፡ ያቈርጠዋል ፤ ካህኑም ፡ በመ
ሠዊያው ፡ ላይ ፡ በእሳቱ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ በእን
፲፫ ጨቱ ፡ ላይ ፡ ያረበርበዋል ፤ የሆድ ፡ ዕቃው
ንና ፡ እግሮቹን ፡ ግን ፡ በውኃ ፡ ያጥባል ። ካህ
ኑም ፡ ሁሉን ፡ አቅርቦ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡
ያቃጥለዋል ፤ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የእ
ሳት ፡ ቍርባን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ ነው ።
፲፬ ለእግዚአብሔርም ፡ የሚቀርበው ፡ ቍርባን ፡
የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ከወፎች ፡ ቢሆን ፥
ቍርባኑን ፡ ከዋኖስ ፡ ወይም ፡ ከርግብ ፡ ያቀር
፲፭ በል ። ካህኑም ፡ ወደ ፡ መሠዊያው ፡ ያቀርብ
ዋል ፥ ራሱንም ፡ ይቈለምመዋል ፥ በመሠዊያ
ውም ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ። ደሙም ፡ በመሠ
፲፮ ዊያው ፡ አጠገብ ፡ ይንጠፈጠፋል ፤ የሆድ ፡
ዕቃውንም ፡ ከላባዎች ፡ ጋር ፡ ለይቶ ፡ በመሠዊ
ያው ፡ አጠገብ ፡ በምሥራቅ ፡ ወገን ፡ በአመዱ ፡
፲፯ ስፍራ ፡ ይጥለዋል ፤ በክንፎቹም ፡ ይቀድደዋል ፥
ነገር ፡ ግን ፡ አይከፍለውም ። ካህኑም ፡ በመ
ሠዊያው ፡ ላይ ፡ በእሳቱ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ በእ
ንጨቱ ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ፤ የሚቃጠል ፡
መሥዋዕት ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ዘንድ ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የእህል ፡ ቍርባን ፡ ለእግ
ዚአብሔር ፡ ሲያቀርብ ፡ ቍርባኑ ፡ ከመልካም ፡
ዱቄት ፡ ይሁን ፤ ዘይትም ፡ ያፈስስበታል ፥ ዕጣ
፪ ንም ፡ ይጨምርበታል ፥ ወደ ፡ አሮንም ፡ ልጆች ፡
ወደ ፡ ካህናቱ ፡ ያመጣዋል ፤ ከመልካም ፡ ዱቄ
ቱና ፡ ከዘይቱም ፡ አንድ ፡ እፍኝ ፡ ሙሉና ፡ ዕጣ
ኑን ፡ ሁሉ ፡ ወስዶ ፡ ካህኑ ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲሆን ፡ ለመ
ታሰቢያ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ።
፫ ከእህሉም ፡ ቍርባን ፡ የተረፈው ፡ ለአሮንና ፡
ለልጆቹ ፡ ይሆናል ፤ ይህም ፡ ለእግዚአብሔር ፡
የሚሆን ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡
ነው ።
፬ በእቶን ፡ የተጋገረውን ፡ የእህል ፡ ቍርባን ፡
ስታቀርብ ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ የመልካም ፡
ዱቄት ፡ የቀጣ ፡ እንጐቾ ፡ ወይም ፡ በዘይት ፡
፭ የተቀባ ፡ ስስ ፡ ቂጣ ፡ ይሁን ። ቍርባንህም ፡
በምጣድ ፡ የተጋገረ ፡ የእህል ፡ ቍርባን ፡ ቢሆን ፥
በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ የመልካም ፡ ዱቄት ፡
ቂጣ ፡ ይሁን ። ቈርሰህም ፡ ዘይት ፡ ታፈስስበታ
፮ ለህ ፡ የእህል ፡ ቍርባን ፡ ነው ። ቍርባንህም ፡
በመቀቀያ ፡ የበሰለ ፡ የእህል ፡ ቍርባን ፡ ቢሆን ፥
ዘይት ፡ የገባበት ፡ ከመልካም ፡ ዱቄት ፡ የተ
፯ ደረገ ፡ ይሁን ። ከዚህም ፡ የተደረገውን ፡ የእ
ህል ፡ ቍርባን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታመጣ
ለህ ፤ ለካህኑም ፡ ይሰጣል ፥ እርሱም ፡ ወደ ፡
መሠዊያው ፡ ያቀርበዋል ። ካህኑም ፡ ከእህሉ ፡
፰ ቍርባን ፡ መታሰቢያውን ፡ አንሥቶ ፡ የእሳት ፡
ቍርባን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡
እንዲሆን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ።
ከእህሉም ፡ ቍርባን ፡ የተረፈው ፡ ለአሮንና ፡
፱ ለልጆቹ ፡ ይሆናል ፤ ይህም ፡ ለእግዚአብሔር ፡
የሚሆን ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡
ነው ።
እርሾ ፡ ያለበት ፡ ነገር ፡ ማርም ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ይሆን ፤ ዘንድ ፡ አታ
ቀርቡምና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የምታቀርቡት ፡
የእህል ፡ ቍርባን ፡ ሁሉ ፡ እርሾ ፡ አይሁንበት ።
፲፩ እንዚህንም ፡ የበኩራት ፡ ቍርባን ፡ አድርጋ
ችሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ታቀርባላችሁ ፤ እንደ ፡
ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ ግን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አይ
ቃጠሉም ። የምታቀርበውን ፡ የእህል ፡ ቍር
፲፪ ባን ፡ ሁሉ ፡ በጨው ፡ ታጣፍጠዋለህ ፤ የአምላ
ክህንም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ጨው ፡ ከእህል ፡ ቍር
ባንህ ፡ አታጐድልም ፤ በቍርባንህ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡
ጨው ፡ ታቀርበለህ ።
ከበኩራትም ፡ የእህል ፡ ቍርባን ፡ ለእግዚአ
ብሔር ፡ ብታቀርብ ፡ ስለዚህ ፡ ቍርባን ፡ በእሳት ፡
የተጠበሰና ፡ የተፈተገ ፡ የእህል ፡ እሸት ፡ ታቀ
ርባለህ ። ዘይትም ፡ ታፈስስበታለህ ፤ ዕጣንም ፡
ትጨምርበታለህ ፤ የእህል ፡ ቍርባን ፡ ነው ። ከዘ
ኑም ፡ ከተፈተገው ፡ እህል ፡ ከዘይቱም ፡ ወስዶ ፡
ከዕጣኑ ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ መታሰቢያውን ፡ ያቃጥ
ላል ፤ ይህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእሳት ፡ ቍር
ባን ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ቍርባኑም ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ቢሆን ፤ ፩
ከላሞች ፡ ሥንጋ ፡ ተባት ፡ ወይም ፡ አንስት ፡
ቢያቀርብ ፤ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ፊት ፡ ያቅርብ ። እጁንም ፡ ለቍርባን ፡ ፪
በቀረበው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይጭናል ፤ በመገናኛ
ውም ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ አጠገብ ፡ ያርደዋል ፤
የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ካህናቱ ፡ ደሙን ፡ በመሠ
ዊያው ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ይረጩታል ። ከደ ፫
ኅንነቱም ፡ መሥዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእ
ሳት ፡ ቍርባን ፡ አድርጎ ፡ ያቀርበል ፤ የሆድ ፡
ዕቃውን ፡ የሚሸፍነውን ፡ ስብ ፡ በሆድ ፡ ዕቃ
ውም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ስብ ፡ ሁሉ ፥ ሁለቱን ፡ ፬
ኵላሊቶች ፥ በእነርሱም ፡ ላይና ፡ በጎድኑ ፡ አጠ
ገብ ፡ ያለውን ፡ ስብ ፥ በጉበቱም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡
መረብ ፡ ከኵላሊቶች ፡ ጋር ፡ ይወስዳል ። ካህ
ኑም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ፤ በእ
ሳት ፡ ላይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተደረገ ፡ የቍር
ባን ፡ መብል ፡ ነው ።
ቍርባኑም ፡ ፍየል ፡ ቢሆን ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ያቀርበዋል ፤ እጁንም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡
ይጭንበታል ፥ በመገናኛውም ፡ ድንኳን ፡ ፊት ፡
ያርደዋል ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ደሙን ፡ በመ
ሠዊያው ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ይረጩታል ። ከእ
ርሱም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡
አድርጎ ፡ ያቀርበዋል ፤ ሆድ ፡ ዕቃውን ፡ የሚሸ
ፍነውን ፡ ስብ ፡ በሆድ ፡ ዕቃውም ፡ ላይ ፡ ያለ
ውን ፡ ስብ ፡ ሁሉ ፥ ሁለቱንም ፡ ኵላሊቶች ፥
በእነርሱም ፡ ላይና ፡ በጎድኑ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡
ስብ ፥ በጉበቱም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መረብ ፡ ከኵ
ላሊቶች ፡ ጋር ፡ ይወስዳል ። ካህኑም ፡ በመሠዊ
ያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ፤ በእሳት ፡ ላይ ፡ ጣፋጭ ፡
ሽታ ፡ እንዲሆን ፡ የተደረገ ፡ መብል ፡ ነው ። ስቡ ፡
ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነው ። ስብና ፡ ደም ፡
እንዳትበሉ ፡ በምትኖሩበት ፡ ሁሉ ፡ ለልጅ ፡
ልጃችሁ ፡ የዘላለም ፡ ሥርዓት ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተና
ገረው ፦ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡
ንገራቸው ፦ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሳያውቅ ፡
ኃጢአት ፡ ቢሠራ ፥ እግዚአብሔርም ፦ አት
ሥሩ ፡ ካላቸው ፡ ትእዛዛት ፡ አንዲቱን ፡ ቢተላ
ለፍ ፥ የተቀባውም ፡ ካህን ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡
በደል ፡ እንዲቈጠርባቸው ፡ ኃጢአት ፡ ቢሠራ ፥
ስለ ፡ ሠራው ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ነውር ፡ የሌለበት ፡
ወይፈን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለኃጢአት ፡ መሥ
ዋዕት ፡ ያቀርበዋል ። ወይፈኑንም ፡ ወደ ፡ መገ
ናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡
ያመጣዋል ፤ እጁንም ፡ በወይፈኑ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡
ጋር ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ በእሳቱ ፡ ላይ ፡ በሰው ፡
በእንጨቱ ፡ ላይ ፡ ያቃጥሉታል ፤ የእሳት ፡ ቍር
ባን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ ነው ።
ለእግዚአብሔርም ፡ ለደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡
የሚያቀርበው ፡ ቍርባኑ ፡ ከበጎች ፡ ተባት ፡
ወይም ፡ አንስት ፡ ቢሆን ፥ ነውር ፡ የሌለበትን ፡
ያቀርባል ። ለቍርባኑ ፡ ጠቦትን ፡ ቢያቀርብ ፡
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያቀርበዋል ፤ እጁንም ፡
ለቍርባን ፡ በቀረበው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይጭናል ፥
በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ፊት ፡ ያርደዋል ፤ የአ
ሮንም ፡ ልጆች ፡ ደሙን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡
በዙሪያው ፡ ይረጩታል ። ከደኅንነቱም ፡ መሥ
ዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡
አድርጎ ፡ ያቀርባል ፤ ስቡን ፥ እስከ ፡ ጅራባውም ፡
ድረስ ፡ የተቈረጠ ፡ ላቱን ፡ ሁሉ ፥ የሆድ ፡ ዕቃ
ውንም ፡ የሚሸፍነውን ፡ ስብ ፥ በሆድ ፡ ዕቃ
ውም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ስብ ፡ ሁሉ ፥ ሁለቱንም ፡
ኵላሊቶች ፥ በእነርሱም ፡ ላይና ፡ በጎድኑ ፡ አጠ
ገብ ፡ ያለውን ፡ ስብ ፥ በጉበቱም ፡ ላይ ፡ ያለ
ውን ፡ መረብ ፡ ከኵላሊቶች ፡ ጋር ፡ ይወስዳል ። ካህ
ኑም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ፤ በእ
ሳት ፡ ላይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተደረገ ፡ የቍር
ባን ፡ መብል ፡ ነው ።
ቍርባኑም ፡ ፍየል ፡ ቢሆን ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ያቀርበዋል ፤ እጁንም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡
ይጭንበታል ፥ በመገናኛውም ፡ ድንኳን ፡ ፊት ፡
ያርደዋል ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ደሙን ፡ በመ
ሠዊያው ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ይረጩታል ። ከእ
ርሱም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡
አድርጎ ፡ ያቀርበዋል ፤ ሆድ ፡ ዕቃውን ፡ የሚሸ
ፍነውን ፡ ስብ ፡ በሆድ ፡ ዕቃውም ፡ ላይ ፡ ያለ
ውን ፡ ስብ ፡ ሁሉ ፥ ሁለቱንም ፡ ኵላሊቶች ፥
በእነርሱም ፡ ላይና ፡ በጎድኑ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡
ስብ ፥ በጉበቱም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መረብ ፡ ከኵ
ላሊቶች ፡ ጋር ፡ ይወስዳል ። ካህኑም ፡ በመሠዊ
ያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ፤ በእሳት ፡ ላይ ፡ ጣፋጭ ፡
ሽታ ፡ እንዲሆን ፡ የተደረገ ፡ መብል ፡ ነው ። ስቡ ፡
ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነው ። ስብና ፡ ደም ፡
እንዳትበሉ ፡ በምትኖሩበት ፡ ሁሉ ፡ ለልጅ ፡
ልጃችሁ ፡ የዘላለም ፡ ሥርዓት ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተና
ገረው ፦ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡
ንገራቸው ፦ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሳያውቅ ፡
ኃጢአት ፡ ቢሠራ ፥ እግዚአብሔርም ፦ አት
ሥሩ ፡ ካላቸው ፡ ትእዛዛት ፡ አንዲቱን ፡ ቢተላ
ለፍ ፥ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ተጠያቂ ፡ ቢሆን ፡ ፩
ከብቱ ፡ ከሆነ ፡ ከሰዎች ፡ ተለይቶ ፡ ከሚ
ኖሩ ፡ ከብቶ ፡ ሴትዮ ፡ ወይስ ፡ ወንዴ ፡ ስለ ፡
ኃጢአቱ ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ለኃጢአት ፡ ስለ ፡ ሠራ ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ነውር ፡
ያለበት ፡ ሴትዮ ፡ ወይስ ፡ ወንዴ ፡ ከብቶ ፡
ከሆነ ፡ ከሰዎች ፡ ተለይቶ ፡ ከሚኖሩ ፡ ከብቶ ፡
ሴትዮ ፡ ወይስ ፡ ወንዴ ፡ ከብቶ ፡ ከሆነ ፡ ስለ ፡
ኃጢአቱ ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፡ ለኃጢአት ፡ ስለ ፡
ሠራ ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ነውር ፡ ያለበት ፡ ሴትዮ ፡
ወይስ ፡ ወንዴ ፡ ከብቶ ፡ ከሆነ ፡ ስለ ፡ ኃጢ
፲ አቱ ፡ ስለ ፡ ሠራ ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ነውር ፡
ያለበት ፡ ሴትዮ ፡ ወይስ ፡ ወንዴ ፡ ከብቶ ፡
ከሆነ ፡ ስለ ፡ ኃጢ
፲፩ አቱ ፡ ስለ ፡ ሠራ ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ነውር ፡
ያለበት ፡ ሴትዮ ፡ ወይስ ፡ ወንዴ ፡ ከብቶ ፡
ከሆነ ፡ ስለ ፡ ኃጢ
፲፪ አቱ ፡ ስለ ፡ ሠራ ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ነውር ፡
ያለበት ፡ ሴትዮ ፡ ወይስ ፡ ወንዴ ፡ ከብቶ ፡
ከሆነ ፡ ስለ ፡ ኃጢ
፲፫ አቱ ፡ ስለ ፡ ሠራ ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ነውር ፡
ያለበት ፡ ሴትዮ ፡ ወይስ ፡ ወንዴ ፡ ከብቶ ፡
ከሆነ ፡ ስለ ፡ ኃጢ
፲፬ አቱ ፡ ስለ ፡ ሠራ ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ነውር ፡
ያለበት ፡ ሴትዮ ፡ ወይስ ፡ ወንዴ ፡ ከብቶ ፡
ከሆነ ፡ ስለ ፡ ኃጢ
፲፭ አቱ ፡ ስለ ፡ ሠራ ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ነውር ፡
ያለበት ፡ ሴትዮ ፡ ወይስ ፡ ወንዴ ፡ ከብቶ ፡
ከሆነ ፡ ስለ ፡ ኃጢ
፲፮ አቱ ፡ ስለ ፡ ሠራ ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ነውር ፡
ያለበት ፡ ሴትዮ ፡ ወይስ ፡ ወንዴ ፡ ከብቶ ፡
ከሆነ ፡ ስለ ፡ ኃጢ
፲፯ አቱ ፡ ስለ ፡ ሠራ ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ነውር ፡
ያለበት ፡ ሴትዮ ፡ ወይስ ፡ ወንዴ ፡ ከብቶ ፡
ከሆነ ፡ ስለ ፡ ኃጢ
፲፰ አቱ ፡ ስለ ፡ ሠራ ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ነውር ፡
ያለበት ፡ ሴትዮ ፡ ወይስ ፡ ወንዴ ፡ ከብቶ ፡
ከሆነ ፡ ስለ ፡ ኃጢ
፲፱

ዘሌ ፡ ፡ ፡

ፈሪያ ፡ አሥረኛ ፡ ክፍል ፡ መልካሙን ፡ ዱቄት ፡ እኵሌታውን ፡ በጥዋት ፣ እኵሌታውንም ፡ በማታ ፡ ለዘወትር ፡ የእህል ፡ ቍርብን ፡ አድርገው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚያቀርቡት ፡ የአሮ
ፍ፩ ንና ፡ የልጆቹ ፡ ቍርብን ፡ ይህ ፡ ነው ። ከዘይት ፡ ጋር ፡ በምጣድ ፡ ላይ ፡ ይደረጋል ፤ ሲለወስ ፡ ታገ ባዋለህ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እን ዲሆን ፡ የእህሉን ፡ ቍርብን ፡ ቈራርሰህ ፡ ታቀር
ፍ፪ በዋለህ ። ከልጆቹም ፡ በአባቱ ፡ ፋንታ ፡ የተቀ ባው ፡ ካህን ፡ ያቀርበዋል ። ለዘላለም ፡ ሥር ዓት ፡ እንዲሆን ፡ ፈጽሞ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይቃ
ፍ፫ ጠላል ። ከካህኑም ፡ የሚያቀርበው ፡ የእህል ፡ ቍርብን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ይቃጠላል ፤ ከእርሱም ፡ አንዳች ፡ አይበላም ።

ፍ፬ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡
ፍ፭ ተናገረው ፦ አርጋንንና ፡ ልጆቹን ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ተናገራቸው ፦ የኃጢአት ፡ መሥዋ ዕት ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የሚቃጠል ፡ መሥዋ ዕት ፡ በሚታረድበት ፡ ስፍራ ፡ የኃጢአቱ ፡ መሥ ዋዕት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይታረዳል ፤
ፍ፮ እርሱ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ ነው ። ለኃጢአት ፡ የሚሠዋው ፡ ካህን ፡ ይበላዋል ፤ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ዙሪያ ፡ በለው ፡ አደባባይ ፡ በተቀደሰ ፡
ፍ፯ ስፍራ ፡ ይበላል ። ሥጋውን ፡ የሚነካ ፡ ሁሉ ፡ ቅዱስ ፡ ይሆናል ፤ ማናቸው ፡ ልብስ ፡ ደም ፡ ቢረ ጭበት ፡ የተረጨበትን ፡ በተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡
ፍ፰ ታጥበዋለህ ። የሚቀቀልበትም ፡ ሸክላ ፡ ይሰበ ራል ፤ በናስም ፡ ዕቃ ፡ ቢቀቀል ፡ ይፈገፈጋል ፥
ፍ፱ በውኃም ፡ ይለቀለቃል ። ከክህናት ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ወንድ ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱ ፡ ይበላል ፤ እርሱ ፡
ፍ፲ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ ለማስተስረያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ከደሙ ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድንኳን ፡ የሚገባው ፡ የኃጢ አት ፡ መሥዋዕት ፡ ሁሉ ፡ አይበላም ፡ በእሳት ፡ ይቃጠላል ።

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

፩ የበደል ፡ መሥዋዕት ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ፤
፪ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ ነው ። የሚቃጠለውን ፡ መሥ ዋዕት ፡ በሚያርዱበት ፡ ስፍራ ፡ የበደሉን ፡ መሥ ዋዕት ፡ ያርዱታል ፤ ደሙንም ፡ በመሠዊያው
፫ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ይረጨዋል ። ስቡንም ፡ ሁሉ ፡ ላቱንም ፡ የሆድ ፡ ዕቃውንም ፡ የሚሸፍነውን ፡
፬ ስብ ፡ ያቀርበዋል ። ሁለቱንም ፡ ኵላሊቶች ፥ በእነርሱም ፡ ላይና ፡ በጎድኑ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ስብ ፥ በጕበቱም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መረብ ፡ ከኵ
፭ ላሊቶቹ ፡ ጋር ፡ ይወስዳል ። ካህኑም ፡ ለእግዚ አብሔር ፡ የእሳት ፡ ቍርብን ፡ እንዲሆን ፡ በመሠ ዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ፤ እርሱ ፡ የበደል ፡
፮ መሥዋዕት ፡ ነው ። ከካህናት ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ወንድ ፡ ሁሉ ፡ ይበላዋል ፤ በተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡
፯ ይበሉታል ፤ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ ነው ። የኃጢ አት ፡ መሥዋዕት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዲሁ ፡ የበደል ፡ መሥዋዕት ፡ ነው ፤ ለሁለቱ ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ ነው ፤ በእርሱ ፡ የሚያስተሰርይ ፡ ካህን ፡ ይወስደዋል ።
፰ የማናቸውንም ፡ ሰው ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋ ዕት ፡ የሚያቀርብ ፡ ካህን ፡ ያቀረበው ፡ የሚቃ ጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ ቁርበት ፡ ለዚያው ፡ ካህን ፡
፱ ይሆናል ። በእቶን ፡ የተጋገረው ፡ የእህል ፡ ቍር ባን ፡ ሁሉ ፥ በመቀቀያም ፡ ወይም ፡ በምጣድ ፡ የበሰለው ፡ ሁሉ ፡ ለሚያቀርበው ፡ ካህን ፡ ይሆ
፲ ናል ። በዘይትም ፡ የተለወሰው ፡ ወይም ፡ የደ ረቀው ፡ የእህል ፡ ቍርብን ፡ ሁሉ ፡ ለአሮን ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ይሆናል ፤ ለሁሉም ፡ ይሆናል ።
፲፩ ሰው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚያቀርበው ፡ የደ ኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ። ለምስ
፲፪ ጋና ፡ ቢያቀርበው ፥ ከምስጋናው ፡ መሥዋዕት ፡ ጋር ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ የቂጣ ፡ እንጎቻ ፥ በዘ ይትም ፡ የተቀባ ፡ ስስ ፡ ቂጣ ፥ በዘይትም ፡ የተ ለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ ያቀርባል ። ለምስ
፲፫ ጋና ፡ የሚሆነውን ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፡ እርሾ ፡ ያለበትን ፡ ኅብስት ፡ ያቀ ርባል ። ከቍርብኑም ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
፲፬ የማንሣት ፡ ቍርብን ፡ እንዲሆን ፡ ከእነርሱ ፡ አን ዱን ፡ ያነሣል ። እርሱም ፡ የደኅንነትን ፡ መሥ ዋዕት ፡ ደም ፡ ለሚረጨው ፡ ካህን ፡ ይሆናል ።
፲፭ ለምስጋና ፡ የሚሆነው ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋ ዕት ፡ ሥጋ ፡ በሚቀርብበት ፡ ቀን ፡ ይበሉታል ፤ ከእርሱ ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ ምንም ፡ አያድርም ። የቍ
፲፮ ርባኑም ፡ መሥዋዕት ፡ የስእለት ፡ ወይም ፡ የፈ ቃድ ፡ ቢሆን ፥ መሥዋዕቱ ፡ በሚቀርብበት ፡ ቀን ፡ ይብሉት ፤ ከእርሱም ፡ የቀረውን ፡ በነጋው ፡ ይብ
፲፯ ሉት ፤ ከመሥዋዕቱም ፡ ሥጋ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ኛው ፡ ቀን ፡ የሚቆየው ፡ በእሳት ፡ ይቃጠላል ።
፲፰ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ከደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ሥጋ ፡ ቢበላ ፥ አይሠምርም ፤ ላቀረበው ፡ ሰው ፡ የተጠላ ፡ ይሆንበታል ፤ እንጂ ፡ ቍርብን ፡ ሆኖ ፡ አያቈጠርለትም ፤ ከእርሱም ፡ ቢበላ ፡ ኃጢአ
፲፱ ቱን ፡ ይሸከማል ።
ርኩስ ፡ ነገር ፡ የሚነካውን ፡ ሥጋ ፡ አይብሉት ፤ በእሳት ፡ ይቃጠል ። ንጹሕ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡
፳ ግን ፡ ከሥጋው ፡ ይብላ ። ሰውም ፡ የረከሰ ፡ ቢሆን ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ከሆነው ፡ ከደኅን ነት ፡ መሥዋዕት ፡ ሥጋ ፡ ቢበላ ፥ ያ ፡ ሰው ፡ ከሕ
፳፩ ዝቡ ፡ ተለይቶ ፡ ይጥፋ ። ማናቸውንም ፡ ርኩስ ፡ ነገር ፡ ቢነካ ፥ የሰውን ፡ ወይም ፡ የረከሰን ፡ እን ስሳ ፡ ወይም ፡ ሌላውን ፡ የተጠላ ፡ ርኩስን ፡ ቢነካ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ከሆነው ፡ ከደኅንነት ፡ መሥ ዋዕት ፡ ሥጋ ፡ ቢበላ ፥ ያ ፡ ሰው ፡ ከሕዝቡ ፡ ተለ
፳፪ ይቶ ፡ ይጥፋ ።
እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
፳፫ ተናገረው ፦ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ተናገራቸው ፦ የበሬ ፡ ወይም ፡ የበግ ፡ ወይም ፡ የፍየል ፡ ስብ ፡ ከቶ ፡ አትብሉ ። የሞ
፳፬ ተውን ፡ ስብ ፥ አውሬ ፡ የሰበረውንም ፡ ስብ ፡ ለሌላ ፡ ተግባር ፡ አድርጉት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከእርሱ ፡ ምንም ፡ አትብሉ ። ለእግዚአብሔር ፡ በእሳት ፡
፳፭ ከሚቀርበው ፡ ከእንስሳ ፡ ስብ ፡ የሚበላ ፡ ሁሉ ፥

ያ ፡ የበላ ፡ ሰው ፡ ከሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ተለ ይቶ ፡ ይጠፋልና ። በማደሪያዎቻችሁም ፡ ሁሉ ፡ የወፍ ፡ ወይም ፡ የእንስሳ ፡ ደም ፡ ቢሆን ፡ አት
፳፮ ብሉ ። ደም ፡ የሚበላ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ከሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ተለይቶ ፡ ይጥፋ ።
እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
፳፯ ተናገረው ፦ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ተናገራቸው ፦ ለእግዚአብሔር ፡ የደኅ ንነት ፡ መሥዋዕት ፡ የሚያቀርብ ፡ ሰው ፡ ቍር ባኑን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከደኅንነቱ ፡ መሥዋ ዕት ፡ ያመጣል ። የእርሱ ፡ እጆች ፡ ለእግዚአ ብሔር ፡ የእሳቱን ፡ ቍርብን ፡ ያመጣሉ ፤ ፍርም ባው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመወዝወዝ ፡ ቍርብን ፡ ይወዘውዝ ፤ ዘንድ ፡ ስቡንና ፡ ፍርም ባውን ፡ ያመጣል ። ከህኑም ፡ ስቡን ፡ በመሠዊ ያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥላል ፤ ፍርምባውም ፡ ለአሮ ንና ፡ ለልጆቹ ፡ ይሁን ። ከደኅንነት ፡ መሥዋዕ ታችሁ ፡ ቀኝ ፡ ወርቹን ፡ ለማንሣት ፡ ቍርብን ፡ እንዲሆን ፡ ለካህኑ ፡ ትሰጡታላችሁ ። ከአሮ ንም ፡ ልጆች ፡ የደኅንነትን ፡ መሥዋዕት ፡ ደሙ ንና ፡ ስቡን ፡ ለሚያቀርብ ፡ ለእርሱ ፡ ቀኝ ፡ ወርቹ ፡ እድል ፡ ፈንታው ፡ ይሆናል ። የሚወዘወዘውን ፡ ፍርምባና ፡ የሚነሣውን ፡ ወርች ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከደኅንነት ፡ መሥዋዕታቸው ፡ ወስጄ ፡ አለሁ ፥ ለካህኑ ፡ ለአሮንና ፡ ለልጆቹም ፡ ለዘላ ለም ፡ እድል ፡ ፈንታ ፡ እንዲሆን ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ ሰጥቼአቸዋለሁ ።
እግዚአብሔርን ፡ በክህነት ፡ ያገለግሉት ፡ ዘንድ ፡ በቀረባቸው ፡ ቀን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከሆነ ፡ ከአሳት ፡ ቍርብን ፡ የአሮንና ፡ የልጆቹ ፡ እድል ፡ ፈንታ ፡ ይህ ፡ ነው ። ለልጅ ፡ ልጃቸው ፡ ለዘላለም ፡ እድል ፡ ፈንታቸው ፡ እንዲሆን ፡ በቀባ ቸው ፡ ቀን ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ይሰጡአቸው ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘው ፡ ይህ ፡ ነው ። የሚቃጠል ፡ መሥዋዕትና ፡ የእህል ፡ ቍርብን ፥ የኃጢአትና ፡ የበደል ፡ መሥዋዕት ፥ የቅድስ ናና ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ በሲና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ቍር ባናቸውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያቀርቡ ፡ ዘንድ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ባዘዘ ፡ ጊዜ ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ለሙሴ ፡ ያዘዘው ፡ ይህ ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፰ ።

፩ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
፪ ተናገረው ፦ አርጋንን ፥ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ልጆ ቹን ፥ ልብሱንም ፥ የቅብዓቱንም ፡ ዘይት ፥ ለኃ ጢአት ፡ መሥዋዕትም ፡ የሆነውን ፡ ወይፈን ፥
፫ ሁለቱንም ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ የቂጣውንም ፡ እን ጀራ ፡ ሴማት ፡ ውሰድ ፡ ማኅበሩንም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ሰብስበ
፬ ቸው ። ሙሴም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ ፤ ማኅበሩ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ተሰበሰቡ ። ሙሴም ፡ ማኅበ
፭ ሩን ፦ እግዚአብሔር ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ ያዘ ዘው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አላቸው ።
ሙሴም ፡ አርጋንንና ፡ ልጆቹን ፡ አቀረበ ፥ በው
፮ ኃም ፡ አጠባቸው ። ሸሚዝም ፡ አለበሰው ፥
፯ በመታጠቂያም ፡ አስታጠቀው ፥ ቀሚስም ፡ አለ በሰው ፥ ኤፉድም ፡ ደረበለት ፥ በብልሃትም ፡ በተጠለፈ ፡ ቋድ ፡ አስታጠቀውና ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ አሰረው ። የደረት ፡ ኪስ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ አደረገ ፤
፰ በደረቱ ፡ ኪስም ፡ ውስጥ ፡ ኡሪምንና ፡ ቱሚ ምን ፡ አኖረበት ። እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡
፱ እንዳዘዘው ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ መጠምጠሚያውን ፡ አደረገ ፤ በመጠምጠሚያውም ፡ ላይ ፡ በፊቱ ፡ በኩል ፡ የተቀደሰውን ፡ አክሊል ፥ ቅጠል ፡ የሚ መስለውን ፡ የወርቅ ፡ ምልክት ፥ አደረገ ።
ሙሴም ፡ የቅብዓቱን ፡ ዘይት ፡ ወሰደ ፥ ማደ
፲ ሪያውንና ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ቀብቶ ፡ ቀደሳቸው ። ከእርሱም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡
፲፩ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ረጨ ፤ ይቀድሳቸውም ፡ ዘንድ ፡ መሠዊያውንና ፡ ዕቃውን ፡ ሁሉ ፥ የመታጠቢ ያውን ፡ ሰንና ፡ መቀመጫውን ፡ ቀባ ። ከቅብዓ
፲፪ ቱም ፡ ዘይት ፡ በአሮን ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አፈሰሰ ፥ ይቀድሰውም ፡ ዘንድ ፡ ቀባው ። እግዚአብሔ
፲፫ ርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ሙሴ ፡ የአሮንን ፡ ልጆች ፡ አቀረበ ፥ ቀሚሶችንም ፡ አለበሳቸው ፥ በመታጠቂያም ፡ አስታጠቃቸው ፥ ቆብም ፡ ደፋባቸው ።
የኃጢአትንም ፡ መሥዋዕት ፡ ወይፈን ፡ አቀ
፲፬ ረበ ፤ አሮንና ፡ ልጆቹም ፡ በኃጢአቱ ፡ መሥዋ ዕት ፡ ወይፈን ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ እጆቻቸውን ፡ ጫኑ ።
፲፭ አረደውም ፡ ሙሴም ፡ ደሙን ፡ ወስዶ ፡ በጣቱ ፡ የመሠዊያውን ፡ ቀንዶች ፡ ዙሪያ ፡ ቀባ ፥ መሠ ዊያውንም ፡ አነጻው ፡ ደሙንም ፡ ከመሠዊ ያው ፡ በታች ፡ አፈሰሰው ፥ ያስተሰርይለትም ፡
፲፮ ዘንድ ፡ ቀደሰው ። በሆድ ፡ ዕቃውም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ስብ ፡ ሁሉ ፥ የጕበቱንም ፡ መረብ ፥ ሁለቱንም ፡ ኵላሊቶች ፡ ስባቸውንም ፡ ወሰደ ፤ ሙሴም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አቃጠለው ።
፲፯ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ወይ ፈኑን ፥ ቁርበቱንም ፥ ሥጋውንም ፥ ፈርሱ ንም ፡ ከሰፈሩ ፡ ውጭ ፡ በእሳት ፡ አቃጠለ ።
፲፰ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕትም ፡ የሚሆን ፡ አውራ ፡ በግ ፡ አቀረበ ፤ አሮንና ፡ ልጆቹም ፡ በአውራው ፡ በግ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ እጆቻቸውን ፡
፲፱ ጫኑ ። አረደውም ፡ ሙሴም ፡ ደሙን ፡ በመ ሠዊያው ፡ ዙሪያ ፡ ረጨው ። አውራውንም ፡
፳ በግ ፡ በየብልቱ ፡ ቈረጠ ፡ ሙሴም ፡ ጭንቅላ ቱን ፡ ብልቶቹንም ፡ ስቡንም ፡ አቃጠለ ። የሆድ ፡
፳፩ ዕቃውንና ፡ እግሮቹንም ፡ በውኃ ፡ አጠበ ፤ ሙሴም ፡ አውራውን ፡ በግ ፡ ሁሉ ፡ በመሠዊ ያው ፡ ላይ ፡ አቃጠለው ፡ ይህ ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲሆን ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ነበረ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ለእግዚ አብሔር ፡ የእሳት ፡ ቍርብን ፡ ነበረ ።
ለቅድስናም ፡ የሚሆነውን ፡ ሁለተኛውን ፡
፳፪ አውራ ፡ በግ ፡ አቀረበ ፤ አሮንና ፡ ልጆቹም ፡

በአውራው ፡ በግ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ እጆቻቸውን ፡
ጫኑ ። አረደውም ፡ ሙሴም ፡ ከደሙ ፡ ወስዶ ፡
የአሮንን ፡ የቀኝ ፡ ጆሮውን ፡ ጫፍ ፡ የቀኝ ፡
እጁንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ የቀኝ ፡ እግሩንም ፡
አውራ ፡ ጣት ፡ አስነካው ። የአሮንንም ፡ ልጆች ፡
አቀረበ ፡ ሙሴም ፡ የቀኝ ፡ ጆሮአቸውን ፡ ጫፍ ፡
የቀኝ ፡ እጃቸውንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ የቀኝ ፡
እግራቸውንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ ከደሙ ፡ አስነካ ፡
ሙሴም ፡ ደሙን ፡ በመሠዊያው ፡ ዙሪያ ፡ ረጨ ።
ስቡንና ፡ ላቱን ፡ ፡ በሆድ ፡ ዕቃውም ፡ ላይ ፡ ያለ
ውን ፡ ስብ ፡ ሁሉ ፡ የጕበቱንም ፡ መረብ ፡ ሁለ
ቱንም ፡ ኵላሊቶች ፡ ስባቸውንም ፡ ቀኝ ፡ ወር
ቹንም ፡ ወሰደ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ከለው ፡
ከቂጣው ፡ እንጀራ ፡ ሌማት ፡ አንድ ፡ የቂጣ ፡
እንጐቻ ፡ አንድም ፡ የዘይት ፡ እንጀራ ፡ አን
ድም ፡ ስስ ፡ ቂጣ ፡ ወስዶ ፡ በስቡና ፡ በቀኝ ፡
ወርቹ ፡ ላይ ፡ አኖራቸው ። ሁሉንም ፡ በእሮ
ንና ፡ በልጆቹ ፡ እጆች ፡ ላይ ፡ አደረገ ፡ በእግ
ዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ለመወዝወዝ ፡ ቀኑርበን ፡
ወዘወዛቸው ። ሙሴም ፡ ከእጃቸው ፡ ተቀ
ብሎ ፡ በመሠዊያው ፡ በሚቃጠለው ፡ መሥዋ
ዕት ፡ ላይ ፡ አቃጠለው ፡ የጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ መቀ
ደሻ ፡ ነበረ ። እርሱም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእ
ሳት ፡ ቀኑርበን ፡ ነበረ ። ሙሴም ፡ ፍርምባውን ፡
ወስዶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመወዝወዝ ፡
ቀኑርበን ፡ ወዘወዘው ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡
እንዳዘዘው ፡ ይህ ፡ ለቅድስና ፡ ከታረደው ፡
አውራ ፡ በግ ፡ የሙሴ ፡ እድል ፡ ፈንታ ፡ ሆነ ።
ሙሴም ፡ ከቅብዓቱ ፡ ዘይትና ፡ በመሠዊያው ፡
ላይ ፡ ከለው ፡ ከደሙ ፡ ወስዶ ፡ በአሮንና ፡ በል
ብሱ ፡ ላይ ፡ በልጆቹና ፡ በልጆቹ ፡ ልብስ ፡ ላይ ፡
ረጨው ፡ አሮንንና ፡ ልብሱንም ፡ ልጆቹንም ፡
የልጆቹንም ፡ ልብስ ፡ ቀደሰ ።
ሙሴም ፡ አሮንንና ፡ ልጆቹን ፡ አላቸው ፡ —
ሥጋውን ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡
ቀቅሉ ፡ አሮንና ፡ ልጆቹ ፡ ይበሉታል ፡ ብዬ ፡
እንዳዘዝሁ ፡ በዚያ ፡ እርሱንና ፡ በሌማቱ ፡ ያለ
ውን ፡ የቅድስናውን ፡ እንጀራ ፡ ብሉ ። ከሥጋ
ውና ፡ ከእንጀራውም ፡ የተረፈውን ፡ በእሳት ፡
ታቃጥሉታላችሁ ። ሰባት ፡ ቀን ፡ ይክናችኋ
ልና ፡ የክህነታችሁ ፡ ቀን ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡
ሰባት ፡ ቀን ፡ ከማኅበሩ ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ አት
ውጡ ። በዚህ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ለእና
ንተ ፡ ለማስተስረያ ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ እንዲሁ ፡
እግዚአብሔር ፡ አዘዘ ። እግዚአብሔር ፡ እን
ዳሁ ፡ አገዛኖልና ፡ እንዳትሞቱ ፡ በመገናኛው ፡
ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ሌሊቱንና ፡ ቀኑን ፡ ሰባት ፡
ቀን ፡ ተቀመጡ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ሥር
ዓት ፡ ጠብቁ ። አሮንና ፡ ልጆቹም ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ ያዘዘውን ፡ ሁሉ ፡ አደረጉ ።

ምዕራፍ ፡ ፱ ።

በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፤ ሙሴ ፡
አሮንንና ፡ ልጆቹን ፡ የእስራኤልንም ፡ ሽማግሌ
ዎች ፡ ጠራ ። አሮንንም ፡ አለው ፡ — ስለ ፡ ኃጢ
አት ፡ መሥዋዕት ፡ ከመንጋው ፡ እምቦሳውን ፡
ስለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ አውራውን ፡ በግ ፡
ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ ወስደህ ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ፊት ፡ አቅርባቸው ። የእስራኤልንም ፡
ልጆች ፡ — ዛሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይገለጥላችኋ
ልና ፡ ለኃጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ አውራ ፡ ፍየ
ልን ፡ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ ነውር ፡ የሌ
ለባቸውን ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ የሆናቸውን ፡ እም
ቦሳና ፡ ጠቦትን ፡ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ በሬ
ንና ፡ አውራን ፡ በግ ፡ በዘይትም ፡ የተለወሰ ፡ የእ
ህልን ፡ ቀኑርበን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይሠዉ ፡
ዘንድ ፡ ውሰዱ ፡ ብለህ ፡ ንገራቸው ። ሙሴም ፡
ያዘዛቸውን ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡
አመጡ ፡ ማኅበሩም ፡ ሁሉ ፡ ቀርበው ፡ በእግ
ዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቆሙ ። ሙሴም ፡ — ታዩር
ጉት ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘው ፡ ይህ ፡
ነው ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ይገለጥላች
ኋል ፡ አለ ። ሙሴም ፡ አሮንን ፡ — ወደ ፡ መሠ
ዊያው ፡ ቀርበህ ፡ የኃጢአትህን ፡ መሥዋዕትና ፡
የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትህን ፡ ሠዋ ፡ ለራስ
ህና ፡ ለሕዝቡም ፡ አስተስርይ ፤ እግዚአብሔርም ፡
እንዳዘዘ ፡ የሕዝቡን ፡ ቀኑርበን ፡ አቅርብ ፡ አስተ
ስርይላቸውም ፡ አለው ።
አሮንም ፡ ወደ ፡ መሠዊያው ፡ ቀርቦ ፡ ስለ ፡
ራሱ ፡ ኃጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ የሆነውን ፡ እም
ቦሳ ፡ አረደ ። የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ደሙን ፡ አቀ
ረቡለት ፡ ጣቱንም ፡ በደሙ ፡ ውስጥ ፡ ነከር ፡
የመሠዊያውን ፡ ቀንዶች ፡ አስነካ ፡ ደሙንም ፡
ከመሠዊያው ፡ በታች ፡ አፈሰሰው ። እግዚአብ
ሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ከኃጢአቱ ፡ መሥ
ዋዕት ፡ ስቡንና ፡ ኵላሊቶቹን ፡ የጕበቱንም ፡
መረብ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አቃጠለ ። ሥጋ
ውንና ፡ ቁርበቱንም ፡ ከሰፈሩ ፡ ውጭ ፡ በእሳት ፡
አቃጠለ ።
የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ አረደ ፤ የአ
ሮንም ፡ ልጆች ፡ ደሙን ፡ አመጡለት ፡ እርሱም ፡
በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ረጨው ። የሚ
ቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ በየብልቱ ፡ ራሱ
ንም ፡ አመጡለት ፡ እርሱም ፡ በመሠዊያው ፡
ላይ ፡ አቃጠለው ። የሆድ ፡ ዕቃውንና ፡ እግሮቹ
ንም ፡ አጠበ ፤ በመሠዊያውም ፡ በሚቃጠለው ፡
መሥዋዕት ፡ ላይ ፡ አቃጠለው ።
የሕዝቡንም ፡ ቀኑርበን ፡ አቀረበ ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡
ለኃጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ የሆነውን ፡ ፍየል ፡
ወስዶ ፡ አረደው ፡ ስለ ፡ ኃጢአትም ፡ እንደ ፡ ፊተ
ኛው ፡ ሠዋው ። የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡
አቀረበ ፡ እንደ ፡ ሥርዓቱም ፡ አደረገው ። የእህ
ሉንም ፡ ቀኑርበን ፡ አቀረበ ፡ ከእርሱም ፡ እፍኝ ፡
ሙሉ ፡ ወስዶ ፡ በጥዋት ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥ
ዋዕት ፡ ሌላ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አቃጠለው ።
ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ የሆነውን ፡ የደኅንነት ፡ መሥ
ዋዕት ፡ በሬውንና ፡ አውራውን ፡ በግ ፡ አረደ ፤
የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ደሙን ፡ አመጡለት ፡ በመ

ሠዊያውም ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ረጨው ፡ የበ
ሬውንና ፡ የአውራውንም ፡ በግ ፡ ስብ ፡ ላቱንም ፡
የሆድ ፡ ዕቃውንም ፡ የሚሸፍነውን ፡ ስብ ፡ ኵላሊ
ቶቹንም ፡ የጕበቱንም ፡ መረብ ፡ አመጡለት ።
ስቡንም ፡ በፍርምባዎቹ ፡ ላይ ፡ አደረጉ ፡ ስቡ
ንም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አቃጠለ ፡ እግዚአ
ብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ አሮን ፡ ፍርም
ባዎቹንና ፡ ቀኝ ፡ ወርቹን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡
ለመወዝወዝ ፡ ቀኑርበን ፡ ወዘወዘው ።
አሮንም ፡ እጆቹን ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ዘረጋ ፡
ባረከቸውም ፤ የኃጢአቱን ፡ የሚቃጠለውንም ፡
የደኅንነቱንም ፡ መሥዋዕት ፡ ከሠዋ ፡ በኋላ ፡
ወረደ ። ሙሴና ፡ አሮንም ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡
ድንኳን ፡ ገቡ ፡ ወጡም ፡ ሕዝቡንም ፡ ባረኩ ፡
የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ተገ
ለጠ ። እሳትም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ፡
በመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥ
ዋዕት ፡ ስቡንም ፡ በላ ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ አይ
ተው ፡ እልል ፡ አሉ ፡ በግምባራቸውም ፡ ወደቁ ።

ምዕራፍ ፡ ፲ ።

የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ናዳብና ፡ አብዩድ ፡ በየ
ራሳቸው ፡ ጥናውን ፡ ወስደው ፡ እሳት ፡ አደረ
ጉበት ፡ በላዩም ፡ ዕጣን ፡ አኖሩበት ፡ በእግዚአ
ብሔርም ፡ ፊት ፡ እርሱ ፡ ያላዘዛቸውን ፡ ሌላ ፡
እሳት ፡ አቀረቡ ። እሳትም ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ወጥቶ ፡ በላቸው ፡ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡
ሞቱ ። ሙሴም ፡ አሮንን ፡ — እግዚአብሔር ፡ —
ወደ ፡ እኔ ፡ በሚቀርቡ ፡ እቀደስበሁ ፡ በሕዝ
ቡም ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ እከብራለሁ ፡ ብሎ ፡ የተናገ
ረው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለው ፡ አሮንም ፡ ዝም ፡ አለ ።
ሙሴም ፡ የአሮንን ፡ አጎት ፡ የዑዝኤልን ፡ ልጆች ፡
ሚሳኤልንና ፡ ኤልጻፋንን ፡ ጠርቶ ፡ — ቅረቡ ፡
ወንድሞቻችሁንም ፡ ከመቅደሱ ፡ ፊት ፡ አንሥ
ታችሁ ፡ ከሰፈር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ውሰዱአቸው ፡
አላቸው ። እነርሱም ፡ ቀርበው ፡ አነሡአቸው ፡
ሙሴም ፡ እንዳለ ፡ በቀሚሳቸው ፡ ከሰፈር ፡ ወደ ፡
ውጭ ፡ ወሰዱአቸው ። ሙሴም ፡ አሮንን ፡ ፡ ልጆ
ቹንም ፡ አልዓዛርንና ፡ ኢታምርን ፡ — እንዳት
ሞቱ ፡ በማኅበሩም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ቍጣ ፡ እንዳ
ይወርድ ፡ ራሳችሁን ፡ አትንፈጉ ፡ ፡ ልብሳችሁ
ንም ፡ አትቅደዱ ፤ እግዚአብሔር ፡ ስላቃጠለው ፡
ሣቃጠል ፡ ግን ፡ ወንድሞቻችሁ ፡ የእስራኤል ፡
ቤት ፡ ሁሉ ፡ ያልቅሱ ። የእግዚአብሔር ፡ የቅብ
ዓት ፡ ዘይት ፡ በላያችሁ ፡ ነውና ፡ እንዳትሞቱ ፡
ከመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ አትወጡም ፡
አላቸው ። እንደ ፡ ሙሴ ፡ ቃልም ፡ አደረጉ ።
እግዚአብሔርም ፡ አሮንን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
ተናገረው ፡ — እንዳትሞቱ ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡
ድንኳን ፡ ስትገቡ ፡ አንተና ፡ ልጆችህ ፡ የወይን ፡
ጠጅና ፡ የሚያሰክርን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አትጠጡ ፡
ይህም ፡ ለልጅ ፡ ልጃችሁ ፡ የዘላለም ፡ ሥርዓት ፡
ይሆናል ፡ በተቀደሰውና ፡ በልተቀደሰው ፡ በር
ኩሱና ፡ በንጹሑም ፡ መካከል ፡ ትለያላችሁ ፡
እግዚአብሔርም ፡ በሙሴ ፡ ቃል ፡ የነገራቸውን ፡
ሥርዓት ፡ ሁሉ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ታስተ
ምራላችሁ ።
ሙሴም ፡ አሮንን ፡ የተረፉለትንም ፡ ልጆቹን ፡
አልዓዛርንና ፡ ኢታምርን ፡ አላቸው ፡ — ቅዱሱ ፡
ቅዱሳን ፡ ነውና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከሆነው ፡
ከእሳት ፡ ቍርበን ፡ የቀረውን ፡ የእህሉን ፡ ቍር
በን ፡ ውሰዱ ፡ ቂጣም ፡ አድርጋችሁ ፡ በመሠዊ
ያው ፡ አጠገብ ፡ ብሉት ፡ እግዚአብሔርም ፡ እን
ዲህ ፡ አዝዞኛልና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከሆነው ፡
ከእሳት ፡ ቍርበን ፡ ለአንተም ፡ ለልጆችህም ፡ የተ
ሰጠ ፡ ሥርዓት ፡ ነውና ፡ በቅዱስ ፡ ስፍራ ፡ ትበ
ሉታላችሁ ። እነዚህም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡
ከደኅንነት ፡ መሥዋዕቶች ፡ ለአንተና ፡ ለልጆ
ችህ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲሆኑ ፡ ስለ ፡ ተሰጡ ፡ የሚ
ወዘወዘውን ፡ ፍርምባ ፡ የሚነሣውንም ፡ ወርች ፡
አንተ ፡ ከአንተ ፡ ጋርም ፡ ልጆችህ ፡ ሴቶች ፡
ልጆችህም ፡ በንጹሕ ፡ ስፍራ ፡ ትበላላችሁ ።
የሚነሣውን ፡ ወርች ፡ የሚወዘወዘውንም ፡ ፍር
ምባ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመወዝወዝ ፡
ቀኑርበን ፡ እንዲወዘውዙ ፡ የእሳት ፡ ቍርበን ፡
ከሆነው ፡ ስብ ፡ ጋር ፡ ያመጣሉ ፡ እግዚአብሔር ፡
እንዳዘዘ ፡ ለአንተ ፡ ከአንተ ፡ ጋርም ፡ ለልጆችህ ፡
የዘላለም ፡ ሥርዓት ፡ ይሆናል ።
ሙሴም ፡ የኃጢአቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ፍየል ፡
እጅግ ፡ ፈለገው ፡ እነሆም ፡ ተቃጥሎ ፡ ነበር ፡
ሙሴም ፡ የቀሩትን ፡ የአሮንን ፡ ልጆች ፡ አልዓዛር
ንና ፡ ኢታምርን ፡ ተቈጥቶ ፡ — ቅዱሱ ፡ ቅዱሳን ፡
ነውና ፡ የሕዝቡንም ፡ ኃጢአት ፡ እንድትሸ
ከሙ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ እንድታስተ
ሰርዩላቸው ፡ ለእናንተ ፡ ሰጥቶታልና ፡ ስለ ፡
ምን ፡ የኃጢአትን ፡ መሥዋዕት ፡ በቅዱሱ ፡
ስፍራ ፡ አልበላችሁም ? እነሆ ፡ ደሙን ፡ ወደ ፡
መቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ አላገባችሁትም ፡ እኔ ፡ እን
ዳዘዝሁ ፡ በቅዱሱ ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ ትበሉት ፡
ዘንድ ፡ ይገባችሁ ፡ ነበር ፡ አላቸው ። አሮንም ፡
ሙሴን ፡ — እነሆ ፡ ዛሬ ፡ የኃጢአታቸውን ፡ መሥ
ዋዕት ፡ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕታቸውን ፡
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አቀረቡ ፡ ይህም ፡ ሁሉ ፡
ደረሰብኝ ፡ ዛሬስ ፡ የኃጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ በበ
ላሁ ፡ ኖሮ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መልካም ፡
ኖሮአልን ? አለው ። ሙሴም ፡ ሰማ ፡ በፈቱም ፡
መልካም ፡ ሆነ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እን
ዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፡ — ለእስራኤል ፡
ልጆች ፡ እንዲህ ፡ በሉአቸው ፡ — ከምድር ፡ እን
ስሶች ፡ ሁሉ ፡ የምትበሉአቸው ፡ እነዚህ ፡
ናቸው ። የተሰነጠቀ ፡ ሰኰና ፡ ያለውንና ፡ የሚ
ያመሰኳውን ፡ እንስሳ ፡ ሁሉ ፡ ብሉ ። ነገር ፡
ግን ፡ ከሚያመሰኩት ፡ ሰኰናቸውም ፡ ስንጥቅ ፡
ከሆነው ፡ ከእነዚህ ፡ አትበሉም ፡ ግመል ፡ ያመ
ሰኳል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሰኰናው ፡ ስላልተሰነጠቀ ፡

ፍ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ ነው ። ሽክክ ፡ ያመ
ሰኳል ÷ ነገር ፡ ግን ፡ ሰኰናው ፡ ስላልተሰነጠቀ ፡
፮ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ ነው ። ጥንቸልም ፡
ያመሰኳል ÷ ነገር ፡ ግን ፡ ሰኰናው ፡ ስላልተሰን
፯ ፡ ጠቀ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ ነው ። እርያም ፡
ሰኰናው ፡ ተሰንጥቆአል ÷ ነገር ፡ ግን ፡ ስለማያ
፰ ፡ መሰኳ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ ነው ። የእ
ነዚህን ፡ ሥጋ ፡ አትበሉም ÷ በድናቸውንም ፡
አትነኩም ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩሶች ፡ ናቸው ።
፱ ፡ በውኃ ፡ ውስጥ ፡ ከሚኖሩት ፡ ሁሉ ፡ እነዚ
ህን ፡ ትበላላችሁ ፡ በውሆች ፡ በባሕሮችም ፡
በወንዞችም ፡ ውስጥ ፡ ከሚኖሩት ፡ ሁሉ ፡ ክን
፲ ፡ ፍና ፡ ቅርፊት ፡ ያላቸውን ፡ ትበላላችሁ ። በው
ሆች ፡ ውስጥ ፡ ከሚንቀሳቀሱ ÷ በውሆች ፡
ውስጥ ፡ የሕይወት ፡ ነፍስ ፡ ካላቸው ፡ ሁሉ ÷
በባሕሮችና ፡ በወንዞች ፡ ውስጥ ፡ ክንፍና ፡ ቅር
ፊት ፡ የሌላቸው ፡ ሁሉ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የተ
፲፩ ፡ ጸየፉ ፡ ናቸው ። በእናንተም ፡ ዘንድ ፡ የተጸ
የፉ ፡ ይሆናሉ ፤ ሥጋቸውንም ፡ አትበሉም ÷
፲፪ ፡ በድናቸውንም ፡ ትጸየፋላችሁ ። ክንፍና ፡ ቅር
ፊትም ፡ የሌላቸው ፡ በውኃ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖ
ሩት ፡ ሁሉ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የተጸየፉ ፡
ናቸው ።
፲፫ ፡ ከወፎችም ፡ ወገን ፡ የምትጸየፉአቸው ፡ እነ
ዚህ ፡ ናቸው ፡ አይበሉም ፡ የተጸየፉ ፡ ናቸው ፡
፲፬ ፡ ንስር ÷ ገዳ ÷ ዓሣ ፡ አውጭ ÷ ጭላት ÷ ጭል
፲፭ ፡ ፊት ፡ በየወገኑ ÷ ቀጐ ፡ ሁሉ ፡ በየወገኑ ÷
፲፮ ፡ ሰጕን ÷ ጠላቋ ÷ ዝዩ ÷ በቋል ፡ በየወገኑ ÷
፲፯ ፡ ጕጉት ÷ እርኩም ÷ ጋጋኖ ÷ የውኃ ፡ ዶሮ ÷
፲፰ ፡ ይብራ ÷ ጥምብ ፡ አንሣ ፡ አሞራ ÷ ሽመላ ÷
ሳቢሳ ፡ በየወገኑ ÷ ጅንጁላቴ ፡ ወፍ ÷ የሌሊት ፡
ወፍ ።
፲፱ ፡ የሚበርርም ÷ በአራት ፡ እግሮችም ፡ የሚሄድ ፡
ተንቀሳቃሽ ፡ ሁሉ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የተጸየፈ ፡
፳ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሚበርሩት ÷ አራትም ፡
እግሮች ፡ ካሉአቸው ÷ ከእግሮቻቸውም ፡ በላይ ፡
በምድር ፡ ላይ ፡ የሚዘልሉባቸው ፡ ጭኖች ፡
ካሉአቸው ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ እነዚህን ፡ ትበላላ
፳፩ ፡ ችሁ ። ከእነርሱም ፡ እነዚህን ፡ ትበላላችሁ ፡
አራቱን ፡ ዓይነት ፡ አንበጣዎች ፡ በየወገናቸው ።
፳፪ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የሚበርር ÷ አራትም ፡ እግሮች ፡
ያሉት ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ሁሉ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡
የተጸየፈ ፡ ነው ።
፳፫ ፡ በእነዚህም ፡ ርኩስ ፡ ትሆናላችሁ ፤ የእነር
ሱንም ፡ በድን ፡ የሚነካ ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡
፳፬ ፡ ርኩስ ፡ ነው ። ከእነርሱም ፡ በድን ፡ የሚያነሣ ፡
ሁሉ ፡ ልብሱን ፡ ይጠብ ÷ እስከ ፡ ማታም ፡
፳፭ ፡ ርኩስ ፡ ነው ። ሰኰናም ፡ ያለው ÷ ነገር ፡ ግን ፡
ሰኰናው ፡ ያልተሰነጠቀ ÷ የማያመሰኳም ፡ እን
ስሳ ፡ ሁሉ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡
፳፮ ፡ እርሱን ፡ የሚነካ ፡ ሁሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ። በአ
ራት ፡ እግሮቹ ፡ ከሚሄድ ፡ እንስሳ ፡ ሁሉ ፡ በመ
ዳፎቹ ፡ ላይ ፡ የሚሄድ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡
ነው ፤ የእርሱን ፡ በድን ፡ የሚነካ ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡
ማታ ፡ ርኩስ ፡ ነው ። በድናቸውንም ፡ የሚያ
፳፯ ፡ ነሣ ፡ ልብሱን ፡ ይጠብ ÷ እስከ ፡ ማታም ፡ ርኩስ ፡
ነው ። እነርሱም ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩሶች ፡
ናቸው ።
፳፱ ፡ በምድር ፡ ላይም ፡ ከሚንቀሳቀስ ፡ ተንቀሳ
ቃሽ ፡ እነዚህ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩሶች ፡
ናቸው ፡ ሙሞልሞላ ÷ አይጥ ፡ እንሽላሊት ፡
በየወገኑ ÷ ኤሊ ÷ አዘ ÷ ገበሎ ÷ አርጃኖ ÷
፴ ፡ እስስት ። ከሚንቀሳቀሱት ፡ ሁሉ ፡ በእናንተ ፡
፴፩ ፡ ዘንድ ፡ ርኩሶች ፡ የሚሆኑ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።
ከእነርሱም ፡ የሞተውን ፡ የሚነካ ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡
፴፪ ፡ ማታ ፡ ርኩስ ፡ ነው ። ከእነርሱም ፡ የሞተው ፡
በምንም ፡ ላይ ፡ ቢወድቅ ፡ እርሱ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡
የእንጨት ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ ልብስ ፡ ወይም ፡ ቁር
በት ፡ ወይም ፡ ከረጢት ፡ ቢሆን ፡ የሚሠራበት ፡
ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ በውኃ ፡ ውስጥ ፡ ይደረግ ÷
እስከ ፡ ማታም ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡
ንጹሕ ፡ ይሆናል ። ከእነርሱም ፡ እንዳች ፡ በው
ስጡ ፡ የወደቀበትን ፡ የሸክላውን ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡
ሰበሩት ÷ በውስጡም ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ርኩስ ፡
፴፫ ፡ ነው ። በእርሱ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፤ ውኃም ፡
የሚፈስስበት ፡ የሚበላ ፡ መብል ፡ ሁሉ ፡ ርኩስ ፡
ነው ፤ በዚህም ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ያለው ፡ የሚጠጣ ፡
፴፬ ፡ መጠጥ ፡ ሁሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ። ከእነዚህም ፡
በድን ፡ የሚወድቅበት ፡ ሁሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡
አቶን ፡ ወይም ፡ ምድጃ ፡ ቢሆን ፡ ይሰባበራል ፡
ርኩሶች ፡ ናቸው ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩሶች ፡
ይሆናሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ምንጩ ÷ ጕድጓዱም ÷
፴፭ ፡ የውኃውም ፡ ሠራሮ ፡ ንጹሕን ፡ ናቸው ፡ በድና
ቸውን ፡ ግን ፡ የሚነካ ፡ ርኩስ ፡ ነው ። ከበድና
ቸውም ፡ በሚዘራ ፡ ዘር ፡ ላይ ፡ እንዳች ፡ ቢወ
ድቅ ፡ እርሱ ፡ ንጹሕ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በዘሩ ፡
ላይ ፡ ውኃ ፡ ቢፈስስበት ÷ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከበድ
ናቸው ፡ እንዳች ፡ ቢወድቅበት ÷ በእናንተ ፡
ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።
፴፮ ፡ ስመብል ፡ ከሚሆኑላችሁ ፡ እንስሶች ፡ የሞተ ፡
ቢኖር ÷ በድኑን ፡ የሚነካ ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡
ርኩስ ፡ ነው ። ከበድኑም ፡ የሚበላ ፡ ልብሱን ፡ ፡
፴፯ ፡ ያጥበል ÷ እስከ ፡ ማታም ፡ ርኩስ ፡ ይሆናል ፡
በድኑንም ፡ የሚያነሣ ፡ ልብሱን ፡ ይጠብ ÷
እስከ ፡ ማታም ፡ ርኩስ ፡ ነው ።
በምድርም ፡ ላይ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡
፴፰ ፡ ሁሉ ፡ የተጸየፈ ፡ ነው ÷ አትብሉትም ። በሆዱ ፡
፴፱ ፡ የሚሳብ ፡ በአራትም ፡ እግሮች ፡ የሚሳብ ÷ ብዙ ፡
እግሮችም ፡ ያሉት ÷ በምድርም ፡ ላይ ፡ የሚን
ቀሳቀሱ ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ ሁሉ ፡ የተጸየፉ ፡ ናቸ
ውና ፡ አትብሉአቸው ። በሚንቀሳቀሱ ፡ ተን
፴፫ ፡ ቀሳቃሾች ፡ ሁሉ ፡ ሰውነታችሁን ፡ አታስጸይፉ ፡
በእነርሱም ፡ እንዳተረከሱ ፡ ሰውነታችሁን ፡ አታ
ርክሱባቸው ። እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካ
፴፬ ፡ ችሁ ፡ ነኝና ፡ ሰውነታችሁን ፡ ቀድሱ ÷ ቅዱሳ
ንም ፡ ሁኑ ÷ እኔ ፡ ቅዱስ ፡ ነኝና ፤ በምድርም ፡
ላይ ፡ በሚሳብ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ሁሉ ፡ ሰውነታች
ሁን ፡ አታርክሱ ። እኔ ፡ አምላካችሁ ፡ እሆን ፡
፴፭ ፡ ዘንድ ፡ ከግብፅ ፡ ምድር ፡ ያወጣኋችሁ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ነኝ ፤ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ ቅዱስ ፡ ነኝና ፡
እናንተ ፡ ቅዱሳን ፡ ሁኑ ።
የእንስሳና ፡ የወፍ ÷ በውኃም ፡ ውስጥ ፡ የሚ
ንቀሳቀስ ፡ የፍጥረት ፡ ሁሉ ÷ በምድርም ፡ ላይ ፡
የሚንቀሳቀስ ፡ የፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡
ነው ። በርኩስና ፡ በንጹሕ ፡ መካከል ÷ የሕይ
ወት ፡ ነፍስ ፡ ካላቸውም ፡ በምትበሉትና ፡ በማ
ትበሉት ፡ መካከል ፡ እንድትለዩ ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
ተናገረው ፡ ፡ — ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡
ብለህ ፡ ንገራቸው ፡ ፡ — ሴት ፡ ብታረግዝ ፡ ወንድ ፡
ልጅም ፡ ብትወልድ ÷ ሰባት ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ የረ
ከሰች ፡ ናት ፤ እንደ ፡ ሕመምዋ ፡ መርገም ፡
ወራት ፡ ትረከሳለች ። በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡
ልጁ ፡ ከሥጋው ፡ ሸለፈት ፡ ይገረዝ ። ከደምዋም ፡ እስከትነጻ ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ትቀመጥ ፡
የመንጻትዋ ፡ ቀንም ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ የተ
ቀደሰን ፡ ነገር ፡ አትንክ ÷ ወደ ፡ መቅደስም ፡ አት
ግባ ። ሴት ፡ ልጅም ፡ ብትወልድ ፡ እንደ ፡ መር
ገምዋ ፡ ወራት ፡ ሁለት ፡ ሳምንት ፡ ያህል ፡ የረ
ከሰች ፡ ናት ፤ ከደምዋም ፡ እስከትነጻ ፡ ድረስ ፡
ስድሳ ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ ትቀመጥ ።
የመንጻትዋ ፡ ወራትም ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ÷
ለወንድ ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ ለሴት ፡ ልጅ ÷ የእንድ ፡
ዓመት ፡ ጠቦት ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ÷ የር
ግብም ፡ ግልገል ፡ ወይም ፡ ዋኖስ ፡ ለኃጢአት ፡
መሥዋዕት ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡
ወደ ፡ ካህኑ ፡ ታምጣለት ። እርሱም ፡ በእግዚ
አብሔር ፡ ፊት ፡ ያቀርበዋል ፡ ያስተሰርያዋ
ማል ፤ ከደምዋም ፡ ፈሳሽ ፡ ትነጻለች ። ወንድ ፡
ወይም ፡ ሴት ፡ ለምትወልድ ፡ ሴት ፡ ሕጉ ፡ ይህ ፡
ነው ። ጠቦት ፡ ለማምጣት ፡ ገንዘብዋ ፡ ያልበ
ቃት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁለት ፡ ዋኖሶች ፡ ወይም ፡
ሁለት ፡ የርግብ ፡ ግልገሎች ፡ አንዱን ፡ ለሚቃ
ጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ሌላውንም ፡ ለኃጢአት ፡
መሥዋዕት ፡ ታቀርበለች ፡ ካህኑም ፡ ያስተሰር
ይላታል ÷ እርስዋም ፡ ትነጻለች ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እን
ዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፡ ፡ — ማናቸውም ፡ ሰው ፡
በሥጋው ፡ ቁርበት ፡ ላይ ፡ እባጭ ፡ ወይም ፡
ብጕር ፡ ወይም ፡ ቋቂቻ ፡ ቢታይ ÷ በሥጋው ፡
ቁርበት ፡ እንደ ፡ ለምጽ ፡ ደዌ ፡ ቢመስል ÷ ወደ ፡
ካህኑ ፡ ወደ ፡ አሮን ፡ ወይም ፡ ከክህናቱ ፡ ልጆቹ ፡
ወደ ፡ አንዱ ፡ ያምጡት ። ካህኑም ፡ በሥጋው ፡
ቁርበት ፡ ያለውን ፡ ደዌ ፡ ያያል ፤ ጠጕሩም ፡
ተለውጦ ፡ ቢነጣ ፡ ደዌውም ፡ ወደ ፡ ሥጋው ፡
ቁርበት ፡ ቢጠልቅ ÷ እርሱ ፡ የለምጽ ፡ ደዌ ፡ ነው ፤
ካህኑም ፡ አይቶ ፡ ፡ — ርኩስ ፡ ነው ፡ ይበለው ።
ቋቂቻውም ፡ በሥጋው ፡ ቁርበት ፡ ላይ ፡ ቢነጣ ÷
ከቁርበቱም ፡ የጠለቀ ፡ ባይመስል ÷ ጠጕሩም ፡
ባይነጣ ÷ ካህኑ ፡ የታመመውን ፡ ሰው ፡ ሰባት ፡
ቀን ፡ ይዘጋበታል ። በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ካህኑ ፡
፮ ፡ ያየዋል ፤ እነሆም ፡ ደዌው ፡ በዓይኑ ፡ ፊት ፡
እንደ ፡ ነበረ ፡ ቢሆን ÷ በቁርበቱም ፡ ላይ ፡ ባይ
ሰፋ ÷ ካህኑ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ደግሞ ፡ ይዘጋበታል ።
ደግሞ ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ካህኑ ፡ ያየዋል ፤
፯ ፡ እነሆም ፡ ደዌው ፡ ቢከስም ÷ ደዌውም ፡ በቁ
ርበቱ ፡ ላይ ፡ ባይሰፋ ÷ ካህኑ ፡ ፡ — ንጹሕ ፡ ነው ፡
ይለዋል ፤ እከክ ፡ ነው ፡ ልብሱንም ፡ አጥቦ ፡
ንጹሕ ፡ ይሆናል ። ስለ ፡ መንጻቱ ፡ በካህኑ ፡
፰ ፡ ዘንድ ፡ ከታየ ፡ በኋላ ፡ እከኩ ፡ በቁርበቱ ፡ ላይ ፡
ቢሰፋ ÷ እንደ ፡ ገና ፡ ሊታይ ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ይቀ
ርባል ። ካህኑም ፡ ያያል ፤ እነሆም ÷ እከኩ ፡
፱ ፡ በቁርበቱ ፡ ላይ ፡ ቢሰፋ ÷ ካህኑ ፡ ፡ — ርኩስ ፡ ነው ፡
ይለዋል ፤ ለምጽ ፡ ነው ።
የለምጽ ፡ ደዌ ፡ በሰው ፡ ውስጥ ፡ ቢሆን ፡ እር
ሱን ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ያመጡለታል ። ካህኑም ፡
፲ ፡ ያያል ፤ እነሆም ÷ በቁርበቱ ፡ ላይ ፡ ነጭ ፡ እባጭ ፡
ቢሆን ÷ ጠጕሩም ፡ ተለውጦ ፡ ቢነጣ ÷ ሥጋ
ውም ፡ በእባጩ ፡ ውስጥ ፡ ቢያኘር ÷ እርሱ ፡
፲፩ ፡ በሥጋው ፡ ቁርበት ፡ ላይ ፡ አሮጌ ፡ ለምጽ ፡ ነው ÷
ካህኑም ፡ ፡ — ርኩስ ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ እርሱ ፡
ርኩስ ፡ ነውና ፡ አይዘጋበትም ። ለምጹም ፡ በቁ
፲፪ ፡ ርቱ ፡ ላይ ፡ ሰፍቶ ፡ ቢወጣ ÷ ለምጹም ፡ የታመ
መውን ፡ ሰው ፡ ቁርበቱን ፡ ሁሉ ፡ ከራሱ ፡ እስከ ፡
እግሮቹ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ከደነው ፡ ለካህኑ ፡ ቢመ
ስለው ÷ ካህኑ ፡ ያያል ፤ እነሆም ÷ ለምጹ ፡ ሥጋ
፲፫ ፡ ውን ፡ ሁሉ ፡ ቢከድን ፡ የታመመውን ፡ ሰው ፡ ፡ —
ንጹሕ ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ ሥጋው ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡
ተለውጦ ፡ ነጭ ፡ ሆኖአል ፤ ንጹሕ ፡ ነው ። የሚ
፲፬ ፡ ያገው ፡ ሥጋ ፡ ግን ፡ ሲታይበት ፡ ርኩስ ፡ ይሆ
ናል ። ካህኑም ፡ የሚያገው ፡ ሥጋ ፡ አይቶ ፡ ፡ —
፲፭ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ የሚያገው ፡ ሥጋ ፡
ለምጽ ፡ ነውና ፡ ርኩስ ፡ ነው ። የሚያገውም ፡
፲፮ ፡ ሥጋ ፡ ተለውጦ ፡ ቢነጣ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡
ይመጣል ። ካህኑም ፡ ያየዋል ፤ እነሆም ÷ ደዌው ፡
፲፯ ፡ ቢነጣ ፡ ካህኑ ፡ የታመመውን ፡ ፡ — ንጹሕ ፡ ነው ፡
ይለዋል ፤ ንጹሕ ፡ ነው ።
በሥጋውም ፡ ቁርበት ፡ ላይ ፡ ቍስል ፡ ቢሆ
፲፰ ፡ ንና ፡ ቢሽር ÷ በቍስሉም ፡ ስፍራ ፡ ነጭ ፡ እባጭ ፡
፲፱ ፡ ወይም ፡ ቀላ ፡ ያለ ፡ ቋቂቻ ፡ ቢወጣ ÷ በካህኑ ፡
ዘንድ ፡ ይታያል ። ካህኑም ፡ ያያል ፤ እነሆም ÷
፳ ፡ ወደ ፡ ቁርበቱ ፡ ውስጥ ፡ ጠልቆ ፡ ቢታይ ÷ ጠጕ
ሩም ፡ ተለውጦ ፡ ቢነጣ ÷ ካህኑ ፡ ፡ — ርኩስ ፡ ነው ፡
ይለዋል ፤ የለምጽ ፡ ደዌ ፡ ነው ፡ ከቍስሉ ፡ ውስጥ ፡
ወጥቶአል ። ካህኑም ፡ ቢያየው ÷ ነጭም ፡ ጠጕር ፡
፳፩ ፡ ባይኖርበት ÷ ወደ ፡ ቁርበቱም ፡ ውስጥ ፡ ባይ
ጠልቅ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ቢከስም ÷ ካህኑ ፡ ሰባት ፡
ቀን ፡ ይዘጋበታል ። በቁርበቱም ፡ ላይ ፡ ቢሰፋ ÷
፳፪ ፡ ካህኑ ፡ ፡ — ርኩስ ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ ደዌ ፡ ነው ።
ቋቂቻው ፡ ግን ፡ በስፍራው ፡ ቢቆም ፡ ባይሰ
፳፫ ፡ ፋም ÷ የቍስል ፡ ጠባሳ ፡ ነው ፤ ካህኑም ፡ ፡ —
ንጹሕ ፡ ነው ፡ ይለዋል ።

፵፬ በሥጋውም ፡ ቁርበት ፡ የእሳት ፡ ትኵሳት ፡ ቢኖርበት ÷ በተቃጠለውም ፡ ስፍራ ፡ ነጭ ፡
፵፭ ወይም ፡ ቀላ ፡ ያለ ፡ ቋቂቻ ፡ ቢታይ ÷ ካህኑ ፡ ያየዋል ፤ እነሆም ÷ በቋቂቻው ፡ ጠጕሩ ፡ ተለ
ውጦ ፡ ቢነጣ ÷ ወደ ፡ ቁርበቱም ፡ ውስጥ ፡ ቢጠ
ልቅ ÷ ለምጽ ፡ ነው ፤ ከተቃጠለውም ፡ ስፍራ ፡
ወጥቶአል ፤ ካህኑም ፡ — ርኩስ ፡ ነው ፥ ይለዋል ፤
፵፮ የለምጽ ፡ ደዌ ፡ ነው ። ካህኑም ፡ ቢያየው ÷ በቋ
ቂውም ፡ ነጭ ፡ ጠጕር ፡ ባይኖር ፡ ወደ ፡ ቁር
በቱም ፡ ባይጠልቅ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ቢከስም ÷
፵፯ ካህኑ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይዘጋበታል ። ካህኑም ፡
በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ያየዋል ፤ በቁርበቱም ፡ ላይ ፡
ቢሰፋ ፡ ካህኑ ፡ — ርኩስ ፡ ነው ፥ ይለዋል ፤ የለ
፵፰ ምጽ ፡ ደዌ ፡ ነው ። ቋቂቻውም ፡ በስፍራው ፡
ላይ ፡ ቢቆም ÷ በቁርበቱም ፡ ላይ ፡ ባይሰፋ ፡ ነገር ፡
ግን ፡ ቢከስም ፤ የትኵሳት ፡ እባጭ ፡ ነው ፤ የት
ኵሳትም ፡ ጠባሳ ፡ ነውና ፡ ካህኑ ፡ — ንጹሕ ፡
ነው ፥ ይለዋል ።
፵፱ ማናቸውም ፡ ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ በራሱ ፡
ወይም ፡ በአገጩ ፡ ደዌ ፡ ቢኖርበት ÷ ካህኑ ፡
ደዌውን ፡ ያያል ፤ እነሆም ÷ ወደ ፡ ቁርበቱ ፡ ቢጠ
ልቅ ÷ በውስጡም ፡ ቀጭን ፡ ብጫ ፡ ጠጕር ፡ ቢኖ
ርበት ÷ ካህኑ ፡ — ርኩስ ፡ ነው ፥ ይለዋል ፤ ቁረቁር ፡
ነው ፤ የራስ ፡ ወይም ፡ የአገጭ ፡ ለምጽ ፡ ነው ።
፵፩ ካህኑም ፡ የቁረቁሩን ፡ ደዌ ፡ ቢያይ ÷ ወደ ፡ ቁር
በቱም ፡ ባይጠልቅ ÷ ጥቁርም ፡ ጠጕር ፡ ባይኖ
ርበት ÷ ካህኑ ፡ የቁረቁር ፡ ደዌ ፡ ያለበትን ፡ ሰው ፡
፵፪ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይዘጋበታል ። ካህኑም ፡ በሰባተ
ኛው ፡ ቀን ፡ ደዌውን ፡ ያያል ፤ እነሆም ÷ ቁረ
ቁሩ ፡ ባይሰፋ ÷ በውስጡም ፡ ብጫ ፡ ጠጕር ፡
ባይኖር ÷ የቁረቁሩም ፡ መልክ ፡ ወደ ፡ ቁርበቱ ፡
፵፫ ባይጠልቅ ፤ ይላጫል ÷ ቁረቁሩ ፡ ግን ፡ አይላ
ጭም ፡ ካህኑም ፡ ቁረቁር ፡ ያለበትን ፡ ሰው ፡
፵፬ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይዘጋበታል ። ካህኑም ፡
በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ቁረቁሩን ፡ ያያል ፤ እነሆም ÷
ቁረቁሩ ፡ በቁርበቱ ፡ ላይ ፡ ባይሰፋ ፡ መልኩም ፡
ወደ ፡ ቁርበቱ ፡ ባይጠልቅ ÷ ካህኑ ፡ — ንጹሕ ፡
ነው ፥ ይለዋል ፤ ልብሱን ፡ አጥቦ ፡ ንጹሕ ፡ ይሆ
፵፭ ናል ። ነገር ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ቁረቁሩ ፡ በቁርበቱ ፡
፵፮ ላይ ፡ ቢሰፋ ÷ ካህኑ ፡ ያየዋል ፤ እነሆም ፡ ቁረ
ቁሩ ፡ በቁርበቱ ፡ ላይ ፡ ቢሰፋ ፡ ካህኑ ፡ ብጫ
ውን ፡ ጠጕር ፡ አያፈልግም ፤ ርኩስ ፡ ነው ።
፵፯ ቁረቁሩ ፡ ግን ፡ በዓይኑ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡
ቢሆን ÷ ጥቁርም ፡ ጠጕር ፡ ቢበቅልበት ÷ ቁረ
ቁሩ ፡ ሸሮአል ፤ እርሱም ፡ ንጹሕ ፡ ነው ፥ ካህ
ኑም ፡ — ንጹሕ ፡ ነው ፥ ይለዋል ።
፵፰ ማናቸውም ፡ ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ በሥጋው ፡
፵፱ ቁርበት ፡ ላይ ፡ ነጭ ፡ ቋቂቻ ፡ ቢኖርበት ÷ ካህኑ ፡
ያያል ፤ እነሆም ፡ በሥጋቸው ፡ ቁርበት ፡ ላይ ፡
ያለው ፡ ቋቂቻ ፡ ፈገግ ፡ ቢል ፡ አንጐት ፡ ነው ፥
ከቁርበቱ ፡ ውስጥ ፡ ወጥቶአል ፤ ንጹሕ ፡ ነው ።
፶ የሰውም ፡ ጠጕር ፡ ከራሱ ፡ ቢመለጥ ፡ እርሱ ፡
፶፩ ቡሀ ፡ ነው ፥ ነገር ፡ ግን ፡ ንጹሕ ፡ ነው ። ጠጕ
ሩም ፡ ከግምባሩ ፡ ቢመለጥ ፡ እርሱ ፡ ራሰ ፡ በራ ፡
ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ንጹሕ ፡ ነው ። በቡሀነቱ ፡
ወይም ፡ በራሰ ፡ በራነቱ ፡ ነጭ ፡ ወይም ፡ ቀላ ፡
ያለ ፡ ደዌ ፡ በኖርበት ÷ እርሱ ፡ ከቡሀነቱ ፡
ወይም ፡ ከራሰ ፡ በራነቱ ፡ የወጣ ፡ ለምጽ ፡ ነው ።
፶፪ ካህኑም ፡ ያየዋል ፤ እነሆም ÷ የደዌው ፡ እብ
ጠት ÷ በሥጋው ፡ ቁርበት ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ ለምጽ ፡
መስሎ ፡ በቡሀነቱ ፡ ወይም ፡ በራሰ ፡ በራነቱ ፡
ነጭ ፡ ወይም ፡ ቀላ ፡ ያለ ፡ ቢሆን ÷ ለምጻም ፡
ሰው ፡ ነው ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡ ካህኑ ፡ — በእርግጥ ፡
ርኩስ ፡ ነው ፥ ይለዋል ፤ ደዌው ፡ በራሱ ፡ ነው ።
፶፫ የለምጽ ፡ ደዌ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ልብሱ ፡ የተ
ቀደደ ፡ ይሁን ÷ ራሱም ፡ የተገለጠ ፡ ይሁን ÷ ከን
ፈሩንም ፡ ይሸፍን ፤ ርኩስ ፡ ርኩስ ፡ ኀኝ ፥ ይበል ።
፶፬ ደዌው ፡ በለበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ርኩስ ፡ ይሆ
ናል ፤ እርሱ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ ብቻውን ፡ ይቀ
መጣል ፤ መኖሪያውም ፡ ከሰፈር ፡ በውጭ ፡ ይሆ
ናል ።
፶፭ የለምጽም ፡ ደዌ ፡ በልብስ ፡ ላይ ፡ ቢሆን ÷
ልብሱም ፡ የበግ ፡ ጠጕር ፡ ወይም ፡ በፍታ ፡
ቢሆን ÷ በድሩ ፡ ወይም ፡ በማጉ ፡ ላይ ፡ ቢሆን ÷
በፍታ ፡ ወይም ፡ የበግ ፡ ጠጕር ፡ ቢሆን ÷ አጕዛ ፡
ወይም ፡ ከአጕዛ ፡ የሚደረግ ፡ ነገር ፡ ቢሆን ÷
ደዌው ፡ በልብሱ ፡ ወይም ፡ በአጕዛው ፡ ወይም ፡
፶፮ በድሩ ፡ ወይም ፡ በማጉ ፡ ወይም ፡ ከአጕዛው ፡
በሚደረገው ፡ ነገር ፡ አረንጓዴ ፡ ወይም ፡ ቀይ ፡
ቢሆን ÷ የለምጽ ፡ ደዌ ፡ ነው ፤ ለካህኑ ፡ ይታ
ያል ። ካህኑም ፡ ደዌውን ፡ አይቶ ፡ ደዌው ፡ ፶፯
ያለበትን ፡ ነገር ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይዘጋበታል ።
በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ደዌውን ፡ ያያል ፤ ደዌ ፡ ፶፰
ውም ፡ በልብስ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በድሩ ፡ ወይም ፡
በማጉ ፡ ወይም ፡ በአጕዛው ፡ ወይም ፡ ከአጕ
ዛው ፡ በሚደረግ ፡ ነገር ፡ ቢሰፋ ፡ ደዌው ፡ እየ
ፋገ ፡ የሚሄድ ፡ ለምጽ ፡ ነው ፤ ርኩስ ፡ ነው ።
ልብሱን ፡ ያቃጥል ፡ ድሩ ፡ ወይም ፡ ማጉ ፡ የበግ ፡ ፶፱
ጠጕር ፡ ወይም ፡ በፍታ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ከአ
ጕዛው ፡ የተደረገ ፡ ቢሆን ÷ ደዌ ፡ ያለበት ፡ ሁሉ ፡
እየፋገ ፡ የሚሄድ ፡ ለምጽ ፡ ነውና ፡ በእሳት ፡
ይቃጠል ።
ካህኑ ፡ ቢያይ ÷ እነሆም ፡ ደዌው ፡ በድሩ ፡ ፷
ወይም ፡ በማጉ ፡ ወይም ፡ ከአጕዛ ፡ በተደረገ ፡
ነገር ፡ ቢሆን ፡ በልብሱ ፡ ላይ ፡ ባይሰፋ ፡ ካህኑ ፡ ፷፡
ደዌ ፡ ያለበቱ ፡ ነገር ፡ እንዲታጠብ ፡ ይዘዝ ፡
ሌላም ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይዘጋበታል ። ደዌውም ፡ ፷፪
ከታጠበ ፡ በኋላ ፡ ካህኑ ፡ ያያል ፤ እነሆም ÷
ደዌው ፡ መልኩን ፡ ባይለውጥ ፡ ባይሰፋም ÷
ርኩስ ፡ ነው ፥ በእሳት ፡ አቃጥለው ፡ ምልክቱ ፡
በውስጥ ፡ ወይም ፡ በውጭ ፡ ቢሆን ፡ እየፋገ ፡
የሚሄድ ፡ ደዌ ፡ ነው ።
ካህኑም ፡ ቢያይ ፡ እነሆም ፡ ደዌው ፡ ከታጠበ ፡ ፷፫
በኋላ ፡ ቢከስም ፡ ከልብሱ ፡ ወይም ፡ ከአጕዛው ፡
ወይም ፡ ከድሩ ፡ ወይም ፡ ከማጉ ፡ ይቅደደው ።
በልብሱም ፡ ወይም ፡ በድሩ ፡ ወይም ፡ በማጉ ፡ ፷፬
ወይም ፡ ከአጕዛው ፡ በተደረገ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡
ደግሞ ፡ ቢታይ ÷ የወጣ ፡ ለምጽ ፡ ነው ፤ ደዌው ፡

ያለበትን ፡ ነገር ፡ አቃጥለው ። አንተም ፡ ከጠ
ብኸው ፡ ልብስ ፡ ወይም ፡ ከድሩ ፡ ወይም ፡
ከማጉ ፡ ወይም ፡ ከአጕዛው ፡ ከተደረገው ፡ ነገር ፡
ላይ ፡ ደዌው ፡ ቢጠፋ ÷ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ይታጠ
ባል ÷ ንጹሕም ፡ ይሆናል ።
በበግ ፡ ጠጕር ፡ ልብስ ፡ ወይም ፡ በበፍታ ፡
ወይም ፡ በድሩ ፡ ወይም ፡ በማጉ ፡ ወይም ፡ ከአ
ጕዛ ፡ በተደረገ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ቢሆን ÷ ንጹሕ ፡
ወይም ፡ ርኩስ ፡ ያሰኝ ፡ ዘንድ ፡ የለምጽ ፡ ደዌ ፡
ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡
ተናገረው ፡ — በመንጻቱ ፡ ቀን ፡ የለምጻሙ ፡
ሕግ ፡ ይህ ፡ ይሆናል ፤ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ይወስዱ
ታል ። ካህኑም ፡ ከሰፈር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይወ
ጣል ፤ ካህኑም ፡ ያያል ፤ እነሆም ÷ የለምጹ ፡
ደዌ ፡ ከለምጻሙ ፡ ላይ ፡ ቢጠፋ ÷ ካህኑ ፡ ስለ
ሚነጻው ፡ ሰው ፡ ሁለት ፡ ንጹሕን ፡ ወፎች ፡
በሕይወታቸው ÷ የዝግባም ፡ እንጨት ፡ ቀይ ፡
ግምጃም ÷ ሂሶጵም ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፡ ያዝዛል ።
ካህኑም ፡ ከሁለቱ ፡ ወፎች ፡ አንዱን ፡ በሸክላ ፡
ዕቃ ፡ ውስጥ ፡ በምንጭ ፡ ውኃ ፡ ላይ ፡ ያርድ ፡
ዘንድ ፡ ያዝዛል ። ሕያውንም ፡ ወፍ ፡ ዝግባው
ንም ፡ እንጨት ፡ ቀዩንም ፡ ግምጃ ፡ ሂሶጵንም ፡
ወስዶ ፡ ከሕያው ፡ ወፍ ፡ ጋር ፡ በምንጭ ፡ ውኃ ፡
ላይ ፡ በታረደው ፡ ወፍ ፡ ደም ፡ ውስጥ ፡ ይነክ
ራቸዋል ። ከለምጹ ፡ በሚነጻው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡
ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ይረጫል ፤ ንጹሕም ፡ ነው ፥ ይለ
ዋል ÷ ሕያውንም ፡ ወፍ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ይለቅ
ቀዋል ። የነጻውም ፡ ሰው ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ÷
ጠጕሩንም ፡ ሁሉ ፡ ይላጫል ÷ በውኃም ፡ ይታ
ጠባል ÷ ንጹሕም ፡ ይሆናል ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡
ወደ ፡ ሰፈር ፡ ይገባል ÷ ነገር ፡ ግን ፡ ከድንኳኑ ፡
በውጭ ፡ ሆኖ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይቀመጣል ። በሰ
ባተኛውም ፡ ቀን ፡ ጠጕሩን ፡ ሁሉ ፡ ይላጫል ፤
ራሱንም ፡ ጢሙንም ፡ ቅንድቡንም ÷ የገላው
ንም ፡ ጠጕር ፡ ሁሉ ፡ ይላጫል ፤ ልብሱንም ÷
ገላውንም ፡ በውኃ ፡ ያጥባል ፤ ንጹሕም ፡ ይሆ
ናል ።
በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ነውር ፡ የሌለባቸ
ውን ፡ ሁለት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ÷ ነውር ፡ የሌለባት
ንም ፡ አንዲት ፡ የዓመት ፡ እንስት ፡ ጠቦት ÷ ስለ ፡
እህልም ፡ ቀርባን ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከአሥር ፡
እጅ ፡ ሦስት ፡ እጅ ፡ የሆነ ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡
መልከም ፡ ዱቄት ፡ አንድ ፡ የሎግ ፡ መስፈሪ
ያም ፡ ዘይት ፡ ይወስዳል ። የሚያነጻውም ፡
ካህን ፡ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ የሚነጻውንም ፡ ሰው ፡
በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ አጠገብ ፡ በእግ
ዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያኖራቸዋል ። ካህኑም ፡ አን
ዱን ፡ ጠቦት ፡ ወስዶ ፡ ስለ ፡ በደል ፡ መሥዋዕት ፡
ያቀርበዋል ፤ ያንንም ፡ የሎግ ፡ መስፈሪያ ፡ ዘይት ፡
ስለ ፡ መወዝወዝ ፡ ቀርባን ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ይወዘውዘዋል ። የኃጢአትን ፡ መሥዋ
ዕትና ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ በሚያር
ዱበት ፡ በተቀደሰው ፡ ስፍራ ፡ ጠቦቱን ፡ ያር
ደዋል ፤ የኃጢአቱ ፡ መሥዋዕት ፡ ለካህኑ ፡
እንደሚሆን ÷ እንዲሁ ፡ የበደል ፡ መሥዋዕት ፡
ነው ፤ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ ነው ። ካህኑም ፡ ከበ ፲፬
ደል ፡ መሥዋዕት ፡ ደም ፡ ወስዶ ፡ የሚነጻውን ፡
ሰው ፡ የቀኝ ፡ ጆሮውን ፡ ጫፍ ÷ የቀኝ ፡ እጁ
ንም ፡ አውራ ፡ ጣት ÷ የቀኝ ፡ እግሩንም ፡ አውራ ፡
ጣት ፡ ያስነካዋል ። ካህኑም ፡ ከዘይቱ ፡ ከሎግ ፡ ፲፭
መስፈሪያው ፡ ወስዶ ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ ውስጥ ፡ ያፈ
ስሰዋል ። ካህኑም ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ ውስጥ ፡ ፲፮
በለው ፡ ዘይት ፡ ቀኝ ፡ ጣቱን ፡ ነክሮ ፡ ከዘይቱ ፡
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ በጣቱ ፡
ይረጫል ። ካህኑም ፡ በእጁ ፡ ውስጥ ፡ ከቀረው ፡ ፲፯
ዘይት ፡ የሚነጻውን ፡ ሰው ፡ የቀኝ ፡ ጆሮውን ፡
ጫፍ ÷ የቀኝ ፡ እጁንም ፡ አውራ ፡ ጣት ÷ የቀኝ ፡
እግሩንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ የበደል ፡ መሥዋ
ዕት ፡ ደም ፡ በረፈበት ፡ ላይ ፡ ያስነካዋል ። በካ ፲፰
ህኑም ፡ እጅ ፡ ውስጥ ፡ የቀረውን ፡ ዘይት ፡ በሚ
ነጻው ፡ ሰው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ያደርግበታል ፤ ካህ
ኑም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያስተሰርይለ
ታል ። ካህኑም ፡ የኃጢአቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ፲፱
ያቀርባል ÷ ከርኵሰቱም ፡ ለሚነጻው ፡ ሰው ፡
ያስተሰርይለታል ፤ በኋላም ፡ የሚቃጠለውን ፡
መሥዋዕት ፡ ያርዳል ። ካህኑም ፡ የሚቃጠለ ፡ ፳
ውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእህሉን ፡ ቍርባን ፡
በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቀርባል ÷ ካህኑም ፡ ያስ
ተሰርይለታል ፤ እርሱም ፡ ንጹሕ ፡ ይሆናል ።
ድሀም ፡ ቢሆን ፡ ይህንም ፡ ለማምጣት ፡ ገን ፲፭
ዘቡ ፡ ባይበቃው ፡ ማስተስረያ ፡ ይሆንለት ፡ ዘንድ ፡
እንዲወዘወዝ ፡ አንድ ፡ ጠቦት ፡ ለበደል ፡ መሥ
ዋዕት ÷ ከመስፈሪያውም ፡ ከአሥር ፡ እጅ ፡ አንድ ፡
እጅ ፡ የሆነ ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡
ዱቄት ፡ ለእህል ፡ ቍርባን ÷ አንድ ፡ የሎግ ፡ መስ
ፈሪያም ፡ ዘይት ፡ ይወስዳል ። ሁለት ፡ ዋኖሶች ፡ ፲፮
ወይም ፡ የርግብ ፡ ግልገሎች ፡ እንደሚቻለው ÷
አንዱን ፡ ለኃጢአት ፡ መሥዋዕት ÷ ሌላውን ፡
ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ይወስዳል ። በስም
ንተኛውም ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ መንጻት ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡
ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ፊት ፡ ያመጣቸዋል ። ካህኑም ፡ የበደ ፲፯
ሉን ፡ መሥዋዕት ፡ ጠቦት ፡ የሎግ ፡ መስፈሪያ
ውንም ፡ ዘይት ፡ ይወስዳል ፤ ካህኑም ፡ ለመወ
ዝወዝ ፡ ቍርባን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይወ
ዘውዝቸዋል ። የበደሉንም ፡ መሥዋዕት ፡ ጠቦት ፡ ፲፰
ያርዳል ፤ ካህኑም ፡ ከበደሉ ፡ መሥዋዕት ፡ ደም ፡
ወስዶ ፡ የሚነጻውን ፡ ሰው ፡ የቀኝ ፡ ጆሮውን ፡
ጫፍ ÷ የቀኝ ፡ እጁንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ የቀኝ ፡
እግሩንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ ያስነካዋል ። ካህኑም ፡ ፲፱
ከዘይቱ ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ ውስጥ ፡ ያፈሰሰዋል ።
ካህኑም ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ ዘይት ፡ ፳
በቀኝ ፡ ጣቱ ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ያረጨዋል ። ካህኑም ፡ በእጁ ፡ ውስጥ ፡ ፳፡
ካለው ፡ ዘይት ፡ የሚነጻውን ፡ ሰው ፡ የቀኝ ፡ ጆሮ

ውን ፡ ጫፍ ÷ የቀኝ ፡ እጁንም ፡ አውራ ፡ ጣት ÷
የቀኝ ፡ እግሩንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ የበደል
መሥዋዕት ፡ ደም ፡ በረፈበት ፡ ላይ ፡ ያስነካዋል ።
፳፱ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያስተሰርይለት ፡ ዘንድ ፡
በካህኑ ፡ እጅ ፡ ውስጥ ፡ የቀረውን ፡ ዘይት ፡ በሚ
፴ ፡ ነጻው ፡ ሰው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ያደርገዋል ። እንደ
ሚቻለው ፡ ከዋናሶች ፡ ወይም ፡ ከርግብ ፡ ግልገ
፴፩ ፡ ሎች ፡ አንዱን ፡ ያቀርባል ። እንደሚቻለው ፡
አንዱን ፡ ለኃጢአት ፡ መሥዋዕት ÷ ሌላውንም ፡
ከእህል ፡ ቍርባን ፡ ጋር ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋ
ዕት ፡ ያቀርባል ፡ ካህኑም ፡ ለሚነጻው ፡ ሰው ፡
፴፪ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያስተሰርይለታል ። ለመ
ንጻቱ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ ለማያገኝ ፡ የለ
ምጽ ፡ ደዌ ፡ ላለበት ፡ ሰው ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ።
፴፫ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እን
፴፬ ዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፡ — ወደምሰጣችሁ ፡
ርስት ፡ ወደ ፡ ከነዓን ፡ ምድር ፡ በገባችሁ ፡ ጊዜ ÷
እኔም ፡ የለምጽ ፡ ደዌ ፡ በርስታችሁ ፡ ምድር ፡
፴፭ በእንድ ፡ ቤት ፡ ባደረገው ፡ ጊዜ ÷ ባለቤቱ ፡
መጥቶ ፡ ካህኑን ፡ — ደዌ ፡ በቤቴ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡
፴፮ ይመስለኛል ፡ ብሎ ፡ ይንገረው ። ካህኑም ፡ በቤቱ ፡
ውስጥ ፡ ያለው ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ እንዳይረክስ ÷
እርሱ ፡ ደዌውን ፡ ለማየት ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ሰይገባ ÷
ቤቱን ፡ ባዶ ፡ እንዲያደርጉት ፡ ያዝዛል ፡ በኋላም ፡
፴፯ ካህኑ ፡ ቤቱን ፡ ለማየት ፡ ይገባል ። ደዌውንም ፡
ያያል ፡ እነሆም ÷ ደዌው ፡ በግንቡ ፡ ላይ ፡ በአረ
ንጓዴና ፡ በቀይ ፡ ቢኘሮረጕር ÷ መልኩም ፡
፴፰ ወደ ፡ ግንቡ ፡ ውስጥ ፡ ቢጠልቅ ÷ ካህኑ ፡ ከቤቱ ፡
ውስጥ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ በር ፡ ወጥቶ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡
፴፱ ቤቱን ፡ ይዘጋዋል ። ካህኑም ፡ በሰባተኛው ፡
ቀን ፡ ተመልሶ ፡ ያያል ፡ እነሆም ÷ ደዌው ፡ በቤቱ ፡
፵ ግንብ ፡ ላይ ፡ ቢሰፋ ÷ ካህኑ ፡ ደዌ ፡ ያለባቸውን ፡
ድንጋዮች ፡ እንዲያወጡ ÷ ከከተማውም ፡ ወደ ፡
ውጭ ፡ ወደ ፡ ረከሰው ፡ ስፍራ ፡ እንዲጥሉአ
፵፩ ቸው ፡ ያዝዛል ። ቤቱንም ፡ በውስጡ ፡ በዙሪ
ያው ፡ ያስፍቀዋል ፡ የፋቁትንም ፡ የምርጊቱን ፡
አፈር ፡ ከከተማው ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወደ ፡ ረከሰ ፡
፵፪ ስፍራ ፡ ያፈስሱታል ። በእነዚያም ፡ ድንጋዮች ፡
ስፍራ ፡ ሌሎች ፡ ድንጋዮች ፡ ያገባሉ ፤ ሌላም ፡
ጭቃ ፡ ወስደው ፡ ቤቱን ፡ ይመርጉታል ።
፵፫ ደዌውም ፡ ዳግም ፡ ቢመለስ ፡ ድንጋዮቹም ፡
ከወጡ ፡ ቤቱም ፡ ከተፋቀና ፡ ከተመረገ ፡ በኋላ ፡
፵፬ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ቢሰፋ ÷ ካህኑ ፡ ገብቶ ፡ ያያል ፤
እነሆም ÷ ደዌው ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ቢሰፋ ÷
በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ እየፋገ ፡ የሚሄድ ፡
፵፭ ለምጽ ፡ ነው ፡ ርኩስ ፡ ነው ። ቤቱንም ÷ ድንጋ
ዮቹንም ÷ እንጨቱንም ÷ የቤቱንም ፡ ምርጊት ፡
ሁሉ ፡ ያፈርሳል ፡ እነርሱንም ፡ ከከተማው ፡ ወደ ፡
፵፮ ውጭ ፡ ወደ ፡ ርኩስ ፡ ስፍራ ፡ ያወጣል ። በተዘ
ጋበትም ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ የሚገባ ፡
፵፯ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ይሆናል ። በቤ
ቱም ፡ የሚተኛ ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ፡ በቤቱም ፡
የሚበላ ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ።
፵፰ ካህኑም ፡ ገብቶ ፡ ቢያይ ÷ እነሆም ÷ ቤቱ ፡
ከተመረገ ፡ በኋላ ፡ ደዌው ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ባይ
ሰፋ ÷ ደዌው ፡ ስለ ፡ ሻረ ፡ ካህኑ ፡ ቤቱን ፡ —
ንጹሕ ፡ ነው ፡ ይለዋል ። ቤቱንም ፡ ለማንጻት ፡ ፵፱
ሁለት ፡ ወፎች ÷ የዝግባም ፡ እንጨት ÷ ቀይ ፡
ግምጃም ÷ ሂሶጵም ፡ ይወስዳል ። እንደኛው ፡ ፶
ንም ፡ ወፍ ፡ በሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ውስጥ ፡ ከምንጩ ፡
ውኃ ፡ በላይ ፡ ያርዳል ። የዝግባውን ፡ እንጨት ፡ ፶፩
ሂሶጵንም ÷ ቀዩንም ፡ ግምጃ ÷ ሕያውንም ፡ ወፍ ፡
ወስዶ ፡ በታረደው ፡ ወፍ ፡ ደምና ፡ በምንጩ ፡
ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ይነክራቸዋል ÷ ቤቱንም ፡ ሰባት ፡
ጊዜ ፡ ይረጨዋል ። ቤቱንም ፡ በወፉ ፡ ደም ፡ በም ፡ ፶፪
ንጩም ፡ ውኃ ፡ በሕያውም ፡ ወፍ ፡ በዝግባ
ውም ፡ እንጨት ፡ በሂሶጵም ፡ በቀዩም ፡ ግምጃ ፡
ያነጻዋል ። ሕያውንም ፡ ወፍ ፡ ከከተማ ፡ ወደ ፡ ፶፫
ሜዳ ፡ ይሰድደዋል ፤ ለቤቱም ፡ ያስተሰርይለ
ታል ÷ ንጹሕም ፡ ይሆናል ።
ይህም ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ ለሁሉ ፡ ዓይነት ፡ ለምጽ ፡ ፶፬
ደዌ ÷ ለቁረቁርም ÷ በልብስና ፡ በቤትም ፡ ላለ ፡ ፶፭
ለምጽ ÷ ለእባጭም ÷ ለብጉርም ÷ ለቅቁቻም ፡ ፶፮
በሚረክስና ፡ በሚነጻ ፡ ጊዜ ፡ እንዲያስታውቅ ፡ ፶፯
ይህ ፡ የለምጽ ፡ ሕግ ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፭ ።

፩ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እን
ዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፡ — ለእስራኤል ፡
፪ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብላችሁ ፡ ንገሩአቸው ፡ —
ማንም ፡ ሰው ፡ ከሥጋው ፡ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ቢወጣ ÷
ስለሚፈስሰው ፡ ነገር ፡ ርኩስ ፡ ነው ። ስለሚፈ ፫
ስሰው ፡ ነገር ፡ ርኵስነቱ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ፈሳሹ ፡
ነገር ፡ ከሥጋው ፡ ቢፈስስ ፡ ወይም ፡ ከመፍሰሱ ፡
ቢቆም ÷ ርኩስ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ፬
ያለበት ፡ ሰው ፡ የሚተኛበት ፡ መኝታ ፡ ሁሉ ፡
ርኩስ ፡ ነው ፤ የሚቀመጥበትም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
ርኩስ ፡ ነው ። መኝታውንም ፡ የሚነካ ፡ ሁሉ ፡ ፭
ልብሱን ፡ ይጠብ ÷ በውኃም ፡ ይታጠብ ፤ እስከ ፡
ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ነው ። ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ፮
ያለበት ፡ ሰው ፡ በተቀመጠበት ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የሚ
ቀመጥበት ፡ ሰው ፡ ልብሱን ፡ ይጠብ ÷ በው
ኃም ፡ ይታጠብ ÷ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡
ርኩስ ፡ ነው ። ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ያለበትን ፡ የሰ ፯
ውን ፡ ሥጋ ፡ የሚነካ ፡ ልብሱን ፡ ይጠብ ÷ በው
ኃም ፡ ይታጠብ ÷ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡
ነው ። ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ በንጹሕ ፡ ፰
ሰው ፡ ላይ ፡ ቢተፋ ÷ ልብሱን ፡ ይጠብ ÷ በው
ኃም ፡ ይታጠብ ÷ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡
ነው ። ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ የተቀመ ፱
ጠበት ፡ ኮርቻ ፡ ሁሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ። ከበታ ፱
ቹም ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ የሚነካ ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡
ማታ ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ እነዚህንም ፡ ነገ
ሮች ፡ የሚያነሣ ፡ ልብሱን ፡ ይጠብ ÷ በውኃም ፡
ይታጠብ ÷ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡
ነው ። ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ እጁን ፡ ፲፩
በውኃ ፡ ሳይታጠብ ፡ የሚነካው ፡ ሁሉ ፡ ልብ
ሱን ፡ ይጠብ ÷ በውኃም ፡ ይታጠብ ÷ እስከ ፡

ማታም ፡ ርኩስ ፡ ነው ። ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡
ሰው ፡ የሚነካውን ፡ የሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ይስበሩት ፤
የእንጨቱም ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ በውኃ ፡ ይታጠብ ። ፲፪
ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ከፈሳሹ ፡ ነገር ፡
ሲነጻ ፡ ስለ ፡ መንጻቱ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይቈጥራል ፤
ልብሱንም ፡ ያጥባል ÷ ገላውንም ፡ በምንጭ ፡
ውኃ ፡ ይታጠባል ÷ ንጹሕም ፡ ይሆናል ። በስ ፲፫
ምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ሁለት ፡ ዋኖሶች ፡ ወይም ፡
ሁለት ፡ የርግብ ፡ ግልገሎች ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ መገ
ናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ይመጣል ÷ ለካህኑም ፡ ይሰጣቸዋል ።
ካህኑም ፡ አንደኛውን ፡ ለኃጢአት ፡ መሥዋ ፲፬
ዕት ÷ ሌላውንም ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡
ያቀርባል ፤ ካህኑም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡
ስለ ፡ ፈሳሹ ፡ ነገር ፡ ያስተሰርይለታል ።
የማንም ፡ ሰው ፡ ዘር ፡ ከእርሱ ፡ ቢወጣ ÷ ገላ ፲፭
ውን ፡ ሁሉ ፡ በውኃ ፡ ይታጠባል ÷ እስከ ፡ ማታም ፡
ርኩስ ፡ ነው ። ዘር ፡ የነካው ፡ ልብስ ፡ ሁሉ ፡ ቁር
በትም ፡ ሁሉ ፡ በውኃ ፡ ይታጠባል ÷ እስከ ፡
ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ነው ። ወንዱ ፡ በሴ ፲፮
ቲቱ ፡ ቢደርስባት ፡ ሁለቱ ፡ በውኃ ፡ ይታጠቡሉ ÷
እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩሶች ፡ ናቸው ።
ሴት ፡ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ቢኖርባት ፡ በሥጋዋም ፡
ያለው ፡ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ደም ፡ ቢሆን ÷ በመርገ
ምዋ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ትቀመጣለች ፤ የሚነካ ፡
ትም ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ነው ። ፲፱
መርገምም ፡ ስትሆን ፡ የምትተኛበት ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ የምትቀመጥበትም ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ። መኝታዋንም ፡ የሚነካ ፡
ሁሉ ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ÷ በውኃም ፡ ይታጠ
ባል ÷ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ነው ። ፲፯
የምትቀመጥበትንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የሚነካ ፡
ሁሉ ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ÷ በውኃም ፡ ይታጠ
ባል ÷ እስከ ፡ ማታም ፡ ርኩስ ፡ ነው ። በመኝ
ታዋም ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በምትቀመጥበት ፡ ነገር ፡
ላይ ፡ ቢሆን ፡ ሲነካው ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡
ርኩስ ፡ ነው ። ማንም ፡ ከእርስዋ ፡ ጋር ፡ ቢተኛ ፡
መርገምዋም ፡ ቢነካው ÷ ሰባት ፡ ቀን ፡ ርኩስ ፡
ነው ፤ የሚተኛበትም ፡ መኝታ ፡ ሁሉ ፡ ርኩስ ፡
ነው ።
ሴትም ፡ ከመርገም ፡ ቀን ፡ ሌላ ፡ ደምዋ ፡ ብዙ ፡
ቀን ፡ ቢፈስስ ÷ ወይም ፡ ደምዋ ፡ ከመርገምዋ ፡
ወራት ፡ የሚበልጥ ፡ ቢፈስስ ÷ በመርገምዋ ፡
ወራት ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ እንዲሁ ፡ በፈሳሽዋ ፡
ርኵስነት ፡ ወራት ፡ ትሆናለች ፤ ርኩስ ፡ ናት ። ፲፱
ደምዋም ፡ በሚፈስስበት ፡ ወራት ፡ ሁሉ ፡ የምት
ተኛበት ፡ መኝታ ፡ ሁሉ ፡ በመርገምዋ ፡ ጊዜ ፡
እንደ ፡ ነበረው ፡ መኝታ ፡ ያለ ፡ ይሆንባታል ፤
የምትቀመጥበት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ መርገ
ምዋ ፡ ርኵስነት ፡ ርኩስ ፡ ነው ። እነዚህንም ፡
ነገሮች ፡ የሚነካ ፡ ሁሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ ልብሱ ፲፰
ንም ፡ ያጥባል ÷ በውኃም ፡ ይታጠባል ÷ እስከ ፡
ማታም ፡ ርኩስ ፡ ነው ። ከፈሳሽዋም ፡ ብትነጻ ፡
ሰባት ፡ ቀን ፡ ትቈጥራለች ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡
ንጹሕ ፡ ትሆናለች ። በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ፳፱
ሁለት ፡ ዋኖሶች ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ የርግብ ፡ ግል
ገሎች ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡
ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ታመጣቸዋለች ። ካህኑም ፡ ፴
አንደኛውን ፡ ለኃጢአት ፡ መሥዋዕት ÷ ሌላው
ንም ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርባል ፤
ካህኑም ፡ ስለ ፡ ፈሳሽዋ ፡ ርኵስነት ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ፊት ፡ ያስተሰርይላታል ።
እንዲሁም ፡ በእነርሱ ፡ መካከል ፡ ያለችውን ፡ ፴፩
ማደሪያዬን ፡ ባረከሱ ፡ ጊዜ ÷ በርኵስነታቸው ፡
እንዳይሞቱ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከርኵስን
ታቸው ፡ ለያቸው ።
ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ላለበት ፡ ሰው ÷ ይረክስም ፡ ፴፪
ዘንድ ፡ ዘሩ ፡ ለሚወጣበት ፡ ሰው ÷ በመርገም ፴፫
ዋም ፡ ለታመመች ÷ ፈሳሽም ፡ ነገር ፡ ላለባቸው ፡
ለወንድም ፡ ለሴትም ÷ የረከሰችንም ፡ ሴት ፡
ለሚገናኝ ፡ ሰው ፡ ሕጉ ፡ ይኸው ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የቀረቡና ፡ የሞቱ ፡ ፩
ሁለቱ ፡ የአሮን ፡ ልጆች ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ሙሴን ፡ ተናገረው ፤ እግዚአብሔርም ፡ ፪
ሙሴን ፡ አለው ፡ — እኔ ፡ በስርየቱ ፡ መክደኛ ፡
ላይ ፡ በደመናው ፡ ውስጥ ፡ እታያለሁና ፡ እንዳ
ይሞት ፡ በመጋረጃው ፡ ውስጥ ፡ በታቦቱ ፡ ላይ ፡
ወዳለው ፡ ወደ ፡ ስርየቱ ፡ መክደኛ ፡ ወደ ፡ ተቀ
ደሰው ፡ ስፍራ ፡ ሁልጊዜ ፡ እንዳይገባ ፡ ለወን
ድምህ ፡ ለአሮን ፡ ንገረው ። እንዲሁ ፡ አሮን ፡ ፫
ለኃጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ወይፈን ÷ ለሚቃ
ጠል ፡ መሥዋዕትም ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ይዞ ፡
ወደ ፡ ተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡ ይገባ ። የተቀደሰ ፡ ፬
ውን ፡ የበፍታ ፡ ቀሚስ ፡ ይልበስ ÷ የበፍታ
ውም ፡ ሱሪ ፡ በገላው ፡ ላይ ፡ ይሁን ÷ የበፍ
ታውንም ፡ መታጠቂያ ፡ ይታጠቅ ÷ የበፍታ
ውንም ፡ መጠምጠሚያ ፡ ይጠምጥም ፤ እነ
ዚህ ፡ የተቀደሱ ፡ ልብሶች ፡ ናቸው ፤ ገላው
ንም ፡ በውኃ ፡ ታጥቦ ፡ ይልበሳቸው ። ከእስራ ፫
ኤልም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ለኃጢአት ፡ መሥ
ዋዕት ፡ ሁለት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ÷ ለሚቃጠ
ልም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ይው
ሰድ ።
አሮንም ፡ ለእርሱ ፡ ያለውን ፡ የኃጢአቱን ፡ ፮
መሥዋዕት ፡ ወይፈን ፡ ያቀርባል ÷ ለራሱም ፡
ለቤተ ፡ ሰቡም ፡ ያስተሰርያል ። ሁለቱንም ፡ ፯
አውራ ፡ ፍየሎች ፡ ወስዶ ፡ በመገናኛው ፡ ድን
ኳን ፡ ደጃፍ ፡ አጠገብ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡
ያቆማቸዋል ። አሮንም ፡ በሁለቱ ፡ ፍየሎች ፡ ፰
ላይ ፡ ዕጣ ፡ ይጥልባቸዋል ÷ አንዱን ፡ ዕጣ ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ ሌላውንም ፡ ዕጣ ፡ ለሚለቀቅ ።
አሮንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዕጣ ፡ የሆነበትን ፡ ፱
ፍየል ፡ ያቀርባል ÷ ስለ ፡ ኃጢአትም ፡ መሥዋ
ዕት ፡ ያደርገዋል ። የመለቀቅም ፡ ዕጣ ፡ የሆነበ
ትን ፡ ፍየል ፡ ያስተሰርይበት ፡ ዘንድ ÷ ለመለቀ ፲
ቅም ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ይሰድደው ፡ ዘንድ ፡

በሕይወቱ፥ በእግዚአብሔር፤ ፊት፥ ያቆመዋል ።
፲፩ አሮንም ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ኃጢአት ፡ የሚሠዋ
ውን ፡ መሥዋዕት ፡ ወይፈኑን ፡ ያቀርባል ፤
ለራሱም ፡ ለቤተ ፡ ሰቡም ፡ ያስተሰርያል ፡ ስለ ፡
ኃጢአቱ ፡ የእርሱን ፡ መሥዋዕት ፡ ወይፈኑን ፡
፲፪ ያርዳል ። በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ካለው ፡
መሠዊያ ፡ ላይ ፡ የእሳት ፡ ፍም ፡ አምጥቶ ፡ ጥና
ውን ፡ ይሞላል ÷ ከተወቀጠውም ፡ ከጣፋጭ ፡
ዕጣን ፡ እጁን ፡ ሙሉን ፡ ይወስዳል ፡ ወደ ፡ መጋ
፲፫ ረጃውም ፡ ውስጥ ፡ ያመጣዋል ። እንዳይሞ
ትም ፡ የጢሱ ፡ ደመና ፡ በምስክሩ ፡ ላይ ፡ ያለ
ውን ፡ መክደኛ ፡ ይሸፍን ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ፊት ፡ ዕጣኑን ፡ በእሳቱ ፡ ላይ ፡ ያደርጋል ።
፲፬ ከወይፈኑም ፡ ደም ፡ ወስዶ ፡ በስርየቱ ፡ መክደኛ ፡
ላይ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ በጣቱ ፡ ይረጨዋል ፡
ከደሙም ፡ በመክደኛው ፡ ፊት ፡ በጣቱ ፡ ሰባት ፡
ጊዜ ፡ ያረጫል ።
፲፭ ስለ ፡ ሕዝቡም ፡ ኃጢአት ፡ የሚሠዋውን ፡
መሥዋዕት ፡ ፍየል ፡ ያርዳል ÷ ደሙንም ፡ ወደ ፡
መጋረጃው ፡ ውስጥ ፡ ያመጣዋል ፡ በወይፈኑም ፡
ደም ፡ እንዳደረገ ፡ በፍየሉ ፡ ደም ፡ ያደርጋል ፤
በመክደኛውም ፡ ላይና ፡ በመክደኛውም ፡ ፊት ፡
፲፮ ይረጨዋል ። ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ርኵስነት ፡
ከመተላለፋቸውም ፡ ከኃጢአታቸውም ፡ የተ
ነሣ ፡ ለመቅደሱ ፡ ያስተሰርይለታል ፤ እንዲ
ሁም ፡ በርኵስነታቸው ፡ መካከል ፡ ከእነርሱ ፡
ጋር ፡ ለኖረች ፡ ለመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ያደር
፲፯ ጋል ። እርሱም ፡ ለማስተስረይ ፡ ወደ ፡ መቅ
ደሱ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ለራሱ ÷ ለቤተ ፡ ሰቡም ÷
ለእስራኤል ፡ ጉባዔ ፡ ሁሉ ፡ አስተስርዮ ፡ እስኪ
ወጣ ፡ ድረስ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡
ማንም ፡ አይኖርም ። በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡
ወዳለው ፡ ወደ ፡ መሠዊያ ፡ ወጥቶ ፡ ያስተሰርይ
ለታል ፡ ከወይፈኑም ፡ ደም ፡ ከፍየሉም ፡ ደም ፡
ወስዶ ፡ በመሠዊያው ፡ ዙሪያ ፡ ያሉትን ፡ ቀን
፲፱ ዶች ፡ ያስነክል ። ከደሙም ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡
ሰባት ፡ ጊዜ ፡ በጣቱ ፡ ይረጫል ÷ ከእስራኤልም ፡
ልጆች ፡ ርኵስነት ፡ ያነጻዋል ÷ ይቀድሰውማል ።
፳ መቅደሱንም ÷ የመገናኛውንም ፡ ድንኳን ÷
መሠዊያውንም ፡ ማስተስረይ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡
፳፩ ሕያውን ፡ ፍየል ፡ ያቀርባል ፡ አሮንም ፡ ሁለ
ቱን ፡ እጆቹን ፡ በሕያው ፡ ፍየል ፡ ራስ ፡ ላይ ፡
ይጭናል ÷ በላዩም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡
በደል ፡ ሁሉ ፡ መተላለፋቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ኃጢ
አታቸውንም ፡ ሁሉ ፡ ይናዝዛል ፤ በፍየሉም ፡
ራስ ፡ ላይ ፡ ያሸክመዋል ÷ በተዘጋጀው ፡ ሰውም ፡
፳፪ እጅ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ይሰድደዋል ። ፍየ
ሉም ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ በረሀ ፡
ይሸከማል ፤ ፍየሉንም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡
ይለቅቀዋል ።
፳፫ አሮንም ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ይገ
ባል ÷ ወደ ፡ መቅደሱም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ የለበሰ
ውን ፡ የበፍታ ፡ ልብስ ፡ ያወልቃል ÷ በዚያም ፡
፳፬ ይተወዋል ፡ በተቀደሰውም ፡ ስፍራ ፡ ገላውን ፡
በውኃ ፡ ይታጠባል ÷ ሌላውንም ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡
ይወጣል ፤ የእርሱንም ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋ
ዕት ÷ የሕዝቡንም ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡
ያቀርባል ÷ ለራሱም ፡ ለሕዝቡም ፡ ያስተሰር
ያል ። የኃጢአቱንም ፡ መሥዋዕት ፡ ስብ ፡ በመ ፳፭
ሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ። ለመለቀቅ ፡ የሚ ፳፮
ሆነውን ፡ ፍየል ፡ የወሰደ ፡ ሰው ፡ ልብሱን ፡
ያጥባል ÷ ገላውንም ፡ በውኃ ፡ ይታጠባል ÷ ከዚ
ያም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ይገባል ። ለማስተስ ፳፯
ረያም ፡ እንዲሆን ፡ ይማቸው ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡
የገባውን ፡ የኃጢአቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ወይፈ
ንና ፡ የኃጢአቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ፍየል ፡ ከሰ
ፈሩ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ያወጡአቸዋል ፤ ቁርበታ
ቸውንም ÷ ሥጋቸውንም ÷ ፈርሰቸውንም ፡ በእ
ሳት ፡ ያቃጥላሉ ። ያቃጠላቸውም ፡ ሰው ፡ ልብ ፳፰
ሱን ፡ ያጥባል ÷ ገላውንም ፡ በውኃ ፡ ይታጠ
ባል ÷ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሰፈር ፡ ይገባል ።
ይህም ፡ የዘላለም ፡ ሥርዓት ፡ ይሁንላችሁ ፤ ፳፱ የካ
በዚህ ፡ ቀን ፡ ትነጹ ፡ ዘንድ ፡ ማስተስረያ ፡ ይሆ
ንላችኋልና ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በአ
ሥረኛው ፡ ቀን ፡ ራሳችሁን ፡ አስጨንቋት ÷ የአ
ገር ፡ ልጅም ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ የተቀመ
ጠም ፡ እንግዳ ፡ ሥራን ፡ ሁሉ ፡ አትሥሩበት ፡
በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ከኃጢአታችሁ ፡
ሁሉ ፡ ትነጻላችሁ ። ታላቅ ፡ ሰንበት ፡ ይሆንላ ፳፱ የካ
ችኋል ÷ ራሳችሁንም ፡ ታዋርዳላችሁ ፤ የዘላለም ፳፱ የካ
ሥርዓት ፡ ነው ። የሚቀባውም ፡ በአባቱም ፡
ፋንታ ፡ ካህን ፡ ሊሆን ፡ የሚክነው ፡ ካህን ፡ ያስ
ተስርይ ÷ የተቀደሰውንም ፡ የበፍታ ፡ ልብስ ፡
ይልበስ ፤ ለቅድስተ ፡ ቅዱሳንም ፡ ያስተስርይ ፳፱ የካ
ለመገናኛውም ፡ ድንኳን ፡ ለመሠዊያውም ፡ ያስ
ተስርይ ፤ ለካህናቱም ፡ ለጉባኤውም ፡ ሕዝብ ፳፱ የካ
ሁሉ ፡ ያስተስርይ ። ይህም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በዓ
መት ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ስለ ፡ ኃጢአታ
ቸው ፡ ሁሉ ፡ ያስተሰርይ ፡ ዘንድ ፡ የዘላለም ፡
ሥርዓት ፡ ይሁንላችሁ ። እግዚአብሔርም ፡
ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ፩
ተናገረው ፡ — ለአሮንና ፡ ለልጆቹ ፡ ለእስራኤ ፪
ልም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ንገር ፡ — ፡
እግዚአብሔር ፡ ያዘዘው ፡ ይህ ፡ ነው ÷ እንዲህም ፡
አለ ፡ — ከእስራኤል ፡ ቤት ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ፫
በሬ ፡ ወይም ፡ በግ ፡ ወይም ፡ ፍየል ፡ በያርድ ÷
በሰፈሩ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ከሰፈሩ ፡ ውጭ ፡ ቢያ ፬
ርደው ÷ በእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ፊት ፡ ለአ
ግዚአብሔር ፡ ቍርባን ፡ ያቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡
መገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ በያመጣው ÷
ደሙ ፡ በዚያ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ይቈጠርበታል ፤
ደም ፡ አፍስሶአል ፤ ያም ፡ ከሕዝቡ ፡ ተለይቶ ፡
ይጥፋ ። ስለዚህ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በሜዳ ፡ ፭
የሚያርዱትን ፡ መሥዋዕታቸውን ፡ ወደ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡
ያመጡታል ፤ ወደ ፡ ካህኑም ፡ አምጥተው ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ለደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡
ይሠዉታል ። ካህኑም ፡ በመገናኛው ፡ ድን
ኳን ፡ ደጃፍ ፡ በለው ፡ በእግዚአብሔር ፡ መሠ
ዊያ ፡ ላይ ፡ ደሙን ፡ ይረጨዋል ÷ ስቡንም ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲሆን ፡
ያቃጥለዋል ። መሥዋዕታቸውንም ፡ ደግሞ ፡
ከከቅለው ፡ ላመነዘሩባቸው ፡ ለሰይጣናት ፡ አይ ፮
ሠዉ ። ይህ ፡ ለእነርሱ ፡ ለልጅ ፡ ልጃቸው ፡
ለዘላለም ፡ ሥርዓት ፡ ይሁን ።
ለእነርሱም ፡ እንዲህ ፡ በላቸው ፡ — ከእስራ ፯
ኤል ፡ ቤት ፡ በመካከላቸውም ፡ ከሚኖሩ ፡ እን
ግዶች ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የሚቃጠል ፡ መሥ
ዋዕት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕት ፡ ቢያቅርብ ÷
ለእግዚአብሔር ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ መገና
ኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ በያመጣው ÷ ያ ፡ ሰው ፡
ከሕዝቡ ፡ ተለይቶ ፡ ይጥፋ ።
ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ወይም ፡ በመካከላ ፮
ቸው ፡ ከሚኖሩ ፡ እንግዶች ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡
ደም ፡ ቢበላ ÷ ደም ፡ በሚበላው ፡ በዚያ ፡ ሰው ፡
ላይ ፡ ፊቴን ፡ አከብድበታለሁ ÷ ያንንም ፡ ሰው ፡
ከሕዝቡ ፡ ለይቼ ፡ አጠፋዋለሁ ። የሥጋ ፡ ሕይ
ወት ፡ በደሙ ፡ ውስጥ ፡ ነውና ፤ ደሙም ፡ ከሕይ
ወቱ ፡ የተነሣ ፡ ያስተሰርያልና ፤ በመሠዊያው ፡
ላይ ፡ ለነፍሳችሁ ፡ ማስተስረያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡
ሰጥ ፡ ለእናንተ ፡ ሰጠሁት ። ስለዚህ ፡ የእስራ
ኤል ፡ ልጆች ፡ — ከእናንተ ፡ ማንም ፡ ደምን ፡
አይበላም ÷ በመካከላችሁም ፡ ከሚኖሩ ፡ እንግ
ዶች ፡ ማንም ፡ ደምን ፡ አይበላም ፡ አልሁ ። ፱
ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በመካከላቸውም ፡
ከሚኖሩ ፡ እንግዶች ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የሚ
በላ ፡ እንስሳ ፡ ወይም ፡ ወፍ ፡ እያደነ ፡ ቢይዝ ÷
ደሙን ፡ ያፈስሰል ፡ በአፈርም ፡ ይከድነዋል ።
የሥጋ ፡ ሁሉ ፡ ሕይወትና ፡ ደሙ ፡ አንድ ፡ ነውና ፤
ስለዚህ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ — የሥጋ ፡ ሁሉ ፡
ሕይወት ፡ ደሙ ፡ ነውና ፤ የሥጋውን ፡ ሁሉ ፡
ደም ፡ አትብሉ ፤ የሚበላውም ፡ ሁሉ ፡ ተለ
ይቶ ፡ ይጥፋ ፡ አልኋቸው ። የሞተውን ፡ ወይም ፡
ለአውሬ ፡ የሰበረውን ፡ የሚበላ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ÷
ይኑር ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ እንግዳ ፡ ቢሆን ÷ ልብ
ሱን ፡ ያጥባል ÷ በውኃም ፡ ይታጠባል ÷ እስከ ፡
ማታም ፡ ርኩስ ፡ ይሆናል ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡
ንጹሕ ፡ ይሆናል ። ልብሱንና ፡ ገላውን ፡ በያ
ዕለቱ ፡ ግን ፡ ኃጢአቱን ፡ ይሸከማል ።

ምዕራፍ ፡ ፲፰ ።

እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
ተናገረው ፡ — ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡
ብለህ ፡ ንገራቸው ፡ — ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡
አምላካችሁ ፡ ነኝ ። እንደ ፡ ተቀመጣችሁበት ፡
እንደ ፡ ግብፅ ፡ ምድር ፡ ሥራ ፡ አትሥሩ ፤
እኔም ፡ ወደ ፡ እርስዋ ፡ እንደማገባችሁ ፡ እንደ ፡
ከነዓን ፡ ምድር ፡ ሥራ ፡ አትሥሩ ፤ በሥርዓታ
ቸውም ፡ አትሂዱ ። ፍርዴን ፡ አድርጉ ÷ በእር
ስዋም ፡ ትሄዱ ፡ ዘንድ ፡ ሥርዓቴን ፡ ጠብቁ ፤
እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ነኝ ። የሚ ፫
ሠራቸው ፡ ሰው ፡ በእነርሱ ፡ በሕይወት ፡ ይኖ
ራልና ፡ ሥርዓቴንና ፡ ፍርዴን ፡ ጠብቁ ፤ እኔ ፡
እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።
ከእናንተም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ኃፍረት ፡ ሥጋ ፡ ፮
ውን ፡ ይገልጥ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ዘመዱ ፡ ሁሉ ፡
አይቅረብ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ። የአባ ፯
ትህን ፡ ኃፍረት ፡ ሥጋና ፡ የእናትህን ፡ ኃፍረት ፡
ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ እናትህ ፡ ናት ፤ ኃፍረት ፡
ሥጋዋን ፡ አትግለጥ ። የአባትህን ፡ ሚስት ፡ ፰
ኃፍረት ፡ ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ የአባትህ ፡ ኃፍረት ፡
ሥጋ ፡ ነው ። የእኅትህን ፡ ኃፍረት ፡ ሥጋ ፡ አት ፱
ግለጥ ፤ የአባትህ ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ የእናትህ ፡
ልጅ ÷ በቤት ፡ ወይም ፡ በውጭ ፡ የተወለደች ፡
ብትሆን ÷ ኃፍረት ፡ ሥጋዋን ፡ አትግለጥ ። የወ ፱
ንድ ፡ ልጅህን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ኃፍረት ፡ ሥጋዋን ፡
ወይም ፡ የሴት ፡ ልጅህን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ኃፍረት ፡
ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ የአንተ ፡ ኃፍረት ፡ ሥጋ ፡
ነውና ። ከአባትህ ፡ የተወለደችውን ፡ የአባት ፲፩
ህን ፡ ሚስት ፡ ልጅ ፡ ኃፍረት ፡ ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤
እኅትህ ፡ ናት ፤ ኃፍረት ፡ ሥጋዋን ፡ አትግለጥ ።
የአባትህን ፡ እኅት ፡ ኃፍረት ፡ ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ ፲፪
የአባትህ ፡ ዘመድ ፡ ናት ። የእናትህን ፡ እኅት ፡ ፲፫
ኃፍረት ፡ ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ የእናትህ ፡ ዘመድ ፡
ናት ። የአባትህን ፡ ወንድም ፡ ኃፍረት ፡ ሥጋ ፡ ፲፬
አትግለጥ ÷ ወደ ፡ ሚስቱም ፡ አትቅረብ ፤ የአ
ጎትህ ፡ ሚስት ፡ ናት ። የምራትህን ፡ ኃፍረት ፡
ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ የልጅህ ፡ ሚስት ፡ ናት ፤ ፲፭
ኃፍረት ፡ ሥጋዋን ፡ አትግለጥ ። የወንድምህን ፡ ፲፮
ሚስት ፡ ኃፍረት ፡ ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ የወንድ
ምህ ፡ ኃፍረት ፡ ሥጋ ፡ ነው ። የሴትንና ፡ የሴት ፡ ፲፯
ልጅዋን ፡ ኃፍረት ፡ ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ የወንድ ፡
ልጅዋን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ የሴት ፡ ልጅዋን ፡
ሴት ፡ ልጅ ፡ ኃፍረት ፡ ሥጋዋን ፡ ትገልጥ ፡ ዘንድ ፡
አታግባ ፤ ዘመዶች ፡ ናቸው ፤ ዝሙት ፡ ነው ።
ሚስትህ ፡ በሕይወት ፡ ሳለች ፡ እኅትዋ ፡ ጣውን ፲፰
ትዋ ፡ እንዳትሆን ÷ ኃፍረት ፡ ሥጋዋን ፡ ትገልጥ ፡
ዘንድ ፡ ከእርስዋ ፡ ጋር ፡ እኅትዋን ፡ አታግባ ።
እርስዋም ፡ በመርገምዋ ፡ ርኵሰት ፡ ሳለች ፡ ፲፱
ኃፍረት ፡ ሥጋዋን ፡ ትገልጥ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሴት ፡
አትቅረብ ። እንዳትረክስበትም ፡ ከባልንጀራህ ፡ ፳
ሚስት ፡ ጋር ፡ አትተኛ ። ከዘርህም ፡ ለሞሎክ ፡ ፳፩
በእሳት ፡ አሳልፈህ ፡ አትስጥ ÷ የአምላክህንም ፡
ስም ፡ አታርክስ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።
ከሴትም ፡ ጋር ፡ እንደምትተኛ ፡ ከወንድ ፡ ጋር ፡ ፳፪
አትተኛ ፤ ጸያፍ ፡ ነገር ፡ ነውና ። እንዳትረክ ፳፫
ስበትም ፡ ከእንስሳ ፡ ጋር ፡ አትተኛ ፤ ሴት ፡ ከእ
ርሱ ፡ ጋር ፡ ትተኛ ፡ ዘንድ ፡ በእንስሳ ፡ ፊት ፡
አትቁም ፤ የተጠላ ፡ ነገር ፡ ነውና ።
በእነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ከሥጋችሁ ፡ የማሳድዳቸው ፡ ፳፬
አሕዛብ ፡ ረክሰዋልና ፤ በእነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡
አትርከሱ ። ምድሪቱም ፡ ረከሰች ፡ ስለዚህ ፡ ፳፭
ኃጢአትዋን ፡ በእርስዋ ፡ ላይ ፡ እመልሳለሁ ÷

ምድሪቱም ፡ የሚኖሩበትን ፡ ሰዎች ፡ ትተፋለች ። ፳፮ ሥርዓቴንና ፡ ፍርዴን ፡ ጠብቁ ፤ እናንተም ፡ የአገሩ ፡ ሎጆች ፡ በእናንተም ፡ መካከል ፡ የሚኖሩት ፡ እንግዶች ፡ ከዚህ ፡ ርኵሰት ፡ ምንም ፡ ፳፯ አትሥሩ ፤ ከእናንተ ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ የአገሩ ፡ ልጆች ፡ ይህን ፡ ርኵሰት ፡ ሁሉ ፡ ሠርተዋልና ፡ ፳፰ ምድሪቱም ፡ ረከሳለችና ፡ በረከሳችኋት ፡ ጊዜ ፡ ምድሪቱ ፡ ከእናንተ ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ ሕዝብ ፡ ፳፱ እንደ ፡ ተፋች ፤ እናንተንስ ፡ እንዳትተፋችሁ ። ከዚህ ፡ ርኵሰት ፡ ሁሉ ፡ ማናቸውን ፡ የሚያደርግ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ከሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ተለይቶ ፡ ይጠፋልና ። ፴ ስለዚህ ፡ ከእናንተ ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ የሠሩትን ፡ ጸያፍ ፡ የሆነውን ፡ ወግ ፡ ሁሉ ፡ እንዳትሠሩ ፥ በእርሱም ፡ እንዳትረክሱ ፡ ሥርዓቴን ፡ ጠብቁ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ነኝ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፱ ።

፩ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ፪ ተናገረው ፦ — ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ — እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ቅዱስ ፡ ነኝና ፡ እናንተ ፡ ፫ ቅዱሳን ፡ ሁኑ ። ከእናንተ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እናቱንና ፡ አባቱን ፡ ይፍራ ፥ ሰንበታቴንም ፡ ጠብቁ ፤ ፬ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ነኝ ። ወደ ፡ ጣዖታትም ፡ ዘወር ፡ አትበሉ ፥ ቀልጠው ፡ የተሠሩትንም ፡ የአማልክት ፡ ምስሎች ፡ ለእናንተ ፡ አታድርጉ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ነኝ ።

፭ የደኅንነትንም ፡ መሥዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስትሠዉ ፡ እርሱን ፡ ይስ ፤ እንድታሰኙ ፮ በት ፡ ሠዉት ። በምትሠዉት ፡ ቀንና ፡ በነጋው ፡ ይበላል ፤ እስከ ፡ ሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ፯ ቢተርፍ ፡ በእሳት ፡ ይቃጠላል ። በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ቢበላ ፡ ጸያፍ ፡ ነው ፥ ደስም ፡ አያሰ ፰ ኝም ፡ የበላውም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰውን ፡ ነገር ፡ አርክሶአልና ፡ ኃጢአቱን ፡ ይሸከማል ፤ ያም ፡ ሰው ፡ ከሕዝቡ ፡ ተለይቶ ፡ ይጥፋ ።

፱ የምድራችሁንም ፡ መከር ፡ በሰበሰባችሁ ፡ ጊዜ ፡ የእርሻችሁን ፡ ድንበር ፡ ፈጽማችሁ ፡ አትጨዱ ፥ የመከሩንም ፡ ቃርሚያ ፡ አትልቀሙ ። ፱ የወይንህንም ፡ ቃርሚያ ፡ አትቃርም ፥ የወደቀውንም ፡ የወይንህን ፡ ፍሬ ፡ አትሰብስብ ፤ ለድሆችና ፡ ለእንግዶች ፡ ተወው ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ነኝ ።

፲፩ አትስረቁ ፥ አትካዱም ፥ ከእናንተም ፡ እርስ ፡ ፲፪ በርሳችሁ ፡ ሐሰት ፡ አትነጋገሩ ። በስሜም ፡ በሐሰት ፡ አትማሉ ፥ የአምላካችሁንም ፡ ስም ፡ አታርክሱ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

፲፫ በባልንጀራህ ፡ ግፍ ፡ አታድርግ ፥ አትቀማውም ። የሞያተኛው ፡ ዋጋ ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ ድረስ ፡ ፲፬ በእንተ ፡ ዘንድ ፡ አይደርብህ ። ደንቆሮውን ፡ አትስደብ ፥ በዕውርም ፡ ፊት ፡ ዕንቅፋት ፡ አታድርግ ፥ ነገር ፡ ግን ፡ አምላክህን ፡ ፍራ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

በፍርድ ፡ ዓመፃ ፡ አታድርጉ ፤ ለድሀ ፡ አታ ፲፭ ድላ ፥ ባለ ፡ ጠጋውንም ፡ አታክብር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለባልንጀራህ ፡ በእውነት ፡ ፍረድ ። በሕዝብህ ፡ ፲፮ መካከል ፡ በሸንጋይነት ፡ አትዙር ፤ በባልንጀራህም ፡ ደም ፡ ላይ ፡ አትቁም ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ወንድምህን ፡ በልብህ ፡ አትጥላው ፤ በባል ፲፯ ንጀራህ ፡ ምክንያት ፡ ኃጢአት ፡ እንዳይሆን ፡ ብህ ፡ ገሥጸው ። አትበቀልም ፥ በሕዝብህም ፡ ፲፰ ልጆች ፡ ቂም ፡ አትያዝ ፥ ነገር ፡ ግን ፡ ባልንጀራህን ፡ እንደ ፡ ራስህ ፡ ውደድ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ሥርዓቴን ፡ ጠብቁ ። እንስሳህ ፡ ከሌላ ፡ ዓይ ፲፱ ነት ፡ ጋር ፡ አይደባለቅ ፤ በእርሻህም ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ዘር ፡ አትዝራ ፤ ከሁለት ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ የተሠራ ፡ ልብስ ፡ አትልበስ ።

ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከሴት ፡ ባሪያ ፡ ጋር ፡ ፳ ቢተኛ ፥ እርስዋም ፡ ለባል ፡ የተሰጠች ፡ ዋጋዋም ፡ ያልተከፈለ ፡ እርነት ፡ ያልወጣች ፡ ብትሆን ፥ ቅጣት ፡ አለባቸው ፤ እርነት ፡ አልወጣችምና ፡ አይገደሉም ። እርሱም ፡ የበደሉን ፡ መሥዋዕት ፡ ፳፩ ይዞ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ይመጣል ፥ ለበደልም ፡ መሥዋዕት ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ያመጣል ። ካህኑም ፡ ስለ ፡ ሠራው ፡ ኃጢአት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ፳፪ በበደል ፡ መሥዋዕት ፡ በግ ፡ ያስተሰርይለታል ፥ የሠራውም ፡ ኃጢአት ፡ ይቀርለታል ።

ወደ ፡ አገሩም ፡ በገባችሁ ፡ ጊዜ ፥ የሚበላ ፡ ፳፫ የፍሬ ፡ ዛፍ ፡ ሁሉ ፡ በተከላችሁም ፡ ጊዜ ፥ ፍሬውን ፡ እንዳልተገረዘ ፡ ትቈጥሩታላችሁ ፥ ሦስት ፡ ዓመት ፡ እንዳልተገረዘ ፡ ይሆንላችኋል ፤ አይበላም ። የአራተኛውም ፡ ዓመት ፡ ፍሬ ፡ ሁሉ ፡ ለእግ ፳፬ ዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ቅዱስ ፡ ይሁን ። ፍሬውም ፡ ፳፭ ይበዛላችሁ ፡ ዘንድ ፡ የአምስተኛውን ፡ ዓመት ፡ ፍሬ ፡ ብሉ ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ነኝ ።

ከደሙ ፡ ጋር ፡ ምንም ፡ አትብሉ ፡ አስማ ፳፮ ትም ፡ አታድርጉ ፥ ሞራ ፡ ገላጭም ፡ አትሁኑ ። የራስ ፡ ጠጕራችሁንም ፡ ዙሪያውን ፡ አትከርክ ፳፯ ሙት ፥ ጢማችሁንም ፡ ዙሪያውን ፡ አትቀነጥ ፳፰ ጡት ። ስለ ፡ ሞተውም ፡ ሥጋችሁን ፡ አትንጩ ፥ ገላችሁንም ፡ አትንቀሱት ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ምድሪቱ ፡ ከግልሙትና ፡ ከርኵሰትም ፡ እንዳ ፳፱ ትሞላ ፡ ሴት ፡ ልጅህን ፡ ታመነዝር ፡ ዘንድ ፡ አታርክሳት ። ሰንበታቴን ፡ ጠብቁ ፥ መቅደሴንም ፡ ፴ አክብሩ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ወደ ፡ መናፍስት ፡ ጠሪዎችና ፡ ወደ ፡ ጠንቋ ፴፩ ዮች ፡ አትሂዱ ፤ እንዳተረክስባቸውም ፡ አት ፡ ፈልጉአቸው ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ነኝ ።

በሽበታም ፡ ፊት ፡ ተነሣ ፥ ሽማግሌውንም ፡ ፴፪ አክብር ፥ አምላክህንም ፡ ፍራ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

በአገራችሁ ፡ ውስጥ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ እን ፴፫ ግዳ ፡ ቢቀመጥ ፡ ግፍ ፡ አታድርጉበት ። እና ፴፬ ንተ ፡ በግብፅ ፡ ምድር ፡ እንግዶች ፡ ነበራችሁና ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ የሚቀመጥ ፡ እንግዳ ፡ እንደ ፡ አገር ፡ ሎጅ ፡ ይሁንላችሁ ፥ እርሱንም ፡ እንደ ፡ ራስህ ፡ ውደድ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላ ፴፭ ካችሁ ፡ ነኝ ።

በፍርድ ፥ በመለካትም ፥ በመመዘንም ፥ በመ ፴፮ ስፈርም ፡ ዓመፃ ፡ አታድርጉ ። የእውነትም ፡ ሚዛን ፥ የእውነትም ፡ መመዛኛ ፥ የእውነትም ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፥ የእውነትም ፡ የኢን ፡ መስ ፡ ፈሪያ ፡ ይሁንላችሁ ፤ ከግብፅ ፡ ምድር ፡ ያወጣ ፴፯ ኋችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ ። ሥርዓቴን ፡ ሁሉ ፡ ፍርዴንም ፡ ሁሉ ፡ ጠብቁ ፡ አድርጉም ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ምዕራፍ ፡ ፳ ።

እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ፩ ተናገረው ፦ — ደግሞ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ — ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወይም ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ከሚቀመጡ ፡ እንግዶች ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ዘሩን ፡ ለሞሎክ ፡ ቢሰጥ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ፤ የአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ በድንጋይ ፡ ይውገረው ። መቅደሴን ፡ ያረክስ ፡ ዘንድ ፥ የተቀደሰውንም ፡ ስሜን ፡ ያጐሰቍል ፡ ዘንድ ፡ ዘሩን ፡ ለሞሎክ ፡ ሰጥቶአልና ፡ እኔ ፡ ፫ ዘዚያ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ፊቴን ፡ አዙዳለሁ ፥ ከሕ ፡ ዝቡም ፡ መካከል ፡ ለይቼ ፡ አጠፋዋለሁ ። ዘሩ ፡ ንም ፡ ለሞሎክ ፡ ሲሰጥ ፥ የአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ያን ፡ ቸል ፡ ቢለው ፡ ባይገድሉትም ፥ እኔ ፡ በዚያ ፡ ሰውና ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡ ላይ ፡ ፊቴን ፡ አከብዳለሁ ፡ ፡ ከ ፡ ሕዝቡም ፡ መካከል ፡ ለይቼ ፡ አጠፋዋለሁ ። ከ ፡ ሞሎክም ፡ ጋር ፡ ያመነዝሩ ፡ ዘንድ ፡ የሚከተሉትን ፡ ሁሉ ፡ ከሕዝባቸው ፡ መካከል ፡ ለይቼ ፡ አጠፋለሁ ።

መናፍስት ፡ ጠሪዎችንና ፡ ጠንቋዮችንም ፡ ፬ ሚከተል ፥ በሥራቸውም ፡ በሚያመነዝር ፥ ፫ ዘዚያ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ፊቴን ፡ አከብዳለሁ ፥ ከሕ ፡ ዝቡም ፡ መካከል ፡ ለይቼ ፡ አጠፋዋለሁ ። እን ፬ ዳዲህ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ነኝና ፡ ሰውነታችሁን ፡ ቀድሱ ፥ ቅዱሳንም ፡ ሁኑ ። ሥርዓቴን ፡ ጠብቁ ፥ አድርጉትም ፤ እኔ ፡ የም ፡ ቀድሳችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ። ማናቸውም ፡ ፭ ሰው ፡ አባቱን ፡ ወይም ፡ እናቱን ፡ ቢሰድብ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ፥ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ሰድቦ ፡ አልና ፡ ደሙ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ፮ ወይም ፡ ከባልንጀራው ፡ ሚስት ፡ ጋር ፡ ቢያመ ፡ ነዝር ፡ አመንዝራውና ፡ አመንዝራይቱ ፡ ፈጽ ፡ ሞው ፡ ይገደሉ ። ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከአባቱ ፡ ሚስት ፡ ጋር ፡ ቢተኛ ፡ የአባቱን ፡ ኀፍረት ፡ ሠ ፡ ገለጠአል ፤ ሁለቱ ፡ ፈጽሞው ፡ ይገደሉ ፡ ፡ ደማቸው ፡ በላያቸው ፡ ነው ። ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከምራቱ ፡ ጋር ፡ ቢተኛ ፡ ሁለቱ ፡ ፈጽ ፡ ሞው ፡ ይገደሉ ፤ ጸያፍ ፡ ነገር ፡ አድርገዋል ፤ ፈጽመው ፡ ይገደሉ ፡ ደማቸው ፡ በላያ ፡ ቸው ፡ ነው ። ማናቸውም ፡ ሰው ፡ እናቲቱንና ፡ ፱ ልጂቱን ፡ ቢያገባ ፡ ርኵሰት ፡ ነው ፤ በመካከላ ፡ ችሁ ፡ ኃጢአት ፡ እንዳይሆን ፡ እርሱና ፡ እነርሱ ፡ በእሳት ፡ ይቃጠሉ ። ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከእ ፡ ፲ ንስሳ ፡ ጋር ፡ ቢገናኝ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ፤ እንስ ፡ ሳቱንም ፡ ግደሉአት ። ማናቸይቱም ፡ ሴት ፡ ፡ ፲፩ ወደ ፡ እንስሳ ፡ ብትቀርብ ፥ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ብትገናኝ ፥ ሴቲቱንና ፡ እንስሳውን ፡ ግደል ፤ ፈጽመው ፡ ይገደሉ ፡ ደማቸው ፡ በላያቸው ፡ ነው ።

ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የአባቱን ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ ፡ ፲፪ የእናቱን ፡ ልጅ ፡ እኅቱን ፡ ቢያገባ ፥ ኀፍረተ ፡ ሠ ፡ ገዋንም ፡ ቢያይ ፥ እርስዋም ፡ ኀፍረተ ፡ ሠ ፡ ገ ፡ ውን ፡ ብታይ ፥ ይህ ፡ ጸያፍ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ በሕ ፡ ዝባቸውም ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ይገደሉ ፤ የእኅ ፡ ቱን ፡ ኀፍረተ ፡ ሠ ፡ ገ ፡ ለጠአልና ፡ ኃጢአቱን ፡ ይሸከማል ። ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከበለ ፡ መር ፡ ፲፫ ገም ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ ቢተኛ ፡ ኀፍረተ ፡ ሠ ፡ ገዋንም ፡ ቢ ፡ ገለጥ ፥ ፈሳሽዋን ፡ ገለጠአልና ፥ እርስዋም ፡ የደምዋን ፡ ፈሳሽ ፡ ገለጣለችና ፡ ሁለቱ ፡ ከሕዝ ፡ ባቸው ፡ መካከል ፡ ተለይተው ፡ ይጥፉ ። የአባ ፡ ፲፬ ትህን ፡ ወይም ፡ የእናትህን ፡ እኅት ፡ ኀፍረተ ፡ ሠ ፡ ገ ፡ አትግለጥ ፤ ይህን ፡ የሚያደርግ ፡ የዘመ ፡ ድን ፡ ኀፍረተ ፡ ሠ ፡ ገ ፡ ገልጠአል ፤ ኃጢአ ፡ ቸውን ፡ ይሸከማሉ ። ሰውም ፡ ከእኅቱ ፡ ሚስት ፡ ፲፭ ጋር ፡ ቢተኛ ፡ የአኅቱን ፡ ኀፍረተ ፡ ሠ ፡ ገ ፡ ገልጠአል ፤ ኃጢአታቸውን ፡ ይሸከማሉ ፤ ያለ ፡ ልጅ ፡ ይሞታሉ ። ሰውም ፡ የወንድሙን ፡ ፲፮ ሚስት ፡ ቢያገባ ፡ ርኵሰት ፡ ነው ፤ የወንድሙን ፡ ኀፍረተ ፡ ሠ ፡ ገ ፡ ገልጠአል ፤ ያለ ፡ ልጅ ፡ ይሆ ፡ ናሉ ።

እንግዲህ ፡ ትቀመጡበት ፡ ዘንድ ፡ የማገባችሁ ፡ ፲፯ ምድር ፡ እንዳትተፋችሁ ፡ ሥርዓቴን ፡ ሁሉ ፥ ፍርዴንም ፡ ሁሉ ፡ ጠብቁ ፥ አድርጉትም ። ከፈ ፡ ታችሁ ፡ በምጥላቸውም ፡ ሕዝብ ፡ ወግ ፡ አት ፡ ፲፰ ሄዱ ፤ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አድርገዋልና ፡ ተጸየፍኋ ፡ ቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ እናንተን ፦ ምድራቸ ፡ ፲፱ ውን ፡ ትወርሰላችሁ ፡ ትወርሱአትም ፡ ዘንድ ፡ ወተትና ፡ ማር ፡ የምታፈስሰውን ፡ ምድር ፡ እሰ ፡ ጣችኋለሁ ፡ አልኋችሁ ። እኔ ፡ ከአሕዛብ ፡ የለ ፡ የኋችሁ ፡ አምላካችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ። ፲ እንግዲህ ፡ ከሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለእኔ ፡ ቅዱሳን ፡ ሁኑ ፤ ዘንድ ፡ ከአሕ ፡ ዛብ ፡ ለይቻችኋለሁና ፡ ቅዱሳን ፡ ትሆኑልኛላ ፡ ችሁ ።

ሰው ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ መናፍስትን ፡ ቢጠሩ ፡ ፳፩

ዘፍ ፡ ፡ ፡

፲፯ ፡ ብሔር ፡ አቅርቡ ። ከየማደሪያችሁ ፡ ከመስፈሪ
ያው ፡ ከአሥር ፡ እጅ ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ ከሆነ ፡ መል
ካም ፡ ዳቄት ፡ የተሠራ ፡ ሁለት ፡ የመወዝወዝ ፡
እንጀራ ፡ ታመጣላችሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ለበኩራት ፡ ቀሪበን ፡ እንዳሆን ፡ በእርሾ ፡ ይጋ
፲፰ ገራል ። ከእንጀራውም ፡ ጋር ፡ ነውር ፡ የሌለባ
ቸውን ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ሰባት ፡ ጠቦቶች ፡
አንድ ፡ ወይፈንም ፡ ሁለትም ፡ አውራ ፡ በጎች ፡
ታቀርባላችሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠል ፡
መሥዋዕት ፡ ይሁኑ ፡ ከእህልም ፡ ቀሪበን ፡
ከመጠጡም ፡ ቀሪበን ፡ ጋር ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲሆን ፡ የእሳት ፡ ቀሪበን ፡
፲፱ ፡ ይሁኑ ። አንድም ፡ አውራ ፡ ፍየል ፡ ለኃጢአት ፡
መሥዋዕት ፡ ሁለትም ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡
ጠቦቶች ፡ ለደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ አቅርቡ ። ካ
ፍ ፡ ከሁኑም ፡ ከበሁራቱ ፡ እንጀራ ፡ ከሁለቱም ፡ ጠበ
ቶች ፡ ጋር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመወዝ
ወዝ ፡ ቀሪበን ፡ ይወዘወዛቸዋል ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ፈንታ ፡ ነው ፡ ለካህኑ ፡ ይሁን ።
፳፩ ፡ በዚያም ፡ ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይሆንላችሁ ፡
ዘንድ ፡ ታውጃላችሁ ፡ የተግባር ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡
አታድርጉበት ፡ በምትቀመጡበት ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡
ለልጅ ፡ ልጃችሁ ፡ የዘላለም ፡ ሥርዓት ፡ ነው ።
፳፪ ፡ የምድራችሁንም ፡ መከር ፡ በሰበሰባችሁ ፡
ጊዜ ፡ የእርሻችሁን ፡ ድንበር ፡ ፈጽማችሁ ፡
አትጨዱ ፥የመከሩንም ፡ ቃርሚያ ፡ አትልቀሙ ፡
ለድሆችና ፡ ለእንግዶች ፡ ተዉት ፡ እኔ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ነኝ ። ።
፳፫ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
፳፬ ፡ ተናገረው ፡ — ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡
ብለህ ፡ ንገራቸው ፡ — በሰባተኛው ፡ ወር ፡ በመ
ጀመሪያው ፡ ቀን ፡ ዕረፍት ፥ በመለከት ፡ ድምፅ ፡
መታሰቢያ ፥ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይሁንላችሁ ። ።
፳፭ ፡ የተግባር ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አታድርጉበት ፥ ለእ
ግዚአብሔርም ፡ የእሳት ፡ ቀሪበንን ፡ አቅርቡ ። ።
፳፮ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
፳፯ ፡ ተናገረው ፡ — በዚህ ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ አሥ
ረኛው ፡ ቀን ፡ የማስተስረያ ፡ ቀን ፡ ነው ፤ የተ
ቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይሁንላችሁ ፤ ሰውነታችሁን ፡
አስጨንቁት ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ የእሳት ፡
፳፰ ፡ ቀሪበንን ፡ አቅርቡ ። በእምላካችሁም ፡ በእግ
ዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ማስተስረያ ፡ ይሆንላችሁ ፡
ዘንድ ፡ የማስተስረያ ፡ ቀን ፡ ነውና ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡
፳፱ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አትሥሩ ። በዚያም ፡ ቀን ፡ የማ
ይቀረፅ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከሕዝቡ ፡ ተለይቶ ፡
፴ ፡ ይጥፋ ። በዚያም ፡ ቀን ፡ ሥራ ፡ የሚሠራውን ፡
ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከሕዝቡ ፡ መካከል ፡ አጠፋዋለሁ ።
፴፩ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አታድርጉበት ፤ በምትቀመጡ
በት ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ለልጅ ፡ ልጃችሁ ፡ የዘላለም ፡
፴፪ ፡ ሥርዓት ፡ ነው ። የዕረፍት ፡ ሰንበት ፡ ይሁንላ
ችሁ ፥ ሰውነታችሁንም ፡ አዋርዱ ፤ በወሩ ፡
በዘጠኝኛው ፡ ቀን ፡ በማታ ፡ ጊዜ ፥ ከማታ ፡
ጀምራችሁ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፥ ሰንበታች
ሁን ፡ አድርጉ ።

፴፫ ፡ ለግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተና
ገረው ፡ — ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡
ንገራቸው ፡ በዚህ ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ ከአ
ሥራ ፡ አምስተኛው ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ሰባት ፡
ቀን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የዳስ ፡ በዓል ፡ ይሆናል ።
፴፮ ፡ በመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይሁን ፤
የተግባር ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አታድርጉበት ። ሰባት ፡
፴፯ ፡ ቀን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእሳት ፡ ቀሪበንን ፡ አቅ
ርቡ ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡
ይሁንላችሁ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ የሚቃጠለ
ውን ፡ ቀሪበን ፡ አቅርቡ ፤ ዋና ፡ ጉባኤ ፡ ነው ፤
የተግባር ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አታድርጉበት ።
፴፰ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፥ የእህሉንም ፡
ቀሪበን ፥ መሥዋዕቱንም ፥ የመጠጡንም ፡
ቀሪበን ፥ በየቀኑ ፡ የእሳት ፡ ቀሪበን ፡ ወደ ፡
እግዚአብሔር ፡ ታቀርቡባቸው ፡ ዘንድ ፡ የተቀ
ደሱ ፡ ጉባኤዎች ፡ እንዲሆኑ ፡ የምታውጁአቸው ፡
የእግዚአብሔር ፡ በዓላት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።
እነዚህም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሰንበታት ፡ ሌላ ፥
፴፱ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ከምትሰጡት ፡ ከስጦታችሁ ፡
ሌላ ፥ ከስእለታችሁም ፡ ሁሉ ፡ ሌላ ፥ በፈቃዳ
ችሁም ፡ ከምታቀርቡአቸው ፡ ሁሉ ፡ ሌላ ፡
ናቸው ።
፴፱ ፡ ከሰባተኛውም ፡ ወር ፡ በአሥራ ፡ አምስተ
ኛው ፡ ቀን ፡ የምድሩን ፡ ፍሬ ፡ ካከማቻችሁ ፡
በኋላ ፥የእግዚአብሔርን ፡ በዓል ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡
ጠብቁ ፤ በመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ ዕረፍት ፡ ይሁን ፥
በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ዕረፍት ፡ ይሁን ። በመ
ጀመሪያው ፡ ቀን ፡ የመልካም ፡ ዛፍ ፡ ፍሬ ፥ የሰ
ሌን ፡ ቅርንጫፍ ፥ የለመለመውን ፡ ዛፍ ፡ ቅርን
ጫፍ ፥ የወንዝም ፡ አኻያ ፡ ዛፍ ፡ ውሰዱ ፤ በእ
ምላካችሁም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሰባት ፡
ቀን ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ። ይህንንም ፡ በዓል ፡ በየዓ
፴፩ ፡ መቱ ፤ ሰባት ፡ ቀን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አድርጉ ፤
ለልጅ ፡ ልጃችሁ ፡ የዘላለም ፡ ሥርዓት ፡ ነው ፤
በሰባተኛው ፡ ወር ፡ ትጠብቁታላችሁ ። ሰባት ፡
፴፪-፴፫ ፡ ቀን ፡ በዳሶች ፡ ውስጥ ፡ ትቀመጣላችሁ ፤ ከግ
ብፅ ፡ ምድር ፡ ባወጣኋቸው ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤ
ልን ፡ ልጆች ፡ በዳስ ፡ ውስጥ ፡ እንዳስቀመጥኋ
ቸው ፡ የልጅ ፡ ልጆቻችሁ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፥
በእስራኤል ፡ ያሉት ፡ የአገር ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡
በዳስ ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጡ ፤ እኔ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ነኝ ። ሙሴም ፡ የእግዚአ
ብሔርን ፡ በዓላት ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተና
ገረ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፭ ።

፩ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
፪ ፡ ተናገረው ፡ — መብራቱን ፡ ሁልጊዜ ፡ እንድታበ
ራበት ፡ ለመብራት ፡ ዋና ፡ ተወቅጦ ፡ የተጠለለ ፡
የወይራ ፡ ዘይት ፡ ያመጡልህ ፡ ዘንድ ፡ የእስራ
ኤልን ፡ ልጆች ፡ እዘዛቸው ። በምስክሩ ፡ መጋ
፫ ፡ ረጃ ፡ ውጭ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡
አሮን ፡ ከማታ ፡ እስከ ፡ ማለዳ ፡ ድረስ ፡ በእግዚ

አብሔር ፡ ፊት ፡ ሁልጊዜ ፡ ያስናዳው ፡ ለዘላ
ለም ፡ ለልጅ ፡ ልጃችሁ ፡ ሥርዓት ፡ ይሁን ።
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በጥሩ ፡ መቅረዝ ፡ ላይ ፡
መብራቶቹን ፡ ሁልጊዜ ፡ ያስናዳቸው ።
መልካሙንም ፡ ዳቄት ፡ ወስደህ ፡ አሥራ ፡
ሁለት ፡ ኅብስት ፡ ጋግር ፡ በእንድ ፡ ኅብስት ፡
ውስጥ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከአሥር ፡ እጅ ፡ ሁለት ፡
እጅ ፡ ይሁን ። እነዚህንም ፡ ስድስት ፡ ስድስቱን ፡
በሁለት ፡ ተርታ ፡ አድርገህ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ በጥሩ ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ አኑራቸው ። ለእግዚአ
ብሔርም ፡ ለኅብት ፡ ቀሪበን ፡ በእንጀራው ፡ ላይ ፡
ለመታሰቢያ ፥ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በሁለቱ ፡ ተርታ ፡
ላይ ፡ ጥሩ ፡ ዕጣን ፡ አድርግ ። በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ሁልጊዜ ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ሁሉ ፡ በተርታ ፡
ያድርገው ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ የዘላ
ለም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ነው ። ለአሮንና ፡ ለልጆ
ቹም ፡ ይሁን ፤ በኅብት ፡ ከተደረገው ፡ ከእግዚ
አብሔር ፡ ቀሪበን ፡ በዘላለም ፡ ሥርዓት ፡ ለእ
ርሱ ፡ ቅዱሰ ፡ ቅዱሳን ፡ ነውና ፡ በተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡
ይብሉት ።
፲ ፡ አባቱ ፡ ግብፃዊ ፡ የነበረ ፡ የእስራኤላዊት ፡
ልጅ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ወጣ ፡
የእስራኤላዊቲ ፡ ልጅና ፡ አንድ ፡ እስራኤላዊ ፡
በሰፈር ፡ ውስጥ ፡ ተጣሉ ፡ የእስራኤላዊቱም ፡
ልጅ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ሰደበ ፥ አቃለ
ለውም ፡ ወደ ፡ ሙሴም ፡ አመጡት ። እናቱም ፡
ከዳን ፡ ነገድ ፡ የደብራይ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ፥ ስም
፲፩ ፡ ዋም ፡ ሰሎሚት ፡ ነበረ ። ከእግዚአብሔርም ፡
እፍ ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ፍርድ ፡ እስኪወጣላቸው ፡
ድረስ ፡ በግዞት ፡ አኖሩት ።
፲፪ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
ተናገረው ፡ — ተሳዳቢውን ፡ ከሰፈሩ ፡ ወደ ፡
ውጭ ፡ አውጣው ፡ የሰሙትም ፡ ሁሉ ፡ እጆቹ
ን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይጫኑበት ፡ ማኅበሩም ፡
ሁሉ ፡ ይውገረው ። ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እን
ዲህ ፡ ብለህ ፡ ትነግራለህ ፡ — ማናቸውም ፡ ሰው ፡
አምላኩን ፡ ቢሰድብ ፡ ኃጢአቱን ፡ ይሸከማል ።
፲፫ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ስም ፡ የሚሰድብ ፡ ፈጽሞ ፡
ይገደል ፤ ማኅበሩም ፡ ሁሉ ፡ ይውገሩት ፤
መጻተኛ ፡ ወይም ፡ የአገር ፡ ልጅ ፡ ቢሆን ፥
የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ በሰደበ ፡ ጊዜ ፡ ይገ
ደል ። ስውንም ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ የሚ
፲፬ ፡ ሞታ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ። እንስሳንም ፡ እስኪ
ሞት ፡ ድረስ ፡ የሚሞታ ፡ ሕይወት ፡ በሕይወት ፡
ፋንታ ፡ ከሚውን ፡ ይክፈል ። ሰውም ፡ ባልንጀ
ራውን ፡ ቢጐዳ ፥ እርሱ ፡ እንዳደረገ ፡ እንዲሁ ፡
ይደረግበት ። ስብራት ፡ በስብራት ፡ ፋንታ ፥
፲፭ ፡ ዓይን ፡ በዓይን ፡ ፋንታ ፥ ጥርስ ፡ በጥርስ ፡ ፋንታ ፥
ሰውን ፡ እንደ ፡ ጐዳ ፡ እንዲሁ ፡ ይደረግበት ።
እንስሳውንም ፡ የሚገድል ፡ ካሣ ፡ ይተካ ፡ ሰው
ንም ፡ የሚገድል ፡ ይገደል ። እኔ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ነኝና ፡ ለመጻተኛና ፡ ለአገር ፡
ልጅ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሕግ ፡ ይሁንላችሁ ።
ሙሴም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተናገራቸው ፡
ተሳዳቢውንም ፡ ከሰፈሩ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አወ
ጡት ፥ በድንጋይም ፡ ወገሩት ። የእስራኤልም ፡
ልጆች ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡
አደረጉ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፮ ።

፩ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡
ላይ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፡ — ለእስራኤል ፡
፪ ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ንገራቸው ፡ — እኔ ፡ ወደም
ሰማችሁ ፡ ምድር ፡ በገባችሁ ፡ ጊዜ ፡ ምድሪቱ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ሰንበት ፡ ታድርግ ። ስድስት ፡
፫ ፡ ዓመት ፡ እርሻህን ፡ ዝራ ፥ ስድስት ፡ ዓመትም ፡
ወይንህን ፡ ቍረጥ ፡ ፍሬዋንም ፡ አግባ ። በሰባ
፬ ፡ ተኛው ፡ ዓመት ፡ ግን ፡ ለምድሪቱ ፡ የዕረፍት ፡
ሰንበት ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ሰንበት ፡ ትሁን ፤
እርሻህን ፡ አትዝራ ፤ ወይንህንም ፡ አትቍረጥ ።
፭ ፡ የምድራችሁን ፡ የገበ ፡ አትጨደው ፥ ያልተቈ
ረጠውንም ፡ የወይንህን ፡ ፍሬ ፡ አታከማች ፤
ለምድሪቱ ፡ የዕረፍት ፡ ሰንበት ፡ ዓመት ፡ ይሁን ።
፮ ፡ የምድርም ፡ ሰንበት ፡ ለእንተ ፡ ለወንድ ፡ ባሪ
ያህም ፥ ለሴት ፡ ባሪያህም ፥ ለምንደኛም ፡ ለከ
ንተ ፡ ጋር ፡ ለሚኖር ፡ ለመጻተኛም ፡ ምግብ ፡
ይሁን ። ለእንስሶችህም ፡ በምድርህም ፡ ላሉት ፡
፯ ፡ አራዊት ፡ ፍሬዋ ፡ ሁሉ ፡ መኖ ፡ ይሁን ።
፰ ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ሰባት ፡ አድርገህ ፡ የዓመታትን ፡
ሰንበት ፡ ሰባት ፡ ቀመር ፤ የሰባት ፡ ዓመታትም ፡
ሰንበት ፡ ዘመን ፡ አርባ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ትቈ
ጥራለህ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡
፱ ፡ በአሥረኛው ፡ ቀን ፡ በቀንደ ፡ መለከት ፡ ታውጃ
ለህ ፤ በማስተስረያ ፡ ቀን ፡ በምድራችሁ ፡ ሁሉ ፡
በቀንደ ፡ መለከት ፡ ታውጃላችሁ ። አምሳኛ ፡
፲ ፡ ውንም ፡ ዓመት ፡ ትቀድሳላችሁ ፥ በምድሪቱም ፡
ለሚኖሩባት ፡ ሁሉ ፡ ነጻነትን ፡ ታውጃላችሁ ፤
እርሱ ፡ ለእናንተ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ነው ፤ ሰው ፡
ሁሉ ፡ ወደ ፡ርስቱና ፡ ወደ ፡ ወገኑ ፡ ይመለስ ።
፲፩ ፡ ያ ፡ አምሳኛው ፡ ዓመት ፡ ለእናንተ ፡ ኢዮቤልዩ ፡
ይሆናል ፤ በእርሱም ፡ እትገሩ ፥ የገበውንም ፡
አትጨዱ ፥ የወይኑንም ፡ ፍሬ ፡ አታከማቹ ።
፲፪ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ነውና ፡ የተቀደሰ ፡ ይሁንላችሁ ፤
በሜዳ ፡ ላይ ፡ የበቀለውን ፡ ብሉ ።
፲፫ ፡ በዚች ፡ በኢዮቤልዩ ፡ ዓመት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡
ወደ ፡ ርስቱ ፡ ይመለሳል ። ለባልንጀራህም ፡
፲፬ ፡ አንዳች ፡ ብትሸጥለት ፥ ወይም ፡ ከባልንጀራህ ፡
እጅ ፡ ብትገዛ ፥ ሰው ፡ ባልንጀራውን ፡ አያታ
ልል ። ከኢዮቤልዩ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ዓመታቱ ፡
፲፭ ፡ ቍጥር ፡ ከባልንጀራህ ፡ ትገዛለህ ፤ እርሱም ፡
እንደ ፡ መከሩ ፡ ዓመታት ፡ ቍጥር ፡ ይሸጥልሃል ።
እንደ ፡ ዓመታቱ ፡ ብዛት ፡ ዋጋውን ፡ ታበዛለህ ፥
፲፮ ፡ እንደ ፡ ዓመታቱም ፡ ማነስ ፡ ዋጋውን ፡ ታሳንሳ
ለህ ፤ እንደ ፡ መከሩ ፡ ቍጥር ፡ ይሸጥልሃል ።
እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ነኝና ፥
፲፯ ፡ ሰው ፡ ባልንጀራውን ፡ አያታልል ፥ ነገር ፡ ግን ፡
አምላክህን ፡ ፍራ ።
፲፰ ፡ ሥርዓቴንም ፡ አድርጉ ፥ ፍርዶቼንም ፡ ጠብቁ ፡

አድርጉትም ፡ በምድሪቱም ፡ ውስጥ ፡ በጸጥታ ፡ ፲፱ ፡ ትኖራላችሁ ። ምድሪቱም ፡ ፍሬዋን ፡ ትሰጣ
ለች ፥ እስክትጠግቡም ፡ ድረስ ፡ ትበላላችሁ ፡
በእርስዋም ፡ ውስጥ ፡ በጸጥታ ፡ ትኖራላችሁ ።
፳ ፡ እናንተም ፡— ካልዘራን ፡ እህላችንንም ፡ ካላከ
ማቸን ፡ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ምን ፡ እንበላ
፳፩ ፡ ለን ? ብትሉ ፥ እኔ ፡ በስድስተኛው ፡ ዓመት ፡
በረከቴን ፡ በላያችሁ ፡ አዝዛለሁ ፡ ምድሪቱም ፡
፳፪ ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡ ፍሬ ፡ ታፈራለች ። በስምንተ
ኛውም ፡ ዓመት ፡ ትዘራላችሁ ፥ ከአሮጌውም ፡
እህል ፡ ትበላላችሁ ፡ ፍሬዋ ፡ እስኪገባ ፥ እስከ ፡
ዘጠኝኛው ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፥ ከአሮጌው ፡ እህል ፡
ትበላላችሁ ።

፳፫ ፡ ምድርም ፡ ለእኔ ፡ ናትና ፥ እናንተም ፡ ከእኔ ፡
ጋር ፡ እንግዶችና ፡ መጻተኞች ፡ ናችሁና ፡ ምድ
፳፬ ፡ ርን ፡ ለዘላለም ፡ አትሽጡ ። በርስታችሁም ፡
ምድር ፡ ሁሉ ፡ መቤዠርትን ፡ ለምድሪቱ ፡ አድ
፳፭ ፡ ርጉ ። ወንድምህም ፡ ቢደኸይ ፡ ከርስቱ ፡ ሸጦ ፥
ለእርሱ ፡ የቀረበ ፡ ዘመዱ ፡ መጥቶ ፡ ወንድሙ ፡ የሸ
፳፮ ፡ ጠውን ፡ ይቤዝዋል ። የሚቤዝውም ፡ ሰው ፡
ቢያገ ፥ እርሱም ፡ እጁ ፡ ቢረጥብ ፥ ለመቤዝ
፳፯ ፡ ትም ፡ የሚበቃ ፡ ቢያገኝ ፡ የሸያጩን ፡ ዘመን ፡
ቈጥሮ ፡ የቀረውን ፡ ወደ ፡ ገዛው ፡ ሰው ፡ ይመ
፳፰ ፡ ልስ ፡ እርሱም ፡ ወደ ፡ ርስቱ ፡ ይመለስ ። ለራ
ሱም ፡ ዕዳውን ፡ መክፈል ፡ ባይችል ፡ ሸያጩ ፡
በገዛው ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ እስከ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ዓመት ፡
ድረስ ፡ ይቀመጥ ፡ በኢዮቤልዩም ፡ ዓመት ፡
ይውጣ ፥ እርሱም ፡ ወደ ፡ ርስቱ ፡ ይመለስ ።

፳፱ ፡ ሰውም ፡ ቅጥር ፡ ባለበት ፡ ከተማ ፡ መኖሪያ ፡
ቤትን ፡ ቢሸጥ ፥ ከተሸጠ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡
እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ለመቤዠት ፡ ይችላል ፡
ለእንድ ፡ ሙሉ ፡ ዓመት ፡ መቤዠት ፡ ይችላል ።
፴ ፡ አንድ ፡ ዓመትም ፡ እስኪፈፈረስ ፡ ባይቤዝው ፥
ቅጥር ፡ ባለበት ፡ ከተማ ፡ የሚሆን ፡ ቤት ፡ ለገ
ዛው ፡ ሥልጅ ፡ ልጁ ፡ ለዘላለም ፡ ይጸናለታል ፡
፴፩ ፡ በኢዮቤልዩም ፡ ከእርሱ ፡ አይወጣም ። ቅጥር ፡
በሌለበት ፡ መንደር ፡ ያሉ ፡ ቤቶች ፡ ግን ፡ እንደ ፡
እርሻ ፡ ይቈጠራሉ ፥ ይቤዝሯሉ ፥ በኢዮቤል
፴፪ ፡ ዩም ፡ ይወጣሉ ። በእነርሱ ፡ ከተማ ፡ ያሉ ፡ የሌ
ዋውያን ፡ ቤት ፡ ግን ፡ ሌዋውያን ፡ ለዘላለም ፡
፴፫ ፡ መቤዝገት ፡ ይችላሉ ። ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከሌ
ዋውያን ፡ ቢገዛ ፥ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካ
ከል ፡ የሌዋውያን ፡ ከተማ ፡ ቤቶች ፡ ርስቶቻ
ቸው ፡ ናቸውና ፡ በርስቱ ፡ ከተማ ፡ ያለ ፡ የተሸ
፴፬ ፡ ጠው ፡ ቤት ፡ በኢዮቤልዩ ፡ ይመለሳል ። በከ
ተማቸውም ፡ ዙሪያ ፡ ያሉትም ፡ መሰምርያ ፡ የዘ
ላለም ፡ ርስታቸው ፡ ናትና ፡ አትሸጥም ።

፴፭ ፡ ወንድምህ ፡ ቢደኸይ ፡ እጁም ፡ በአንተ ፡
ዘንድ ፡ ቢደክም ፡ አጽናው ፡ እንግዳና ፡
እንደ ፡ መጻተኛም ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ይኑር ።
፴፮ ፡ ወንድምህ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ከእ
ርሱ ፡ ምንም ፡ ወለድ ፡ ወይም ፡ ትርፍ ፡ አትው
፴፯ ፡ ሰድ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አምላክህን ፡ ፍራ ። ብር
ህን ፡ በወለድ ፡ አታበድረው ፡ መኖህንም ፡ በት
ርፍ ፡ አትስጠው ። የከነዓንን ፡ ምድር ፡ እሰጣ ፴፰ ፡
ችሁ ፡ ዘንድ ፡ አምላክም ፡ እሆናችሁ ፡ ዘንድ ፡
ከግብፅ ፡ ምድር ፡ ያወጣኋችሁ ፡ እኔ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ነኝ ።

፴፱ ፡ ወንድምህም ፡ ቢደኸይ ፡ ራሱንም ፡ ለአንተ ፡
ቢሸጥ ፥ እንደ ፡ ባሪያ ፡ አድርገህ ፡ አትግዛው ።
እንደ ፡ ምንደኛና ፡ እንደ ፡ መጻተኛ ፡ ከአንተ ፡
ጋር ፡ ይሁን ፡ እስከ ፡ ኢዮቤልዩም ፡ ዓመት ፡
ያገልግልህ ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ እርሱ ፡ ከል ፴፩
ጆቹ ፡ ጋር ፡ ከእንተ ፡ ይውጣ ፥ ወደ ፡ ወገኖ
ቹም ፡ ወደ ፡ አባቱም ፡ ርስት ፡ ይመለስ ። ከግ ፴፪
ብፅ ፡ ምድር ፡ ያወጣኋቸው ፡ ባሪያዎቼ ፡ ናቸ
ውና ፡ እንደ ፡ ባሪያዎች ፡ አይሸጡ ። በጽኑ ፴፫
እጅ ፡ አትግዛው ፥ ነገር ፡ ግን ፡ አምላክህን ፡
ፍራ ። ወንድ ፡ ባሪያና ፡ ሴት ፡ ባሪያ ፡ መግዛት ፡ ፴፬
ብትፈልግ ፡ ግን ፡ በዙሪያችሁ ፡ ካሉት ፡ ከእነ
ርሱ ፡ ከአሕዛብ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ባሪያዎችን ፡
ግዙ ። ደግሞም ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ከሚ ፴፭
ቀመጡት ፡ መጻተኞች ፥ በምድራችሁም ፡
ውስጥ ፡ ከወለዱአቸው ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡
ከሚቀመጡት ፡ ከዘራቸው ፡ ውስጥ ፡ ባሪያዎ
ችን ፡ ግዙ ፡ ርስትም ፡ ይሁኑላችሁ ። ከእናን ፴፮
ተም ፡ በኋላ ፡ ልጆቻችሁ ፡ ይወርሱአቸው ፡
ዘንድ ፡ ተዉአቸው ፡ ከእነርሱም ፡ ባሪያዎችን ፡
ለዘላለም ፡ ትወስዳላችሁ ፥ ነገር ፡ ግን ፡ የእስራ
ኤልን ፡ ልጆች ፡ ወንድሞቻችሁን ፡ በጽኑ ፡
እጅ ፡ አትግዙአቸው ።

፴፯ ፡ በአንተም ፡ ዘንድ ፡ የሚኖር ፡ መጻተኛ ፡
ወይም ፡ እንግዳ ፡ ሀብታም ፡ ቢሆን ፥ ወንድም
ህም ፡ በእርሱ ፡ አጠገብ ፡ ቢደኸይ ፥ ራሱንም ፡
ለመጻተኛው ፡ ወይም ፡ ለእንግዳው ፡ ወይም ፡ ለወ
ገኖቹ ፡ ዘር ፡ ቢሸጥ ፥ ከተሸጠ ፡ በኋላ ፡ መቤ ፴፰
ዠት ፡ ይችላል ፡ ከወንድሞቹ ፡ አንዱ ፡ ይቤ
ዝው ፥ ወይም ፡ አጎቱ ፡ ወይም ፡ የአጎቱ ፡ ልጅ ፡ ፴፱
ይቤዝው ፡ ወይም ፡ ከወገኑ ፡ ለእርሱ ፡ የቀ
ረበ ፡ ዘመድ ፡ ይቤዝው ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡
እጁ ፡ ቢረጥብ ፡ ራሱን ፡ ይቤዝው ። ከገዛውም ፡ ፵
ሰው ፡ ጋር ፡ ከገዛበት ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡
ኢዮቤልዩ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ይቍጠር ፡ የሸያ
ጩም ፡ ብር ፡ እንደ ፡ ዓመታቱ ፡ ቍጥር ፡ ይሁን ፡
እንደ ፡ ምንደኛውም ፡ ዘመን ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡
ይሁን ። ብዙ ፡ ዓመታትም ፡ ቢቀሩ ፡ እንደ ፡ ፵፩
እነርሱ ፡ ቍጥር ፡ ከሽያጩ ፡ ብር ፡ የመቤዠርቱን ፡
ዋጋ ፡ ይመልስ ። እስከ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ዓመት ፡ ፵፪
ድረስ ፡ ጥቂቶች ፡ ዓመታት ፡ ቢቀሩ ፡ ከእ
ርሱ ፡ ጋር ፡ ይቈጥራል ፡ እንደ ፡ ዓመታቱም ፡
መጠን ፡ የመቤዠርቱን ፡ ዋጋ ፡ ይመልስ ።
በየዓመቱ ፡ እንደ ፡ ምንደኛ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ፵፫
ይኑር ፡ በፊትህ ፡ በጽኑ ፡ እጅ ፡ አይግዛው ።
በዚህ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ባይቤዝ ፡ በኢዮ ፵፬
ቤልዩ ፡ ዓመት ፡ እርሱ ፡ ከልጆቹ ፡ ጋር ፡ ይውጣ ።
የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለእኔ ፡ ባሪያዎች ፡ ናቸ ፵፭
ውና ፡ ከግብፅ ፡ ምድር ፡ ያወጣኋቸው ፡ ባሪያዎቼ ፡
ናቸው ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ነኝ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፮ ።

፩ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ነኝና ፡
ለእናንተ ፡ ጣዖት ፡ አታድርጉ ፥ የተቀረጸም ፡
ምስል ፡ ወይም ፡ ሐውልት ፡ አታቁሙ ፡ ትሰግ
ዱለትም ፡ ዘንድ ፡ በምድራችሁ ፡ ላይ ፡ የተቀ
ረጸ ፡ ድንጋይ ፡ አታኑሩ ። ሰንበታቴን ፡ ጠብቁ ፡
መቅደሴንም ፡ ፍሩ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።
፪ ፡ በሥርዓቴ ፡ ብትሄዱ ፥ ትእዛዛቴንም ፡ ብትጠ
ብቁ ፡ ብታደርጉትም ፥ ዝናባችሁን ፡ በወቅቱ ፡
አዘንባለሁ ፥ ምድሪቱም ፡ እህልዋን ፡ ትሰጣ
ለች ፥ የሜዳው ፡ ዛፎችም ፡ ፍሬአቸውን ፡ ይሰ
ጣሉ ። የእህሉም ፡ ማበራየት ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡
እስከ ፡ ወይኑ ፡ መቍረጥ ፡ ይደርሳል ፥ የወይ
ኑም ፡ መቍረጥ ፡ እስከ ፡ እህሉ ፡ መዝራት ፡ ይደ
ርሳል ፡ እስክትጠግቡም ፡ ድረስ ፡ እንጀራች
ሁን ፡ ተበላላችሁ ፥ በምድራችሁም ፡ ላይ ፡ በጸ
ጥታ ፡ ትኖራላችሁ ። በምድራችሁም ፡ ላይ ፡
ሰላምን ፡ እሰጣለሁ ፥ ማንም ፡ ሳያስፈራችሁ ፡
ትተኛላችሁ ፡ ክፉዎችንም ፡ አራዊት ፡ ከምድ
ራችሁ ፡ አጠፋለሁ ፥ ሰይፍም ፡ በምድራችሁ ፡
ላይ ፡ አያልፍም ። ጠላቶቻችሁንም ፡ ታሳድዳ
ላችሁ ፥ በፊታችሁም ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ።
ከእናንተም ፡ አምስቱ ፡ መቶውን ፡ ያሳድዳሉ ፥
መቶውም ፡ አሥሩን ፡ ሺህ ፡ ያሳድዳሉ ፡ ጠላቶ
ቻችሁም ፡ በፊታችሁ ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ።
፰ ፡ ፊቴም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ይሆናል ፡ እንድታፈሩም ፡
አደርጋችኋለሁ ፥ አበዛችሁማለሁ ፡ ቃል ፡ ኪዳ
ኔንም ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ አጸናለሁ ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡
የተቀመጠውንም ፡ አሮጌውን ፡ እህል ፡ ትበላላ
ችሁ ፡ ከአዲሱም ፡ በፊት ፡ አሮጌውን ፡ ታወጣ
ላችሁ ። ማደሪያዬንም ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡
አደርጋለሁ ፥ ነፍሴም ፡ አትጸየፋችሁም ። በመ
ካከላችሁም ፡ እሄዳለሁ ፥ እኔም ፡ አምላክ ፡ እሆ
ናችኋለሁ ፥ እናንተም ፡ ሕዝብ ፡ ትሆኑኛላችሁ ።
፱ ፡ ባሪያዎች ፡ እንዳትሆኑአቸው ፡ ከግብፅ ፡ ምድር ፡
ያወጣኋችሁ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችሁ ፡
ነኝ ፡ የባርነታችሁን ፡ ቀንበር ፡ ሰብሬአለሁ ፡ ቀና ፡
ብላችሁ ፡ እንድትሄዱ ፡ አድርጌአችኋለሁ ።
፲ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ባትሰሙኝ ፥ እነዚህንም ፡ ትእዛ
ዞች ፡ ሁሉ ፡ ባታደርጉ ፥ ሥርዓቴንም ፡ ብትንቁ ፥
ቅስእዛዛቴንም ፡ ሁሉ ፡ እንዳታደርጉ ፥ ቃል ፡ ኪዳ
ኔንም ፡ እንድታፈርሱ ፡ ነፍሳችሁ ፡ ፍርዴን ፡
ብትጸየፍ ፥ እኔም ፡ እንዲህ ፡ አደርግባችኋለሁ ፡
ፍርሃትን ፥ ክሳትንም ፥ ዓይናችሁንም ፡ የሚያፈ
ዝዝ ፡ ሰውነታችሁንም ፡ የሚያግስን ፥ ትኩሳት ፡
አወርድባችኋለሁ ፡ ዘራችሁንም ፡ በከንቱ ፡ ትዘ
ራላችሁ ፥ ጠላቶቻችሁ ፡ ይብሉታልና ። ፊቴ
ንም ፡ አከብድባችኋለሁ ፥ በጠላቶቻችሁም ፡
ፊት ፡ ትወድቃላችሁ ፡ የሚጠሉአችሁም ፡ ይገዙ
አችኋል ፡ ማንም ፡ ሳያሳድዳችሁ ፡ ትሸሻላችሁ ።
፲፩ ፡ እስከዚህም ፡ ድረስ ፡ ባትሰሙኝ ፥ ስለ ፡ ኃጢአ
ታችሁ ፡ በቅጣታችሁ ፡ ላይ ፡ ሰባት ፡ እጥፍ ፡ እጨ
ምራለሁ ። የኃይላችሁንም ፡ ትዕቢት ፡ እሰብ
ራለሁ ፡ ሰማያችሁንም ፡ እንደ ፡ ብረት ፥ ምድራ
ችሁንም ፡ እንደ ፡ ናስ ፡ አደርጋለሁ ። ጉልበታ ፲፪ ፡
ችሁም ፡ በከንቱ ፡ ያልቃል ፡ ምድራችሁም ፡
እህልዋን ፡ አትሰጥም ፥ የምድርም ፡ ዛፎች ፡
ፍሬአቸውን ፡ አይሰጡም ።

፲፫ ፡ በእንቢተኝነትም ፡ ብትሄዱብኝ ፡ ባትሰሙ ፲፭ ፡
ኝም ፥ እንደ ፡ ኃጢአታችሁ ፡ መጠን ፡ በመቅ
ሠፍት ፡ ላይ ፡ ሰባት ፡ እጥፍ ፡ እጨምራለሁ ።
በመካከላችሁም ፡ የምድርን ፡ አራዊት ፡ እሰድዳ ፲፮ ፡
ለሁ ፡ ልጆቻችሁንም ፡ ይነጥቃሉ ፥ እንስሶቻ
ችሁንም ፡ ያጠፋሉ ፥ እናንተንም ፡ ያሳንሳሉ ፡
መንገዶቻችሁም ፡ በረሀ ፡ ይሆናሉ ።

፲፯ ፡ እስከዚህም ፡ ድረስ ፡ ባትቀጡ ፥ በእንቢተኝ
ነትም ፡ ብትሄዱ ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በእንቢተኝ ፲፰ ፡
ነት ፡ እሄድባችኋለሁ ፡ ስለ ፡ ኃጢአታችሁም ፡
ሰባት ፡ እጥፍ ፡ እመታችኋለሁ ። የቃል ፡ ኪዳ
ኔንም ፡ በቀል ፡ ይበቀልባችሁ ፡ ዘንድ ፡ ሰይፍ ፡
አመጣባችኋለሁ ፡ ወደ ፡ ከተማችሁም ፡ ትሰበሰ
ባላችሁ ፥ ቸነፈርንም ፡ እሰድድባችኋለሁ ፡ በጠ
ላትም ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣችኋለሁ ። የእህ ፲፱ ፡
ላችሁንም ፡ ድጋፍ ፡ በሰበርሁ ፡ ጊዜ ፥ አሥር ፡
ሴቶች ፡ እንጀራቸውን ፡ በአንድ ፡ ምጣድ ፡ ይጋ
ግራሉ ፥ በሚዛንም ፡ መዝነው ፡ እንጀራችሁን ፡
ይመልሱላችኋል ፡ በበላችሁም ፡ ጊዜ ፡ አትጠ
ግቡም ።

፳ ፡ እስከዚህም ፡ ድረስ ፡ ባትሰሙኝ ፥ በእንቢተ ፲፯ ፡
ኝነትም ፡ ብትሄዱብኝ ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በቍጣ ፲፰ ፡
እሄድባችኋለሁ ፡ ስለ ፡ ኃጢአታችሁም ፡ ሰባት ፡
እጥፍ ፡ እቀጣችኋለሁ ። የወንዶች ፡ ልጆቻች ፲፱ ፡
ሁንም ፡ ሥጋ ፡ ትበላላችሁ ፡ የሴቶች ፡ ልጆቻ
ችሁንም ፡ ሥጋ ፡ ትበላላችሁ ። የከረብታ ፡ መስ ፴ ፡
ገጃዎቻችሁንም ፡ አፈርሳለሁ ፥ የፀሐይ ፡ ምስ
ሎቻችሁንም ፡ አጠፋለሁ ፥ ሬሳችሁንም ፡ በጣ
ዖቶቻችሁ ፡ ሬሳዎች ፡ ላይ ፡ እጥላለሁ ፡ ነፍሴም ፡
ትጸየፋችኋለች ። ከተሞቻችሁንም ፡ ባድማ ፴፩ ፡
አደርጋለሁ ፥ መቅደሶቻችሁንም ፡ አፈርሳለሁ ፥
መልካሙንም ፡ መዓዛችሁን ፡ አላሸትትም ። ምድ ፴፪ ፡
ሪቱንም ፡ የተፈታች ፡ አደርጋለሁ ፡ የሚቀመጡ
ባት ፡ ጠላቶቻችሁም ፡ በእርስዋ ፡ የተነሣ ፡ ይደ
ነቃሉ ። እናንተንም ፡ ከአሕዛብ ፡ መካከል ፡ እበ ፴፫ ፡
ትናችኋለሁ ፥ ሰይፍንም ፡ አስመዝዝባችኋለሁ ፡
ምድራችሁም ፡ የተፈታች ፡ ትሆናለች ፥ ከተሞ
ቻችሁም ፡ ባድማ ፡ ይሆናሉ ።

፴፬ ፡ በዚያም ፡ በተፈታችበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡
እናንተም ፡ በጠላቶቻችሁ ፡ ምድር ፡ ሳላችሁ ፥
ምድሪቱ ፡ ሰንበት ፡ በማድረግዋ ፡ ትደሰታለች ፡
በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ምድሪቱ ፡ ታርፋለች ፥ ሰንበ
ትንም ፡ በማድረግዋ ፡ ትደሰታለች ። እናንተ ፡ ፴፭ ፡
ተቀምጣችሁባት ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ በሰንበቶቻችሁ ፡
አላረፈችም ፡ ነበርና ፡ በተፈታችበት ፡ ዘመን ፡
ሁሉ ፡ ታርፋለች ። በጠላቶቻችሁም ፡ ምድ ፴፮ ፡
ሮች ፡ ሳሉ ፡ ከእናንተ ፡ ተለይተው ፡ በቀሩት ፡
ላይ ፡ በልባቸው ፡ ድንጋጤን ፡ እሰድድባቸዋለሁ ፡
በነፋስም ፡ የምትንቀሳቀስ ፡ የቅጠል ፡ ድምፅ ፡

ታሽብራቸዋለች ፡ ከሰይፍ፡ እንደሚሸሹ ፡ ይሸ
ሻሉ ፡ ማንም ፡ ሳያሳድዳቸው ፡ ይወድቃሉ ። ፡
ሰ፲፯ ፡ ማንም ፡ ሳያሳድዳቸው ፡ ከሰይፍ ፡ እንዳሸሹ ፡
እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይሰነካከላሉ ፡ እናንተም ፡
በጠላቶቻችሁ ፡ ፊት ፡ መቆም ፡ አትችሉም ።
ሰ፲፰ ፡ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ ታልቃላችሁ ፡ የጠላ
ሰ፲፱ ፡ ቶቻችሁም ፡ ምድር ፡ ትውጣችኋለች ። ከእና
ንተም ፡ ተለይተው ፡ የቀሩት ፡ በጠላቶቻቸው ፡
ምድር ፡ ላይ ፡ በኃጢአታቸው ፡ ይከሳሉ ፡ በአ
በቶቻቸውም ፡ ኃጢአት ፡ ደግሞ ፡ ከእነርሱ ፡
ጋር ፡ ይከሳሉ ።

ሰ፡ በእኔም ፡ ላይ ፡ በእንቢተኝነት ፡ ስለ ፡ ጌዴ
ብኝ ፡ የበደሉኝን፡ በደል ፥ኃጢአታቸውንም ፥
የአባቶቻቸውንም ፡ ኃጢአት ፡ ይናዘዛሉ ።
ሰ፳ ፡ እኔም ፡ ደግሞ ፡ በእንቢተኝነት ፡ ጌድሁባቸው ፡
ወደ ፡ ጠላቶቻቸውም ፡ ምድር ፡ አገባኋቸው ፡
ነገር ፡ ግን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ያልተገረዘው ፡ ልባ
ቸው ፡ ቢዋረድ ፥የኃጢአታቸውንም ፡ቅጣት ፡
ሰ፳፪ ፡ ቢቀበሉ ፥ እኔ ፡ ለያዕቆብ ፡ የማልሁትን ፡ ቃል ፡
ኪዳኔን ፡ አስበለሁ ፡ ደግሞ ፡ ለይስሐቅና ፡ ለአ
ብርሃም ፡ የማልሁትን ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ አስባ
ሰ፳፫ ፡ ለሁ ፡ ምድሪቱንም ፡ አስባለሁ ። ምድርም ፡
ከእነርሱ ፡ መጥፋት ፡ የተነሣ ፡ ባዶ ፡ ትቀራለች ፡
እነርሱም ፡ ሳይኖሩ ፡ በተፈታችበት ፡ ዘመን ፡
ሰንበት ፡ በማድረግዋ ፡ ትደሰታለች ፡ ፍርዴ
ንም ፡ ስለ ፡ ናቁ ፥ ነፍሳቸውም ፡ ሥርዓቴን ፡
ስለ ፡ ተጸየፈች ፡ የኃጢአታቸውን ፡ ቅጣት ፡
ሰ፳፬ ፡ ይሸከማሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡
አምላካቸው ፡ ነኝና ፡ እነርሱ ፡ በጠላቶቻቸው ፡
ምድር ፡ ሳሉ ፥ እስከጠፋቸው ፡ ድረስ ፡ ከእነር
ሱም ፡ ጋር ፡ ያለኝን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እስከፈርስ ፡
ድረስ ፡ አልጥላቸውም ፡ አልጸየፋቸውምም ።
ሰ፳፭ ፡ እኔ ፡ አምላካቸው ፡ እሆን ፡ ዘንድ ፡ አሕዛብ ፡
እያዩ ፡ ከግብፅ ፡ ምድር ፡ ያወጣኋቸውን ፡ የአባ
ቶቻቸውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ አስ
ባለሁ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።
ሰ፳፮ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በእርሱና ፡ በእስራኤል ፡
ልጆች ፡ መካከል ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ በሙሴ ፡
እጅ ፡ ያደረጋቸው ፡ ሥርዓቶችና ፡ ፍርዶች ፡
ሕጋችም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፳፯ ።

፩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
፪ ፡ ተናገረው ፡— ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡
ብለህ ፡ ንገራቸው ፡—ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሰውን ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ሊሰጥ ፡ ቢሳል ፡ አንተ ፡ እን
ደምትገምተው ፡ መጠን ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ዋጋውን ፡
፫ ፡ ይስጥ ። ለወንድ ፡ ከሀያ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ስድሳ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ መቅ
ደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ ግምቱ ፡ አምሳ ፡ የብር ፡
፬ ፡ ሰቅል ፡ ይሁን ። ሴትም ፡ ብትሆን ፡ ግምትዋ ፡
፭ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡ ይሁን ። ከአምስት ፡ ዓመትም ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሀያ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ግምቱ ፡
ለወንድ ፡ ሀያ ፡ ሰቅል ፥ለሴትም ፡ አሥር ፡ ሰቅል ፡
ይሁን ። ከአንድ ፡ ወርም ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ፮ ፡
ዓመት ፡ ድረስ ፡ ለወንድ ፡ ግምቱ ፡ አምስት ፡
የብር ፡ ሰቅል ፥ ለሴትም ፡ ግምትዋ ፡ ሦስት ፡
የብር ፡ ሰቅል ፡ ይሁን ። ከስድሳ ፡ ዓመትም ፡ ፯ ፡
ጀምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ወንድ ፡ ቢሆን ፡ ግምቱ ፡
አሥራ ፡ አምስት ፡ ሰቅል ፥ ለሴትም ፡ አሥር ፡
ሰቅል ፡ ይሁን ። ለግምቱም ፡ የሚከፍለውን ፡ ፰ ፡
ቢያጣ ፡ ግን ፡ በከህኑ ፡ ፊት ፡ ይቁም ፥ ከህኑም ፡
የተሰለመውን ፡ ሰው ፡ ይገምተው ፡ ከህኑም ፡ የተ
ሰለመ ፡ ሰው ፡ እንደሚችል ፡ መጠን ፡ ይገም
ተው ።

ለእግዚአብሔርም ፡መሥዋዕት ፡አድርጎ ፡የሚ ፱ ፡
ያቀርበው ፡ እንስሳ ፡ ቢሆን ፥ ሰው ፡ ከእነዚህ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ የሚሰጠው ፡ ሁሉ ፡ ቅዱስ ፡
ይሆናል ። መልከሙን ፡ በክፉ ፥ ክፉውንም ፡ ፲ ፡
በመልካም ፡ አይለውጥ ፡ እንስሳንም ፡ በእንስሳ ፡
ቢለውጥ ፡ እርሱና ፡ ልዋጩ ፡ የተቀደሱ ፡ ይሆ
ናሉ ። እንስሳው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሥዋ ፲፩ ፡
ዕት ፡ መሆን ፡ የማይገባው ፡ ርኩስ ፡ ቢሆን ፥
እንስሳውን ፡ በከህኑ ፡ ፊት ፡ ያኑረው ። መል ፲፪ ፡
ካምም ፡ ቢሆን ፡ ክፉም ፡ ቢሆን ፡ ከህኑ ፡ ይገም
ተው ፥ ከህኑም ፡ እንደሚገምተው ፡ መጠን ፡
እንዲሁ ፡ ይሁን ። ይቤዣውም ፡ ዘንድ ፡ ቢወ ፲፫ ፡
ድድ ፡ ከግምቱ ፡ በላይ ፡ አምስተኛ ፡ ይጨምር ።
ሰውም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ይሆን ፡ ፲፬ ፡
ዘንድ ፡ ቤቱን ፡ ቢቀድስ ፥ ከህኑ ፡ መልካም ፡
ወይም ፡ ክፉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይገምተዋል ፥ ከህ
ኑም ፡ እንደሚገምተው ፡ መጠን ፡ እንዲሁ ፡
ይቆማል ። የቀደሰውም ፡ ሰው ፡ ቤቱን ፡ ይቤ ፲፭ ፡
ዣው ፥ዘንድ ፡ ቢወድድ ፡ ከግምቱ ፡ ገንዘብ ፡ በላይ ፡
አምስተኛ ፡ ይጨምር ፥ ቤቱም ፡ ለእርሱ ፡ ይሆ
ናል ።

ሰውም ፡ ከርስቱ ፡ እርሻ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፲፮ ፡
ቢቀድስ ፥ እንደ ፡ መዘራቱ ፡ መጠን ፡ ይገመት ፡
አንድ ፡ የቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ ገብስ ፡ የሚዘራበት ፡
እርሻ ፡ አምሳ ፡ የብር ፡ ሰቅል ፡ ይገመታል ።
እርሻውንም ፡ ከኢዮቤልዩ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ፲፯ ፡
ቢቀድስ ፥እንደ ፡ ግምቱ ፡ መጠን ፡ ይቆማል ።
እርሻውንም ፡ ከኢዮቤልዩ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ፲፰ ፡
ቢቀድስ ፥ ከህኑ ፡ እስከ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ዓመት ፡
ድረስ ፡ እንደ ፡ ቀሩት ፡ ዓመታት ፡ ገንዘቡን ፡ ይቈ
ጥርለታል ፡ ከግምቱም ፡ ይጐድላል ። እርሻው ፲፱ ፡
ንም ፡ የቀደሰ ፡ ሰው ፡ ይቤዣው ፡ ዘንድ ፡ ቢወ
ድድ ፥ከግምቱ ፡ ገንዘብ ፡ በላይ ፡ አምስተኛ ፡ ይጨ
ምር ፡ ለእርሱም ፡ ይሆናል ። እርሻውንም ፡ ባይቤ ፲፩ ፡
ዣው ፥ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ቢሸጥ ፥ እንደ ፡
ገና ፡ ይቤዣው ፡ ዘንድ ፡ አይቻለውም ። እር ፲፪ ፡
ሻው ፡ ግን ፡ በኢዮቤልዩ ፡ ሲወጣ ፡ እንደ ፡ እርም ፡
ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ እርሻ ፡ ይሆናል ፡
ርስቱ ፡ ለከህኑ ፡ ይሆናል ። ከርስቱ ፡ እርሻ ፡ ያል ፲፫ ፡
ሆነውን ፡ የገዛውን ፡ እርሻ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ቢቀድስ ፥ ከህኑ ፡ እስከ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ዓመት ፡ ፲፬ ፡
ድረስ ፡ የግምቱን ፡ ዋጋ ፡ ይቈጥርለታል ፡ በዚ
ያም ፡ ቀን ፡ ግምቱን ፡ እንደ ፡ ተቀደሰ ፡ ነገር ፡

ለእግዚአብሔር ፡ ይሰጣል ። በኢዮቤልዩ ፡
ዓመት ፡ እርሻው ፡ የምድሪቱ ፡ በለ ፡ ርስት ፡ ወደ ፡
ነበረው ፡ ወደ ፡ ሸጠው ፡ ሰው ፡ ይመለሳል ።
ግምቱም ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡
ሚዛን ፡ ይሆናል ፤ ሰቅሉ ፡ ዘይ ፡ አዕሊ ፡ ይሆ
ናል ።

ለእግዚአብሔር ፡ ግን ፡ የሚቀርበውን ፡ የእን
ስሳ ፡ በኩራት ፡ ማንም ፡ ይቀድሰው ፡ ዘንድ ፡ አይ
ቻለውም ፡ በሬ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በግ ፡ ለእግዚ
አብሔር ፡ ነው ። የረከሰም ፡ እንስሳ ፡ ቢሆን ፡
እንደ ፡ ግምቱ ፡ ይቤዣው ፥ በእርሱም ፡ የዋ
ጋውን ፡ አምስተኛ ፡ ይጨምርበታል ፡ ባይቤ
ዣም ፡ እንደ ፡ ግምቱ ፡ ይሸጣል ።

ለእግዚአብሔርም ፡ የተሰየ ፡ እርም ፡ የሆነ ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፥ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ እንስሳ ፡
ወይም ፡ የርስቱ ፡ እርሻ ፡ ቢሆን ፥ አይሸጥም ፥
አይቤዣም ፤ እርም ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለአ
ግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ ነው ። ከሰዎ ፳፱ ፡
ችም ፡ እርም ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ አይቤዣም ፡ ፈጽሞ ፡
ይገደላል ።

የምድርም ፡ አሥራት ፥ ወይም ፡ የምድር ፡ ፴ ፡
ዘር ፡ ወይም ፡ የዛፍ ፡ ፍሬ ፡ ቢሆን ፥ የእግዚአ
ብሔር ፡ ነው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ነው ።
ሰውም ፡ አሥራቱን ፡ ሊቤዥ ፡ ቢወድድ ፥ አም ፴፩ ፡
ስተኛ ፡ ይጨምርበታል ። ከበሬም ፡ ሁሉ ፡ ከአ ፴፪ ፡
ሥር ፡ አንድ ፥ ከአረኛውም ፡ በትር ፡ በታች ፡
ከሚያልፍ ፡ በግና ፡ ፍየል ፡ ሁሉ ፡ ከአሥር ፡
አንድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ይሆናል ።
መልካም ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡ እንዲሆን ፡ አይመር ፴፫ ፡
ምር ፥ አይለውጥም ፡ ቢለውጠውም ፡ እርሱና ፡
ልዋጩ ፡ የተቀደሱ ፡ ይሆናሉ ፡ አይቤዣውም ።

እግዚአብሔር ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ለእስ ፴፬ ፡
ራኤል ፡ ልጆች ፡ ሙሴን ፡ ያዘዘው ፡ ትእዛዛት ፡
እነዚህ ፡ ናቸው ።

ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ በሲና ፡ ምድረ ፡
በዳ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፥ በሁለተ
ኛው ፡ ወር ፡ በመጀመሪያው ፡ ቀን ፥ ከግብፅ ፡
ምድር ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓመት ፡
እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፡— የእስራኤልን ፡
ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ ድምር ፥ በየወገናቸው ፥
በየአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፥በየስማቸው ፡ ቍጥር ፥
ወንዱን ፡ በየራሱ ፡ ውስጥ ። ከሀያ ፡ ዓመት ፡
ጀምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያለውን ፥ ከእስራ
ኤል ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጡትን ፡ ሁሉ ፥ እን
ቍና ፡ አርን ፡ በየሠራዊቶቻቸው ፡ ቍጠሩአቸው ። ከ
የነገዱም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የአባቶቹ ፡ ቤት ፡
ኈለቃ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ይሁን ። ከእናንተም ፡
ጋር ፡ የሚቆሙት ፡ ሰዎች ፡ ስሞቻቸው ፡ እነ
ዚህ ፡ ናቸው ፡ ከሮቤል ፡ የሰዲዮር ፡ ልጅ ፡
ኤሊሱር ፥ ከስምዖን ፡ የሱሪሰዳይ ፡ ልጅ ፡ ሰለ
ሚኤል ፥ ከይሁዳ ፡ የአሚናዳብ ፡ ልጅ ፡ ነአ
ሶን ፥ ከይሳኮር ፡ የሶገር ፡ ልጅ ፡ ናትናኤል ፥
ከዝብሎን ፡ የኬሎን ፡ ልጅ ፡ ኤልያብ ፥ ከዮሴፍ ፡
ልጆች ፡ ከኤፍሬም ፡ የዓሚሁድ ፡ ልጅ ፡ ኤሊ
ሳማ ፥ ከምናሴ ፡ የፍዳሱር ፡ ልጅ ፡ ገማልኤል ፥
ከብንያም ፡ የጋዲዮን ፡ ልጅ ፡ አቢዳን ፥ ከዳን ፡
የአሚሳዳይ ፡ ልጅ ፡ አኪዔዘር ፥ ከአሴር ፡ የአ
ክራን ፡ ልጅ ፡ ፋግኤል ፥ ከጋድ ፡ የራጉኤል ፡
ልጅ ፡ ኤሊሳፍ ፥ ከንፍታሌም ፡ የዔናን ፡ ልጅ ፡
አኪሬ ። ከማኅበሩ ፡ የተመረጡ ፡ የእስራኤል ፡
አእላፍ ፡ ታላላቆች ፥ የአባቶቻቸው ፡ ነገድ ፡
አለቆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። ሙሴና ፡ አሮንም ፡
እነዚህን ፡ በስማቸው ፡ የተጠሩትን ፡ ሰዎች ፡
ወሰዱአቸው ፡ ፤ በሁለተኛውም ፡ ወር ፡ በመጀ
መሪያው ፡ ቀን ፡ ማኅበሩን ፡ ሁሉ ፡ ሰበሰቡአ
ቸው ፤ ከሀያ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡
ያለውን ፡ በየራሱ ፡ በየወገኑም ፡ በየአባቶቻቸ
ውም ፡ ቤቶች ፡ በየስማቸው ፡ ቍጥር ፡ ትውል
ዳቸውን ፡ ተናገሩ ። እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ፲፱ ፡
እንዳዘዘ ፡ እንዲሁ ፡ በሲና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ቈጠ
ራቸው ።

የእስራኤል ፡ በኩር ፡ የሮቤል ፡ ልጆች ፡ በየ ፳ ፡
ትውልዳቸው ፥ በየወገናቸው ፥ በየአባቶቻ
ቸው ፡ ቤቶች ፥ እንደየስማቸው ፡ ቍጥር ፥ በየ
ራሳቸው ፥ ከሀያ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ከዚያም ፡
በላይ ፡ ያለው ፡ ወንድ ፡ ሁሉ ፥ ወደ ፡ ሰልፍ ፡
የሚወጡት ፡ ሁሉ ፥ ከሮቤል ፡ ነገድ ፡ የተቈ ፳፩ ፡
ጠሩ ፡ እርባ ፡ ስድስት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡
ነበሩ ።

የስምዖን ፡ ልጆች ፡ በየትውልዳቸው ፥ በየ ፳፪ ፡
ወገናቸው ፥ በየአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ የተቈ
ጠሩ ፥ እንደየስማቸው ፡ ቍጥር ፥ በየራሳቸው ፥
ከሀያ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያለው ፡
ወንድ ፡ ሁሉ ፥ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጡት ፡ ሁሉ ፥
ከስምዖን ፡ ነገድ ፡ የተቈጠሩት ፡ አምሳ ፡ ዘጠኝ ፡ ፳፫ ፡
ሺህ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

የጋድ ፡ ልጆች ፡ በየትውልዳቸው ፥ በየወገ ፳፬ ፡
ናቸው ፥ በየአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፥ እንደየስ
ማቸው ፡ ቍጥር ፥ ከሀያ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ከዚ
ያም ፡ በላይ ፡ ያሉት ፥ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወ
ጡት ፡ ሁሉ ፥ ከጋድ ፡ ነገድ ፡ የተቈጠሩት ፡ ፳፭ ፡
እርባ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡
ነበሩ ።

የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ በየትውልዳቸው ፥ በየወ ፳፮ ፡
ገናቸው ፥ በየአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፥ እንደ
የስማቸው ፡ ቍጥር ፥ ከሀያ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡

ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉት ÷ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚ
ፀ፲፮ ፡ ወጡት ፡ ሁሉ ÷ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ የተቈጠሩት ፡
ሰባ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ። ፡ ፡ ፡

፲፭ በዳ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦— የሌዊን ፡ ልጆች ፡ በየአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ በየወገናቸውም ፡ ቍጠር ፡ ወንዱን ፡ ሁሉ ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ ጀምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ ቍጠራቸው ። ፲፮ ሙሴም ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንዳዘ ፲፯ ዘው ፡ ቈጠራቸው ። የሌዊ ፡ ልጆች ፡ በየስማቸው ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ጌድሶን ፡ ቀዓት ፡ ፲፰ ሜራሪ ። የጌድሶንም ፡ ልጆች ፡ ስሞች ፡ በየወገናቸው ፤ እነዚህ ፡ ናቸው ፦ ሎቤኒ ፡ ሰሚኢ ። ፲፱ የቀዓትም ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፤ እንበረም ፡ ፡ ይስዓር ፡ ኬብሮን ፡ ዑዝኤል ። የሜራሪም ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፤ ሞሖሊ ፡ ሙሲ ። የሌዋውያን ፡ ወገኖች ፡ በየአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

፳፩ ለጌድሶን ፡ የሎቤናውያን ፡ ወገን ፡ የሰሚአውያንም ፡ ወገን ፡ ነበሩት ፤ የጌድሶናውያን ፡ ወገኖች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። ከእነርሱ ፡ የተቈጠሩት ፡ ፳፪ የወንዶች ፡ ሁሉ ፡ ቍጥር ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ ጀምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ የተቈጠሩት ፡ ሰባት ፡ ፳፫ ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ። የጌድሶናውያን ፡ ወገኖች ፡ ከማደሪያው ፡ በኋላ ፡ በምዕራብ ፡ ፳፬ በኩል ፡ ይሰፍራሉ ። የጌድሶናውያንም ፡ አባቶች ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ የዳኤል ፡ ልጅ ፡ ኤሊሳፍ ፡ ፳፭ ይሆናል ። ጌድሶናውያንም ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ የሚጠብቁት ፡ ማደሪያው ፡ ድንኳኑም ፡ መደረቢያውም ፡ የመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ፳፮ መጋረጃ ፡ በማደሪያውና ፡ በመሠዊያው ፡ ዙሪያ ፡ ያለው ፡ የአደባባዩ ፡ መጋረጃ ፡ የአደባባዩም ፡ ደጃፍ ፡ መጋረጃ ፡ ለማገልገሉም ፡ ያሉት ፡ ገመዶች ፡ ሁሉ ፡ ይሆናል ።

፳፯ ከቀዓትም ፡ የእንበረግውያን ፡ ወገን ፡ የይስዓራውያንም ፡ ወገን ፡ የኬብሮናውያንም ፡ ወገን ፡ የዑዝኤላውያንም ፡ ወገን ፡ ነበሩ ፤ የቀዓታውያን ፡ ወገኖች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። ፳፱ ወንዶች ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ቍጥራቸው ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ ጀምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ስምንት ፡ ሺህ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ፤ መቅደሱንም ፡ ይጠብቁ ፡ ፳፱ ነበር ። የቀዓት ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ በማደሪያው ፡ ፴ አጠገብ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ይሰፍራሉ ። የቀዓታውያንም ፡ ወገኖች ፡ አባቶች ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ ፴፩ የዑዝኤል ፡ ልጅ ፡ ኤሊሳፈን ፡ ይሆናል ። ታቦቱንም ፡ ገበታውንም ፡ መቅረዙንም ፡ መሠዊያዎቹንም ፡ የሚያገለግሉበትንም ፡ የመቅደሱን ፡ ዕቃ ፡ መጋረጃውንም ፡ ማገልገያውንም ፡ ሁሉ ፡ ፴፪ ይጠብቃሉ ። የሌዋውያንም ፡ አለቆች ፡ አለቃ ፡ የክህኑ ፡ የአሮን ፡ ልጅ ፡ አልዓዛር ፡ ይሆናል ፤ እርሱም ፡ መቅደሱን ፡ በሚጠብቁት ፡ ላይ ፡ ይሆናል ።

፴፫ ከሜራሪ ፡ የሞሖላያውያን ፡ ወገን ፡ የሙሳያውያንም ፡ ወገን ፡ ነበሩ ፤ የሜራሪ ፡ ወገኖች ፡ እነዚህ ፡ ፴፬ ናቸው ። ከእነርሱም ፡ ወንዶች ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ቍጥራቸው ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ ጀምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ የተቈጠሩት ፡ ስድስት ፡ ሺህ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ። የሜራሪም ፡ ወገኖች ፡ አባቶች ፡ ፴፭ ቤት ፡ አለቃ ፡ የአቢካኢል ፡ ልጅ ፡ ሱሪኤል ፡ ነበረ ፤ በማደሪያው ፡ አጠገብ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ይሰፍራሉ ። የሜራሪም ፡ ልጆች ፡ የሚጠብቁት ፡ ፴፮ የማደሪያው ፡ ሳንቆች ፡ መወርወሪያዎችም ፡ ተራዳዎችም ፡ እግሮቹም ፡ ዕቃውም ፡ ሁሉ ፡ ማገልገያውም ፡ ሁሉ ፡ በዙሪያውም ፡ የሚቆሙ ፡ ፴፯ የአደባባዩ ፡ ምሰሶች ፡ እግሮቹም ፡ ካስማዎቹም ፡ አውታሮቹም ፡ ይሆናሉ ።

በማደሪያውም ፡ ፊት ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ፴፰ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ፊት ፡ በስተ ፡ ፀሐይ ፡ መውጫ ፡ የሚሰፍሩት ፡ ሙሴና ፡ አሮን ፡ ልጆቹም ፡ ይሆናሉ ፤ መቅደሱንም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ይጠብቃሉ ፤ ልዩም ፡ ሰው ፡ ቢቀርብ ፡ ይገደል ።

፴፱ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ሙሴና ፡ አሮን ፡ የቈጠሩአቸው ፡ ከሌዋውያን ፡ ወንዶች ፡ ሁሉ ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ ጀምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ በየወገናቸው ፡ የተቈጠሩት ፡ ሁሉ ፡ ሀያ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ነበሩ ።

፴፪ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦— የእስራኤልን ፡ ፴፫ ልጆች ፡ ወንዱን ፡ በሙሉ ፡ ሁሉ ፡ ቍጠር ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ ጀምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉትን ፡ የስማቸውን ፡ ቍጥር ፡ ውሰድ ፤ ሌዋውያንንም ፡ ፴፬ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በሙሉ ፡ ሁሉ ፡ ፋንታ ፡ የሌዋውያንንም ፡ እንስሶች ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንስሶች ፡ በሙሉ ፡ ሁሉ ፡ ፋንታ ፡ ለእኔ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ውሰድ ፤ አለው ። ሙሴም ፡ ፴፭ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በሙሉ ፡ ሁሉ ፡ ቈጠረ ። ከእነርሱም ፡ ፴፮ የተቈጠሩ ፡ ወንዶች ፡ በሙሉ ፡ ሁሉ ፡ በየስማቸው ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ ጀምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ሀያ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ሦስት ፡ ነበሩ ።

፴፯ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦— ሌዋውያንን ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፴፰ በሙሉ ፡ ፋንታ ፡ የሌዋውያንንም ፡ እንስሶች ፡ በእንስሶቻቸው ፡ ፋንታ ፡ ውሰድ ፤ ሌዋውያንም ፡ ለእኔ ፡ ይሁኑ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ። ፴፱ በሌዋውያን ፡ ላይ ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በሙሉ ፡ ስለ ፡ ተረፉት ፡ ስለ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ሦስት ፡ ፴፩ ቤዛ ፡ በየራሱ ፡ አምስት ፡ ሰቅል ፡ ውሰድ ፤ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ ትወስዳለህ ፤ ሰቅሉም ፡ ሀያ ፡ አዖሊ ፡ ነው ። ስለ ፡ ተረፉትም ፡ ፴፪ የመቤዣውን ፡ ገንዘብ ፡ ለአሮንና ፡ ለልጆቹ ፡ ስጥ ። ሙሴም ፡ በሌዋውያን ፡ ከተቤዣቸት ፡ ፴፫ በላይ ፡ ከተረፉት ፡ ዘንድ ፡ የመቤዣውን ፡ ገንዘብ ፡ ወሰደ ። ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በሙሉ ፡ ገንዘቡን ፡ ሺህ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ አምስት ፡ ሰቅል ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ ወሰደ ። ፴፬ እንደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ሙሴ ፡ የመቤዣውን ፡ ገንዘብ ፡ ለአሮንና ፡ ለልጆቹ ፡ ሰጠ ።

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦— ከሌዊ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ በየወገናቸው ፡ በየአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ ፪ የቀዓትን ፡ ልጆች ፡ ድምር ፡ ውሰድ ፤ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አምሳ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ለአገልግሎት ፡ የሚገቡበትን ፡ ሁሉ ፡ ትደምራለህ ። ፫ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ በንዋየ ፡ ቅድሳቱ ፡ ዘንድ ፡ የቀዓት ፡ ልጆች ፡ ሥራ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ከሰፈሩ ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፡ አሮንና ፡ ልጆቹ ፡ ገብተው ፡ የሚሸፍነውን ፡ መጋረጃ ፡ ያውርዱ ፡ የምስክሩንም ፡ ታቦት ፡ ይጠቅልሉበት ፤ ፬ በላዩም ፡ የአቆስጣውን ፡ ቁርበት ፡ መሸፈኛ ፡ ያድርጉበት ፡ ከእርሱም ፡ በላይ ፡ ሁለንተናው ፡ ሰማያዊ ፡ የሆነ ፡ መጐናጸፊያ ፡ ይዘርጉበት ፡ መሎጊያዎቹንም ፡ ያግቡ ። ፭ በገጽ ፡ ኅብስት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ ሰማያዊውን ፡ መጐናጸፊያ ፡ ይዘርጉበት ፡ በእርሱም ፡ ላይ ፡ ወጭቶቹን ፡ ጭልፋዎቹንም ፡ ጽዋዎቹንም ፡ ሰላማዊ ፡ ሰማያዊ ፡ ሰማ ፡ ፮ ፡ ለማፍሰስም ፡ መቅጃዎቹን ፡ ያድርጉ ፡ ሁልጊዜም ፡ የሚኖር ፡ እንጀራ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ይሁን ። ፯ በእነርሱም ፡ ላይ ፡ ቀዩ ፡ መጐናጸፊያ ፡ ይዘርጉ ፡ በአቆስጣውም ፡ ቁርበት ፡ መሸፈኛ ፡ ይሸፍኑት ፡ መሎጊያዎቹንም ፡ ያግቡ ። ፰ ሰማያዊውንም ፡ መጐናጸፊያ ፡ ይውሰዱ ፡ የሚያበራውንም ፡ መቅረዝ ፡ ቀንዲሎቹንም ፡ መኰስተሪያዎቹንም ፡ የኩስታሪ ፡ ማድረጊያዎቹንም ፡ ፡ ፱ አርሱንም ፡ ለማገልገል ፡ የዘይቱን ፡ ዕቃዎች ፡ ሁሉ ፡ ይሸፍኑ ፤ አርሱንና ፡ ዕቃዎቹን ፡ ሁሉ ፡ በአቆስጣ ፡ ቁርበት ፡ መሸፈኛ ፡ ውስጥ ፡ ያድርጉ ፡ ፡ ፲ ቦርጉ ፡ በመሸከሚያውም ፡ ላይ ፡ ያድርጉት ። በወርቁም ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ሰማያዊውን ፡ መጐናጸፊያ ፡ ይዘርጉበት ፡ ፡ በአቆስጣም ፡ ቁርበት ፡ መሸፈኛ ፡ ይሸፍኑት ፡ መሎጊያዎቹንም ፡ ያግቡ ። ፲፩ በመቅደስም ፡ ውስጥ ፡ የሚያገለግሉበትን ፡ የማገልገያውን ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ይውሰዱ ፡ በሰማያዊውም ፡ መጐናጸፊያ ፡ ውስጥ ፡ ያስቀምጡት ፡ በአቆስጣም ፡ ቁርበት ፡ መሸፈኛ ፡ ይሸፍኑት ፡ በመሸከሚያውም ፡ ላይ ፡ ያድርጉት ። ፲፪ አመዱንም ፡ ከመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያስወግዱ ፡ ሐምራዊውንም ፡ መጐናጸፊያ ፡ ይዘርጉበት ፡ የሚያገለግሉበትን ፡ ዕቃውን ፡ ሁሉ ፡ ማንደጃዎቹን ፡ ሜንጦቹንም ፡ መጫሪያዎቹንም ፡ ድስቶቹንም ፡ የመሠዊያውን ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ያስቀምጡበት ፡ በእርሱም ፡ የአቆስጣን ፡ ቁርበት ፡ መሸፈኛ ፡ ይዘርጉ ፡ መሎጊያዎቹንም ፡ ያግቡ ። ፲፫ ከሰፈሩም ፡ ሲነሡ ፡ አሮንና ፡ ልጆቹ ፡ መቅደሱንና ፡ የመቅደሱን ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ከሸፈኑ ፡ በኋላ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የቀዓት ፡ ልጆች ፡ ሊሸከሙት ፡ ይመጣሉ ፤ እንዳይሞቱ ፡ ግን ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳቱን ፡ አይንኩ ። በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ፡ ፲፭ ዘንድ ፡ የቀዓት ፡ ልጆች ፡ ሸክም ፡ ይህ ፡ ነው ። የክህኑም ፡ የአሮን ፡ ልጅ ፡ አልዓዛር ፡ በመ ብራቱ ፡ ዘይት ፡ በጣፋጩም ፡ ዕጣን ፡ ላይ ፡ ፡ ሁልጊዜም ፡ በሚቀርበው ፡ በእህሉ ፡ ቍርባ ፡ ፲፮ ፡ ፡ ፡

ሁሉ ፡ ይህ ፡ ነው ።

፴፱ ፡ ሙሴና ፡ አሮንም ፡ የሕዝቡም ፡ አለቆች ፡ የቀዓትን ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፡ በየአባቶ-
፵ ፡ ቸውም ፡ ቤቶች ፡ ቈጠሩአቸው ። በመገናኛው ፡
ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አገ-
ልግሎት ፡ የገቡትን ፡ ሁሉ ፡ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አምሳ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ያሉትን ፡
፴፩ ፡ ቈጠሩአቸው ፡ በየወገናቸውም ፡ ከእነርሱ ፡
የተቈጠሩት ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡
፴፪ ፡ አምሳ ፡ ነበሩ ። እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡
እንዳዘዘ ፥ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ያገ-
ለገሉት ፡ ሁሉ ፥ ከቀዓታውያን ፡ ወገኖች ፡ የተ-
ቈጠሩት ፤ ሙሴና ፡ አሮን ፡ የቈጠሩአቸው ፥
እነዚህ ፡ ናቸው ።

፴፫ ፡ በየወገናቸውም ፡ በየአባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡
፴፬ ፡ የተቈጠሩት ፡ የጌድሶን ፡ ልጆች ፥ በመገናኛው ፡
ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ለአገልግ-
ሎት ፡ የገቡት ፥ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡
፴፭ ፡ አምሳ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ያሉት ፥ በየወገናቸ-
ውም ፡ በየአባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡ የተቈጠ-
ሩት ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡
፴፮ ፡ ነበሩ ። እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ እንዳ-
ዘዘ ፥ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ያገለገ-
ሉት ፡ ሁሉ ፥ ከጌድሶን ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ የተ-
ቈጠሩት ፥ ሙሴና ፡ አሮን ፡ የቈጠሩአቸው ፥
እነዚህ ፡ ናቸው ።

፴፯ ፡ በየወገናቸውም ፡ በየአባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡
ከሜራሪ ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ የተቈጠሩት ፥
፴፰ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ አገ-
ልግሎት ፡ የገቡት ፡ ሁሉ ፡ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አምሳ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ያሉት ፥
፴፱ ፡ በየወገናቸው ፡ የተቈጠሩት ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡
፵ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ። እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡
እጅ ፡ እንዳዘዘ ፥ ከሜራሪ ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡
የተቈጠሩት ፥ ሙሴና ፡ አሮን ፡ የቈጠሩአቸው ፥
እነዚህ ፡ ናቸው ።

፴፫ ፡ በየወገናቸውና ፡ በየአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡
ከሌዋውያን ፡ የተቈጠሩት ፡ ሁሉ ፥ ሙሴና ፡
አሮን ፡ የእስራኤልም ፡ አለቆች ፡ የቈጠሩአቸው ፥
፴፪ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ሥራውን ፡
ለመሥራትና ፡ ዕቃውን ፡ ለመሸከም ፡ የገቡት ፡
ሁሉ ፥ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አምሳ ፡
፴፫ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ያሉት ፥ ከእነርሱ ፡ የተቈጠ-
ሩት ፡ ስምንት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡
፴፬ ፡ ነበሩ ። እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ እያን-
ዳንዳቸው ፡ በየአገልግሎታቸውና ፡ በየሸክማ-
ቸው ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ ተቈጠሩ ፤ እግዚአብ-
ሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘ ፡ እንዲሁ ፡ በእርሱ ፡
ተቈጠሩ ።

ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፩ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
፪ ፡ ተናገረው ፡ — የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለምጻሙን ፡
ሁሉ ፥ ፈሳሽ ፡ ነገርም ፡ ያለበትን ፡ ሁሉ ፥ በሬ-
ሳም ፡ የረከሰውን ፡ ሁሉ ፡ ከሰፈሩ ፡ እንዲያወጡ ፡
፫ ፡ እዘዛቸው ፡ ወንዱንና ፡ ሴቱን ፡ አውጡ ፤ እኔ ፡
በመካከከሉ ፡ የማድርበትን ፡ ሰፈራቸውን ፡ እንዳ-
፬ ፡ ያረክሱ ፡ ከሰፈሩ ፡ አውጡአቸው ። የእስራኤ-
ልም ፡ ልጆች ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ፥ ከሰፈሩ ፡
አወጡአቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንደ ፡
ተናገረው ፥ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲሁ ፡
አደረጉ ።

፭ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
ተናገረው ፡ — ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ንገራቸው ፡ —
፮ ፡ ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእ-
ዛዝ ፡ ይተላለፍ ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ የሚሠራውን ፡
ኃጢአት ፡ ቢሠራ ፥ በዚያም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ በደል ፡
ቢሆን ፥ በሠራው ፡ ኃጢአት ፡ ይናዘዝ ፡ የወ-
፯ ፡ ሰደውንም ፡ በሙሉ ፡ ይመልስ ፡ አምስተኛው-
ንም ፡ ይጨምርበት ፥ ለበደለውም ፡ ሰው ፡ ይስ-
ጠው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይመልስለት ፡ ዘንድ ፡ ሰው-
ዮው ፡ ዘመድ ፡ ባይኖረው ፥ ስለ ፡ በደል ፡ ለእ-
ግዚአብሔር ፡ የሚመልሰው ፡ ነገር ፡ ለካህኑ ፡
ይሁን ፤ ይህም ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ማስተስረያ ፡ ከሚ-
ደረግበት ፡ አውራ ፡ በግ ፡ በላይ ፡ ይጨመር ።
የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ለካህኑ ፡ የሚያቀርቡት ፡
የተቀደሰ ፡ የማንሣት ፡ ቍርባን ፡ ሁሉ ፡ ለእርሱ ፡
ይሁን ። የተቀደሰ ፡ የሰው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፥ ሰውም ፡
ለካህኑ ፡ የሚሰጠው ፡ ሁሉ ፡ ለእርሱ ፡ ይሁን ።

፲፪ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
ተናገረው ፡ — ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ንገራቸው ፡ —
፲፫ ፡ የማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ከእርሱ ፡ ፈቀቅ ፡
ብትል ፥ በእርሱም ፡ ላይ ፡ ብትበድል ፥ ከሌላም ፡
ሰው ፡ ጋር ፡ ብትተኛ ፥ ከባልዋም ፡ ዓይን ፡ ቢሸ-
ሸግ ፥ እርስዋም ፡ ተሰውራ ፡ ብትረክስ ፥ ምስክ-
ርም ፡ ባይኖርባት ፥ በምንዝርም ፡ ባትገኝ ፥ በባ-
፲፬ ፡ ልዋም ፡ ላይ ፡ የቅንዓት ፡ መንፈስ ፡ ቢመጣበት ፥
እርስዋም ፡ ስትረክስ ፡ ስለ ፡ ሚስቱ ፡ ቢቀና ፤
ወይም ፡ እርስዋ ፡ ሳትረክስ ፡ የቅንዓት ፡ መን-
ፈስ ፡ ቢመጣበት ፥ ስለ ፡ ሚስቱም ፡ ቢቀና ፤
፲፭ ፡ ሰው ፡ ሚስቱን ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ያምጣት ፥
የኢፍ ፡ መስፈሪያም ፡ አሥረኛ ፡ እጅ ፡ ገብስ ፡
ዱቄት ፡ ቍርባን ፡ ስለ ፡ እርስዋ ፡ ያምጣ ፤ የቅ-
ንዓት ፡ ቍርባን ፡ ነውና ፥ ኃጢአትንም ፡ የሚ-
ያሳስብ ፡ የመታሰቢያ ፡ ቍርባን ፡ ነውና ፡ ዘይት ፡
አያፍስስበት ፥ ዕጣንም ፡ አይጨምርበት ።

፲፮ ፡ ካህኑም ፡ ያቀርባታል ፡ በእግዚአብሔርም ፡
ፊት ፡ ያቆማታል ፤ ካህኑም ፡ የተቀደሰ ፡ ውኃ ፡
፲፯ ፡ በሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ይወስዳል ፤ ካህኑም ፡ በማደሪ-
ያው ፡ ውስጥ ፡ ከሰው ፡ ትቢያ ፡ ወስዶ ፡ በውኃ ፡
ላይ ፡ ይረጨዋል ፤ ካህኑም ፡ ሴቲቱን ፡ በእግ-
፲፰ ፡ ዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያቆማታል ፥ የሴቲቱንም ፡
ራስ ፡ ይገልጣል ፥ በእጅዋም ፡ ለመታሰቢያ ፡
የሚሆነውን ፡ የእህል ፡ ቍርባን ፥ ለቅንዓት ፡
ቍርባን ፥ ያኖራል ፤ በካህኑም ፡ እጅ ፡ እርግማ-
ንን ፡ የሚያመጣው ፡ መራራ ፡ ውኃ ፡ ይሆናል ።
፲፱ ፡ ካህኑም ፡ ያምላታል ፥ ሴቲቱንም ፡ እንዲህ ፡
ይላታል ፡ — ሴላ ፡ ወንድ ፡ አልተኛሽ ፥ በልሽ-

ንም ፡ አልተውሽ ፥ ራስሽንም ፡ አላረከሽ ፡
እንደ ፡ ሆነ ፥ እርግማንን ፡ ከሚያመጣ ፡ ከዚህ ፡
፳ ፡ መራራ ፡ ውኃ ፡ ንጹሕ ፡ ሁኚ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በል-
ሽን ፡ ትተሽ ፡ ረክሰሽ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፥ ከባልሽም ፡
ሌላ ፡ ከወንድ ፡ ጋር ፡ ተኝተሽ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
ካህኑም ፡ ሴቲቱን ፡ በመርገም ፡ መሐላ ፡ ያምላ-
፳፩ ፡ ታል ፥ ካህኑም ፡ ሴቲቱን ፡ — እግዚአብሔር ፡
ጭንሽን ፡ እያሰለሰለ ፡ ሆድሽንም ፡ እየነፋ ፥ እግ-
ዚአብሔር ፡ ለመርገምና ፡ ለመሐላ ፡ በሕዝብሽ ፡
መካከል ፡ ያድርግሽ ፤ እርግማንንም ፡ የሚያ-
፳፪ ፡ መጣ ፡ ይህ ፡ ውኃ ፡ ወደ ፡ ሆድሽ ፡ ይግባ ፥ ሆድሽ-
ንም ፡ ይንፋው ፥ ጭንሽንም ፡ ያበስብሰው ፡ ይላ-
ታል ፤ ሴቲቱም ፡ — አሜን ፡ አሜን ፡ ትላለች ።
፳፫ ፡ ካህኑም ፡ እነዚህን ፡ መርገሞች ፡ በሰሌዳ ፡ ይጽ-
ፈዋል ፥ በመራራውም ፡ ውኃ ፡ ይደመስሰዋል ፡
እርግማን ፡ የሚያመጣውንም ፡ መራራ ፡ ውኃ ፡
ለሴቲቱ ፡ ያጠጣታል ፡ የእርግማኑም ፡ ውኃ ፡
፳፬ ፡ በገባባት ፡ ጊዜ ፡ መራራ ፡ ይሆናል ። ካህኑም ፡
የቅንዓቱን ፡ የእህል ፡ ቍርባን ፡ ከሴቲቱ ፡ እጅ ፡
ይወስዳል ፥ የእህሉንም ፡ ቍርባን ፡ በእግዚአ-
ብሔር ፡ ፊት ፡ ይወዘውዘዋል ፤ ወደ ፡ መሠዊያ-
ውም ፡ ያመጣዋል ፤ ካህኑም ፡ ከእህሉ ፡ ቍር-
፳፭ ፡ ባን ፡ አንድ ፡ እፍኝ ፡ ሙሉ ፡ ለመታሰቢያው ፡
ወስዶ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ፥ ከዚ-
ያም ፡ በኋላ ፡ ለሴቲቱ ፡ ውኃውን ፡ ያጠጣታል ።
ውኃውን ፡ ካጠጣት ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ይሆናል ፡
፳፮ ፡ ረክሳና ፡ በባልዋ ፡ ላይ ፡ አመንዝራ ፡ እንደ ፡
ሆነች ፥ እርግማንን ፡ የሚያመጣው ፡ ውኃ ፡
ገብቶ ፡ መራራ ፡ ይሆንባታል ፥ ሆድዋም ፡ ይነ-
ፋል ፥ ጭንዋም ፡ ይሰለስላል ፤ ሴቲቱም ፡ በሕዝ-
ብዋ ፡ መካከል ፡ ለመርገም ፡ ትሆናለች ። ያልረ-
፳፯ ፡ ከሰች ፡ ያለ ፡ ነውርም ፡ እንደ ፡ ሆነች ፥ ንጹሕ ፡
ትሆናለች ፥ ልጆችንም ፡ ታረግዛለች ።
፳፰ ፡ ሴት ፡ ባልዋን ፡ ትታ ፡ በረከሰች ፡ ጊዜ ፥
ወይም ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ የቅንዓት ፡ መንፈስ ፡ በመ-
ጣባት ፡ ጊዜ ፥ ስለ ፡ ሚስቱም ፡ በቀና ፡ ጊዜ ፥
የቅንዓት ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ሴቲቱንም ፡ በእግ-
ዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያቁማት ፥ ካህኑም ፡ እንደ ፡
ዚህ ፡ ሕግ ፡ ሁሉ ፡ ያድርግባት ። ሰውዮውም ፡
ከኃጢአት ፡ ንጹሕ ፡ ይሆናል ፥ ሴቲቱም ፡ ኃጢ-
አትዋን ፡ ትሸከማለች ።

ምዕራፍ ፡ ፮ ።

፩ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
፪ ፡ ተናገረው ፡ — ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ንገራ-
ቸው ፡ — ሰው ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ራሱን ፡ የተለየ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ የናዝራዊነት ፡
ስእለት ፡ ቢሳል ፥ ከወይን ፡ ጠጅና ፡ ከሚያሰክር ፡
 መጠጥ ፡ ራሱን ፡ የተለየ ፡ ያድርግ ፤ ከወይን ፡
ወይም ፡ ከሌላ ፡ ነገር ፡ የሚገኘውን ፡ ሆምጣጤ ፡
አይጠጣ ፥ የወይንም ፡ ጭማቂ ፡ አይጠጣ ፤ የወ-
ይን ፡ እሸት ፡ ወይም ፡ ዘቢብ ፡ አይብላ ። ራሱን ፡
የተለየ ፡ ባደረገበት ፡ ወራት ፡ ሁሉ ፡ ከወይን ፡
የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከውስጡ ፡ ፍሬ ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ገፈፎው ፡ ድረስ ፡ አይብላ ።

፭ ፡ ራሱን ፡ ለመለየት ፡ ስእለት ፡ በደረገበት ፡
ወራት ፡ ሁሉ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ምላጭ ፡ አይደር-
ስም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተለየበት ፡ ወራት ፡
እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ የተቀደሰ ፡ ይሆናል ፡ የራ-
ሱንም ፡ ጠጕር ፡ ያሳድጋል ።

፮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ራሱን ፡ የተለየ ፡ በደረገ-
በት ፡ ወራት ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ሬሳ ፡ አይቅረብ ።
፯ ፡ ለአምላኩ ፡ ያደረገው ፡ ስእለት ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡
ነውና ፡ አባቱ ፡ ወይም ፡ እናቱ ፡ ወይም ፡ ወን-
ድሙ ፡ ወይም ፡ እኅቱ ፡ ሲሞቱ ፡ ሰውነቱን ፡ አያ-
ርክስባቸው ። ራሱን ፡ የተለየ ፡ ባደረገበት ፡
፰ ፡ ወራት ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡
ነው ።

፱ ፡ ሰውም ፡ በአጠገቡ ፡ ድንገት ፡ ቢሞት ፡ የተ-
ለየውንም ፡ ራሱን ፡ ቢያረክስ ፥ እርሱ ፡ በሚነጻ-
በት ፡ ቀን ፡ ራሱን ፡ ይላጭ ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡
፲ ፡ ይላጨው ። በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ሁለት ፡
ዋኖሶች ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ የርግብ ፡ ግልገሎች ፡
ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡
ያምጣ ፡ ካህኑም ፡ አንዱን ፡ ለኃጢአት ፡ መሥ-
፲፩ ፡ ዋዕት ፡ ሁለተኛውንም ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋ-
ዕት ፡ ያቀርበዋል ፡ በሬሳም ፡ የተነካ ፡ ኃጢአት ፡
ሠርቶአልና ፡ ያስተሰርይለታል ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡
ራሱን ፡ ይቀድሰዋል ። ራሱን ፡ የተለየ ፡ ያደረ-
፲፪ ፡ ገበትን ፡ ወራትም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይቀድ-
ሳል ፥ የአንድ ፡ ዓመትም ፡ ተበት ፡ ጠቦት ፡ ለበ-
ደል ፡ መሥዋዕት ፡ ያምጣ ፤ ናዝራዊነቱ ፡ ግን ፡
ረክሶአልና ፡ ያለፈው ፡ ወራት ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡
ይሆናል ።

፲፫ ፡ የመለየቱ ፡ ወራት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ የናዝ-
ራዊው ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡
ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ይቅረብ ፡ ቍርባኑንም ፡ ለእግ-
፲፬ ፡ ዚአብሔር ፡ ያቅርብ ፤ ነውር ፡ የሌለበት ፡ የአ-
ንድ ፡ ዓመት ፡ ተበት ፡ ጠቦት ፡ ለሚቃጠል ፡
መሥዋዕት ፥ ነውርም ፡ የሌለባትን ፡ የአንድ ፡
ዓመት ፡ እንስት ፡ ጠቦት ፡ ለኃጢአት ፡ መሥዋ-
ዕት ፥ ነውርም ፡ የሌለበትን ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ለደ-
ኅንነት ፡ መሥዋዕት ፤ አንድ ፡ ሌማትም ፡ ቂጣ ፡
፲፭ ፡ እንጀራ ፥ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ ከመልካም ፡ ዱቄ-
ትም ፡ የተሠሩ ፡ እንጉቻዎች ፥ በዘይትም ፡ የተ-
ቀባ ፡ ስስ ፡ ቂጣ ፥ የእህሉንም ፡ ቍርባን ፥ የመ-
ጠጡንም ፡ ቍርባን ፡ ያቅርብ ። ካህኑም ፡ በእግ-
፲፮ ፡ ዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያቅርባቸዋል ፡ የኃጢአቱ-
ንም ፡ መሥዋዕት ፡ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋ-
ዕት ፡ ያሳርግለታል ። አውራውንም ፡ በግ ፡ ለደ-
፲፯ ፡ ኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ከሌማቱ ፡ ቂጣ ፡ እንጀራ ፡
ጋር ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያቅርባል ፡ ካህኑም ፡
ደግሞ ፡ የእህሉን ፡ ቍርባንና ፡ የመጠጡን ፡
ቍርባን ፡ ያቅርባል ። ናዝራዊውም ፡ የተለየ ፡
፲፰ ፡ ውን ፡ የራሱን ፡ ጠጕር ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡
አጠገብ ፡ ይላጫል ፥ የመለየቱንም ፡ ራስ ፡ ጠጕር ፡
ወስዶ ፡ ከደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ በታች ፡ ወዳ-
ለው ፡ እሳት ፡ ይጥለዋል ። ካህኑም ፡ የተቀቀለ ፡
፲፱ ፡

ውን ፡ የአውራውን ፡ በግ ፡ ወርች ÷ ከሌማቱም ፡
አንድ ፡ ቂጣ ፡ እንጐቻ ፡ ሐንደም ፡ ስስ ፡ ቂጣ ፡
ደወስዳል ÷ የተለየውንም ፡ የራስ ፡ ጠጕር ፡ ከተ
ላጨ ፡ በኋላ ፡ በናዝራዊው ፡ እጆች ፡ ላይ ፡ ያኖ
ራቸዋል ፡ ካህኑም ፡ እነዚህን ፡ ለመወዝወዝ ፡
ቍርባን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይወዝውዛ
ቸዋል ፡ ይህም ፡ ከሚወዘወዘው ፡ ፍርምባና ፡
ከሚነሣው ፡ ወርች ፡ ጋር ፡ ለካህኑ ፡ የተቀደሰ ፡
ነው ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ናዝራዊው ፡ ወይን ፡
ይጠጣ ፡ ዘንድ ፡ ይችላል ።

ስእለቱን ፡ የተሳለው ፡ የናዝራዊ ፡ እጁም ፡
ከሚያገኘው ፡ ሌላ ፡ ስለ ፡ ናዝራዊነቱ ፡ ለእግ
ዚአብሔር ፡ የሚያቀርበው ፡ የቍርባኑ ፡ ሕግ ፡
ይህ ፡ ነው ፤ ስእለቱን ፡ እንደ ፡ ተሳለ ፡ እንደ ፡
ናዝራዊነቱ ፡ ሕግ ፡ እንዳሁ ፡ ያደርጋል ።

እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
ተናገረው ፦— ለአሮንና ፡ ለልጆቹ ፡ ንገራቸው ፦—
የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ስትባርኩአቸው ፡ እን
ዲህ ፡ በሉአቸው ፡ ፦—

እግዚአብሔር ፡ ይባርክህ ፡ ይጠብቅህም ፡
እግዚአብሔር ፡ ፊቱን ፡ ያብራልህ ÷ ይራራ
ልህም ፡
እግዚአብሔር ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ ያንሣ ÷
ሰላምንም ፡ ይስጥህ ።

እንዲሁ ፡ ስሜን ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡
ያደርጋሉ ፤ እኔም ፡ እባርካቸዋለሁ ።

ምዕራፍ ፡ ፯ ።

እንዲህም ፡ ሆነ ፡ ሙሴ ፡ ማደሪያውን ፡ ፈጽሞ ፡
ከተከለ ፡ በኋላ ÷ እርሱንና ፡ ዕቃውን ፡ ሁሉ ፡
ከቀባና ፡ ከቀደሰ ፡ በኋላ ÷ መሠዊያውንና ፡ ዕቃ
ውንም ፡ ሁሉ ፡ ከቀባና ፡ ከቀደሰ ፡ በኋላ ፡ የእ
ስራኤል ፡ አለቆች ÷ የአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡
አለቆች ÷ ቍርባናቸውን ፡ አቀረቡ ፤ እነዚህም ፡
ከተቈጠሩት ፡ በላይ ፡ የተሾሙ ፡ የነገዶች ፡ አለ
ቆች ፡ ነበሩ ። መባቸውንም ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ አቀረቡ ÷ የተከደኑ ፡ ስድስት ፡ ሰረገሎች ፡
አሥራ ፡ ሁለትም ፡ በሬዎች ፤ በየሁለቱም ፡ አለ
ቆች ፡ አንድ ፡ ሰረገላ ፡ አቀረቡ ÷ ሁሉም ፡ እያ
ንዳንዱ ፡ አንድ ፡ በሬ ፡ በማደሪያው ፡ ፊት ፡
አቀረቡ ። እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡
ብሎ ፡ ተናገረው ፦— ለመገናኛው ፡ ድንኳን ፡
ማገልገል ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ከእነርሱ ፡ ተቀብለህ ፡
ለሌዋውያን ፡ ለእያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ አገልግሎ
ታቸው ፡ ስጣቸው ። ሙሴም ፡ ሰረገሎችንና ፡
በሬዎችን ፡ ተቀብሎ ፡ ለሌዋውያን ፡ ሰጣቸው ።
ለጌድሶን ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ አገልግሎታቸው ፡
ሁለት ፡ ሰረገሎችንና ፡ አራት ፡ በሬዎችን ፡ ሰጣ
ቸው ። ከካህኑም ፡ ከአሮን ፡ ልጅ ፡ ከኢታምር ፡
እጅ ፡ በታች ፡ ላሉት ፡ ለሜራሪ ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡
አገልግሎታቸው ፡ አራት ፡ ሰረገሎችንና ፡ ስም
ንት ፡ በሬዎችን ፡ ሰጣቸው ። ለቀዓት ፡ ልጆች ፡
ግን ፡ መቅደሱን ፡ ማገልገል ፡ የእነርሱ ፡ ነውና ÷
በትከሻቸውም ፡ ይሸከሙት ፡ ነበርና ፡ ምንም ፡
አልሰጣቸውም ። መሠዊያውም ፡ በተቀባ ፡ ፡ ፲ ፡
ቀን ፡ አለቆቹ ፡ መሠዊያውን ፡ ለመቀደስ ፡ ቍር
ባንን ፡ አቀረቡ ፡ አለቆቹም ፡ መባቸውን ፡ በመ
ሠዊያው ፡ ፊት ፡ አቀረቡ ። እግዚአብሔርም ፡ ፡ ፲፩ ፡
ሙሴን ፡— አለቆቹ ፡ መሠዊያውን ፡ ለመቀደስ ፡
መባቸውን ፡ አያንዳንዱ ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ ያቅ
ርቡ ፡ አለው ።

በመጀመሪያውም ፡ ቀን ፡ መባውን ፡ ያቀረበ ፡ ፡ ፲፪ ፡
ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ የአሚናዳብ ፡ ልጅ ፡ ነአሶን ፡
ነበረ ። መባውም ፡ ለአህል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ ፡ ፲፫ ፡
የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሎ ÷ ሚዛኑ ፡
እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡
ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ÷ ሚዛኑም ፡
ሰባ ፡ ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፡ ዕጣንም ፡ ፡ ፲፬ ፡
የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ አሥር ፡ ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡
የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋ ፡ ፡ ፲፭ ፡
ዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ÷ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ÷
አንድ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤ ለኃ ፡ ፡ ፲፮ ፡
ጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤
ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ሁለት ፡ በሬዎች ÷ ፡ ፡ ፲፯ ፡
አምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ÷ አምስት ፡ አውራ ፡
ፍየሎች ÷ አምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡
የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የአሚናዳብ ፡ ልጅ ፡
የነአሶን ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

በሁለተኛውም ፡ ቀን ፡ የይሳኮር ፡ አለቃ ፡ የሶ ፡ ፡ ፲፰ ፡
ገር ፡ ልጅ ፡ ናትናኤል ፡ አቀረበ ። ለመበውም ፡ ፡ ፲፱ ፡
ለአህል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መል
ካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሎትን ÷ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡
መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡
የሆነውን ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ÷ ሚዛኑም ፡
ሰባ ፡ ሰቅል ፡ የሆነውን ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፡
ዕጣንም ፡ የተሞላውን ፡ ሚዛኑ ፡ አሥር ፡ ሰቅል ፡ ፡ ፳ ፡
የሆነውን ፡ አንድ ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤ ለሚቃ ፡ ፡ ፳፩ ፡
ጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ÷ አንድ ፡
አውራ ፡ በግ ÷ አንድ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡
ጠቦት ፤ ለኃጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ ፡ ፳፪ ፡
አውራ ፡ ፍየል ፤ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ፡ ፳፫ ፡
ሁለት ፡ በሬዎች ÷ አምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ÷
አምስት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ÷ አምስት ፡ የአንድ ፡
ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ አቀረበ ፤ ፡
የሶገር ፡ ልጅ ፡ የናትናኤል ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ የዛብሎን ፡ ልጆች ፡ ፡ ፳፬ ፡
አለቃ ፡ የኬሎን ፡ ልጅ ፡ ኤልያብ ፡ መበውም ፡ ፡ ፳፭ ፡
ለአህል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መል
ካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሎ ÷ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅ
ደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡
የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ÷ ሚዛኑም ፡ ሰባ ፡
ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፡ ዕጣንም ፡ ፡ ፳፮ ፡
የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ አሥር ፡ ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡
የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋ ፡ ፡ ፳፯ ፡
ዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ÷ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ÷
አንድ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤ ለኃ ፡ ፡ ፳፰ ፡
ጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤
ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ሁለት ፡ በሬዎች ÷ ፡ ፡ ፳፱ ፡
አምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ÷ አምስት ፡ አውራ ፡
ፍየሎች ÷ አምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡
የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የዛብሎን ፡ ልጅ ፡ የኤ
ሊያብ ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

በአራተኛውም ፡ ቀን ፡ የሮቤል ፡ ልጆች ፡ ፡ ፳፱ ፡
አለቃ ፡ የሰዲዮር ፡ ልጅ ፡ ኤሊሱር ፡ መበውም ፡
ለአህል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መል
ካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሎ ÷ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅ
ደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡
የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ÷ ሚዛኑም ፡ ሰባ ፡
ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፡ ዕጣንም ፡ ፡ ፴
የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ አሥር ፡ ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡
የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ ፡ ፴፩ ፡
አንድ ፡ ወይፈን ÷ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ÷ አንድ ፡
የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤ ለኃጢአ ፡ ፡ ፴፪ ፡
ትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤
ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ሁለት ፡ በሬዎች ÷ ፡ ፡ ፴፫ ፡
አምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ÷ አምስት ፡ አውራ ፡
ፍየሎች ÷ አምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡
የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የሮቤል ፡ ልጅ ፡ የኤ
ሊያብ ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

በአምስተኛውም ፡ ቀን ፡ የስምዖን ፡ ልጆች ፡
አለቃ ፡ የሱሪሰዳይ ፡ ልጅ ፡ ሰለሚኤል ፤ መባ ፡
ውም ፡ ለአህል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡
መልካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሎ ÷ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡
መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡
የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ÷ ሚዛኑም ፡ ሰባ ፡
ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፡ ዕጣንም ፡ ፡ ፴፪ ፡
የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ አሥር ፡ ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡
የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ፡ ፴፫ ፡
አንድ ፡ ወይፈን ÷ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ÷ አንድ ፡
የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤ ለኃጢአ ፡ ፡ ፴፬ ፡
ትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤
ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ሁለት ፡ በሬዎች ÷ ፡ ፡ ፴፭ ፡
አምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ÷ አምስት ፡ አውራ ፡
ፍየሎች ÷ አምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡
የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የሱሪሰዳይ ፡ ልጅ ፡ የሰ
ለሚኤል ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

በስድስተኛውም ፡ ቀን ፡ የዔሌፍሌም ፡ ልጆች ፡ ፡ ፴፮ ፡
አለቃ ፡ የዓሚሁድ ፡ ልጅ ፡ ኤሊሳማ ፡ መበውም ፡ ፡ ፴፯ ፡
ለአህል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡
ዱቄት ፡ የተሞሎ ÷ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡
ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡ የሆነ ፡
አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ÷ ሚዛኑ ፡ ሰባ ፡ ሰቅል ፡
የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፡ ዕጣንም ፡ የተ ፡ ፡ ፴
ሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ አሥር ፡ ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡
የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ ፡ ፴፩ ፡
አንድ ፡ ወይፈን ÷ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ÷ አንድ ፡
የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤ ለኃጢአ ፡ ፡ ፴፪ ፡
ትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤
ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ሁለት ፡ በሬዎች ÷ ፡ ፡ ፴፫ ፡
አምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ÷ አምስት ፡ አውራ ፡
ፍየሎች ÷ አምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡
የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የዔሌፍሌም ፡ ልጆች ፡
ለአህል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መል
ካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሎ ÷ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅ
ደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡
የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ÷ ሚዛኑ ፡ ሰባ ፡
ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፡ ዕጣንም ፡ ፡ ፴
የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ አሥር ፡ ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡
የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ፡ ፴፯ ፡
አንድ ፡ ወይፈን ÷ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ÷ አንድ ፡
የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤ ለኃጢአ ፡ ፡ ፴፰ ፡
ትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤
ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ሁለት ፡ በሬዎች ÷ ፡ ፡ ፴፱ ፡
አምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ÷ አምስት ፡ አውራ ፡
ፍየሎች ÷ አምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡
የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የዔሌፍሌም ፡ ልጆች ፡
ለአህል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መል
ካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሎ ÷ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅ
ደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡
የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ÷ ሚዛኑ ፡ ሰባ ፡
ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፡ ዕጣንም ፡ ፡ ፴
የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ አሥር ፡ ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡
የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ፡ ፴፯ ፡
አንድ ፡ ወይፈን ÷ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ÷ አንድ ፡
የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤ ለኃጢአ ፡ ፡ ፴፰ ፡
ትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤
ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ሁለት ፡ በሬዎች ÷ ፡ ፡ ፴፱ ፡
አምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ÷ አምስት ፡ አውራ ፡
ፍየሎች ÷ አምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡
የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የዔሌፍሌም ፡ ልጆች ፡
ለአህል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መል

ካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሉ ÷ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅ
ደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡
የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ÷ ሚዛኑም ፡ ሰባ ፡
ፍ፡፡ ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፤ ዕጣንም ፡
የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ አሥር ፡ ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡
ፍ፡፡ የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡
አንድ ፡ ወይፈን ÷ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ÷ አንድ ፡
ፍ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤ ለኃጢአትም ፡
ፍ፡፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፡ ለደኅንነ
ትም ፡ መሥዋዕት ፡ ሁለት ፡ በሬዎች ÷ አምስት ፡
አውራ ፡ በጎች ÷ አምስት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ÷
አምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦ
ቶች ፡ ነበረ ፤ የአሚሳዳይ ፡ ልጅ ፡ የአኪዔዘር ፡
መስ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።
ፍ፡፡ በአሥራ ፡ አንደኛውም ፡ ቀን ፡ የአሴር ፡
ልጆች ፡ አለቃ ፡ የኤክራን ፡ ልጅ ፡ ፋግኤል ፡
ፍ፡፡ መበውም ፡ ለእህል ፡ ቍርበን ፡ በዘይት ፡ የተለ
ወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሉ ÷ ሚዛኑ ፡
እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡
ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ÷ ሚዛኑም ፡
ፍ፡፡ ሰባ ፡ ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፤ ዕጣ
ንም ፡ የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ አሥር ፡ ሰቅል ፡ የሆነ ፡
ፍ፡ አንድ ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥ
ዋዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ÷ አንድ ፡ አውራ ፡
በግ ÷ አንድ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤
ፍ፡ ለኃጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡
ፍ፡ ፍየል ፡ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ሁለት ፡
በሬዎች ÷ አምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ÷ አምስት ፡
አውራ ፡ ፍየሎች ÷ አምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡
ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የኤክራን ፡
ልጅ ፡ የፋግኤል ፡ መስ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።
ፍ፡ በአሥራ ፡ ሁለተኛውም ፡ ቀን ፡ የንፍታሌም ፡
ፍ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የዔናን ፡ ልጅ ፡ አኪራ ፡ መስ
ውም ፡ ለእህል ፡ ቍርበን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡
መልካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሉ ÷ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡
መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡
የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ÷ ሚዛኑም ፡ ሰባ ፡
ፍ፡ ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፤ ዕጣንም ፡
ፍ፡ የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ አሥር ፡ ሰቅል ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡
ፍ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋ
ዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ÷ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ÷
ፍ፡ አንድ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤ ለኃ
ጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፡
ፍ፡ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ሁለት ፡ በሬዎች ÷
አምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ÷ አምስት ፡ አውራ ፡
ፍየሎች ÷ አምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡
የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የዔናን ፡ ልጅ ፡ የአኪራ ፡
መስ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።
ፍ፡ መሠዊያው ፡ በተቀባ ፡ ቀን ፡ የእስራኤል ፡
አለቆች ፡ ለመቀደሽው ፡ ያቀረቡት ፡ ቍርበን ፡
ይህ ፡ ነበረ ፤ አሥራ ፡ ሁለት ፡ የብር ፡ ወጭቶች ÷
አሥራ ፡ ሁለት ፡ የብር ፡ ድስቶች ÷ አሥራ ፡
ፍ፡ ሁለት ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋዎች ፤ እያንዳንዱም ፡
የብር ፡ ወጭት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ÷ እያንዳ
ንዱም ፡ ድስት ፡ ሰባ ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ፤ የዚህም ፡
ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ብር ፡ በመቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡
ሁለት ፡ ሺህ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ።
ፍ፡ ዕጣንም ፡ የተሞሉ ፡ አሥራ ፡ ሁለቱ ፡ የወርቅ ፡
ጭልፋዎች ÷ እያንዳንዱ ፡ በመቅደሱ ፡ ሰቅል ፡
ሚዛን ፡ አሥር ፡ አሥር ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ፤ የጭል
ፋዎቹ ፡ ወርቅ ፡ ሁሉ ፡ መቶ ፡ ዘጠ ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ።
ፍ፡ የሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ ከብት ፡ ሁሉ ፡ ከእ
ሁሉ ፡ ቍርበን ፡ ጋር ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ወይፈ
ኖች ÷ አሥራ ፡ ሁለትም ፡ አውራ ፡ በጎች ÷
አሥራ ፡ ሁለትም ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡
ጠቦቶች ፡ ነበሩ ፤ የኃጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡
አውራ ፡ ፍየሎች ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ነበሩ ።
ፍ፡ የደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ከብት ፡ ሁሉ ፡ ዘፍ ፡
አራት ፡ በሬዎች ÷ ስድሳም ፡ አውራ ፡ በጎች ÷
ስድሳም ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ÷ ስድሳም ፡ የአ
ንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበሩ ።
መሠዊያው ፡ ከተቀባ ፡ በኋላ ፡ ለመቀደሽው ፡
የቀረበ ፡ ቍርበን ፡ ይህ ፡ ነበረ ።
ፍ፡ ሙሴም ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድንኳን ፡ እር
ሱን ፡ ለመነጋገር ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ በምስክሩ ፡
ታቦት ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ ከስርየት ፡ መክደኛ ፡
በላይ ፡ ከኪሩቤልም ፡ መካከል ፡ ድምፁ ፡ ሲና
ገረው ፡ ይሰማ ፡ ነበር ፤ እርሱም ፡ ይናገረው ፡
ነበር ።

ምዕራፍ ፡ ፰ ።

እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ፩፡
ተናገረው ፦ መብራቶቹን ፡ ስትለኵስ ፡ ሰባቱ ፡ ፪፡
መብራቶች ፡ በመቅረዙ ፡ ፊት ፡ ያበራሉ ፡ ብለህ ፡
ለአሮን ፡ ንገረው ። አሮንም ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ፤ ፫፡
እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘ ፡ በመቅረዙ ፡
ፊት ፡ መብራቶቹን ፡ ለኵሰ ። መቅረዙም ፡ እን ፬፡
ዲህ ፡ ሠሩት ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር ፤ ከተቀጠቀጠ ፡
ወርቅ ፡ ተሠራ ፡ እስከ ፡ አገዳውና ፡ እስከ ፡ አበ
ቦቹ ፡ ድረስ ፡ ከተቀጠቀጠ ፡ ሥራ ፡ ነበረ ፤ እግ
ዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳሳየው ፡ ምሳሌ ፡ መቅ
ረዙን ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።
፭፡ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
ተናገረው ፦ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ፮፡
ሌዋውያንን ፡ ወስደህ ፡ አንጻቸው ። ታነጻቸው ፡ ፯፡
ዘንድ ፡ እንዲህ ፡ ታደርግላቸዋለህ ፤ ኃጢአትን ፡
የሚያነጻውን ፡ ውኃ ፡ እርጫቸው ÷ በገላቸ
ውም ፡ ሁሉ ፡ ምላጭ ፡ ያሳልፉ ÷ ልብሳቸውንም ፡
ይጠቡ ÷ ይታጠቡም ። ወይፈንን ÷ ለእህሉም ፡ ፰፡
ቍርበን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄ
ትን ፡ ይውሰዱ ÷ ሌላውንም ፡ ወይፈን ፡ ለኃጢ
አት ፡ መሥዋዕት ፡ ውሰድ ። ሌዋውያንንም ፡ ፱፡
በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ፊት ፡ አቅርብ ፤ የእስ
ራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ ሰብስብ ።
ሌዋውያንንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አቅር ፡ ፲፡
ባቸው ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በሌዋውያን ፡
ላይ ፡ እጃቸውን ፡ ይጫኑባቸው ። አሮንም ፡ ፲፩፡
ሌዋውያን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡

ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ስጦታ ፡ አድ
ርጎ ፡ ሌዋውያንን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያቅ
ርብ ። ሌዋውያኑም ፡ በወይፈኖቹ ፡ ራሶች ፡ ላይ ፡
እጆቻቸውን ፡ ይጫኑ ፡ ለሌዋውያንም ፡ ስለ ፡
ማስተስረያ ፡ አንዱን ፡ ለኃጢአት ፡ መሥዋዕት ÷
ሁለተኛውንም ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ አቅርብ ። ሌዋውያንንም ፡ በአ
ሮንና ፡ በልጆቹ ፡ ፊት ፡ አቁማቸው ÷ በእግዚአ ፡ ፲፪፡
ብሔርም ፡ ፊት ፡ ስጦታ ፡ አድርገህ ፡ አቅርብ
ቸው ። እንዲሁ ፡ ሌዋውያንን ፡ ከእስራኤል ፡
ልጆች ፡ መካከል ፡ ለይ ፡ ሌዋውያንም ፡ ለእኔ ፡
ይሁኑ ።
ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ሌዋውያን ፡ የመገናኛውን ፡
ድንኳን ፡ አገልግሎት ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡ ይገ ፡ ፲፫፡
ባሉ ፡ ታነጻቸውማለህ ÷ ስጦታም ፡ አድርገህ ፡
ታቀርባቸዋለህ ። እነርሱም ፡ ከእስራኤል ፡
ልጆች ፡ መካከል ፡ ፈጽሞ ፡ ለእኔ ፡ ተሰጥተዋ
ልና ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በኵራት ፡ ሁሉ ÷
ማኅፀን ፡ በሚከፍት ፡ ሁሉ ፡ ፋንታ ፡ ለእኔ ፡ ወስ
ጀአቸዋለሁ ። በግብፅ ፡ ምድር ፡ ያለውን ፡
በኵር ፡ ሁሉ ፡ በገደልሁበት ፡ ቀን ፡ የእስራኤ
ልን ፡ ልጆች ፡ በኵራት ፡ ሁሉ ÷ ሰው ፡ ወይም ፡
እንስሳ ÷ ለእኔ ፡ ቀድሻለሁ ፤ የእኔ ፡ ናቸው ። ፡ ፲፭፡
በእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በኵራት ፡ ሁሉ ፡ ፋንታ ፡
ሌዋውያንን ፡ ወስጀአለሁ ። የእስራኤልም ፡
ልጆች ፡ ወደ ፡ መቅደሱ ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ መቅ
ሠፍት ፡ እንዳያገኛቸው ÷ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡
ያስተሰርዩላቸው ፡ ዘንድ ÷ የእስራኤልንም ፡
ልጆች ፡ አገልግሎት ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡
ውስጥ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ሌዋውያንን ፡ ከእስራ
ኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ለአሮንና ፡ ለልጆቹ ፡
ስጦታ ፡ አድርጌ ፡ ሰጥቼአቸዋለሁ ።
ሙሴና ፡ አሮን ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡
ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁ ፡ በሌዋውያን ፡ ላይ ፡
አደረጉ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ስለ ፡ ሌዋ
ውያን ፡ እንዳዘዘው ፡ እንዲሁ ፡ የእስራኤል ፡
ልጆች ፡ አደረጉላቸው ። ሌዋውያንም ፡ ከኃ
ጢአት ፡ ተጣጠቡ ÷ ልብሳቸውንም ፡ አጠቡ ፤
አሮንም ፡ ስጦታ ፡ አድርጎ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ አቀረበቸው ÷ አሮንም ፡ ያነጻቸው ፡ ዘንድ ፡
አስተሰረየላቸው ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ሌዋው
ያን ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ በአሮ
ንና ፡ በልጆቹ ፡ ፊት ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ይሠሩ ፡
ዘንድ ፡ ገቡ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ስለ ፡
ሌዋውያን ፡ እንዳዘዘው ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉላ
ቸው ።
እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
ተናገረው ፦ የሌዋውያን ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ፡
ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ከዚያም ፡
በላይ ፡ ያሉት ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ሥራ ፡
ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡ ይገቡሉ ። ዕድሜአቸውም ፡
አምሳ ፡ ዓመት ፡ ሲሞላ ፡ የአገልግሎታቸውን ፡
ሥራ ፡ ይተዋሉ ÷ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አይሠሩም ፡
የተሰጣቸውን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ወንድሞቻ ፡
ቸውን ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ያገለ
ግሉ ፡ የድንኳኑን ፡ አገልግሎት ፡ አይሠሩም ።
እንዲሁ ፡ ስለ ፡ ሥራቸው ፡ በሌዋውያን ፡ ላይ ፡
ታደርጋለህ ።

ምዕራፍ ፡ ፱ ።

ከግብፅም ፡ ምድር ፡ በወጡ ፡ በሁለተኛው ፡ ፩፡
ዓመት ፡ በመጀመሪያው ፡ ወር ፡ በሲና ፡ ምድረ ፡
በዳ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
ተናገረው ፦ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በጊዜው ፡ ፪፡
ፋሲካውን ፡ ያደርጉ ፡ በዚህ ፡ ወር ፡ በአሥራ ፡ ፫፡
አራተኛው ፡ ቀን ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ በጊዜው ፡ አድ
ርጉት ፤ እንደ ፡ ሥርዓቱ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ፍር
ዱም ፡ ሁሉ ፡ አድርጉት ። ሙሴም ፡ ፋሲካን ፡ ፬፡
ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ተናገ
ራቸው ። በመጀመሪያውም ፡ ወር ፡ በአሥራ ፡ ፭፡
አራተኛው ፡ ቀን ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ በሲና ፡ ምድረ ፡
በዳ ፡ ፋሲካን ፡ አደረጉ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡
እንዳዘዘው ፡ እንዲሁ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡
አደረጉ ። በሞተ ፡ ሰው ፡ ሬሳ ፡ የረከሱ ፡ ሰዎ ፡ ፮፡
ችም ፡ ነበሩ ÷ ስለዚህም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ፋሲካን ፡
ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ። በዚያም ፡ ቀን ፡
ወደ ፡ ሙሴና ፡ ወደ ፡ አሮን ፡ ቀረቡ ። እነዚ ፡ ፯፡
ያም ፡ ሰዎች ፦ በሞተ ፡ ሰው ፡ ሬሳ ፡ ረክሰናል ፤
በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ በጊዜው ፡ ቍር
በን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዳናቀርብ ፡ ስለ ፡ ምን ፡
እንከለከላለን ? አሉት ። ሙሴም ፦ እግዚአ ፡ ፰፡
ብሔር ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ የሚያዝዘውን ፡ እስክ
ሰማ ፡ ድረስ ፡ ቁዩ ፡ አላቸው ።
እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ፱፡
ተናገረው ፦ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ፡ ፲፡
ብለህ ፡ ንገራቸው ፦ ከእናንተ ፡ ወይም ፡ ከት
ውልዶቻችሁ ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ በራሳ ፡ ቢረከስ ፡
ወይም ፡ ሩቅ ፡ መንገድ ፡ ቢሄድ ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ፋሲካን ፡ ያድርግ ። በሁለተ ፡ ፲፩፡
ኛው ፡ ወር ፡ በአሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ በመሸ ፡
ጊዜ ፡ ያድርጉት ፤ ከቂጣ ፡ እንጀራና ፡ ከመራራ ፡
ቅጠል ፡ ጋር ፡ ይብሉት ። ከእርሱም ፡ እስከ ፡ ፲፪፡
ነገ ፡ ምንም ፡ አያስቀሩ ÷ ከእርሱም ፡ አጥንትን ፡
አይሰብሩ ፤ እንደ ፡ ፋሲካ ፡ ሥርዓት ፡ ሁሉ ፡ ያድ
ርጉት ። ነገር ፡ ግን ፡ ንጹሕ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በመ ፡ ፲፫፡
ንገድም ፡ ላይ ፡ ያልዘነ ፡ ፋሲካን ፡ ባያደርግ ÷
ያ ፡ ሰው ፡ ከሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ ተለይቶ ፡ ይጠፋል ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ቍርበን ፡ በጊዜው ፡ አላቀ
ረበምና ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ኃጢአቱን ፡ ይሸከማል ። ፡
በመካከላችሁም ፡ መጻተኛ ፡ ቢኖር ÷ ለእግዚአ ፡ ፲፬፡
ብሔር ፡ ፋሲካን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ቢወድድ ÷
እንደ ፡ ፋሲካ ፡ ሥርዓት ፡ እንደ ፡ ፍርዱም ፡ እን
ዲሁ ፡ ያድርግ ፤ ለመጻተኛና ፡ ለአገር ፡ ልጅ ፡
አንድ ፡ ሥርዓት ፡ ይሁንላችሁ ።
ማደሪያውም ፡ በተተከለ ፡ ቀን ፡ ደመናው ፡ ፲፭፡
የምስክሩን ፡ ድንኳን ፡ ሸፈነው ፤ ከማታም ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ጥዋት ፡ ድረስ ፡ በማደሪያው ፡
ላይ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ይመስል ፡ ነበር ። እንዲሁ ፡ ፲፮፡

ዘፍጥ ፡ ፡ ፡

ረው ፡ መንፈስ ፡ ወስዶ ፡ በሰባው ፡ ሽማግሌዎች ፡
ላይ ፡ አደረገ ፡ መንፈሱም ፡ በላያቸው ፡ በደረ ፡
ጊዜ ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡
አልተናገሩም ፡ ።

ከእነርሱም ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ በሰፈር ፡ ቀር
ተው ፡ ነበር ፡ የአንዱም ፡ ስም ፡ ኤልዳድ ፡ የሁ
ለተኛውም ፡ ሞዳድ ፡ ነበረ ፡ መንፈስም ፡ ወረ
ደባቸው ፡ እነርሱም ፡ ከተጻፉት ፡ ጋር ፡ ነበሩ ፡
ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ ግን ፡ አልወጡም ፡ ነበር ፡ በሰ
ፈሩም ፡ ውስጥ ፡ ሳሉ ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩ ፡ ።
አንድ ፡ ጕብዝ ፡ ሰው ፡ እየሮጠ ፡ መጥቶ ፡ — ኤል
ዳድና ፡ ሞዳድ ፡ በሰፈር ፡ ትንቢት ፡ ይናገራሉ ፡
ብሎ ፡ ለሙሴ ፡ ነገረው ፡ ከልጅነቱ ፡ ጀምሮ ፡
የሙሴ ፡ አገልጋይ ፡ የነበረው ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡
ኢያሱ ፡ — ጌታዬ ፡ ሙሴ ፡ ሠይ ፡ ከልክላቸው ፡
አለው ፡ ። ሙሴም ፡ — የእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡
ሁሉ ፡ ነቢያት ፡ ቢሆኑ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በእ
ነርሱ ፡ ላይ ፡ መንፈሱን ፡ ቢያወርድ ፡ አንተ ፡
ስለ ፡ እኔ ፡ ትቀናለህን ? አለው ። ሙሴም ፡
ከእስራኤል ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ሰፈር ፡
ተመለሰ ፡ ።

ነፋስም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ፡
ከባሕርም ፡ ድርጭቶችን ፡ አመጣ ፡ የአንድ ፡
ቀንም ፡ መንገድ ፡ ያህል ፡ በዚህ ፡ የአንድ ፡
ቀንም ፡ መንገድ ፡ ያህል ፡ በዚያ ፡ በሰፈሩ ፡ ላይ ፡
በተናቸው ፡ በዚያም ፡ በሰፈሩ ፡ ዙሪያ ፡ ከፍታው ፡
ከምድር ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፡ ።
በዚያም ፡ ቀን ፡ ሁሉ ፡ በሌሊትም ፡ ሁሉ ፡ በን
ጋውም ፡ ሁሉ ፡ ሕዝቡ ፡ ተነሥተው ፡ ድርጭ
ትን ፡ ሰበሰቡ ፡ ከሁሉ ፡ ዋቂት ፡ የሰበሰበ ፡ አሥር ፡
የቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ የሚያህል ፡ ሰበሰበ ፡ በሰ
ፈሩም ፡ ዙሪያ ፡ ሁሉ ፡ አሰጡት ። ሥጋውም ፡
ገና ፡ በጥርሳቸው ፡ መካከል ፡ ሳለ ፡ ሳያኝኩትም ፡
የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ነደደ ፡
እግዚአብሔርም ፡ ሕዝቡን ፡ በታላቅ ፡ መቅሠ
ፍት ፡ እጅግ ፡ መታ ። የጕመጁ ፡ ሕዝብ ፡ በዚያ ፡
ተቀብረዋልና ፡ የዚያ ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ የምኞት ፡
መቃብር ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ። ሕዝቡም ፡ ከም
ኞት ፡ መቃብር ፡ ወደ ፡ ሐጼሮት ፡ ተነሡ ፡ በሐ
ጼሮትም ፡ ተቀመጡ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

ሙሴም ፡ ኢትዮጵያዊቱን ፡ አግብቶአልና ፡
ባገባት ፡ በኢትዮጵያዊቱ ፡ ምክንያት ፡ ማርያ
ምና ፡ አሮን ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ተናገሩ ። እነር
ሱም ፡ ፡ በውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ ብቻ ፡
ተናግሮአልን ? በእኛስ ፡ ደግሞ ፡ የተናገረ ፡
አይደለምን ? አሉ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሰማ ።
ሙሴም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ከሉት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
ይልቅ ፡ እጅግ ፡ ትሑት ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

እግዚአብሔርም ፡ ወዲያው ፡ ሙሴንና ፡ አሮ
ንን ፡ ማርያምንም ፡ ፡ ሦስታችሁ ፡ ወደ ፡ መገና
ኛው ፡ ድንኳን ፡ ውጡ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፡ ሦስ
ቱም ፡ ወጡ ። እግዚአብሔርም ፡ በደመና ፡
ዓምድ ፡ ወረደ ፡ በድንኳኑም ፡ ደጃፍ ፡ ቆመ ፡
አሮንንና ፡ ማርያምን ፡ ጠራ ፡ ሁለቱም ፡ ወጡ ።
እርሱም ፡ — ቃሌን ፡ ስሙ ፡ በመከከላችሁ ፡
ነቢይ ፡ ቢኖር ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ በራእይ ፡
እገለጥለታለሁ ፡ ወይም ፡ በሕልም ፡ እናገረዋ
ለሁ ። ባሪያዬ ፡ ሙሴ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አይደ
ለም ፡ እርሱ ፡ በቤቴ ፡ ሁሉ ፡ የታመነ ፡ ነው ።
እኔ ፡ አፍ ፡ ለአፍ ፡ በግልጥ ፡ እናገረዋለሁ ፡ በም
ሳሌ ፡ አይደለም ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ መልክ ፡
ያያል ፡ በባሪያዬ ፡ በሙሴ ፡ ላይ ፡ ትናገሩ ፡ ዘንድ ፡
ስለ ፡ ምን ፡ አልፈራችሁም ? አለ ።

እግዚአብሔርም ፡ ተቈጥቶባቸው ፡ ሄደ ።
ደመናውም ፡ ከድንኳኑ ፡ ተነሣ ፡ እነሆም ፡ ማር
ያም ፡ ለምጻም ፡ ሆነች ፡ እንደ ፡ አመዳይም ፡
ነጭ ፡ ሆነች ፡ አሮንም ፡ ማርያምን ፡ ተመለ
ከተ ፡ እነሆም ፡ ለምጻም ፡ ሆና ፡ ነበር ። አሮ
ንም ፡ ሙሴን ፡ — ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ስንፍና ፡ አደ
ርገናልና ፡ በድለንማልና ፡ እባክህ ፡ ኃጢአት ፡
አታድርግብን ። ከእናቴ ፡ ሆድ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡
ግማሽ ፡ ሥጋው ፡ ተበልቶ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ እር
ስዋ ፡ አትሁን ። ሙሴም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
እየጮኸ ፡ አቤቱ ፡ እባክህ ፡ አድናት ፡ አለው ።
እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ — አባትዋ ፡ ምራ
ቱን ፡ በፊትዋ ፡ ቢተፋባት ፡ ስንኳ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡
ታፍር ፡ ዘንድ ፡ ይገባት ፡ ነበር ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡
ከሰፈር ፡ ውጭ ፡ ተዘግታ ፡ ትቀመጥ ፡ ከዚያም ፡
በኋላ ፡ ትመለስ ፡ አለው ። ማርያምም ፡ ከሰፈር ፡
ውጭ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ተዘግታ ፡ ተቀመጠች ፡
ማርያምም ፡ እስከ ፡ ተመለሰ ፡ ድረስ ፡ ሕዝቡ ፡
አልተጓዙም ፡ ።

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡ ፡ ከሐጼሮት ፡ ተጓዙ ፡
በፋራንም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሰፈሩ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
ተናገረው ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የምሰጣትን ፡
የከነዓንን ፡ ምድር ፡ ይሰልሉ ፡ ዘንድ ፡ ሰዎችን ፡
ላክ ፡ ከአባቶች ፡ ነገድ ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ በመ
ካከላቸው ፡ አለቃ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ትልካላ
ችሁ ። ሙሴም ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡
ከፋራን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ላካቸው ፡ እነርሱም ፡
ሁሉ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ አለቆች ፡ ነበሩ ።
ስማቸውም ፡ ይህ ፡ ነበረ ፡ ከሮቤል ፡ ነገድ ፡ የዘ
ኩር ፡ ልጅ ፡ ሰሙኤል ፡ ከስምዖን ፡ ነገድ ፡ የሱሪ ፡
ልጅ ፡ ሰፋጥ ፡ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ የዮፎኒ ፡ ልጅ ፡
ካሌብ ፡ ከይሳኮር ፡ ነገድ ፡ የዮሴፍ ፡ ልጅ ፡ ይግ
አል ፡ ከኤፍሬም ፡ ነገድ ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ አውሴ ፡
ከብንያም ፡ ነገድ ፡ የፈራቶ ፡ ልጅ ፡ ፈልጢ ፡ ከዘብ
ሎን ፡ ነገድ ፡ የሶዲ ፡ ልጅ ፡ ጉዲኤል ፡ ከዮሴፍ ፡
ነገድ ፡ እርሱም ፡ የምናሴ ፡ ነገድ ፡ የሱሲ ፡ ልጅ ፡
ጋዲ ፡ ከዳን ፡ ነገድ ፡ የገማሊ ፡ ልጅ ፡ ዓሚኤል ፡
ከአሴር ፡ ነገድ ፡ የሚካኤል ፡ ልጅ ፡ ሰቱር ፡
ከንፍታሌም ፡ ነገድ ፡ የያቢ ፡ ልጅ ፡ ናቢ ፡
ከጋድ ፡ ነገድ ፡ የማኪ ፡ ልጅ ፡ ጉዲኤል ።

ሙሴ ፡ ምድሪቱን ፡ ይሰልሉ ፡ ዘንድ ፡ ሙሴ ፡ የላካቸው ፡
ሰዎች ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ። ሙሴም ፡ የነዌን ፡
ልጅ ፡ አውሴን ፡ ኢያሱ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ሙሴም ፡ የከነዓንን ፡ ምድር ፡ ይሰልሉ ፡ ዘንድ ፡
ላካቸው ፡ አላቸውም ፡ — ከዚህ ፡ በደቡብ ፡
በኩል ፡ ውጡ ፡ ወደ ፡ ተራሮችም ፡ ሂዱ ፡ ምድ
ሪቱንም ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ በእርስዋም ፡
የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ብርቱዎች ፡ ወይም ፡ ደካሞች ፡
ዋቂቶች ፡ ወይም ፡ ብዙዎች ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ የሚ
ኖሩበትም ፡ ምድር ፡ መልካም ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡
የሚኖሩበትስ ፡ ከተሞች ፡ ሰፈሮች ፡ ወይም ፡
አጥሮች ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ምድሪቱም ፡ ወፍራም ፡
ወይም ፡ ስስ ፡ ዛፍ ፡ ያለባት ፡ ወይም ፡ የሌለባት ፡
እንደ ፡ ሆነች ፡ እዩ ፡ ከምድሪቱ ፡ ፍሬ ፡ አምጡ ፡
እያዘአችሁ ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ወይኑ ፡ አስቀ
ድሞ ፡ ፍሬ ፡ የሚያፈራበት ፡ ወራት ፡ ነበረ ።
ወጡም ፡ ምድሪቱንም ፡ ከጺን ፡ ምድረ ፡
በዳ ፡ በሐማት ፡ ዳር ፡ እስከ ፡ ሰዎ ፡ ሰዎ ፡
ሬሖብ ፡ ድረስ ፡ ሰለሉ ። በደቡብም ፡ በኩል ፡
ወጡ ፡ ወደ ፡ ኬብሮንም ፡ ደረሱ ፡ በዚያም ፡
የዔናቅ ፡ ልጆች ፡ አኪመን ፡ ሴሲ ፡ ተላሚ ፡
ነበሩ ። ኬብሮንም ፡ በግብፅ ፡ ከለችው ፡ ከጣኔ
ዎስ ፡ በፊት ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ተሠርታ ፡ ነበር ።
ወደ ፡ ኤሽኮልም ፡ ሸለቆ ፡ መጡ ፡ ከዚያም ፡
ከወይኑ ፡ አንድ ፡ ዘለላ ፡ የነበረበትን ፡ አረግ ፡
ቈረጡ ፡ ሁለቱም ፡ ሰዎች ፡ በመሎጊያ ፡ ተሸ
ከሙት ፡ ደግሞም ፡ ከሮማኑ ፡ ከበለሶም ፡
አመጡ ። የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከዚያ ፡ ስለ ፡
ቈረጡት ፡ ዘለላ ፡ የዚያን ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ የኤሽ
ኮል ፡ ሸለቆ ፡ ብለው ፡ ጠሩት ።

ምድሪቱንም ፡ ሰልለው ፡ ከአርባ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡
ተመለሱ ። በፋራን ፡ ምድረ ፡ በዳና ፡ በቃዴስ ፡
ወዳሉት ፡ ወደ ፡ ሙሴና ፡ ወደ ፡ አሮን ፡ ወደ ፡
እስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ ሄደው ፡
ደረሱ ፡ ወሬውንም ፡ ለእነርሱና ፡ ለማኅበሩ ፡
ሁሉ ፡ ነገሩአቸው ፡ የምድሪቱንም ፡ ፍሬ ፡ አሳ
ዩአቸው ። እንዲህም ፡ ብለው ፡ ነገሩት ፡ — ወደ ፡
ላከኸን ፡ ምድር ፡ ደረስን ፡ እርስዋም ፡ ወተ
ትና ፡ ማር ፡ ታፈስሳለች ፡ ፍሬዋም ፡ ይህ ፡ ነው ።
ነገር ፡ ግን ፡ በምድሪቱ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ኃያ
ላኑ ፡ ናቸው ፡ ከተሞቻቸውም ፡ የተመሸጉ ፡ እጅ
ግም ፡ የጸኑ ፡ ናቸው ፡ ደግሞም ፡ በዚያ ፡ የዔና
ቅን ፡ ልጆች ፡ አየን ። በደቡብም ፡ ምድር ፡ አማ
ሌቅ ፡ ተቀምጦአል ፡ በተራሮቹም ፡ ኬጢያዊና ፡
ኢያቡሳዊ ፡ አሞራዊም ፡ ተቀምጠዋል ፡ ከነዓ
ናዊም ፡ በባሕር ፡ ዳርና ፡ በዮርዳኖስ ፡ አጠገብ ፡
ተቀምጦአል ።

ካሌብም ፡ ሕዝቡን ፡ በሙሴ ፡ ፊት ፡ ዝም ፡
አሰኘና ፡ — ማሸነፍ ፡ እንችላለንና ፡ እንውጣ ፡
እንውረሰው ፡ አለ ። ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የወጡ ፡
ሰዎች ፡ ግን ፡ — በጭራ ፡ ከእኛ ፡ ይበረታሉና ፡
በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ መውጣት ፡ አንችልም ፡
አሉ ። ስለ ፡ ሰለሉአትም ፡ ምድር ፡ ክፉ ፡ ወሬ ፡
ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እያወሩ ፡ — እኛ ፡ ዘረን ፡
የሰለልናት ፡ ምድር ፡ የሚኖሩበትን ፡ ሰዎች ፡
የምትበላ ፡ ምድር ፡ ናት ፡ በእርስዋም ፡ ዘንድ ፡
ያየናቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ረጃጅም ፡ ሰዎች ፡
ናቸው ። በዚያም ፡ ከኔፊሊም ፡ ወገን ፡ የሆኑ ፡
ትን ፡ ኔፊሊም ፡ የሚናቅን ፡ ልጆች ፡ አየን ፡
እኛም ፡ በዓይናችን ፡ ግምት ፡ እንደ ፡ አንበጣ
ዎች ፡ ነበርን ፡ ደግሞም ፡ እኛ ፡ በዓይናቸው ፡
ዘንድ ፡ እንዲሁ ፡ ነበርን ፡ አሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

ማኅበሩም ፡ ሁሉ ፡ ድምፃቸውን ፡ አንሥተው ፡
ጮኹ ፡ ሕዝቡም ፡ በዚያ ፡ ሌሊት ፡ አለቀሱ ።
የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ በሙሴና ፡ በአ
ሮን ፡ ላይ ፡ አጕረመረሙ ፡ ማኅበሩም ፡ ሁሉ ፡ —
በግብፅ ፡ ምድር ፡ ብንሞት ፡ ምነው ፡ በሞትን ፡ ኖሮ !
ወይም ፡ በዚህ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ምነው ፡ በሞትን ፡
ኖሮ ! እግዚአብሔርም ፡ በሰይፍ ፡ እንሞት ፡
ዘንድ ፡ ወደዚች ፡ ምድር ፡ ስምን ፡ ያገባናል ?
ሴቶቻችንና ፡ ልጆቻችን ፡ ምርኮ ፡ ይሆናሉ ፡
ወደ ፡ ግብፅ ፡ መመለስ ፡ እይሻለንምን ? አሉአ
ቸው ።

እርስ ፡ በርሳቸውም ፡ — ኑ ፡ አለቃ ፡ ሾመን ፡
ወደ ፡ ግብፅ ፡ እንመለስ ፡ ተባባሉ ። ሙሴና ፡
አሮንም ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ጉባኤ ፡ ፊት ፡
በግምባራቸው ፡ ወደቁ ። ምድርን ፡ ከሰለሉት ፡
ጋር ፡ የነበሩት ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱና ፡ የዮፎኒ ፡
ልጅ ፡ ካሌብ ፡ ልብሳቸውን ፡ ቀደዱ ። ለእስራ
ኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ — ዘረን ፡ የሰ
ለልናት ፡ ምድር ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ናት ።
እግዚአብሔርስ ፡ ከወደደን ፡ ወተትና ፡ ማር ፡
ወደምታፈስሰው ፡ ወደዚች ፡ ምድር ፡ ያገባ
ናል ፡ እርስዋንም ፡ ይሰጠናል ። ነገር ፡ ግን ፡ በእ
ግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ አታምፁ ፡ እንደ ፡ እንጀራ ፡
ይሆኑልናልና ፡ የምድሪቱን ፡ ሰዎች ፡ አትፍሩ ፡
ጥላቸው ፡ ክላያቸው ፡ ተገፍፎአል ፡ እግዚአ
ብሔርም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ነው ፡ አትፍሩአቸው ፡
ብለው ፡ ተናገሩአቸው ። ማኅበሩ ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡
በድንጋይ ፡ ይወግሩአቸው ፡ ዘንድ ፡ ተማከሩ ።
የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡
ሁሉ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ተገለጠ ።

እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ — ይህ ፡ ሕዝብ ፡
እስከ ፡ መቼ ፡ ይንቀኛል ? በፊቱስ ፡ በደረግሁት ፡
ተአምራት ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ አያምንብ
ኝም ? ክርስታቸው ፡ አጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ በቸ
ነፈር ፡ እመታቸዋለሁ ፡ አንተንም ፡ ከእነርሱ ፡
ለሚበዛና ፡ ለሚጠነክር ፡ ሕዝብ ፡ አደርግሃለሁ ፡
አለው ።

ሙሴም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አለው ፡ — ግብፃ
ውያን ፡ ይሰማሉ ፡ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ ከመከከ
ቸው ፡ በኃይልህ ፡ አውጥተኸዋልና ፡ ለዚ
ችም ፡ ምድር ፡ ሰዎች ፡ ይናገራሉ ። አንተ ፡
እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡
ሆንህ ፡ ሰምተዋል ፡ አንተም ፡ አቤቱ ፡ ፊት ፡
ለፊት ፡ ተገልጠሃል ፡ ደመናህም ፡ በላያቸው ፡

ቆሞአል ፤ በቀንም ፡ በደመና ፡ ዓምደ ÷ በሌ
ሊትም ፡ በእሳት ፡ ዓምድ ፡ በፈታቸው ፡ ትሄዳ
፲፫ ፡ ለህ ። ይህን ፡ ሕዝብ ፡ አንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡
፲፬ ፡ ብትገድል ፡ ዝናህን ፡ የሰሙ ፡ አሕዛብ ፡— እግ
ዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ማለላቸው ፡
ምድር ፡ ያገባቸው ፡ ዘንድ ፡ አልቻለምና ፡ በም
ድረ ፡ በዳ ፡ ገደላቸው ፡ ብለው ፡ ይናገራሉ ።
፲፭ ፡ ፲፮ ፡ አሁንም ÷ እባክህ ፡— እግዚአብሔር ፡ ታጋሽና ፡
ምሕረቱ ፡ የበዛ ፡ አበሳንና ፡ መተላለፍን ፡ ይቅር ፡
የሚል ÷ ኃጢአተኞችንም ፡ ከቶ ፡ የማያነጻ ÷
የአባቶችን ፡ ኃጢአት ፡ እስከ ፡ ሦስትና ፡ እስከ ፡
አራት ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ በልጆች ፡ ላይ ፡ የሚ
ያመጣ ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ እንደ ፡ ተናገርህ ÷ የጌታ ፡
፲፱ ፡ ኃይል ፡ ታላቅ ፡ ይሁን ። ይህን ፡ ሕዝብ ፡ ከግ
ብፅ ፡ ምድር ፡ ከወጣህ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡
ድረስ ፡ ይቅር ፡ እንዳልሃቸው ÷ እባክህ ÷ እንደ ፡
ምሕረትህ ፡ ብዛት ፡ የዚህን ፡ ሕዝብ ፡ ኃጢአት ፡
ይቅር ፡ በል ።

፳ ፡ እግዚአብሔርም ፡ አለ ፡— እንደ ፡ ቃልህ ፡
፳፡ ይቅር ፡ አልሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡
በእውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምድርን ፡
፳፪ ፡ ሁሉ ፡ ይሞላል ። በግብፅ ፡ ምድርና ፡ በምድረ ፡
በዳ ፡ ያደረግሁትን ፡ ተአምራቴንና ፡ ክብሬን ፡
ያዩ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ አሥር ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡
፳፫ ፡ ተፈታተኑኝ ÷ ነገሬንም ፡ ስላልሰሙ ÷ በእው
ነት ፡ ለአባቶቻቸው ፡ የማልሁላቸውን ፡ ምድር ፡
አያዩም ፡ ከእነርሱም ፡ የናቀኝ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡
፳፬ ፡ አያያትም ፡ ፤ ባሪያዬ ፡ ካሌብ ፡ ግን ፡ ሌላ ፡ መን
ፈስ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ፈጽሞም ፡ ስለ ፡
ተከተለኝ ፡ እርሱ ፡ ወደ ፡ ገባበት ፡ ምድር ፡ አገ
፳፭ ፡ ባዋለሁ ፡ ዘሩም ፡ ይወርሳታል ። አማሌቅና ፡
ከነዓናዊውም ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጦ
አል ፡ በነጋው ፡ ተመልሳችሁ ፡ በኤርትራ ፡
ባሕር ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሂዱ ።
፳፮ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እን
፳፯ ፡ ዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፡— የሚያጒረመርም
ብኝን ፡ ይህን ፡ ክፉ ፡ ሕዝብ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ እታ
ገሠዋለሁ ? በእኔ ፡ ላይ ፡ የሚያጒረመርሙትን ፡
የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ማጒረምረም ፡ ሰማሁ ።
፳፰ ፡ እንዲህ ፡ በላቸው ፡— እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡
በጆሮዬ ፡ እንደ ፡ ተናገራችሁት ፡ እንዲሁ ፡ በእ
ውነት ፡ አደርግባችኋለሁ ÷ ይላል ፡ እግዚአብ
፳፱ ፡ ሔር ፡ በድኖቻችሁ ፡ በዚህ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ የወ
ድቃሉ ፡ የተቈጠራችሁ ፡ ሁሉ ÷ እንደ ፡ ቍጥ
ራችሁ ፡ ከሀያ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡
የሆነ ፡ ሁሉ ÷ እናንተ ፡ ያጒረመረማችሁብኝ ÷
፴ ፡ ከሦፎኒ ፡ ልጅ ፡ ከኬሌብና ፡ ከነዌ ፡ ልጅ ፡ ከኢ
ያሱ ፡ በቀር ፡ በእርስዋ ፡ እስቀምጣችሁ ፡ ዘንድ ፡
እጒን ፡ ዘርግቼ ፡ ወደ ፡ ማልሁላችሁ ፡ ምድር ፡
፴፩ ፡ በእውነት ፡ እናንተ ፡ አትገቡም ። ምርኮኛ ፡
ይሆናሉ ፡ ያላችኋቸውን ፡ ልጆቻችሁን ፡ እነር
ሱን ፡ አገባቸዋለሁ ÷ እናንተም ፡ የናቃችኋትን ፡
፴፪ ፡ ምድር ፡ ያውቃሉ ። እናንተ ፡ ግን ፡ በድኖቻ
፴፫ ፡ ችሁ ፡ በዚህ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ይወድቃሉ ። ልጆ
ቻችሁም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ይቅ
በዘበዛሉ ÷ በድኖቻችሁም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡
እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ ግልሙትናችሁን ፡ ይሸከ
ማሉ ። ምድረቱን ፡ በሰለላችሁባት ፡ ቀን ፡ ፴፬ ፡
ቍጥር ÷ አርባ ፡ ቀን ÷ ስለ ፡ አንድ ፡ ቀንም ፡
አንድ ፡ ዓመት ÷ ኃጢአታችሁን ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡
ትሸከማላችሁ ÷ ቍጣዬንም ፡ ታውቃላችሁ ።
እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡— በእኔ ፡ ላይ ፡ በተሰበ ፴፭ ፡
ሰበ ፡ በዚህ ፡ ክፉ ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ እን
ዲህ ፡ አደርጋለሁ ፡ ብዬ ፡ ተናገርሁ ፤ በዚህ ፡
ምድረ ፡ በዳ ፡ ያልቃሉ ÷ በዚያም ፡ ይሞታሉ ።
ምድረቱንም ፡ ሊሰልሉ ፡ ሙሴ ፡ ልኳቸው ፡ ፴፮ ፡
የተመለሱት ፡ ሰዎች ፡ ክፉ ፡ ወሬም ፡ ስለ ፡ ምድ
ሪቱ ፡ እያወሩ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ማኅበሩ ፡ ሁሉ ፡
እንዲያጒረመርሙ ፡ ያደረጉ ፡ ክፉ ፡ ወሬ ፡ የወሩ ፡ ፴፯ ፡
እነዚያ ፡ ሰዎች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በመ
ቅሠፍት ፡ ሞቱ ። ነገር ፡ ግን ፡ ምድሪቱን ፡ ሊሰ ፴፰ ፡
ልሉ ፡ ከሄዱ ፡ ሰዎች ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱና ፡
የዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ካሌብ ፡ በሕይወት ፡ ተቀመጡ ።
ሙሴም ፡ ይህን ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ፴፱ ፡
ነገረ ፡ ሕዝቡም ፡ እጅግ ፡ አዘኑ ። በነጋውም ፡ ፴ ፡
ማልደው ፡ ተነሡ ÷ ወደ ፡ ተራራውም ፡ ራስ ፡
ወጥተው ፡— እነሆ ÷ መጣን ፤ እኛ ፡ በድለናልና ፡
እግዚአብሔር ፡ ወዳለው ፡ ስፍራ ፡ እንወጣለን ፡
አሉ ። ሙሴም ፡ አለ ፡— የእግዚአብሔርን ፡ ፴፩ ፡
ትእዛዝ ፡ ለምን ፡ ትተላለፋላችሁ ? አይጠቅማ
ችሁም ። እግዚአብሔር ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ፴፪ ፡
አይደለምና ፡ በጠላቶቻችሁ ፡ ፊት ፡ እንዳትወ
ድቁ ፡ እትውጡ ። አማሌቃዊና ፡ ከነዓናዊ ፡ በፊ ፴፫ ፡
ታችሁ ፡ ናቸውና ፡ በሰይፍ ፡ ትወድቃላችሁ ፡
እግዚአብሔርን ፡ ከመከተል ፡ ተመልሳችኋልና ፡
እግዚአብሔር ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ አይሆንም ። ፴፬ ፡
እነርሱ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ራስ ፡ ሊወጡ ፡
ደፈሩ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ ታቦትና ፡ ሙሴ ፡ ከሰፈሩ ፡ አልተነሡም ። ፴፭ ፡
በዚያም ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ የተቀመጡ ፡ አማሌቃ
ዊና ፡ ከነዓናዊ ፡ ወረዱ ÷ መትተዋቸውም ፡
እስከ ፡ ሐርማ ፡ ድረስ ፡ አሳደዱአቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፭ ።

እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ፩ ፡
ተናገረው ፡— ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ፪ ፡
ብለህ ፡ ንገራቸው ፡— ወደምሰጣችሁ ፡ ወደ ፡
መኖሪያችሁ ፡ ምድር ፡ በገባችሁ ፡ ጊዜ ÷ ስለ ፡ ፫ ፡
ታችሁን ፡ ልትፈጽሙ ፡ ወይም ፡ በፈቃዳችሁ ÷
ወይም ፡ በበዓላችሁ ÷ ለእግዚአብሔር ፡ ማኅሌ ፡
ሽታ ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ከበሬ ፡ ወይም ፡ ከበግ ፡
መንጋ ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ወይም ፡
መሥዋዕት ፡ የሚሆን ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ ብታቀርቡ ÷ ቍርባኑን ፡ ለእግዚ ፩ ፡ ፡
አብሔር ፡ የሚያቀርብ ፡ ከሚቃጠል ፡ መሥዋ
ዕት ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ መሥዋዕት ፡ ጋር ፡ ለአያ
ንዳንዱ ፡ ጠቦት ፡ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ አራተኛ ፡
እጅ ፡ በሆነ ፡ ዘይት ፡ የተለወሰ ፡ ከመስፈሪያው ፡

121 ኦሪት ፡ ዘጉልቊ ። ፲፭ ፡ ፡ ፡

በዘርፋም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሰማያዊ ፡ ፈትል ፡ ያደ
ርጉ ፡ ዘንድ ፡ እዘዛቸው ። የእግዚአብሔርንም ፡
ትእዛዝ ፡ ሁሉ ፡ ታስቡና ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ÷
እርስዋን ፡ በመከተል ፡ ያመነዝራችሁበትን ፡ የል
ባችሁንና ፡ የዓይኖቻችሁን ፡ ፈቃድ ፡ እንዳት
ከተሉ ÷ ትእዛዜን ፡ ሁሉ ፡ ታስቡና ፡ ታደርጉ ፡
ዘንድ ÷ ለአምላካችሁም ፡ ቅዱሳን ፡ ትሆኑ ፡
ዘንድ ፡ ዘርፉ ፡ በልብሳችሁ ፡ ላይ ፡ እንዲታይ ፡
ይሁን ። እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችሁ ፡
ነኝ ፡ አምላክ ፡ እሆናችሁ ፡ ዘንድ ፡ ከግብፅ ፡
ምድር ፡ ያወጣኋችሁ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡
አምላካችሁ ፡ ነኝ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

፩ የሌዊም ፡ ልጅ ፡ የቀዓት ፡ ልጅ ፡ የይስዓር ፡ ልጅ ፡
ቆሬ ፡ ከሮቤልም ፡ ልጆች ፡ የኤልያብ ፡ ልጆች ፡
ዳታንና ፡ አቤሮን ፡ የፋሌትም ፡ ልጅ ፡ አን ፡
፪ በሙሴ ፡ ላይ ፡ ተነሡ ። ከእስራኤልም ፡ ሌጆች ፡
ሁለት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ሰዎች ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡
ወሰዱ ፡ ከጉባኤው ፡ የተመረጡ ፡ ዝናቸውም ፡
፫ የተሰማ ፡ የማኅበሩ ፡ አለቆች ፡ ነበሩ ። በሙ
ሴና ፡ በአሮን ፡ ላይ ፡ ተሰብስበው ፦ ማኅበሩ ፡
ሁሉ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ቅዱሳን ፡ ናቸውና ÷
እግዚአብሔርም ፡ በመካከላቸው ፡ ነውና ፡ እና
ንተ ፡ እጅግ ፡ አብዝታችኋል ፤ በእግዚአብሔ
ርም ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ ትታበያላችሁ ?
አሉ ።
፬ ሙሴም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በግምባሩ ፡ ወደቀ ፤
፭ ለቆሬም ፡ ለወገኑም ፡ ሁሉ ፦ ነገ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ለእርሱ ፡ የሚሆነውን ÷ ቅዱስም ፡
የሚሆነውን ፡ ያስታውቃል ፤ የመረጠውንም ፡
፮ ሰው ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ያቀርበዋል ። እንዲሁ ፡
አድርጉ ፤ ቆሬና ፡ ወገንህ ፡ ሁሉ ÷ ጥናዎቹን ፡
፯ ውሰዱ ፤ ነገም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እሳት ፡
አድርጉባቸው ÷ ዕጣንም ፡ ጨምሩባቸው ፤ እን
ዲህም ፡ ይሆናል ፤ እግዚአብሔር ፡ የሚመር
ጠው ፡ እርሱ ፡ ቅዱስ ፡ ይሆናል ፤ እናንተ ፡
የሌዊ ፡ ልጆች ፡ ሆይ ÷ እጅግ ፡ አብዝታችኋል ፡
፰ ብሎ ፡ ተናገራቸው ። ሙሴም ፡ ቆሬን ፡ አለው ፦
፱ እናንተ ፡ የሌዊ ፡ ልጆች ÷ ስሙ ፤ የእስራኤል ፡
አምላክ ፡ ከእስራኤል ፡ ማኅበር ፡ የለያችሁ ÷
የእግዚአብሔርንም ፡ ማደሪያ ፡ አገልግሎት ፡
ትሠሩ ፡ ዘንድ ÷ እንድታገለግሉአቸውም ፡ በማ
ኅበሩ ፡ ፊት ፡ ትቆሙ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡
፲ ያቀረባችሁ ፡ አይበቃችሁምን ? አንተን ፡ ከአ
ንተም ፡ ጋር ፡ የሌዊን ፡ ልጆች ፡ ወንድሞች
ህን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አቅርበአል ፤ ክህነት
፲፩ ንም ፡ ደግሞ ፡ ትፈልጋላችሁን ? ስለዚህም ፡
አንተና ፡ ወገንህ ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡
ተሰብስባችኋል ፤ በእርሱም ፡ ላይ ፡ ታጕረመ
ርሙ ፡ ዘንድ ፡ አሮን ፡ ማን ፡ ነው ?
፲፪ ሙሴም ፡ የኤልያብን ፡ ልጆች ፡ ዳታንና ፡ አቤ
ሮንን ፡ እንዲጠሩአቸው ፡ ላከ ፤ እነርሱም ፦
፲፫ አንመጣም ፤ በምድረ ፡ በዳ ፡ ትገድለን ፡ ዘንድ ፡
ወተትና ፡ ማር ፡ ከምታፈስሰው ፡ ምድር ፡ ያወ
ጣኸን ፡ አይበቃህምን ? ደግመህ ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡
ራስህን ፡ አለቃ ፡ ታደርጋለህን ? ደግሞ ፡ ወተ
፲፬ ትና ፡ ማር ፡ ወደምታፈስስ ፡ ምድር ፡ አላገባ
ኸንም ÷ እርሻና ፡ ወይንም ፡ አላወረስኸንም ፤
የእነዚህንስ ፡ ሰዎች ፡ ዓይኖቻቸውን ፡ ታወጣለ
ህን ? አንመጣም ፡ አሉ ።
፲፭ ሙሴም ፡ እጅግ ፡ ተቈጣ ÷ እግዚአብሔር
ንም ፦ ወደ ፡ ቍርባናቸው ፡ አትመልከት ፤
እኔ ፡ ከእነርሱ ፡ አንድ ፡ አህያ ፡ ስንኳ ፡ አልወሰ
ድሁም ÷ ከእነርሱም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አልበደል
ሁም ፡ አለው ። ሙሴም ፡ ቆሬን ፦ ነገ ፡ አንተ ÷
፲፮ ወገንህም ፡ ሁሉ ÷ አሮንም ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ሁኑ ፡ ሁላችሁም ፡ ጥናዎቻችሁን ፡
፲፯ ውሰዱ ÷ ዕጣንም ፡ አድርጉባቸው ÷ እያንዳንዳ
ችሁም ፡ ጥናዎቻችሁን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ አምጡ ÷ ሁለት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ጥናዎች ፤
አንተ ፡ ደግሞ ፡ አሮንም ፡ ጥናዎቻችሁን ፡
አምጡ ፡ አለው ። እያንዳንዱም ፡ ጥናውን ፡
፲፰ ወሰደ ÷ እሳትም ፡ አደረገበት ÷ ዕጣንም ፡ ጨመ
ረበት ÷ ከመሴና ፡ ከአሮንም ፡ ጋር ፡ በመገና
ኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ቆመ ። ቆሬም ፡ ማኅበ
፲፱ ሩን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡
በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ሰበሰበ ፤ የእግዚአሔሩም ፡
ክብር ፡ ለማኅበሩ ፡ ሁሉ ፡ ተገለጠ ።
እግዚአሔሩም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እን
፳ ዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦ ሁሉን ፡ በቅጽበት ፡
፳፩ አጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ ከዚህ ፡ ማኅበር ፡ መካከል ፡
ፈቀቅ ፡ በሉ ። እነርሱም ፡ በግምባራቸው ፡ ወድ
፳፪ ቀው ፦ አምላክ ፡ ሆይ ÷ አንተ ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡
ነፍስ ፡ አምላክ ÷ አንድ ፡ ሰው ፡ ኃጢአት ፡
ቢሠራ ፡ አንተ ፡ በማኅበሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ትቈ
ጣለህን ? አሉ ። እግዚአሔሩም ፡ ሙሴን ፡
፳፫ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦ ለማኅበሩ ፦
፳፬ ከቆሬና ፡ ከዳታን ፡ ከአቤሮንም ፡ ማደሪያ ፡ ዙሪያ ፡
ፈቀቅ ፡ በሉ ፡ ብለህ ፡ ንገራቸው ።
ሙሴም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ዳታንና ፡ ወደ ፡
፳፭ አቤሮን ፡ ሄደ ፤ የእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡
ተከተሉት ። ማኅበሩንም ፦ እባካችሁ ÷ ከእነ
፳፮ ዚህ ፡ ክፉዎች ፡ ድንኳን ፡ ፈቀቅ ፡ በሉ ፤ በኃጢ
አታቸውም ፡ ሁሉ ፡ እንዳትጠፋ ፡ ለእነርሱ ፡
የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ አትንኩ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ።
ከቆሬና ፡ ከዳታን ፡ ከአቤሮንም ፡ ማደሪያ ፡ ከዙ
፳፯ ሪያውም ፡ ሁሉ ፡ ፈቀቅ ፡ አሉ ፤ ዳታንና ፡ አቤ
ሮንም ፡ ሴቶቻቸውም ፡ ልጆቻቸውም ፡ ሕፃናቶ
ቻቸውም ፡ ወጥተው ፡ በድንኳኖቻቸው ፡ ደጃፍ ፡
ቆሙ ። ሙሴም ፡ አለ ፦ ይህን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡
፳፰ አደርግ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአሔሩ ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡
እንጂ ፡ ከልቤ ፡ እንዳይደለ ፡ በዚህ ፡ ታውቃላ
ችሁ ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እንደሚሞቱ ፡
፳፱ ቢሞቱ ÷ ወይም ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ቢቀሠፉ ፡
እግዚአሔሩ ፡ አልላከኝም ። እግዚአሔሩ ፡
፴ ግን ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ቢፈጥር ÷ ምድርም ፡ አፍዋን ፡
ከፍታ ፡ እነርሱን ፡ ለእነርሱም ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡

ብትውጣቸው ÷ በሕይወታቸውም ፡ ወደ ፡
ሲኦል ፡ ቢወርዱ ÷ ያን ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡
እግዚአሔሩን ፡ እንደ ፡ ናቁ ፡ ታውቃላችሁ ።
እንዲህም ፡ ሆነ ፤ ይህን ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ መናገር ፡
ባፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ከበታቻቸው ፡ ያለው ፡ መሬት ፡
ተሰነጠቀ ፤ ምድሪቱም ፡ አፍዋን ፡ ከፍታ ፡ እን
ርሱን ፡ ቤተ ፡ ሰበቻቸውንም ÷ ለቆሬም ፡ የን
በሩትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ÷ ዕቃዎቻቸውንም ፡
ሁሉ ፡ ዋጠቻቸው ። እነርሱም ፡ ለእነርሱም ፡
የነበሩ ፡ ሁሉ ፡ በሕይወታቸው ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡
ወረዱ ፤ ምድሪቱም ፡ ተዘጋችባቸው ÷ ከጉባኤ
ውም ፡ መካከል ፡ ጠፉ ። በዙሪያቸው ፡ የነበሩ ፡
የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ከጩኸታቸው ፡
የተነሣ ፦ ምድሪቱ ፡ እንዳትውጠን ፡ ብለው ፡
በረሩ ። እሳትም ፡ ከእግዚአሔሩ ፡ ዘንድ ፡
ወጥታ ፡ ያዋኑ ፡ የነበሩትን ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡
አምሳ ፡ ሰዎች ፡ በላች ።
እግዚአሔሩም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
ተናገረው ፦ ለአሮን ፡ ልጅ ፡ ለአልዓዛር ፡
እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ንገረው ፦ ተቀድሰዋልና ፡ ጥና
ዎቹን ፡ ከተቃጠሉት ፡ ዘንድ ፡ ውሰድ ÷ እሳቱ
ንም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ጣለው ፤ በኃጢአታቸው ፡
ሰውነታቸውን ፡ ያጠፋትን ፡ የእነዚያን ፡ ሰዎች ፡
ጥናዎች ፡ ጠፍጥፈህ ፡ ለመሠዊያ ፡ መለበጫ ፡
አድርጋቸው ፤ በእግዚአሔሩ ፡ ፊት ፡ አቅርበ
ዋቸዋልና ፡ የተቀደሱ ፡ ናቸው ÷ ለእስራኤልም ፡
ልጆች ፡ ምልክት ፡ ይሆናሉ ። ካህኑም ፡ አልዓ
ዛር ፡ የተቃጠሉት ፡ ሰዎች ፡ ያቀረቡአቸውን ፡
የናስ ፡ ጥናዎች ፡ ወስዶ ፡ ጠፍጥፎም ፡ ለመሠዊ
ያው ፡ መለበጫ ፡ አደረጋቸው ። በቆሬና ፡ በወ
ገኑ ፡ የደረሰው ፡ እንዳይደርስበት ÷ ከአሮን ፡
ልጆች ፡ ያልሆነ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በእግዚአሔሩ ፡
ፊት ፡ ዕጣን ፡ ያጥን ፡ ዘንድ ፡ እንዳይቀርብ ÷ እግ
ዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ÷ ለእስ
ራኤል ፡ ልጆች ፡ መታሰቢያ ፡ አደረጋቸው ።
በነጋውም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡
ሁሉ ፦ እናንተ ፡ የእግዚአሔሩን ፡ ሕዝብ ፡
ገድላችኋል ፡ ብለው ፡ በሙሴና ፡ በአሮን ፡ ላይ ፡
እጕረመረሙ ። እንዲህም ፡ ሆነ ፤ ማኅበሩ ፡
በሙሴና ፡ በአሮን ፡ ላይ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡
ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድንኳን ፡ አዩ ፤ እነሆም ÷
ደመናው ፡ ሸፈነው ÷ የእግዚአሔሩም ፡ ክብር ፡
ተገለጠ ። ሙሴና ፡ አሮንም ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡
ድንኳን ፡ ፊት ፡ መጡ ። እግዚአሔሩ ፡ ሙሴን ፡
እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦ ከዚህ ፡ ማኅበር ፡
መካከል ፡ ፈቀቅ ፡ በሉ ÷ እኔም ፡ በቅጽበት ፡
አጠፋቸዋለሁ ። በግምባራቸውም ፡ ወደቁ ።
ሙሴም ፡ አሮንን ፦ ጥናህን ፡ ውሰድ ÷ ከመሠ
ዊያውም ፡ ላይ ፡ እሳት ፡ አድርግበት ÷ ዕጣንም ፡
ጨምርበት ÷ ወደ ፡ ማኅበሩም ፡ ፈጥነህ ፡ ውሰ
ደው ፡ አስተስርይላቸው ፤ ከእግዚአሔሩ ፡
ፊት ፡ ቍጣ ፡ ወጥቶአልና ፡ መቅሠፍት ፡ ጀምሮ ፡
አል ፡ አለው ። አሮንም ፡ ሙሴ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡
ጥናውን ፡ ወስዶ ፡ ወደ ፡ ጉባኤው ፡ መካከል ፡
ሮጠ ፤ እነሆም ÷ መቅሠፍቱ ፡ በሕዝቡ ፡ መካ
ከል ፡ ጀምሮ ፡ ነበር ፤ ዕጣንም ፡ ጨመረ ÷ ለሕ
ዝቡም ፡ አስተሰረየላቸው ። በሙታንና ፡ በሕ
ያዋን ፡ መካከል ፡ ቆመ ፤ መቅሠፍቱም ፡ ተከለ
ከለ ። በቆሬም ፡ ምክንያት ፡ ከሞቱት ፡ ሌላ ፡
በመቅሠፍቱ ፡ የሞቱት ፡ አሥራ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡
ሰባት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ። አሮንም ፡ ወደ ፡ ሙሴ ፡
ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ተመለሰ ፤
መቅሠፍቱም ፡ ተከለከለ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

እግዚአሔሩም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
ተናገረው ፦ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ንገራቸው ÷
ከእነርሱም ፡ ከእያንዳንዱ ፡ ከየአባቶቻቸው ፡
ቤት ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ በትር ÷ ከአለቆቻቸው ፡
ከየአባቶቻቸው ፡ ቤት ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ በት
ሮች ÷ ውሰድ ፤ የእያንዳንዱንም ፡ ስም ፡ በየበ
ትሩ ፡ ላይ ፡ ጻፍ ። አንድ ፡ በትርም ፡ ለአባቶቻ
ቸው ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ ይሆናልና ፡ በሌዊ ፡ በትር ፡
ላይ ፡ የአሮንን ፡ ስም ፡ ጻፍ ። እኔ ፡ ከእናንተ ፡
ጋር ፡ በምገናኝበት ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡
ውስጥ ፡ በምስክሩ ፡ ፊት ፡ አኑራቸው ። እንዲ
ህም ፡ ይሆናል ፤ የመረጥሁት ፡ ሰው ፡ በትር ፡
ታቈጠቍጣለች ፤ በእናንተም ፡ ላይ ፡ የሚያጕር
መርሙ ፡ ብቻ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ አጠፋለሁ ። ሙሴም ፡
ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተናገራቸው ፤ አለቆቻ
ቸው ፡ ሁሉ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ በትሮች ÷ እያ
ንዳንዱም ፡ አለቃ ፡ በየአባቱ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡
አንድ ፡ በትር ÷ ሰጡት ፤ የአሮንም ፡ በትር ፡
በበትሮቻቸው ፡ መካከል ፡ ነበረች ። ሙሴም ፡
በትሮቹን ፡ በእግዚአሔሩ ፡ ፊት ፡ በምስክሩ ፡
ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ አኖራቸው ።
እንዲህም ፡ ሆነ ፤ በነጋው ፡ ሙሴ ፡ ወደ ፡ ምስ
ክሩ ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ገባ ፤ እነሆም ÷ ለሌዊ ፡
ቤት ፡ የሆነች ፡ የአሮን ፡ በትር ፡ አቈጠቈጠች ÷
ለመለመችም ÷ አበባም ፡ አወጣች ÷ የበሰለ ፡
ለውዝም ፡ አፈራች ። ሙሴም ፡ በትሮችን ፡
ሁሉ ፡ ከእግዚአሔሩ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡
ልጆች ፡ ሁሉ ፡ አወጣቸው ፤ እነርሱም ፡ አዩ ÷ እያ
ንዳንዱም ፡ በትሩን ፡ ወሰደ ። እግዚአሔሩም ፡
ሙሴን ፦ የአሮንን ፡ በትር ፡ ወደ ፡ ምስክሩ ፡
ፊት ፡ መልስ ፤ ማጕረምረማቸው ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡
እንዲጠፋ ፡ እነርሱም ፡ እንዳይሞቱ ፡ ለሚያምፁ
ብኝ ፡ ልጆች ፡ ምልክት ፡ ሆኖ ፡ ትጠበቅ ፡ አለው ።
ሙሴም ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ፤ እግዚአሔሩ ፡
፲፩ እንዳዘዘው ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።
የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ሙሴን ፡ ፦ እነሆ ÷
፲፪ እንሞታለን ÷ እንጠፋለን ÷ ሁላችንም ፡ እንጠ
ፋለን ። የሚቀርብ ፡ ሁሉ ÷ ወደ ፡ እግዚአብ
፲፫ ሔር ፡ ማደሪያ ፡ የሚቀርብ ÷ ይሞታል ፤ በውኑ ፡
ሁላችን ፡ እንሞታለንን ? ብለው ፡ ተናገሩት ።

ምዕራፍ ፡ ፲፰ ።

፩ እግዚአብሔርም ፡ አሮንን ፡ አለው ፡ — አንተ ፡ ከአንተም ፡ ጋር ፡ ልጆችህና ፡ የአባቶችህ ፡ ቤት ፡ የመቅደስን ፡ ኃጢአት ፡ ትሸከማላችሁ ፥ አንተም ፡ ከአንተም ፡ ጋር ፡ ልጆችህ ፡ የክህነታችሁን ፡ ኃጢአት ፡ ትሸከማላችሁ ። ፪ ደግሞም ፡ የአባትህን ፡ የሌዊን ፡ ነገድ ፡ ወንድሞችህን ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ አቅርብ ፤ ከአንተም ፡ ጋር ፡ በአንድነት ፡ ይሁኑ ፥ ያገልግሉህም ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ከአንተም ፡ ጋር ፡ ልጆችህ ፡ በምስክሩ ፡ ድንኳን ፡ ፊት ፡ ትሆናላችሁ ። ፫ እነርሱም ፡ ትእዛዝህን ፡ የድንኳኑንም ፡ ሁሉ ፡ አገልግሎት ፡ ይጠብቁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንዳይሞቱ ፡ እናንተም ፡ ደግሞ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ እንዳትሞቱ ፡ እነርሱ ፡ ወደ ፡ መቅደሱ ፡ ዕቃና ፡ ወደ ፡ መሠዊያው ፡ አይቅረቡ ። ፬ ነገር ፡ ግን ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ በአንድነት ፡ ይሁኑ ፥ ለድንኳኑም ፡ አገልግሎት ፡ ሁሉ ፡ የመገናኛውን ፡ ድንኳን ፡ ይጠብቁ ፤ ሌላም ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ አይቅረብ ። ፭ እንደ ፡ ገና ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ቍጣ ፡ እንዳይሆንባቸው ፡ እናንተ ፡ መቅደሱንና ፡ መሠዊያውን ፡ ጠብቁ ። ፮ እኔም ፥ እነሆ ፥ ሌዋውያንን ፡ ወንድሞቻችሁን ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ወስጄአለሁ ፤ የመገናኛውን ፡ ድንኳን ፡ አገልግሎት ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተሰጡ ፡ ለእናንተ ፡ ስጦታ ፡ ናቸው ። ፯ አንተም ፡ ከአንተም ፡ ጋር ፡ ልጆችህ ፡ ለመሠዊያው ፡ ሥራ ፡ የሚሆነውን ፡ ሁሉ ፥ በመጋረጃውም ፡ ውስጥ ፡ የሚሆነውን ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ክህነታችሁን ፡ ጠብቁ ፥ አገልግሎም ፡ ክህነቱን ፡ ለስጦታ ፡ አገልግሎት ፡ ሰጥቼአችኋለሁ ፤ ሌላም ፡ ሰው ፡ ቢቀርብ ፡ ይገደል ።

፰ እግዚአብሔርም ፡ አሮንን ፡ ተናገረው ፡ እንዲህም ፡ አለው ፡ — እነሆ ፥ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለእኔ ፡ የቀደሱትን ፡ የማንሣት ፡ ቍርባኔን ፡ ሁሉ ፡ ለአንተ ፡ ሰጥቼሃለሁ ፤ ስለ ፡ መቀባትህ ፡ ለአንተና ፡ ለልጆችህ ፡ ድርሻ ፡ እንዲሆን ፡ ለዘላለም ፡ ሰጥቼሃለሁ ። ፱ በእሳት ፡ ከሚቀርበው ፡ ከተቀደሰው ፡ ይህ ፡ ለአንተ ፡ ይሆናል ፤ ለእኔ ፡ የሚያመጡት ፡ መበቸው ፡ ሁሉ ፥ የእህሉ ፡ ቍርባናቸው ፡ ሁሉ ፥ የኃጢአታቸውም ፡ መሥዋዕት ፡ ሁሉ ፥ የበደላቸውም ፡ መሥዋዕት ፡ ሁሉ ፥ ለአንተ ፡ ለልጆችህም ፡ የተቀደሰ ፡ ይሆናል ። ፱ በተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡ ብላው ፤ ወንዶች ፡ ሁሉ ፡ ይብሉት ፤ የተቀደሰ ፡ ይሆንልሃል ። ፱ ይህም ፡ ለአንተ ፡ ነው ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለስጦታ ፡ ያቀረቡትን ፡ የማንሣትና ፡ የመወዝወዝ ፡ ቍርባን ፡ ሁሉ ፡ ለአንተ ፡ ከአንተም ፡ ጋር ፡ ለወንዶችና ፡ ለሴቶች ፡ ልጆችህ ፡ ድርሻ ፡ እንዲሆን ፡ ለዘላለም ፡ ሰጥቼሃለሁ ፤ በቤትህ ፡ ውስጥ ፡ ንጹሕ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ይብላው ። ፱ ለእግዚአብሔር ፡ ካሚ ፡ ሰጡት ፡ የፍሬ ፡ መጀመሪያ ፡ ከዘይትና ፡ ከወይን ፡ ከእህልም ፡ የተመረጠውን ፡ ሁሉ ፡ ለአንተ ፡ ሰጥቼሃለሁ ። ፱ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያመጡት ፡ በምድራቸው ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ የፍሬ ፡ መጀመሪያ ፡ ለአንተ ፡ ይሆናል ፤ በቤትህ ፡ ውስጥ ፡ ንጹሕ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ይብላው ። ፱ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ እርም ፡ የሆነው ፡ ሁሉ ፡ ለአንተ ፡ ይሆናል ። ፱ ከሰው ፡ ወይም ፡ ከእንስሳ ፡ ቢሆን ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ከሚያቀርቡት ፡ ሥጋ ፡ ሁሉ ፡ ማኅፀን ፡ የሚከፍት ፡ ሁሉ ፡ ለአንተ ፡ ይሆናል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የሰውን ፡ በኵራት ፡ ፈጽሞ ፡ ትቤዣዋለህ ፥ ያልነጻውንም ፡ እንስሳ ፡ በኵራት ፡ ትቤዣዋለህ ። ፱ ከአንድ ፡ ወር ፡ ጀምሮ ፡ የምትቤዣውን ፡ እንደ ፡ ግምትህ ፡ ትቤዣዋለህ ፤ ግምቱም ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ አምስት ፡ ሰቅል ፡ ይሆናል ። ፱ እርሱም ፡ ሀያ ፡ አበቢ ፡ ነው ። ፱ ነገር ፡ ግን ፡ የላም ፡ በኵራት ፡ ወይም ፡ የበግ ፡ በኵራት ፡ ወይም ፡ የፍየል ፡ በኵራት ፡ አትቤዣም ፤ የተቀደሱ ፡ ናቸው ፤ ደማቸውን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ትረጨዋለህ ፥ ስባቸውንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲሆን ፡ ለአሳት ፡ ቍርባን ፡ ታቃጥለዋለህ ። ፱ ሥጋቸውም ፡ ለአንተ ፡ ይሆናል ፤ እንደ ፡ መወዝወዝ ፡ ፍርምባ ፡ እንደ ፡ ቀኙም ፡ ወርች ፡ ለአንተ ፡ ይሆናል ። ፱ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከተቀደሰው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አንሥተው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያቀረቡትን ፡ ለአንተ ፡ ከአንተም ፡ ጋር ፡ ለወንዶችና ፡ ለሴቶች ፡ ልጆችህ ፡ ድርሻ ፡ እንዲሆን ፡ ለዘላለም ፡ ሰጥቼሃለሁ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለአንተ ፡ ከአንተም ፡ ጋር ፡ ለዘርህ ፡ የጨው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለዘላለም ፡ ነው ።

፱ እግዚአብሔርም ፡ አሮንን ፡ አለው ፡ — በምድራቸው ፡ ርስት ፡ በመካከላቸውም ፡ ድርሻ ፡ አይሆንልህም ፤ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ድርሻህና ፡ ርስትህ ፡ እኔ ፡ ነኝ ። ፱ ለሌዋም ፡ ልጆች ፥ እነሆ ፥ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ አገልግሎት ፡ ስለሚያገለግሉ ፥ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ አሥራት ፡ ርስት ፡ አድርጌ ፡ ሰጥቼአለሁ ። ፱ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኃጢአትን ፡ እንዳይሸከሙ ፡ እንዳይሞቱም ፥ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድንኳን ፡ አይቅረቡ ። ፱ ሌዋውያን ፡ ግን ፡ የመገናኛውን ፡ ድንኳን ፡ አገልግሎት ፡ ይሥሩ ፥ እነርሱም ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ይሸከማሉ ፤ ለልጅ ፡ ልጃችሁ ፡ ለዘላለም ፡ ሥርዓት ፡ ይሆናል ፤ በእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ርስት ፡ አይወርሱም ። ፱ ለእግዚአብሔር ፡ የማንሣት ፡ ቍርባን ፡ የሚያቀርቡትን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ አሥራት ፡ ለሌዋውያን ፡ ርስት ፡ አድርጌ ፡ ሰጥቼአለሁ ፤ ስለዚህ ፡ — በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ርስት ፡ አይወርሱም ፡ አልኋቸው ።

፱ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፡ — ለሌዋውያን ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ንገራቸው ፡ — ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለእናንተ ፡ ርስት ፡ አድርጌ ፡ የሰጠኋችሁን ፡ አሥራት ፡ በተቀበላችሁ ፡ ጊዜ ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ለማንሣት ፡

ቍርባን ፡ የአሥራት ፡ አሥራት ፡ ታቀርባላችሁ ። የማንሣት ፡ ቍርባናችሁም ፡ እንደ ፡ አውድማው ፡ እህልና ፡ እንደ ፡ ወይን ፡ መጭመቂያው ፡ ፍሬ ፡ ይቈጠርላችኋል ። ፱ እንዲሁ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከምትቀበሉት ፡ አሥራት ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የማንሣት ፡ ቍርባን ፡ ታቀርባላችሁ ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ የማንሣት ፡ ቍርባን ፡ ለካህኑ ፡ ለአሮን ፡ ትሰጣላችሁ ። ፱ ከምትቀበሉት ፡ ስጦታ ፡ ሁሉ ፥ ከተመረጠው ፡ ከተቀደሰውም ፡ ድርሻ ፡ ሁሉ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ የማንሣት ፡ ቍርባን ፡ ሁሉ ፡ ታቀርባላችሁ ። ስለዚህ ፡ ትላቸዋለህ ፡ — ከእርሱ ፡ የተመረጠውን ፡ ባነሣችሁ ፡ ጊዜ ፥ እንደ ፡ አውድማው ፡ እህልና ፡ እንደ ፡ ወይን ፡ መጭመቂያው ፡ ፍሬ ፡ ለሌዋውያን ፡ ይቈጠራል ። ፱ እናንተም ፡ ቤተ ፡ ሰበቻችሁም ፥ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ የማገልገላችሁ ፡ ዋጋ ፡ ነውና ፤ በሁሉ ፡ ስፍራ ፡ ትበሉታላችሁ ። ፱ የተመረጠውንም ፡ ከእርሱ ፡ ባነሣችሁ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ኃጢአትን ፡ አትሸከሙም ፤ እንዳትሞቱም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የቀደሱትን ፡ አታረከሱም ።

ምዕራፍ ፡ ፲፱ ።

፡ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፡ — እግዚአብሔር ፡ ያዘዘው ፡ የሕጉ ፡ ትእዛዝ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ መልካሚቱን ፥ ነውርም ፡ የሌለባትን ፥ ቀንበር ፡ ያልተጫነባትን ፡ ቀይ ፡ ጊደር ፡ ያመጡልህ ፡ ዘንድ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ንገራቸው ። ፱ እርስዋንም ፡ ለካህኑ ፡ ለአልዓዛር ፡ ትሰጣላችሁ ፥ እርስዋንም ፡ ከሰፈር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይወስዳታል ፥ አንድ ፡ ሰውም ፡ በፊቱ ፡ ያርዳታል ። ፱ ካህኑም ፡ አልዓዛር ፡ ከደምዋ ፡ በጣቱ ፡ ይወስዳል ፥ ከደምዋም ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ፊት ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ይረጫል ። ፱ ጊደሪቱም ፡ በፊቱ ፡ ትቃጠላለች ፤ ቍርበትዋም ፡ ሥጋዋም ፡ ደምዋም ፡ ፈርስዋም ፡ ይቃጠላል ። ፱ ካህኑም ፡ የዝግባ ፡ እንጨት ፡ ሂሶጵም ፡ ቀይ ፡ ግምጃም ፡ ወስዶ ፡ ጊደሪቱ ፡ በምትቃጠልበት ፡ እሳት ፡ መካከል ፡ ይጥለዋል ። ፱ ካህኑም ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ፥ ገላውንም ፡ በውኃ ፡ ይታጠባል ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ይገባል ፤ ካህኑም ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ርኩስ ፡ ይሆናል ። ፱ ያቃጠላትም ፡ ሰው ፡ ልብሱን ፡ በውኃ ፡ ያጥባል ፥ ገላውንም ፡ በውኃ ፡ ይታጠባል ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ይሆናል ። ፱ ንጹሕም ፡ ሰው ፡ የጊደሪቱን ፡ አመድ ፡ ያከማቻል ፤ ከሰፈሩም ፡ ውጭ ፡ በንጹሕ ፡ ስፍራ ፡ ያኖረዋል ፤ ርኩሰትም ፡ ለማያነጻ ፡ ውኃ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ይጠበቃል ፤ ከኃጢአት ፡ ለማንጻት ፡ የሚሆን ፡ ነው ። ፱ የጊደሪቱንም ፡ አመድ ፡ ያከማቸ ፡ ሰው ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ይሆናል ፤ ይህ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በመኖከላቸው ፡ ለሚኖር ፡ መጻተኛ ፡ ለዘላለም ፡ ሥርዓት ፡ ይሆናል ።

፱ የሞተውን ፡ ሰው ፡ በድን ፡ የሚነካ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ርኩስ ፡ ይሆናል ፤ ፱ በዚህም ፡ ውኃ ፡ በሦስተኛውና ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ሁለመናውን ፡ ያጠራል ፥ ንጹሕም ፡ ይሆናል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በሦስተኛውና ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ሁለመናውን ፡ ባያጠራ ፡ ንጹሕ ፡ አይሆንም ። ፱ የሞተውን ፡ ሰው ፡ በድን ፡ የነካ ፡ ሁለመናውን ፡ ባያጠራ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ማደሪያ ፡ ያረከሰል ፤ ያ ፡ ሰው ፡ ከእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ተለይቶ ፡ ይጠፋል ፤ በእርሱም ፡ ላይ ፡ የሚያነጻ ፡ ውኃ ፡ አልተረጨምና ፤ ርኩስ ፡ ይሆናል ፤ ርኩሰቱ ፡ ገና ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ሰው ፡ በድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ቢሞት ፡ ሕጉ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ የሚገባ ፡ ሁሉ ፡ በድንኳኑም ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ርኩስ ፡ ይሆናል ። ፱ መክደኛው ፡ ያልታሰረ ፡ የተከፈተ ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ። ፱ በሜዳም ፡ በሰይፍ ፡ የተገደለውን ፡ ወይም ፡ የሞተውን ፡ በድን ፡ ወይም ፡ የሰውን ፡ አጥንት ፡ ወይም ፡ መቃብር ፡ የሚነካ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ርኩስ ፡ ይሆናል ። ፱ ከኃጢአት ፡ ለማንጻት ፡ እንድትሆን ፡ ከተቃጠለች ፡ ጊደር ፡ አመድ ፡ ለርኩሱ ፡ ይወስዱለታል ፥ በዕቃውም ፡ ውስጥ ፡ የምንጭ ፡ ውኃ ፡ ይቀላቀልበታል ። ፱ ንጹሕም ፡ ሰው ፡ ሂሶጵን ፡ ወስዶ ፡ በውኃው ፡ ውስጥ ፡ ያጠልቀዋል ፤ በድንኳኑም ፥ በዕቃውም ፡ ሁሉ ፥ በዚያም ፡ ባሉ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፥ አጥንቱንም ፡ ወይም ፡ የተገደለውን ፡ ወይም ፡ የሞተውን ፡ ወይም ፡ መቃብሩን ፡ በነካው ፡ ላይ ፡ ይረጨዋል ፤ ንጹሕም ፡ በሦስተኛውና ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ በርኩሱ ፡ ላይ ፡ ይረጨዋል ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ያጠራዋል ፤ እርሱም ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ፥ ገላውንም ፡ በውኃ ፡ ይታጠባል ፥ በማታም ፡ ጊዜ ፡ ንጹሕ ፡ ይሆናል ።

ሰውም ፡ ርኩስ ፡ ቢሆን ፡ ሁለመናውንም ፡ ባያጠራ ፥ ያ ፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መቅደስ ፡ አርክሶአልና ፤ ከጉባኤው ፡ መካከል ፡ ተለይቶ ፡ ይጠፋል ፤ በሚያነጻ ፡ ውኃ ፡ አልተረጨም ፤ ርኩስ ፡ ነው ። ፱ ይህም ፡ የዘላለም ፡ ሥርዓት ፡ ይሆንላችኋል ። ፱ የሚያነጻውን ፡ ውኃ ፡ የሚረጭ ፡ ሰው ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ፤ የሚያነጻውንም ፡ ውኃ ፡ የሚነካ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ይሆናል ። ፱ ርኩሱም ፡ የሚነካው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ርኩስ ፡ ይሆናል ፤ የሚነካውም ፡ ሰው ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ይሆናል ።

ምዕራፍ ፡ ፳ ።

፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ በመጀመሪያው ፡ ወር ፡ ወደ ፡ ጺን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ መጡ ፤ ሕዝቡም ፡ በቃዴስ ፡ ተቀመጡ ፤ ማርያምም ፡ በዚያ ፡ ሞተች ፥ በዚያም ፡ ተቀበረች ።

ለማኅበሩም ፡ ውኃ ፡ አልነበረም ፤ በሙሴና ፡ በአሮንም ፡ ላይ ፡ ተሰበሰቡ ። ፱ ሕዝቡም ፡ ሙሴን ፡

ተጣሉት ÷ እንዲህም ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ፡—
ወንድሞቻችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በሞቱ ፡
፪ ጊዜ ፡ እኛም ፡ ምነው ፡ በሞትን ፡ ኖር ! እኛ ፡
ከብቶቻችንም ፡ በዚያ ፡ እንሞት ፡ ዘንድ ፡ የአ
ግዚአብሔርን ፡ ጉባኤ ፡ ወደዚህ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡
፫ ለምን ፡ አመጣችሁ ? ወደዚህ ፡ ክፉ ፡ ስፍራ ፡
ታመጡን ፡ ዘንድ ፡ ከግብፅ ፡ ለምን ፡ አወጣች
ሁን ? ዘርና ፡ በለስ ፡ ወይንም ፡ ሮማንም ፡ የሌ
ለበት ፡ ስፍራ ፡ ነው ፤ የሚጠጣም ፡ ውኃ ፡ የለ
፮ በትም ። ሙሴና ፡ አርጎንም ፡ ከጉባኤው ፡ ፊት ፡
ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ሄደው ፡
በግምባራቸው ፡ ወደቁ ፤ የእግዚአብሔርም ፡
፯ ክብር ፡ ተገለጠላቸው ። እግዚአብሔርም ፡
፰ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፡— በትር
ህን ፡ ውሰድ ፤ አንተና ፡ ወንድምህ ፡ አሮን ፡
ማኅበሩን ፡ ሰብስቡ ÷ ድንጋዩም ፡ ውኃን ፡ እን
ዲሰጥ ፡ እነርሱ ፡ ሲያዩ ፡ ተናገሩት ፤ ከድንጋ
ዩም ፡ ውኃ ፡ ታወጣላቸዋለህ ፤ እንዲሁም ፡
ማኅበሩን ፡ ከብቶቻቸውንም ፡ ታጠጣላቸዋለህ ።
፱ ሙሴም ፡ እንደ ፡ ታዘዘ ፡ በትሩን ፡ ከእግዚአብ
ሔር ፡ ፊት ፡ ወሰደ ።
፲ ሙሴና ፡ አሮንም ፡ ጉባኤውን ፡ በድንጋዩ ፡
ፊት ፡ ሰብስበው ፡— እናንተ ፡ ዓመፀኞች ÷ እን
ግዲህ ፡ ስሙ ፤ በውኑ ፡ ከዚህ ፡ ድንጋይ ፡ ውኃን ፡
፲፩ እናወጣላችኋለን ? አላቸው ። ሙሴም ፡ እጁን ፡
ዘርግቶ ፡ ድንጋዩን ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ በበትሩ ፡
መታው ፤ ብዙም ፡ ውኃ ፡ ወጣ ÷ ማኅበሩም ፡
፲፪ ከብቶቻቸውም ፡ ጠጡ ። እግዚአብሔርም ፡
ሙሴንና ፡ አሮንን ፡— በእስራኤል ፡ ልጆች ፡
ፊት ፡ ትቀድሱኝ ፡ ዘንድ ፡ በእኔ ፡ አላመናችሁ
ምና ፡ ስለዚህ ፡ ወደ ፡ ሰጠኋቸው ፡ ምድር ፡ ይህን ፡
፲፫ ጉባኤ ፡ ይዛችሁ ፡ አትገቡም ፡ አላቸው ። የእ
ስራኤል ፡ ልጆች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ጠብ ፡
ያደረጉበት ÷ እርሱም ፡ ቅዱስ ፡ መሆኑን ፡ የገ
ለጠበት ፡ ይህ ፡ የመሪባ ፡ ውኃ ፡ ነው ።
፲፬ ሙሴም ፡ ከቃዴስ ፡ ወደ ፡ ኤዶምያስ ፡ ንጉሥ ፡
መልእክተኞችን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ላከ ፡— ወን
ድምህ ፡ እስራኤል ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ያገኘ
፲፭ ንን ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፡ አንተ ፡ ታውቃለህ ፤ አባ
ቶቻችን ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ወረዱ ÷ በግብፅም ፡
እጅግ ፡ ዘመን ፡ ተቀመጥን ፡ ግብፃውያንም ፡ እኛ
፲፮ ንና ፡ አባቶቻችንን ፡ በደሉ ፡ ወደ ፡ እግዚአብ
ሔርም ፡ በጮኽን ፡ ጊዜ ፡ ድምፃችንን ፡ ሰማ ÷
መልአኩንም ፡ ሰድዶ ፡ ከግብፅ ፡ አወጣን ፤ እነ
ሆም ÷ በምድርህ ፡ ዳርቻ ፡ ባለችው ፡ ከተማ ፡
፲፯ በቃዴስ ፡ ተቀምጠናል ። እባክህ ÷ በምድርህ ፡
ላይ ፡ እንለፍ ፤ ወደ ፡ እርሻም ፡ ወደ ፡ ወይንም ፡
አንገባም ÷ ከጉድጓዶችም ፡ ውኃን ፡ አንጠጣም ፡
በንጉሡ ፡ ጐዳና ፡ እንሄዳለን ፤ ዳርቻህንም ፡ እስ
ከናልፍ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡
፲፰ አንልም ። ኤዶምያስም ፡— በሰይፍ ፡ እንዳል
ገጥምህ ፡ በምድሬ ፡ ላይ ፡ አታልፍም ፡ አለው ።
፲፱ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡— በጐዳናው ፡ እንሄዳ
ለን ÷ እኔም ፡ ከብቶቹም ፡ ከውኃህ ፡ ብንጠጣ ፡
ዋጋውን ፡ እንከፍላለን ÷ ሌላም ፡ ምንም ፡ ስናደ
ርግም ፤ ብቻ ፡ በእግራችን ፡ እንሰፍ ፡ አሉት ።
እርሱም ፡— አታልፍም ፡ አለ ። ኤዶምያስም ፡ ፳
በብዙ ፡ ሕዝብና ፡ በጽኑ ፡ እጅ ፡ ሊገጥመው ፡
ወጣ ። ኤዶምያስም ፡ እስራኤል ፡ በዳርቻው ፡ ፳፩
እንዳያልፍ ፡ ከለከለ ፤ ስለዚህ ፡ እስራኤል ፡ ከእ
ርሱ ፡ ተመለሰ ።
ከቃዴስም ፡ ተጓዙ ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ፳፪
ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ሖር ፡ ተራራ ፡ መጡ ።
እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ በኤዶም ፡ ፳፫
ያስ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡ ባለው ፡ በሖር ፡ ተራራ ፡
እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፡— አሮን ፡ ወደ ፡ ፳፬
ወገኑ ፡ ይከማች ፤ በመሪባ ፡ ውኃ ፡ ዘንድ ፡ በቃሴ ፡
ላይ ፡ ስለ ፡ ዐመፃችሁ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡
ወደ ፡ ሰጠኋት ፡ ምድር ፡ አይገባም ። አሮን ፡ ፳፭
ንና ፡ ልጁን ፡ አልዓዛርን ፡ ይዘህ ፡ ወደ ፡ ሖር ፡
ተራራ ፡ ላይ ፡ አምጣቸው ፡ ከአሮንም ፡ ልብሱን ፡ ፳፮
አውጣ ÷ ልጁንም ፡ አልዓዛርን ፡ አልብሰው ፡
አሮንም ፡ ወደ ፡ ወገኑ ፡ ይከማች ÷ በዚያም ፡
ይሙት ። ሙሴም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘ ፡ ፳፯
አደረገ ፤ ማኅበሩም ፡ ሁሉ ፡ እያዩ ፡ ወደ ፡ ሖር ፡
ተራራ ፡ ወጡ ። ሙሴም ፡ የአሮንን ፡ ልብስ ፡ ፳፰
አወጣ ÷ ልጁንም ፡ አልዓዛርን ፡ አለበሰው ፡
አሮንም ፡ በዚያ ፡ በተራራው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ሞተ ፤
ሙሴና ፡ አልዓዛርም ፡ ከተራራው ፡ ወረዱ ።
ማኅበሩም ፡ ሁሉ ፡ አሮን ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ባዩ ፡ ፳፱
ጊዜ ÷ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ ለአሮን ፡
ሠላሳ ፡ ቀን ፡ አለቀሱ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፩ ።

በደቡብም ፡ በኩል ፡ ተቀምጦ ፡ የነበረው ፡ ፩
ከነዓናዊው ፡ የዓራድ ፡ ንጉሥ ፡ በአታሪም ፡ መን
ገድ ፡ እስራኤል ፡ እንደ ፡ መጡ ፡ ሰማ ፤ ከእስራ
ኤልም ፡ ጋር ፡ ሰልፍ ፡ አደረገ ፤ ከእነርሱም ፡
ምርኮ ፡ ማረከ ። እስራኤልም ፡ ለእግዚአብ ፪
ሔር ፡— እነዚህን ፡ አሳልፈህ ፡ በእጄ ፡ ብትሰጣ
ቸው ፡ ከተሞቻቸውን ፡ እርም ፡ ብዬ ፡ አጠፋ
ለሁ ፡ ብሎ ፡ ስእለት ፡ ተሳለ ። እግዚአብሔርም ፡ ፫
የእስራኤልን ፡ ድምፅ ፡ ሰማ ÷ ከነዓናውያንንም ፡
አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፤ እነርሱንም ፡ ከተሞቻቸው
ንም ፡ እርም ፡ ብለው ፡ አጠፋ ፤ የዚያንም ፡
ስፍራ ፡ ስም ፡ ሔርማ ፡ ብለው ፡ ጠሩት ።
ከሖርም ፡ ተራራ ፡ ከኤዶምያስ ፡ ምድር ፡ ፬
ርቀው ፡ ሊዞሩ ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡ መንገድ ፡
ተጓዙ ፤ የሕዝቡም ፡ ሰውነት ፡ ከመንገዱ ፡ የተ
ነሣ ፤ ደከመ ። ሕዝቡም ፡ በእግዚአብሔርና ፡ ፭
በሙሴ ፡ ላይ ፡— በምድረ ፡ በዳ ፡ እንሞት ፡ ዘንድ ፡
ከግብፅ ፡ ለምን ፡ አወጣችሁን ? እንጀራ ፡ የለም ÷
ውኃ ፡ የለም ፤ ሰውነታችንም ፡ ይህን ፡ ቀላል ፡
እንጀራ ፡ ተጸየፈ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ። እግዚአብ ፮
ሔርም ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ እባቦችን ፡ ሰደደ ÷ ሕዝ
ቡንም ፡ ነደፉ ፤ ከእስራኤልም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡
ሞቱ ። ሕዝቡም ፡ ወደ ፡ ሙሴ ፡ መጥተው ፡— ፯
በእግዚአብሔርና ፡ በእንተ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተናገ

ርን ፡ በድለናል ፤ እባቦችን ፡ ከእኛ ፡ ያርቅልን ፡
ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸልይልን ፡ አሉት ።
ሙሴም ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ጸለየ ። እግዚአብሔርም ፡
ሙሴን ፡— እባብን ፡ ሠርተህ ፡ በዓላማ ፡ ላይ ፡ ፰
ስቀል ፤ የተነደፈውም ፡ ሁሉ ፡ ሲያያት ፡ በሕይ
ወት ፤ ይኖራል ፡ አለው ። ሙሴም ፡ የናሱን ፡
እባብ ፡ ሠርቶ ፡ በዓላማ ፡ ላይ ፡ ሰቀለ ፤ እባብም ፡
የነደፈችው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የናሱን ፡ እባብ ፡ በየ ፡
ጊዜ ፡ ዳነ ።
፲ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ተጓዙ ÷ በአቦትም ፡
ሰፈሩ ። ከአቦትም ፡ ተጕዘው ፡ በሞዓብ ፡ ፊት ፡
ለፊት ፡ ባለችው ፡ ምድረ ፡ በዳ ÷ በፀሐይ ፡
መውጫ ፡ በኩል ÷ በኢዮዓባሪም ፡ ሰፈሩ ። ከዚ
ያም ፡ ተጕዘው ፡ በዘሬድ ፡ ሸለቆ ፡ ሰፈሩ ። ከዚ
ያም ፡ ተጕዘው ፡ ከአሞራውያን ፡ ዳርቻ ፡ በሚ
ወጣው ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ በአርኖን ፡ ማጆ ፡
ሰፈሩ ፤ አርኖን ፡ በሞዓብና ፡ በአሞራውያን ፡
መካከል ፡ ያለ ፡ የሞዓብ ፡ ዳርቻ ፡ ነውና ። ስለ
ዚህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ የጦርነት ፡ መጽሐፍ ፡
እንዲህ ፡ ተብሎ ፡—
ዋህብ ፡ በሱፋ ÷
የአርኖንም ፡ ሸለቆች ÷
ወደ ፡ ዔር ፡ ማደሪያ ፡ የሚወርድ ፡
በሞዓብም ፡ ዳርቻ ፡ የሚጠጋ ፡
የሸለቆች ፡ ፈሳሽ ።
፲፱ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ብኤር ፡ ተጓዙ ፤ ይኸውም ፡
እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡— ሕዝቡን ፡ ሰብስብ ፡
ውኃንም ፡ እሰጣቸዋለሁ ፡ ብሎ ፡ የተናገረለት ፡
ጕድጓድ ፡ ነው ።
፳ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ እስራኤል ፡ ይህን ፡ መዝሙር ፡
ዘመረ ፡—
እንተ ፡ ምንጭ ፡ ሆይ ÷ ፍለቅ ፡ እናንተ ፡
ዘምሩለት ፤
በበትረ ፡ መንግሥት ፡ በበትራቸውም ፡
የሕዝብ ፡ አዛውንቶች ፡ ያጐደጐዱት ÷
አለቆችም ፡ የቈፈሩት ፡ ጕድጓድ ።
፳፩ ከምድረ ፡ በዳም ፡ ወደ ፡ መቴና ፡ ተጓዙ ፤ ከመ
ቴናም ፡ ወደ ፡ ነሃሊኤል ÷ ከነሃሊኤልም ፡ ወደ ፡
ባሞት ÷ ከባሞትም ፡ ምድረ ፡ በዳውን ፡ ከላይ ፡
ወደሚመለከተው ፡ ወደ ፡ ፈስጋ ፡ ተራራ ፡ ራስ ፡
በሞዓብ ፡ በረሀ ፡ ወዳለው ፡ ሸለቆ ፡ ተጓዙ ።
፳፪ እስራኤልም ፡— በምድርህ ፡ ላይ ፡ እንለፍ ፤
ወደ ፡ እርሻና ፡ ወደ ፡ ወይን ፡ ቦታ ፡ አንገባም ፤
ከጕድጓዶም ፡ ውኃን ፡ አንጠጣም ፤ ከምድርህ ፡
ዳርቻ ፡ እስከንወጣ ፡ ድረስ ፡ በንጉሥ ፡ ጐዳና ፡
እንሄዳለን ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ አሞራውያን ፡ ንጉሥ ፡
፳፫ ወደ ፡ ሴዎን ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ ። ሴዎ
ንም ፡ ፤ እስራኤል ፡ በምድሩ ፡ ላይ ፡ ያልፍ ፡ ዘንድ ፡
እንቢ ፡ አለ ፤ ሰዎንም ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ ሰበ
ሰበ ÷ እስራኤልንም ፡ ለመውጋት ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡
በዳ ፡ ወጣ ÷ ወደ ፡ ያህጽም ፡ መጣ ÷ ከእስራኤ
ልም ፡ ጋር ፡ ተዋጋ ። እስራኤልም ፡ በሰይፍ ፡
መታው ፤ ምድሩንም ፡ ከአርኖን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡
አሞን ፡ ልጆች ፡ እስከ ፡ ያቦቅ ፡ ድረስ ፡ ወረሰ ፤
የአሞንም ፡ ልጆች ፡ ዳርቻ ፡ የጸና ፡ ነበረ ።
እስራኤልም ፡ እነዚህን ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ ወሰደ ፤ ፳፭
እስራኤልም ፡ በአሞራውያን ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡
በሐሴቦንና ፡ በመንደሮቹ ፡ ሁሉ ፡ ተቀመጠ ።
ሐሴቦንም ፡ የአሞራውያን ፡ ንጉሥ ፡ የሴዎን ፡ ፳፮
ከተማ ፡ ነበረ ፤ እርሱም ፡ የፊተኛውን ፡ የሞዓ
ብን ፡ ንጉሥ ፡ ወግቶ ፡ እስከ ፡ አርኖን ፡ ድረስ ፡
ምድሩን ፡ ሁሉ ፡ ከእጁ ፡ ወስዶ ፡ ነበር ። ስለ ፳፯
ዚህ ፡ በምሳሌ ፡ እንዲህ ፡ ተብሎ ፡ ተነገረ ፡—
ወደ ፡ ሐሴቦን ፡ ኑ ፤
የሴዎን ፡ ከተማ ፡ ይሠራ ÷ ይመሥረት ፤
እሳት ፡ ከሐሴቦን ÷ ነበልባልም ፡ ከሴዎን ፡ ፳፰
ከተማ ፡ ወጣ ፤
የሞዓብን ፡ ዔር ÷ የአርኖንን ፡ ተራራ ፡ አለ ፡
ቆች ፡ በላ ፤
ሞዓብ ፡ ሆይ ÷ ወዮልህ ! ፳፱
የከሞስ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ÷ ጠፋህ ፤
ወንዶች ፡ ልጆቹን ፡ ለሸሽት ÷ ሴቶች ፡
ልጆቹንም ፡ ለምርኮ ÷
ለአሞራውያን ፡ ንጉሥ ፡ ለሴዎን ፡ ሰጠ ።
ገተርናቸው ፤ ከሐሴቦን ፡ እስከ ፡ ዴቦን ፡ ፴፡
ድረስ ፡ ጠፋ ፤
ኖፋም ፡ እስከ ፡ ዴርሱ ፡ እስከ ፡ ሜድባ ፡ አፈ
ረስናቸው ።
፴፩ እስራኤልም ፡ እንደ ፡ ዚህ ፡ በአሞራውያን ፡ ምድር ፡
ተቀመጡ ። ሙሴም ፡ ሰላዮችን ፡ ወደ ፡ ኢያ ፴፪
ዜር ፡ ሰደደ ፤ መንደሮችዋንም ፡ ወሰዱ ÷ በዚ
ያም ፡ የነበሩትን ፡ አሞራውያን ፡ አባረሩ ።
ተመልሰውም ፡ በባሳን ፡ መንገድ ፡ ወጡ ፤ ፴፫
የባሳንም ፡ ንጉሥ ፡ ዐግ ፡ ከሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡
በኤድራይ ፡ ይወጋቸው ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ። እግ ፴፬
ዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡— እርሱንና ፡ ሕዝቡን ፡
ሁሉ ፡ ምድሩንም ፡ አሳልፌ ፡ በእጅህ ፡ ሰጥቼ ፡
አለሁና ፡ አትፍራው ፡ በሐሴቦንም ፡ በተቀመ
ጠው ፡ በአሞራውያን ፡ ንጉሥ ፡ በሴዎን ፡ እን
ዳደረግህ ፡ እንዲሁ ፡ ታደርግበታለህ ፡ አለው ።
እርሱንና ፡ ልጆቹን ፡ ሕዝቡንም ፡ ሁሉ ፡ መቱ ፡ ፴፭
ሰውም ፡ አልቀረለትም ፡ ምድሩንም ፡ ወረሱ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ተጓዙ ÷ በኢያሪኮ ፡ ፩
ፊት ፡ ለፊት ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ባለው ፡ በሞ
ዓብ ፡ ሜዳ ፡ ሰፈሩ ።
፪ የሴፎር ፡ ልጅ ፡ በላቅ ፡ እስራኤል ፡ በአሞራ ፡
ውያን ፡ ላይ ፡ ያደረገውን ፡ ሁሉ ፡ አየ ። ብዙም ፡ ፫
ነበረና ፡ ሞዓብ ፡ ከሕዝቡ ፡ እጅግ ፡ ፈራ ፤ ከእ
ስራኤልም ፡ ልጆች ፡ የተነሣ ፡ ሞዓብ ፡ ደነገጠ ።
ሞዓብም ፡ የምድያምን ፡ ሽማግሌዎች ፡— በሬ ፡ ፬
የሚመለመውን ፡ ሣር ፡ እንደሚጨርስ ፡ ይህ ፡
ጭፍራ ፡ በዙሪያችን ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ይጨር
ሳል ፡ አላቸው ። በዚያን ፡ ጊዜም ፡ የሴፎር ፡
ልጅ ፡ በላቅ ፡ የሞዓብ ፡ ንጉሥ ፡ ነበረ ። በወ ፭፡፮፡
ንዙ ፡ አዘገብ ፡ ባለችው ፡ በሕዝቡ ፡ ልጆች ፡
ምድር ፡ በፋቱራ ፡ ወደ ፡ ተቀመጠው ፡ ወደ ፡

ቢያር ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ በለዓም ፡— እነሆ ÷ ከግብፅ ፡ የወጣ ፡ ሕዝብ ፡ አለ ፤ እነሆም ÷ የምድሩን ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ ሸፈነ ÷ በአቅራቢያችንም ፡ ተቀምጦአል ፤ አሁንም ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ከእኔ ፡ ይበልጣልና ፤ ልወጋቸውና ፡ ከምድሪቱ ፡ ላሳድዳቸው ፡ እችል ፡ እንደ ፡ ሆነ ÷ እባክህ ፡ ና ፡ ርገምልኝ ፤ አንተ ፡ የመረቅኸው ፡ ምሩቅ ፡ የረገምኸውም ፡ ርጉም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አውቃለሁና ፡ ብሎ ፡ ይጠሩት ፡ ዘንድ ፡ መልእክተኞቹን ፡ ላከ ።

፯ ፡ የሞዓብ ፡ ሽማግሌዎችና ፡ የምድያም ፡ ሽማግሌዎችም ፡ የምዋርቱን ፡ ዋጋ ፡ በእጃቸው ፡ ይዘው ፡ ሄዱ ፤ ወደ ፡ በለዓምም ፡ ሠራቡ ÷ የበ
፰ ፡ ላቅንም ፡ ቃል ፡ ነገሩት ። እርሱም ፡— ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ በዚህ ፡ እደሩ ÷ እግዚአብሔርም ፡ እንደሚነግረኝ ፡ እመልስላችኋለሁ ፡ አላቸው ፡ የሞዓብም ፡ አለቆች ፡ በበለዓም ፡ ዘንድ ፡ ተቀመጡ ።
፱ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ወደ ፡ በለዓም ፡ መጥቶ ፡— እነዚህ ፡ በአንተ ፡ ዘንድ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ እነማ ፡
፱፡፲፩ ፡ ናቸው ? አለው ። በለዓምም ፡ እግዚአብሔርን ፡— የሞዓብ ፡ ንጉሥ ፡ የሴፎር ፡ ልጅ ፡ ባላቅ ፡— እነሆ ÷ ከግብፅ ፡ የወጣ ፡ ሕዝብ ፡ የምድርን ፡ ፊት ፡ ሸፈነ ÷ አሁንም ፡ ና ፡ እርስትም ፡ ርገምልኝ ፤ ምናልባት ፡ እወጋው ፡ አሳድደውም ፡
፡ ዘንድ ፡ እችል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡
፡ ልኮአል ፡ አለው ። እግዚአብሔርም ፡ በለዓ
ምን ፡— ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ አትሂድ ፤ የተባረከ ፡ ነውና ፡ ሕዝቡን ፡ አትረግምም ፡ አለው ። በለ
ዓምም ፡ ሲነጋ ፡ ተነሥቶ ፡ የባላቅን ፡ አለቆች ፡— ከእናንተ ፡ ጋር ፡ እሄድ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልፈቀደምና ፡ ወደ ፡ ምድራችሁ ፡ ሂዱ ፡ አላ
፡ ቸው ። የሞዓብ ፡ አለቆች ፡ ተነሡ ÷ ወደ ፡ በላ
ቅም ፡ መጥተው ፡— በለዓም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ እልፈቀደም ፡ አሉት ።

፡ ባላቅም ፡ ደግሞ ፡ ከፊተኞች ፡ የበዙና ፡ የከ
፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ፡ በሩ ፡ ሌሎችን ፡ አለቆች ፡ ሰደደ ። ወደ ፡ በለዓ
ምም ፡ መጥተው ፡— የሴፎር ፡ ልጅ ፡ ባላቅ ፡— ክብርህን ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ አደርገዋለሁና ÷ የተ
ናገርኸውንም ፡ ሁሉ ፡ አደርግልሃለሁና ፡ እባ
ክህ ÷ ወደ ፡ እኔ ፡ ትመጣ ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ አይ
ከልክልህ ፤ እባክህ ÷ ና ÷ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ ርገ
፡ ፲፮ ፡ ምልኝ ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ። በለዓምም ፡
መልሶ ፡ የባላቅን ፡ ባሪያዎች ፡— ባላቅ ፡ በቤቱ ፡
የሞላውን ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ቢሰጠኝ ÷ በትንሹ ፡
ወይም ፡ በትልቁ ፡ ቢሆን ፡ የአምላኬን ፡ የእግ
ዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እተላለፍ ፡ ዘንድ ፡ አይቻ
፡ ፲፱ ፡ ለኝም ፤ አሁንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ደግሞ ፡ የሚ
ነግረኝን ፡ እውቅ ፡ ዘንድ ÷ እባክችሁ ÷ ዛሬ ፡
ሌሊት ፡ ደግሞ ፡ በዚህ ፡ እደሩ ፡ አላቸው ።
፡ ፳ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ወደ ፡ በለዓም ፡ በሌሊት ፡
መጥቶ ፡— ሰዎቹ ፡ ይጠሩህ ፡ ዘንድ ፡ መጥተው ፡
እንደ ፡ ሆነ ÷ ተነሣ ፡ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ ሂድ ፡
ነገር ፡ ግን ፡ የምነግርህን ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ታደር
ጋለህ ፡ አለው ።
፡ ፳፩ ፡ በለዓምም ፡ ሲነጋ ፡ ተነሣ ÷ አህያይቱንም ፡
ጭኖ ፡ ከሞዓብ ፡ አለቆች ፡ ጋር ፡ ሄደ ። እር ፡ ፳፪ ፡
ሱም ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቈጣ ፤ የእ
ግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ሊቋቋመው ፡ በመ
ንገድ ፡ ላይ ፡ ቆመ ። እርሱም ፡ በአህያይቱ ፡
ላይ ÷ ሁለቱም ፡ ሎሌዎቹ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ነበሩ ።
አህያይቱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መልአክ ፡ በመ ፡ ፳፫ ፡
ንገድ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ የተመዘዘም ፡ ሰይፍ ፡ በእጁ ፡
ይዞ ፡ አየ ፤ ሰገደም ÷ በግምባሩም ፡ ወደቀ ።
የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡— አህያህን ፡
ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ለምን ፡ መታህ ? እነሆ ÷ መንገ
ድህ ፡ በፊቴ ፡ ጠማማ ፡ ነውና ፡ አቋቋምህ ፡ ዘንድ ፡
ወጥቼአለሁ ፤ አህያይቱም ፡ አይታኝ ፡ ከፊቴ ፡ ፡ ፳፬ ፡
ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ፈቀቅ ፡ አለች ፤ ከፊቴስ ፡ ፈቀቅ ፡
ባላለች ፡ በእውነት ፡ አሁን ፡ አንተን ፡ በገደል
ሁሀ ÷ እርስዋንም ፡ በዳንጓት ፡ ነበር ፡ አለው ።
በለዓምም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መልአክ ፡— በድ ፡ ፳፭ ፡
ያለሁ ፤ አንተ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ በፊቴ ፡ እንደ ፡
ቆምህብኝ ፡ አላወቅሁም ፤ እንግዲህም ፡ አሁን ፡
አትወድድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እመለሳለሁ ፡ አለው ።
የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ በለዓምን ፡— ፡ ፳፮ ፡
ከሰዎቹ ፡ ጋር ፡ ሂድ ÷ ነገር ፡ ግን ፡ የምናገርህን ፡
ቃል ፡ ብቻ ፡ ትናገራለህ ፡ አለው ። በለዓምም ፡
ከባላቅ ፡ አለቆች ፡ ጋር ፡ ሄደ ።
ባላቅም ፡ በለዓም ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ በሰማ ፡ ፡ ፳፯ ፡
ጊዜ ፡ በአርኖን ፡ ዳር ፡ ዳርቻ ፡ በመጨረሻ ፡ ወዳ

ለችው ፡ ወደ ፡ ሞዓብ ፡ ከተማ ፡ ሊገናኘው ፡
ወጣ ። ባላቅም ፡ በለዓምን ፡— በውኑ ፡ አንተን ፡
ለመጥራት ፡ አልላክሁብህምን ? ለምንስ ፡ ወደ ፡
እኔ ፡ አልመጣህም ? በውኑ ፡ አንተን ፡ ለማክ
በር ፡ እኔ ፡ አልችልምን ? አለው ። በለዓምም ፡
በላቅን ፡— እነሆ ÷ ወደ ፡ አንተ ፡ መጥቼአለሁ ፡
በውኑ ፡ አሁን ፡ አንዳችን ፡ ነገር ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡
እችላለሁን ? እግዚአብሔር ፡ በአፌ ፡ የሚያደ
ርገውን ፡ ቃል ፡ እርሱን ፡ እናገራለሁ ፡ አለው ።
በለዓምም ፡ ከባላቅ ፡ ጋር ፡ ሄደ ÷ ወደ ፡ ቂርያት
ሐጾትም ፡ መጡ ። ባላቅም ፡ በሬዎችንና ፡ በጎ
ችን ፡ አረደ ፡ ወደ ፡ በለዓም ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡
ወዳሉት ፡ አለቆች ፡ ላከ ። በነጋውም ፡ ባላቅ ፡
በለዓምን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ በአል ፡ ኮረብታ ፡ መስ
ገኛ ፡ አወጣው ፤ በዚያም ፡ ሆኖ ፡ የሕዝቡን ፡
ዳርቻ ፡ አየ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፫ ።

፡ በለዓምም ፡ ባላቅን ፡— ሰባት ፡ መሠዊያ ፡
በዚህ ፡ ሥራልኝ ፡ ሰባትም ፡ ወይፈን ፡ ሰባትም ፡
አውራ ፡ በግ ፡ በዚህ ፡ አዘጋጅልኝ ፡ አለው ።
ባላቅም ፡ በለዓም ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ አደረገ ፤
ባላቅና ፡ በለዓምም ፡ በየመሠዊያው ፡ ላይ ፡
አንድ ፡ ወይፈንና ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፡ አሳ
ረጉ ። በለዓምም ፡ ባላቅን ፡— በመሥዋዕትህ ፡
ዘንድ ፡ ቆይ ÷ እኔም ፡ እሄዳለሁ ፡ ምናልባት ፡
እግዚአብሔር ፡ ሊገናኘኝ ፡ ይመጣል ፡ እርሱም ፡
የሚገልጥልኝን ፡ እነግረሃለሁ ፡ አለው ። ወደ ፡
ጉብታም ፡ ሄደ ። እግዚአብሔርም ፡ ከበለዓም ፡
ጋር ፡ ተገናኘ ፡ እርሱም ፡— ሰባት ፡ መሠዊያ
ዎች ፡ አዘጋጀሁ ÷ በየመሠዊያውም ፡ ላይ ፡
አንድ ፡ ወይፈንና ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፡ አሳ
ረጉ ፡ አለው ። እግዚአብሔርም ፡ ቃልን ፡ በበ
ለዓም ፡ አፍ ፡ አድርጎ ፡— ወደ ፡ ባላቅ ፡ ተመ
ለስ ÷ እንዲህም ፡ በል ፡ አለው ። ወደ ፡ እርሱም ፡
ተመለሰ ÷ እነሆም ፡ እርሱና ፡ የሞዓብ ፡ አለቆች ፡
ሁሉ ፡ በመሥዋዕቱ ፡ ዘንድ ፡ ቆመው ፡ ነበር ።
ምሳሌውንም ፡ ይመስል ፡ ጀመር ፡ እንዲህም ፡
አለ ፡—

ባላቅ ፡ ከኤራም ፡ አመጣኝ ÷
የሞዓብ ፡ ንጉሥ ፡ ከምሥራቅ ፡ ተራሮች ፡
ና ÷ ያዕቆብን ፡ ርገምልኝ ፡
ና ÷ እስራኤልን ፡ ተሣላልኝ ፡ ብሎ ።
እግዚአብሔር ፡ ያልረገመውን ፡ እንዴት ፡
እረግማለሁ ?
እግዚአብሔርስ ፡ ያልተሣላውን ፡ እንዴት ፡
እሣላለሁ ?
በአምባቸ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ሆኜ ፡ አየዋለሁ ÷
በኮረብቶችም ፡ ላይ ፡ ሆኜ ፡ እመለከተዋለሁ ፡
እነሆ ÷ ብቻውን ፡ የሚቀመጥ ፡ ሕዝብ ፡
ነው ÷
በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ አይቈጠርም ።
የያዕቆብን ፡ ትቢያ ፡ ማን ፡ ይቈጥራል ?
የእስራኤልስ ፡ እርቦ ፡ ማን ፡ ይቈጥራል ?
የጻድቃንን ፡ ሞት ፡ እኔ ፡ ልሙት ÷
ፍጻሜዬም ፡ እንደ ፡ እርሱ ፡ ፍጻሜ ፡ ትሁን ።
በላቅም ፡ በለዓምን ፡— ያደረግሁብኝ ፡ ምንድር ፡ ፳፩ ፡
ነው ? ጠላቶቼን ፡ ትረግምልኝ ፡ ዘንድ ፡ ጠራ
ሁህ ፡ እነሆም ÷ ፈጽመህ ፡ ባረከካቸው ፡ አለው ።
እርሱም ፡ መልሶ ፡— በውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፳፪ ፡
በአፌ ፡ ያደረገውን ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ አልጠነ
ቀቅምን ? አለው ።
ባላቅም ፡— በዚያ ፡ ሆነህ ፡ ታያቸው ፡ ዘንድ ÷ ፳፫ ፡
እባክህ ÷ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ና ፡ ዳር
ቻቸውንም ፡ ብቻ ፡ ታያለህ ÷ ሁሉን ፡ ግን ፡
አታይም ፡ በዚያም ፡ ሆነህ ፡ እነርሱን ፡ ርገም
ልኝ ፡ አለው ። ወደ ፡ ጾፊምም ፡ ሜዳ ፡ ወደ ፡ ፳፬ ፡
ፈስጋ ፡ ተራራ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ወሰደው ፡ ሰባትም ፡
መሠዊያዎች ፡ ሠራ ÷ በየመሠዊያውም ፡ ላይ ፡
አንድ ፡ ወይፈን ፡ አንድም ፡ አውራ ፡ በግ ፡ አሳ
ረገ ። ባላቅንም ፡— እኔ ፡ ወደዚያ ፡ ለመገናኘት ፡ ፳፭ ፡
ስሄድ ፡ በዚህ ፡ በመሥዋዕትህ ፡ ዘንድ ፡ ቆይ ፡
አለው ። እግዚአብሔርም ፡ በለዓምን ፡ ተገናኘ ÷ ፳፮ ፡
ቃልንም ፡ በአፉ ፡ አድርጎ ፡— ወደ ፡ ባላቅ ፡ ተመ
ለስ ÷ እንዲህም ፡ በል ፡ አለው ። ወደ ፡ እርሱም ፡ ፳፯ ፡
መጣ ፤ እነሆም ÷ እርሱ ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የሞ
ዓብ ፡ አለቆች ፡ በመሥዋዕቱ ፡ ዘንድ ፡ ቆመው ፡
ነበር ፡ ባላቅም ፡— እግዚአብሔር ፡ የተናገረው ፡
ምንድር ፡ ነው ? አለው ። ምሳሌውንም ፡ ይመ ፡ ፳፰ ፡
ስል ፡ ጀመር ÷ እንዲህም ፡ አለ ፡—

ባላቅ ፡ ሆይ ÷ ተነሣ ÷ ስማ ፡
የሴፎር ፡ ልጅ ፡ ሆይ ÷ እድምጠኝ ፡
ሐሰትን ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፳፱ ፡
ሰው ፡ አይደለም ÷
ይጸጸትም ፡ ዘንድ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ አይደ
ለም ።
እርሱ ፡ ያለውን ፡ አያደርገውምን ?
የተናገረውንስ ፡ አይፈጽመውምን ?
እነሆ ÷ ለመባረክ ፡ ትእዛዝን ፡ ተቀብያለሁ ፡ ፳፡
እርሱ ፡ ባርኮአል ÷ እመልሰውም ፡ ዘንድ ፡
አልችልም ።
በያዕቆብ ፡ ላይ ፡ ክፋትን ፡ አልተመለከተም ÷ ፳፩ ፡
በእስራኤልም ፡ ጠማምነትን ፡ አላየም ፡
አምላኩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡
ነው ÷
የንጉሥም ፡ አልልታ ፡ በመካከላቸው ፡ አለ ።
እግዚአብሔር ፡ ከግብፅ ፡ አውጥቶአቸዋል ፡ ፳፪ ፡
ጕልበቱ ፡ እንደ ፡ ቀንድ ፡ እንዳለው ፡ ነው ።
በያዕቆብ ፡ ላይ ፡ አስማት ፡ የለም ÷ ፳፫ ፡
በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ምዋርት ፡ የለም ፡
በጊዜው ፡ ስለ ፡ ያዕቆብና ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡—
እግዚአብሔር ፡ ምን ፡ አደረገ ! ይባላል ።
እነሆ ÷ ሕዝቡ ፡ እንደ ፡ እንስት ፡ አንበሳ ፡ ፳፬ ፡
ይቆማል ÷
እንደ ፡ አንበሳም ፡ ይነሣል ፡
ያደነውን ፡ እስኪበላ ÷
የገደለውንም ፡ ደሙን ፡ እስኪጠጣ ፡ አይተ
ኛም ።

፳፭ ፡ በላቅም ፡ በለዓምን ፡— ከቶ ፡ አትርገማቸው ÷
፳፮ ፡ ከቶም ፡ አትባርክቸው ፡ አለው ። በለዓምም ፡
መልሶ ፡ በላቅን ፡— እግዚአብሔር ፡ የተናገረ
ውን ፡ ሁሉ ፡ አደርጋለሁ ፡ ብዬ ፡ አልተናገርሁህ
ምን ? አለው ።
፳፯ ፡ በላቅም ፡ በለዓምን ፡— ና ÷ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡
እወስድሃለሁ ፡ ምናልባት ፡ በዚህ ፡ ሆነህ ፡ እነር
ሱን ፡ ትረግምልኝ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወ
፳፰ ፡ ድዳል ፡ አለው ። በላቅም ፡ ምድረ ፡ በዳውን ፡
ከላይ ፡ ወደሚመለከተው ፡ ወደ ፡ ፈጎር ፡ ላይ ፡
፳፱ ፡ በለዓምን ፡ ወሰደው ። በለዓምም ፡ በላቅን ፡—
በዚህ ፡ ሰባት ፡ መሠዊያዎች ፡ ሥራልኝ ÷ በዚ
ህም ፡ ሰባት ፡ ወይፈን ፡ ሰባትም ፡ አውራ ፡ በግ ፡
፴ ፡ አዘጋጅልኝ ፡ አለው ። በላቅም ፡ በለዓም ፡ እን
ዳለው ፡ አደረገ ÷ በየመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ አንድ ፡
ወይፈንና ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፡ አሳረገ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፬ ።

፩ ፡ በለዓምም ፡ እግዚአብሔር ፡ እስራኤልን ፡
ይባርክ ፡ ዘንድ ፡ እንዲወድድ ፡ በየ ፡ ጊዜ ÷ አስ
ቀድሞ ፡ ያደርግ ፡ የነበረውን ፡ አስማት ፡ ይሻ ፡
ዘንድ ፡ አልሄደም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡
፪ ፡ በዳ ፡ ፊቱን ፡ አቀና ። በለዓምም ፡ ዓይኑን ፡ አን
ሥቶ ፡ እስራኤል ፡ በየነገዱ ፡ ተቀምጦ ፡ አየ ፤
የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በላዩ ፡ መጣ ።
፫ ፡ ምሳሌውን ፡ ይመስል ፡ ጀመር ÷ እንዲህም ፡
አለ ፡—
የቢዖር ፡ ልጅ ፡ በለዓም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ÷
ዓይኖቹ ፡ የተከፈቱለት ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፤
፬ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ የሚሰማ ÷
ሁሉን ፡ የሚችል ፡ የአምላክን ፡ ራእይ ፡
የሚያይ ÷
የወደቀው ÷ ዓይኖቹም ፡ የተከፈቱለት ፡
እንዲህ ፡ ይላል ፡—
፭ ፡ ያዕቆብ ፡ ሆይ ÷ ድንኳኖችህ ÷
እስራኤል ፡ ሆይ ÷ ማደሪያዎችህ ፡ ምንኛ ፡
ያምራሉ !
፮ ፡ እንደ ፡ ሸለቆች ÷
በወንዝ ፡ ዳር ፡ እንዳሉ ፡ አትክልቶች ÷
እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተከለው ፡ እሬት ፡
በውኃም ፡ ዳር ፡ እንዳሉ ፡ ዝግባዎች ፡ ተዘ
ርግተዋል ።
፯ ፡ ከማድጋዎቹ ፡ ውኃ ፡ ይፈስሳል ÷
ዘሩም ፡ በብዙ ፡ ውኖች ፡ ይሆናል ÷
ንጉሡም ፡ ከአጋግ ፡ ይልቅ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡
ይላል ÷
መንግሥቱም ፡ ይከበራል ።
፰ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከግብፅ ፡ አውጥቶታል ፤
ጦልበቱ ፡ አንድ ፡ ቀንድ ፡ እንዳለው ፡ ነው ፤
ጠላቶቹን ፡ አሕዛብን ፡ ይበላል ÷
አጥንቶቻቸውንም ፡ ይሰባብራል ÷
በፍላጻቹም ፡ ይወጋቸዋል ።
፱ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ዐርፎ ፡ ተኝቶአል ÷
እንደ ፡ እንስቲቱም ፡ አንበሳ ፡ ተጋድሞ
አል ፤
ማን ፡ ያስነሣዋል ?
የሚመርቅህ ፡ ሁሉ ፡ የተመረቀ ፡ ይሁን ÷
የሚረግምህም ፡ ሁሉ ፡ የተረገመ ፡ ይሁን ።
፱ ፡ የበላቅም ፡ ቍጣ ፡ በበለዓም ፡ ላይ ፡ ነደደ ፤
እጆቹንም ፡ አጨበጨበ ፤ በላቅም ፡ በለዓምን ፡—
ጠላቶቼን ፡ ትረግም ፡ ዘንድ ፡ ጠራሁህ ÷ እነ
ሆም ÷ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ፈጽመህ ፡ መረቅሃቸው ፤
አሁንም ፡ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ስፍራህ ፡ ሽሽ ፤ እኔ ፡ ፲፩ ፡
አክብርህ ፡ ዘንድ ፡ ወድጄ ፡ ነበር ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ግን ÷ እነሆ ÷ ክብርህን ፡ ከለከለ ፡ አለው ።
በለዓምም ፡ በላቅን ፡ አለው ፡— በላቅ ፡ በቤቱ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ፡
የሞላውን ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ቢሰጠኝ ÷ መልካ
ሙን ፡ ወይም ፡ ክፉውን ፡ ከልቤ ፡ ሰማድረግ ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እተላለፍ ፡ ዘንድ ፡
አይቻለኝም ! እግዚአብሔር ፡ የተናገረውን ፡
እርሱን ፡ እናገራለሁ ፡ ብዬ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ለላክ
ሃቸው ፡ መልእክተኞችህ ፡ አልተናገርኋቸው
ምን ? አሁንም ÷ እነሆ ÷ ወደ ፡ ሕዝቤ ፡ እሄዳ
ለሁ ፤ ና ÷ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡
በሕዝብህ ፡ ላይ ፡ የሚያደርገውን ፡ እነግርሃለሁ ።
ምሳሌውንም ፡ ይመስል ፡ ጀመር ÷ እንዲህም ፡ ፲፭ ፡
አለ ፡—
የቢዖር ፡ ልጅ ፡ በለዓም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ÷
ዓይኖቹ ፡ የተከፈቱለት ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡
ይላል ፤
የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ የሚሰማ ÷ ፲፮ ፡
የልዑልንም ፡ እውቀት ፡ የሚያውቅ ÷
ሁሉን ፡ የሚችል ፡ የአምላክን ፡ ራእይ ፡
የሚያይ ÷
የወደቀው ÷ ዓይኖቹም ፡ የተከፈቱለት ፡
እንዲህ ፡ ይላል ፡—
አየዋለሁ ÷ አሁን ፡ ግን ፡ አይደለም ፤ ፲፯ ፡
እመለከተዋለሁ ÷ በቅርብ ፡ ግን ፡ አይደ
ለም ፤
ከያዕቆብ ፡ ከከብ ፡ ይወጣል ÷
ከእስራኤል ፡ በትር ፡ ይነሣል ÷
የሞዓብንም ፡ ማዕዘኖች ፡ ይመታል ÷
የሴትንም ፡ ልጆች ፡ ያጠፋል ።
ኤዶምያስም ፡ ርስቱ ፡ ይሆናል ÷ ፲፰ ፡
ጠላቱ ፡ ሴይር ፡ ደግሞ ፡ ርስቱ ፡ ይሆናል ፤
እስራኤልም ፡ በኃይል ፡ ያደርጋል ።
ከያዕቆብም ፡ የሚወጣ ፡ ገዥ ፡ ይሆናል ÷ ፲፱ ፡
ከከተማውም ፡ የቀሩትን ፡ ያጠፋል ።
አማሌቅንም ፡ አይቶ ፡ ምሳሌውን ፡ ይመስል ፡ ፳ ፡
ጀመር ÷ እንዲህም ፡ አለ ፡—
አማሌቅ ፡ የአሕዛብ ፡ አለቃ ፡ ነበረ ፤
ፍጻሜው ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ይመጣል ።
ቄናዊውንም ፡ አይቶ ፡ ምሳሌውን ፡ ይመ ፳፩ ፡
ስል ፡ ጀመር ÷ እንዲህም ፡ አለ ፡—
ማደሪያህ ፡ የጸና ፡ ነው ÷
ጎጆህም ፡ በአምባ ፡ ላይ ፡ ተሠርቶአል ፤
ነገር ፡ ግን ፡ አሦር ፡ እስኪማርክህ ፡ ድረስ ፡ ፳፪ ፡

ቄናዊው ፡ ለጥፋት ፡ ይሠናል ።
ምሳሌውንም ፡ ይመስል ፡ ጀመር ÷ እንዲ
ህም ፡ አለ ፡—
እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ሲያደርግ ፡
አወይ ! ማን ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ?
ከኪቲም ፡ ዳርቻ ፡ መርከቦች ፡ ይመጣሉ ÷
አሦርንም ፡ ያስጨንቃሉ ÷
ዔቦርንም ፡ ያስጨንቃሉ !
እርሱም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ይመ
ጣል ።
፳፭ ፡ በለዓምም ፡ ተነሣ ÷ ተመልሶም ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡
ሄደ ፤ በላቅም ፡ ደግሞ ፡ መንገዱን ፡ ሄደ ።

ምዕራፍ ፡ ፳፭ ።

፩ ፡ እስራኤልም ፡ በሰጢም ፡ ተቀመጡ ፤ ሕዝቡም ፡
ከሞዓብ ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ ያመነዝሩ ፡ ጀመር ።
፪ ፡ ሕዝቡንም ፡ ወደ ፡ አምላኮቻቸው ፡ መሥዋ
ዕት ፡ ጠሩ ፤ ሕዝቡም ፡ በሉ ÷ ወደ ፡ አምላኮቻ
ቸውም ፡ ሰገዱ ። ፫ እስራኤልም ፡ ብዔልፌጎርን ፡
ተከተለ ! የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ በእስራ
ኤል ፡ ላይ ፡ ነደደ ። ፬ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡—
የእግዚአብሔር ፡ የቍጣው ፡ ጽኑት ፡ ከእስራ
ኤል ፡ እንዲመለስ ፡ የሕዝቡን ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡
ወስደህ ፡ በፀሐዩ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ስቀላቸው ፡ አለው ። ሙሴም ፡ የእስራኤልን ፡
ዳኞች ፡— እናንተ ፡ ሁሉ ፡ ብዔልፌጎርን ፡ የተ
ከተሉትን ፡ ሰዎቻችሁን ፡ ግደሉ ፡ አላቸው ።
፮ ፡ እነሆም ÷ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ አንዱ ፡ መጥቶ ፡
በሙሴና ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡
ፊት ፡ ምድያማዊቷን ፡ አንዲቷን ፡ ሴት ፡ ወደ ፡
ወንድሞቹ ፡ አመጣት ፤ እነርሱም ፡ በመገናኛው ፡
ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ያለቅሱ ፡ ነበር ። ፯ የካህኑም ፡
የአሮን ፡ ልጅ ፡ የአልዓዛር ፡ ልጅ ፡ ፊንሐስ ፡
ባየው ፡ ጊዜ ፡ ከማኅበሩ ፡ መካከል ፡ ተነሥቶ ፡
ጦሩ ፡ ይዞ ፡ አነሣ ፡ ያንንም ፡ የእስራኤልን ፡
ሰው ፡ ተከትሎ ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ ገባ ። ፰ እስራኤ
ላዊውንም ፡ ሰውና ፡ ሴቲቱን ፡ ሁለቱን ፡ ሆዳቸ
ውን ፡ ወጋቸው ። ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ መቅ
ሠፍቱ ፡ ተከለከለ ። በመቅሠፍትም ፡ የሞተው ፡
ሀያ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ ነበረ ።
፱ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተና
ገረው ፡— ፡ የካህኑ ፡ የአሮን ፡ ልጅ ፡ የአልዓዛር ፡
ልጅ ፡ ፊንሐስ ፡ በቅንዓቴ ፡ በመካከላቸው ፡ ቀን
ቶአልና ፡ ቍጣዬን ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መለሰ ፤
እኔም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በቅንዓቴ ፡ አላ
ጠፋሁም ። ስለዚህ ÷ እነሆ ÷ የሰላሜን ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ እሰጠዋለሁ ። ለእምላኩም ፡ ቀንዶአ
ልና ÷ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ አስተስርዮአ
ልና ፡ ለእርሱ ፡ ከእርሱም ፡ በኋላ ፡ ለዘሩ ፡ ለዘላ
ለም ፡ ክህነት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይሆንለታል ።
፲ ፡ ከምድያማዊቱም ፡ ጋር ፡ የተገደለው ፡ የእስራ
ኤላዊው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ዘንበሪ ፡ ነበረ ፤ የአባቱ ፡
ቤት ፡ አለቃ ፡ የስምዖናውያን ፡ የሆነ ፡ የሰሉ ፡
ልጅ ፡ ነበረ ። ፡ የተገደለችውም ፡ ምድያማዊት ፡
ስምዋ ፡ ከስቢ ፡ ነበረ ፤ እርስዋም ፡ የሶር ፡ ልጅ ፡
ነበረች ፤ እርሱም ፡ በምድያም ፡ ዘንድ ፡ የአባቱ ፡
ቤት ፡ ወገን ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።
፲፩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተና
ገረው ፡— በፊጎር ፡ በመቅሠፍቱ ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ፲፫ ፡ ፲፪ ፡
ተገደለችው ፡ ስለ ፡ ምድያም ፡ አለቃ ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡
እኅታቸው ፡ ስለ ፡ ከስቢ ፡ በፊጎር ፡ ምክንያት ፡
በሸነገሉአችሁ ፡ ሸንገላ ፡ አስጨንቀዋችኋልና ፡
ምድያማውያንን ፡ አስጨንቁአቸው ፡ ግደሉአ
ቸውም ።

ምዕራፍ ፡ ፳፮ ።

፩ ፡ እንዲህም ፡ ሆነ ፤ መቅሠፍቱ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡
እግዚአብሔር ፡ ሙሴንና ፡ የካህኑን ፡ የአሮን ፡
ልጅ ፡ አልዓዛርን ፡— ፡ ከሀያ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ፪ ፡
ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያለውን ÷ በእስራኤል ፡ ወደ ፡
ሰልፍ ፡ የሚወጣውን ፡ ሁሉ ÷ የእስራኤልን ፡
ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ በየአባቶቻቸው ፡ ቤት ፡
ቍጠሩ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ። ፡ ሙሴና ፡ ካህኑ ፡ ፫ ፡
አልዓዛር ፡ በዮርዳኖስ ፡ አጠገብ ፡ በኢያሪኮ ፡
ፊት ፡ ሰፈሩ ፡ በሞዓብ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡— ፡ እግዚአብ ፪ ፡
ሔር ፡ ሙሴን ፡ ከግብፅም ፡ ምድር ፡ የወጡትን ፡
የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንዳዘዛቸው ÷ ከሀያ ፡
ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡
ሕዝቡን ፡ ቍጠሩ ፡ ብለው ፡ ተናገሩአቸው ።
፮ ፡ የእስራኤል ፡ በኵር ፡ ሮቤል ፤ የሮቤል ፡ ልጆች ፡
ከሄኖኅ ፡ የሄኖኅውያን ፡ ወገን ÷ ከፈሉስ ፡ የፈ
ሉሳውያን ፡ ወገን ÷ ከአስሮን ፡ የአስሮናውያን ፡ ፯ ፡
ወገን ÷ ከከርሚ ፡ የከርማውያን ፡ ወገን ። ፡ እነ ፯ ፡
ዚህ ፡ የሮቤላውያን ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ከእነር
ሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ አርባ ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡ ሰባት ፡
መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ነበሩ ። ፡ የፈሉስም ፡ ልጆች ፤ ፰ ፡
ኤልያብ ። ፡ የኤልያብም ፡ ልጆች ፤ ነሙኤል ÷ ፱ ፡
ዳታን ÷ አቤሮን ፤ እነዚህ ፡ ዳታንና ፡ አቤሮን ፡
ከማኅበሩ ፡ የተመረጡ ፡ ነበሩ ፤ ከቆሬ ፡ ወገን ፡
ጋር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ በመፀ ፡ ጊዜ ፡
ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ ተማሉ ፤ ያም ፡ ወገን ፡ ፲ ፡
በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ምድሪቱ ፡ አፍዋን ፡ ከፍታ ፡
ከቆሬ ፡ ጋር ፡ ዋጠቻቸው ። ፡ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ እሳ
ቲቱ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ አምሳውን ፡ ሰዎች ፡ አቃ
ጠለቻቸው ፤ እነርሱም ፡ ለምልክት ፡ ሆኑ ። ፡
የቆሬ ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ አልሞቱም ። ፲፩ ፡
የስምዖን ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፡ ከነሙ ፡ ፲፪ ፡
ኤል ፡ የነሙኤላውያን ፡ ወገን ÷ ከያሚን ፡ የያ
ሚናውያን ፡ ወገን ÷ ከያኪን ፡ የያኪናውያን ፡
ወገን ÷ ከዛሬ ፡ የዛራውያን ፡ ወገን ÷ ከሳኡል ፡ ፲፫ ፡
የሳኡላውያን ፡ ወገን ። ፡ እነዚህ ፡ የስምዖናው ፲፬ ፡
ያን ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ሀያ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡
ሁለት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።
፲፭ ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፡ ከጽፎን ፡
የጽፎናውያን ፡ ወገን ÷ ከሐጊ ፡ የሐጋውያን ፡
ወገን ÷ ከሹኒ ፡ የሹናውያን ፡ ወገን ÷ ከኤስናን ፡ ፲፮ ፡
የኤስናናውያን ፡ ወገን ÷ ከዔሪ ፡ የዔራውያን ፡
ወገን ÷ ከአሮድ ፡ የአሮዳውያን ፡ ወገን ÷ ከአር ፲፯ ፡

ኤሊ ፡ የአርኤላውያን ፡ ወገን ። እነዚህ ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ከእነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ አርባ ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።
የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ዔርና ፡ አውናን ፤ ዔርና ፡ አውናንም ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ሞቱ ። የይሁዳም ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፤ ከሴሎም ፡ የሴሎማውያን ፡ ወገን ÷ ከፋሬስ ፡ የፋሬሳውያን ፡ ወገን ÷ ከዛራ ፡ የዛራውያን ፡ ወገን ። የፋሬስም ፡ ልጆች ፤ ከኤስሮም ፡ የኤስሮማውያን ፡ ወገን ÷ ከሐሙል ፡ የሐሙላውያን ፡ ወገን ። እነዚህ ፡ የይሁዳ ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ከእነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ ሰባ ፡ ስድስት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።
የይሳኮር ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፡ ከቶላ ፡ የቶላውያን ፡ ወገን ÷ ከፋዋ ፡ የፋዋውያን ፡ ወገን ÷ ከያሱብ ፡ የያሱቡውያን ፡ ወገን ÷ ከሺምሮን ፡ የሺምሮናውያን ፡ ወገን ። እነዚህ ፡ የይሳኮር ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ከእነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ ስድሳ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።
የዛብሎን ፡ ወገኖች ፡ በየወገናቸው ፡ ከሴሬድ ፡ የሴሬዳውያን ፡ ወገን ÷ ከኤሎን ፡ የኤሎናውያን ፡ ወገን ÷ ከያሕልኤል ፡ የያሕልኤላውያን ፡ ወገን ። እነዚህ ፡ የዛብሎናውያን ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ከእነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ ስድሳ ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።
የዮሴፍ ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፤ ምናሴና ፡ ኤፍሬም ። የምናሴ ፡ ልጆች ፤ ከማኪር ፡ የማኪራውያን ፡ ወገን ፡ ማኪር ፡ ገለዓድን ፡ ወለደ ፤ ከገለዓድ ፡ የገለዓዳውያን ፡ ወገን ። የገለዓድ ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ከኢዔዝር ፡ የኢዔዝራውያን ፡ ወገን ÷ ከኬሌግ ፡ የኬሌጋውያን ፡ ወገን ÷ ከአሥሪኤል ፡ የአሥሪኤላውያን ፡ ወገን ÷ ከሴኬም ፡ የሴኬማውያን ፡ ወገን ÷ ከሸሚዳ ፡ የሸሚዳውያን ፡ ወገን ÷ ከአፌር ፡ የአፌራውያን ፡ ወገን ። የአፌርም ፡ ልጅ ፡ ሰለጰዳድ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ እንጂ ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ አልነበሩትም ፤ የሰለጰዳድም ፡ የሴቶች ፡ ልጆቹ ፡ ስም ፡ ማህለህ ÷ ኑዓ ÷ ዔግላ ÷ ሚልካ ÷ ቲርጻ ፡ ነበረ ። እነዚህ ፡ የምናሴ ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ከእነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ አምሳ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።
በየወገናቸው ፡ የኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ከሱቴላ ፡ የሱቴላውያን ፡ ወገን ÷ ከቤኬር ፡ የቤኬራውያን ፡ ወገን ÷ ከታሐን ፡ የታሐናውያን ፡ ወገን ። እነዚህ ፡ የሱቴላ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፤ ከዔዴን ፡ የዔዲናውያን ፡ ወገን ። እነዚህ ፡ የኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ከእነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ ሠላሳ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ። በየወገናቸው ፡ የዮሴፍ ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።
የብንያም ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፡ ከቤላ ፡ የቤላውያን ፡ ወገን ÷ ከአስቤል ፡ የአስቤላውያን ፡ ወገን ÷ ከአሒራን ፡ የአሒራናውያን ፡ ወገን ÷ ከሶፋን ፡ የሶፋናውያን ፡ ወገን ÷ ከሑፋም ፡ የሑፋማውያን ፡ ወገን ። የቤላም ፡ ልጆች ፤ አርድና ፡ ናዕማን ፤ ከአርድ ፡ የአርዳውያን ፡ ወገን ÷ ከናዕማን ፡ የናዕማናውያን ፡ ወገን ። በየወገናቸው ፡ የብንያም ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ከእነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ አርባ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።
በየወገናቸው ፡ የዳን ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ከሱምዔ ፡ የሱምዔያውያን ፡ ወገን ፤ በየወገናቸው ፡ የዳን ፡ ወገኖች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። የሰምዔያውያን ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ከእነርሱ ፡ እንደ ፡ ተቈጠሩ ፡ ስድሳ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።
የአሴር ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፤ ከዩምና ፡ የዩምናውያን ፡ ወገን ÷ ከየሱዋ ፡ የየሱዋውያን ፡ ወገን ÷ ከብሪዓ ፡ የብሪዓውያን ፡ ወገን ። ከብሪዓ ፡ ልጆች ፤ ከሔቤር ፡ የሔቤራውያን ፡ ወገን ÷ ከመልኪኤል ፡ የመልኪኤላውያን ፡ ወገን ። የአሴርም ፡ የሴት ፡ ልጁ ፡ ስም ፡ ሤራሕ ፡ ነበረ ። እነዚህ ፡ የአሴር ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ከእነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ አምሳ ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።
የንፍታሌም ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፤ ከያሕጽኤል ፡ የያሕጽኤላውያን ፡ ወገን ÷ ከጉኒ ፡ የጉናውያን ፡ ወገን ÷ ከዬጽር ፡ የዬጽራውያን ፡ ወገን ÷ ከሺሌም ፡ የሺሌማውያን ፡ ወገን ። በየወገናቸው ፡ የንፍታሌም ፡ ወገኖች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ከእነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ አርባ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።
ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የተቈጠሩት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ስድስት ፡ መቶ ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ነበሩ ።
እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦ ለእነዚህ ፡ በየስማቸው ፡ ቍጥር ፡ ምድረቱ ፡ ርስት ፡ ሆነ ፡ ትከፈላለች ። ለብዙዎቹ ፡ እንደ ፡ ብዛታቸው ÷ ለጥቂቶቹም ፡ እንደ ፡ ጥቂትነታቸው ፡ መጠን ፡ ርስትን ፡ ትሰጣቸዋለህ ። ለሁሉ ፡ እንደ ፡ ቍጥራቸው ፡ መጠን ፡ ርስታቸው ፡ ይሰጣቸዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ምድሪቱ ፡ በዕጣ ፡ ትከፈላለች ፤ እንደ ፡ አባቶቻቸው ፡ ነገድ ፡ ስም ፡ ይወርሳሉ ። በብዙዎችና ፡ በጥቂቶች ፡ መካከል ፡ ርስታቸው ፡ በዕጣ ፡ ትከፈላለች ።
ከሌዋውያንም ፡ በየወገናቸው ፡ የተቈጠሩት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ከጌድሶን ፡ የጌድሶናውያን ፡ ወገን ÷ ከቀዓት ፡ የቀዓታውያን ፡ ወገን ÷ ከሜራሪ ፡ የሜራራውያን ፡ ወገን ። እነዚህ ፡ የሌዊ ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ የሊብናውያን ፡ ወገን ÷ የኬብሮናውያን ፡ ወገን ÷ የሞሖላውያን ፡ ወገን ÷ የሙሳውያን ፡ ወገን ÷ የቆሬያውያን ፡ ወገን ። ቀዓት ፡ እንበረምን ፡ ወለደ ። የእንበረም ፡ ሚስት ፡ ስም ፡ ዮካብድ ፡ ነበረ ። እርስዋ ፡ በግብፅ ፡ ከሌዊ ፡ የተወለደች ፡ የሌዊ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ፤ ለእንበረምም ፡ አሮንንና ፡ ሙሴን ፡ እኅታቸውንም ፡ ማርያምን ፡ ወለደችለት ። ለአሮንም ፡ ናዳብ ÷ አብዩድ ÷ አልዓዛር ÷ ኢታምር ፡ ተወለዱለት ።

በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ሴላ ፡ እሳት ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ ናዳብና ፡ አብዩድ ፡ ሞቱ ። ከእንድ ፡ ወርም ፡ ጀምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉ ፡ ወንዶች ፡ ሁሉ ፡ ከእነርሱ ፡ የተቈጠሩ ፡ ሀያ ፡ ሦስት ፡ ሺህ ፡ ነበሩ ። ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ርስት ፡ አልተሰጣቸውምና ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ አልተቈጠሩም ።
በሞዓብ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ በዮርዳኖስ ፡ አጠገብ ፡ በኢያሪኮ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሲቈጥሩ ÷ ሙሴና ፡ ካህኑ ፡ አልዓዛር ፡ የቈጠሩአቸው ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሙሴና ፡ ካህኑ ፡ አሮን ፡ በሲና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በቈጠሩአቸው ፡ ጊዜ ፡ ከነበሩት ፡ ከእነዚያ ፡ መካከል ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ አልነበረም ። እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፦ በእውነት ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ይሞታሉ ፡ ብሎ ፡ ተናግሮ ፡ አልና ። ከዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ከካሌብ ፡ ከነዋም ፡ ልጅ ፡ ከኢያሱ ፡ በቀር ፡ ከእነርሱ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ስንኳ ፡ አልቀረም ።

ምዕራፍ ፡ ፳፯ ።

ከዮሴፍ ፡ ልጅ ፡ ከምናሴ ፡ ወገኖች ÷ የምናሴ ፡ ልጅ ፡ የማኪር ፡ ልጅ ፡ የገለዓድ ፡ ልጅ ፡ የአፌር ፡ ልጅ ፡ የሰለጰዳድ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ቀረቡ ፡ የእነዚህም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ስም ፡ ማህለህ ÷ ኑዓ ÷ ዔግላ ÷ ሚልካ ÷ ቲርጻ ፡ ነበረ ። በመገናኛውም ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ አጠገብ ፡ በሙሴና ፡ በካህኑ ፡ በአልዓዛር ፡ በአለቆቹም ፡ በማኅበሩም ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ ቆመው ፦ አባታችን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሞተ ፤ በራሱ ፡ ኃጢአት ፡ ሞተ ፡ እንጂ ፡ ከቆሬ ፡ ጋር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ በተሰበሰበ ፡ ወገን ፡ መካከል ፡ አልነበረም ፤ ወንዶችም ፡ ልጆች ፡ አልነበሩትም ። ወንድ ፡ ልጅስ ፡ በይኖረው ፡ የአባታችን ፡ ስም ፡ ከወገኑ ፡ መካከል ፡ ለምን ፡ ይጠፋል ? በአባታችን ፡ ወንድሞች ፡ መካከል ፡ ርስትን ፡ ስጠን ፡ አሉ ። ሙሴም ፡ ነገራቸውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አቀረበ ።
እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦ የሰለጰዳድ ፡ ልጆች ፡ እውነት ፡ ተናግረዋል ፤ በአባታቸው ፡ ወንድሞች ፡ መካከል ፡ የርስት ፡ ድርሻ ፡ ስጣቸው ፡ የአባታቸውን ፡ ርስት ፡ ለእነርሱ ፡ አሳልፈህ ፡ ስጥ ። ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ንገራቸው ፦ ሰው ፡ ቢሞት ፡ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ባይኖረው ÷ ርስቱ ፡ ለሴት ፡ ልጁ ፡ ይሰፍ ፡ ሴት ፡ ልጅም ፡ ባትኖረው ፡ ርስቱን ፡ ለወንድሞቹ ፡ ስጡ ፤ ወንድሞችም ፡ ባይኖሩት ፡ ርስቱን ፡ ለአባቱ ፡ ወንድሞች ፡ ስጡ ፤ የአባቱም ፡ ወንድሞች ፡ ባይኖሩት ፡ ከወገኑ ፡ ለቀረበ ፡ ዘመድ ፡ ርስቱን ፡ ስጡ ፤ እርሱም ፡ ይውረሰው ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሥርዓትና ፡ ፍርድ ፡ ይሁን ።
እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ ወደ ፡ ዚህ ፡ ወደ ፡ ዓባሪም ፡ ተራራ ፡ ውጣ ÷ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ የሰጠኋትን ፡ ምድር ፡ እይ ፤ በየሃትም ፡ ጊዜ ፡ ወንድምህ ፡ አሮን ፡ እንደ ፡ ተከማቸ ፡ እንት ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ወገንህ ፡ ትከማቻለህ ። እናንተ ፡ በጺን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በማኅበሩ ፡ ጠብ ፡ በቃሴ ፡ ላይ ፡ ወምግቻኋልና ÷ በእነርሱም ፡ ፊት ፡ በውኃው ፡ ዘንድ ፡ አልቀደሳችሁኝምና ። ይህም ፡ በጺን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በቃዴስ ፡ ያለው ፡ የመሪባ ፡ ውኃ ፡ ነው ።
ሙሴም ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦ የእግዚአብሔር ፡ ማኅበር ፡ እረኛ ፡ እንደሌለው ፡ መንጋ ፡ እንዳይሆን ÷ በፊታቸው ፡ የሚወጣውን ፡ በፊታቸውም ፡ የሚገባውን ፡ የሚያስወጣቸውንም ፡ የሚያስገባቸውንም ፡ ሰው ፡ የሥጋ ፡ ሁሉ ፡ መንፈስ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ በማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ይሹመው ። እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ መንፈስ ፡ ያለበትን ፡ ሰው ፡ የነዌን ፡ ልጅ ፡ ኢያሱን ፡ ወስደህ ፡ እጅህን ፡ በላዩ ፡ ጫንበት ፤ በካህኑ ፡ በአልዓዛርና ፡ በማኅበሩ ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ አቁመው ÷ እነርሱም ፡ እያዩ ፡ እዘዘው ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ እንዲታዘዙት ፡ ከክብርህ ፡ አኑርበት ። በካህኑም ፡ በአልዓዛር ፡ ፊት ፡ ይቁም ፡ እርሱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በኡሪም ፡ ፍርድ ፡ ይጠይቅለት ፡ እርሱ ፡ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ በቃሉ ፡ ይውጡ ÷ በቃሉም ፡ ይግቡ ። ሙሴም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ ፤ ኢያሱንም ፡ ወስዶ ፡ በካህኑ ፡ በአልዓዛርና ፡ በማኅበሩ ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ አቆመው ፡ እግዚአብሔርም ፡ በሙሴ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ÷ እጁን ፡ በላዩ ፡ ጫነበት ÷ አዘዘውም ።

ምዕራፍ ፡ ፳፰ ።

እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ አዘዛቸው ፦ መብሌን ፡ ለእኔ ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲሆን ፡ በአሳት ፡ የተደረገውን ፡ ቍርባኔን ፡ መበዩን ፡ በየጊዜው ፡ ታቀርቡልኝ ፡ ዘንድ ፡ ጠብቁ ። እንዲህም ፡ ብላቸው ፦ በአሳት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የምታቀርቡት ፡ ቍርባን ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ለዘወትር ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ ሁለት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ታቀርባላችሁ ። አንዱን ፡ ጠቦት ፡ በማለዳ ÷ ሌላውንም ፡ ጠቦት ፡ በማታ ፡ አቅርብ ። ለአህያም ፡ ቍርባን ፡ የኢኑ ፡ መስፈሪያ ፡ አራተኛ ፡ እጅ ፡ በሆነ ፡ ተወቅጦ ፡ በተጠለለ ፡ ዘይት ፡ የተለወሰ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ አሥረኛ ፡ እጅ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ ታቀርባለህ ። በእሳት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲሆን ፡ የቀረበ ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ የተሠራ ፡ ለዘወትር ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ነው ። የመጠጡ ፡ ቍርባን ፡ ለአንድ ፡ ጠቦት ፡ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ አራ

ተኛው ፡ እጅ ፡ ነው ፤ በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ ለመጠጥ ፡ ቀርበን ፡ መጠጥ ፡ ታፈ
ስሳለህ ። ሌላውንም ፡ ጠቦት ፡ በማታ ፡ ጊዜ ፡ ፹ሀ
ታቀርባለህ ፡ የእህሉን ፡ ቀርበንና ፡ የመጠጡን ፡
ቀርበን ፡ በማለዳ ፡ እንዳቀረብህ ፡ በእሳት ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲሆን ፡ ታቀ
ርበዋለህ ።

፹ሀ ፡ በሰንበትም ፡ ቀን ፡ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡
ሁለት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦ
ች ፥ ለእህልም ፡ ቀርበን ፡ በዘይት ፡ የተለ
ወሰ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከአሥር ፡ እጅ ፡ ሁለት ፡
እጅ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፥ የመጠጡንም ፡ ቀርር
ፀ ፡ ታቀርባለችሁ ። በዘወትር ፡ ከሚቃጠለው ፡
መሥዋዕት ፡ ሌላ ፥ ከመጠጡም ፡ ቀርበን ፡ ሌላ ፥
በየሰንበቱ ፡ ሁሉ ፡ የምታቀርቡት ፡ የሚቃጠ
ለው ፡ መሥዋዕት ፡ ይህ ፡ ነው ።

ፀ፩ ፡ በወሩም ፡ መባቻ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃ
ጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ታቀርባላችሁ ፡ ሁለት ፡
ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ ነውርም ፡
የሌለባቸውን ፡ ሰባት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡
ፀ፪ ፡ የበግ ፡ ጠቦች ፥ ለእያንዳንዱም ፡ ወይፈን ፡
ለእህል ፡ ቀርበን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ ከመስ
ፈሪያው ፡ ከአሥር ፡ እጅ ፡ ሦስት ፡ እጅ ፡ መል
ካም ፡ ዱቄት ፥ ለአውራው ፡ በግም ፡ ለእህል ፡
ቀርበን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ ከመስፈሪያው ፡
ከአሥር ፡ እጅ ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፥
ፀ፫ ፡ ለእያንዳንዱም ፡ ጠቦት ፡ ለእህል ፡ ቀርበን ፡ በዘ
ይት ፡ የተለወሰ ፡ ከመስፈሪያው ፡ አሥረኛ ፡ እጅ ፡
መልካም ፡ ዱቄት ፥ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲሆን ፡
ፀ፬ ፡ በእሳት ፡ ታቀርባላችሁ ። የመጠጥ ፡ ቀርበና
ቸውም ፡ ለእንጀ ፡ ወይፈን ፡ የኢን ፡ ግማሽ ፥
ለአውራው ፡ በግም ፡ የኢን ፡ ሢሶ ፥ ለእንዳም ፡
ጠቦት ፡ የኢን ፡ አራተኛ ፡ እጅ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡
ይሆናል ፤ ይህ ፡ ለዓመቱ ፡ የወር ፡ መባቻ ፡ ሁሉ ፡
ፀ፭ ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ነው ። ለእግዚአብሔ
ርም ፡ ለኃጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡
ፍየል ፡ ታቀርባላችሁ ፤ በዘወትር ፡ ከሚቃጠ
ለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከመጠጡ ፡ ቀርበን ፡ ሌላ ፡
ይቀርበል ።

ፀ፮ ፡ በመጀመሪያው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በአሥራ ፡
አራተኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፋሲካ ፡
ፀ፯ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ ወር ፡ በአሥራ ፡ አምስተኛው ፡
ቀን ፡ በዓል ፡ ይሆናል ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ቂጣ ፡ እን
ፀ፰ ፡ ጀራ ፡ ትበላላችሁ ። በመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ የተ
ቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይሆናል ፤ በእርሱም ፡ የተግባ
ፀ፱ ፡ ርን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አትሥሩበት ። በእሳትም ፡
የተደረገውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠለ
ውን ፡ መሥዋዕት ፡ ታቀርባላችሁ ፡ ሁለት ፡
ወይፈኖች ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ ሰባት ፡ የአ
ንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦች ፤ ነውር ፡
ፀ፡ የሌለባቸው ፡ ይሁኑላችሁ ። የእህል ፡ ቀርበና
ቸውንም ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፥
ለአንድ ፡ ወይፈን ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከአሥር ፡
እጅ ፡ ሦስት ፡ እጅ ፥ ለአውራውም ፡ በግ ፡ ከመ
ስፈሪያው ፡ ከአሥር ፡ እጅ ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ ለሰ ፹ፀ፡
ባቱም ፡ ጠቦቶች ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ጠቦት ፡ ከመ
ስፈሪያው ፡ አሥረኛ ፡ እጅ ፡ ታቀርባላችሁ ።
ማስተስረያ ፡ የሚሆንላችሁን ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፹ፁ፡
ፍየል ፡ ለኃጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ታቀርባላ
ችሁ ። ግልጽ ፡ ከሚቀርበው ፡ በዘወትር ፡ ከሚ ፹ፂ፡
ቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ሌላ ፡ እነዚህን ፡ ታቀርባ
ላችሁ ። ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እን ፹ፃ፡
ዲሆን ፡ በእሳት ፡ የሚደረገውን ፡ የቀርበቡን ፡
መብል ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በየዕለቱ ፡ እንዲሁ ፡ ታቀ
ርባላችሁ ፤ በዘወትር ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥ
ዋዕትና ፡ ከመጠጡ ፡ ቀርበን ፡ ሌላ ፡ ይቀርበል ።
በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይሁ ፹ፄ፡
ንላችሁ ፤ የተግባርን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አትሥሩ
በት ።

ደግሞ ፡ በበኩራት ፡ ቀን ፡ ከሰባቱ ፡ ሱባዔ ፡ ፹ፅ፡
በዓላችሁ ፡ አዲሱን ፡ የእህል ፡ ቀርበን ፡ ለእግዚአ
ብሔር ፡ በቀረባችሁ ፡ ጊዜ ፥ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡
ይሆንላችኋል ፤ የተግባርን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አት
ሥሩበት ። ለእግዚአብሔርም ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ ፹ፆ፡
እንዲሆን ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ታቀር
ባላችሁ ፡ ሁለት ፡ ወይፈኖች ፥ አንድ ፡ አውራ ፡
በግ ፥ ሰባት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡
ጠቦቶች ፡ ለእህል ፡ ቀርበናቸው ፡ በዘይት ፡ ፹ፈ፡
የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፥ ለእያንዳንዱ ፡
ወይፈን ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከአሥር ፡ እጅ ፡ ሦስት ፡
እጅ ፥ ለእንዳም ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ከመስፈሪያው ፡
ከአሥር ፡ እጅ ፡ ሁለት ፡ እጅ ፥ ለሰባቱም ፡ ጠቦ ፹ፈ፡
ቶች ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ጠቦት ፡ ከመስፈሪያው ፡
አሥረኛ ፡ እጅ ፡ ታቀርባላችሁ ። ማስተስረያ ፡ ፹ፉ፡
የሚሆንላችሁን ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፡ ለኃ
ጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ታቀርባላችሁ ። በዘወ ፹ፈ፡
ትር ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእህሉ ፡
ቀርበን ፡ ሌላ ፡ እነርሱንና ፡ የመጠጥ ፡ ቀርበና
ቸውን ፡ ታቀርባላችሁ ፤ ነውርም ፡ የሌለባቸው ፡
ይሁኑ ።

ምዕራፍ ፡ ፹ፀ ።

በሰባተኛውም ፡ ወር ፡ ከወሩ ፡ በመጀመሪያ ፡ ፩፡
ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይሁንላችሁ ፡ የተግባ
ርን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አትሥሩበት ፡ መለከቶች ፡
የሚነፉበት ፡ ቀን ፡ ነው ። ለእግዚአብሔር ፡ ፪፡
ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲሆን ፡ የሚቃጠለውን ፡
መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡
በግ ፥ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ ሰባት ፡ የአንድ ፡
ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ለእህል ፡ ፫፡
ቀርበናቸው ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡
ዱቄት ፡ ለወይፈኑ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከአሥር ፡
እጅ ፡ ሦስት ፡ እጅ ፥ ለአውራው ፡ በግ ፡ ከመስፈ
ሪያው ፡ ከአሥር ፡ እጅ ፡ ሁለት ፡ እጅ ፡ ለሰባቱ ፡ ፬፡
ጠቦቶች ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ከመስፈሪያው ፡ አሥ
ረኛ ፡ እጅ ፡ ታቀርባላችሁ ። ማስተስረያም ፡ ፫፡
የሚሆንላችሁን ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፡ ለኃ

ጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ታቀርባላችሁ ። በወሩ ፡
መባቻ ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእህሉ ፡
ቀርበን ፥ በዘወትርም ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋ
ዕትና ፡ ከእህሉ ፡ ቀርበን ፥ ከመጠጡም ፡ ቀር
ፀ ፡ ሌላ ፥ አንድ ፡ ሕጋቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲሆን ፡ በእሳት ፡ የሚቀርቡ ፡
ናቸው ።

ከዚህም ፡ ከሰባተኛው ፡ ወር ፡ በአሥረኛው ፡
ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይሁንላችሁ ፤ ሰውነታ
ችሁን ፡ አስጨንቁት ፡ ከሥራ ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡
አታድርጉ ። ለእግዚአብሔርም ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡
እንዲሆን ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፥ አንድ ፡
ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ ሰባት ፡ የአንድ ፡
ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ታቀርባላችሁ ፡
ነውር ፡ የሌለባቸውም ፡ ይሁኑ ። ለእህል ፡ ቀርር
ፀ ፡ ባናቸውም ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡
ዱቄት ፥ ለወይፈኑ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከአሥር ፡
እጅ ፡ ሦስት ፡ እጅ ፥ ለአውራው ፡ በግ ፡ ከመስፈሪ
ያው ፡ ከአሥር ፡ እጅ ፡ ሁለት ፡ እጅ ፥ ለሰ ፹ፀ፡
ባቱ ፡ ጠቦቶች ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ከመስፈሪያው ፡
አሥረኛ ፡ እጅ ፥ ለኃጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡
አውራ ፡ ፍየል ፡ አቅርቡ ። ከማያስተሰርየው ፡
ከኃጢአት ፡ መሥዋዕት ፥ በዘወትርም ፡ ከሚ
ቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእህሉ ፡ ቀርበን ፥
ከመጠጥ ፡ ቀርበናቸውም ፡ ሌላ ፡ አቅርቡት ።

ከሰባተኛውም ፡ ወር ፡ በአሥራ ፡ አምስተኛው ፡
ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይሁንላችሁ ፤ የተግባ
ርን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አትሥሩበት ፥ ሰባት ፡ ቀንም ፡
ለእግዚአብሔር ፡ በዓል ፡ አድርጉ ። ለእግዚአ
ብሔርም ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲሆን ፡ የሚቃ
ጠለውን ፡ መሥዋዕት ፥ አራ ፡ ሦስት ፡ ወይ
ፈኖች ፥ ሁለት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ አራ ፡
አራት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦ
ች ፤ አቅርቡ ፡ ነውር ፡ የሌለባቸውም ፡ ይሁኑ ።
ለእህል ፡ ቀርበናቸውም ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡
መልካም ፡ ዱቄት ፥ ለአራ ፡ ሦስት ፡ ወይፈ
ኖች ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከአሥር ፡
እጅ ፡ ሦስት ፡ እጅ ፥ ለሁለቱ ፡ አውራ ፡ በጎች ፡
ለእያንዳንዱ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከአሥር ፡ እጅ ፡
ሁለት ፡ እጅ ፥ ለአሥራ ፡ አራቱ ፡ ጠቦቶች ፡ ለእ
ያንዳንዱ ፡ ከመስፈሪያው ፡ አሥረኛ ፡ እጅ ፥
ለኃጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡
ፍየል ፡ ታቀርባላችሁ ። በዘወትር ፡ ከሚቃጠ
ለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእህሉ ፡ ቀርበን ፡ ከመ
ጠጡም ፡ ቀርበን ፡ ሌላ ፡ የሚቀርቡ ፡ ናቸው ።
በሁለተኛውም ፡ ቀን ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ወይ
ፈኖችን ፡ ሁለት ፡ አውራ ፡ በጎችን ፥ ነውር ፡
የሌለባቸው ፡ አሥራ ፡ አራት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡
ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶችን ፥ ለወይፈኖቹ ፡ ለእ
ውራ ፡ በጎቹ ፡ ለጠቦቶቹም ፡ የእህል ፡ ቀርበና
ቸውንና ፡ የመጠጥ ፡ ቀርበናቸውን ፡ እንደ ፡ ቀጥ
ራቸው ፡ መጠን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፥ ለኃጢአትም ፡ ፹ፁ፡
መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፥ በዘወ
ትር ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእህሉ ፡
ቀርበን ፡ ከመጠጡም ፡ ቀርበን ፡ ሌላ ፡ ታቀር
ባላችሁ ።

በአራተኛውም ፡ ቀን ፡ አሥር ፡ ወይፈኖች ፥ ፹ፂ፡
ሁለት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡
አሥራ ፡ አራት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡
ጠቦቶች ፥ ለወይፈኖቹና ፡ ለአውራ ፡ በጎቹ ፡ ፹ፃ፡
ለጠቦቶቹም ፡ የእህል ፡ ቀርበናቸውንና ፡ የመ
ጠጥ ፡ ቀርበናቸውን ፡ እንደ ፡ ቀጥራቸውም ፡
መጠን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፥ ለኃጢአትም ፡ መሥዋ ፹ፄ፡
ዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፥ በዘወትር ፡ ከሚ
ቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእህሉ ፡ ቀርበን ፡
ከመጠጡም ፡ ቀርበን ፡ ሌላ ፡ ታቀርባላችሁ ።

በአምስተኛውም ፡ ቀን ፡ ዘጠኝ ፡ ወይፈኖች ፥ ፹ፄ፡
ሁለት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡
አሥራ ፡ አራት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡
ጠቦቶች ፥ ለወይፈኖቹና ፡ ለአውራ ፡ በጎቹ ፡ ፹ፄ፡
ለጠቦቶቹም ፡ የእህል ፡ ቀርበናቸውንና ፡ የመ
ጠጥ ፡ ቀርበናቸውን ፡ እንደ ፡ ቀጥራቸው ፡
መጠን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፥ ለኃጢአትም ፡ መሥዋ ፹ፅ፡
ዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፥ በዘወትር ፡ ከሚ
ቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእህሉ ፡ ቀርበን ፡
ከመጠጡም ፡ ቀርበን ፡ ሌላ ፡ ታቀርባላችሁ ።

በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ወይፈ ፹ፈ፡
ኖች ፥ ሁለት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ነውር ፡ የሌለባ
ቸውን ፡ አሥራ ፡ አራት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡
ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፥ ለወይፈኖቹና ፡ ለአ ፹ፈ፡
ውራ ፡ በጎቹ ፡ ለጠቦቶቹም ፡ የእህል ፡ ቀርበናቸ
ውንና ፡ የመጠጥ ፡ ቀርበናቸውን ፡ እንደ ፡ ቀጥ
ራቸው ፡ መጠን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፥ ለኃጢአትም ፡ ፹ፉ፡
መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፥ በዘወ
ትር ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእህሉ ፡
ቀርበን ፡ ከመጠጡም ፡ ቀርበን ፡ ሌላ ፡ ታቀር
ባላችሁ ።

በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ሰባት ፡ ወይፈኖች ፥ ፹ፈ፡
ሁለት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡
አሥራ ፡ አራት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡
ጠቦቶች ፥ ለወይፈኖቹና ፡ ለአውራ ፡ በጎቹ ፡ ፹ፈ፡
ለጠቦቶቹም ፡ የእህል ፡ ቀርበናቸውንና ፡ የመ
ጠጥ ፡ ቀርበናቸውን ፡ እንደ ፡ ቀጥራቸው ፡
መጠን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፥ ለኃጢአትም ፡ መሥዋ ፹ፀ፡
ዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፥ በዘወትር ፡ ከሚ
ቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእህሉ ፡ ቀርበን ፡
ከመጠጡም ፡ ቀርበን ፡ ሌላ ፡ ታቀርባላችሁ ።

፴፩ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡
ይሁንላችሁ ፤ የተግባርን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አት
፴፪ ሥሩበት ። ለእግዚአብሔርም ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡
እንዲሆን ፡ በእሳት ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋ
ዕት ÷ አንድ ፡ ወይፈን ÷ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ÷
ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ ሰባት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡
፴፫ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ታቀርባላችሁ ። የእ
ህል ፡ ቍርባናቸውና ፡ የመጠጥ ፡ ቍርባናቸው ፡
ለወይፈኑ ፡ ለአውራውም ፡ በግ ፡ ለጠቦቶቹም ፡
እንደ ፡ ቍጥራቸው ፡ መጠን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ ይሆ
፴፬ ናሉ ። ለኃጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡
አውራ ፡ ፍየል ፡ ታቀርባላችሁ ፡ በዘወትር ፡ ከሚ
ቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእህሉ ፡ ቍርባን ፡ ከመ
ጠጡም ፡ ቍርባን ፡ ሌላ ፡ የሚቀርቡ ፡ ናቸው ።
፴፭ እነዚህንም ፤ ከስእለታችሁና ፡ በፈቃዳችሁ ፡
ከምታመጡት ፡ ሌላ ÷ ለሚቃጠል ፡ መሥዋ
ዕት ÷ ለእህልም ፡ ለመጠጥም ፡ ቍርባን ÷ ለደኅ
ንነትም ፡ መሥዋዕታችሁ ፡ በበዓላችሁ ፡ ጊዜ ፡
፴፮ ለእግዚአብሔር ፡ አቅርቡ ። ሙሴም ፡ ለእስራ
ኤል ፡ ልጆች ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ያዘዘ
ውን ፡ ሁሉ ፡ ነገራቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፴ ።

፩ ሙሴም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ነገራቸት ፡ አለ
ቆች ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፡ — እግዚ
፪ አብሔር ፡ ያዘዘው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ። ሰው ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ስእለት ፡ ቢሳል ÷ ወይም ፡
ራሱን ፡ በመሐላ ፡ ቢያስር ÷ ቃሉን ፡ አይሰበር ፤
፫ ከአፉ ፡ እንደ ፡ ወጣው ፡ ሁሉ ፡ ያድርግ ። ሴትም ፡
ደግሞ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስእለት ፡ ብትሳል ÷
እርስዋም ፡ በአባትዋ ፡ ቤት ፡ ሳለች ፡ በብላቴን
ነትዋ ፡ ጊዜ ፡ ራስዋን ፡ በመሐላ ፡ ብታስር ÷
፬ አባትዋም ፡ ራስዋን ፡ ያሰረችበትን ፡ መሐላ ፡ ስእ
ለትዋንም ፡ ቢሰማ ÷ አባትዋም ፡ ዝም ፡ ቢላት ÷
ስእለትዋ ፡ ሁሉ ፡ ይጸናል ÷ ራስዋንም ፡ ያሰረ
፭ ችበት ፡ መሐላ ፡ ሁሉ ፡ ይጸናል ። አባትዋ ፡
ግን ፡ በሰማበት ፡ ቀን ፡ ቢከለክላት ÷ ስእለትዋ ፡
ራስዋንም ፡ ያሰረችበት ፡ መሐላዋ ፡ አይጸኑም ፡
አባትዋ ፡ ከልክሎአታልና ፡ እግዚአብሔር ፡
ይቅር ፡ ይላታል ።
፮ በተሳለችም ፡ ጊዜ ፡ ራስዋንም ፡ በመሐላ ፡
ያሰረችበት ፡ ነገር ፡ ከእናቷዋ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ባል ፡
፯ ያገባች ፡ ብትሆን ፤ ባልዋም ፡ ቢሰማ ፡ በሰማ
በትም ፡ ቀን ፡ ዝም ፡ ቢላት ፡ ስእለትዋ ፡ ይጸ
ናል ÷ ራስዋንም ፡ ያሰረችበት ፡ መሐላ ፡ ይጸ
፰ ናል ። ባልዋ ፡ ግን ፡ በሰማበት ፡ ቀን ፡ ቢከለክ
ላት ፡ በእርስዋ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ስእለትዋን ፡
ራስዋንም ፡ በመሐላ ፡ ያሰረችበትን ፡ የአፍዋን ፡
ነገር ፡ ከንቱ ፡ ያደርገዋል ፡ እግዚአብሔርም ፡
ይቅር ፡ ይላታል ።
፱ ባልዋ ፡ የሞተባት ፡ ወይም ፡ የተፋታች ፡ ግን ፡
ስእለትዋ ፡ ራስዋንም ፡ ያሰረችበት ፡ መሐላ ፡
ይጸኑባታል ። ሴትም ፡ በባልዋ ፡ ቤት ፡ ሳለች ፡
ብትሳል ÷ ወይም ፡ ራስዋን ፡ በመሐላ ፡ ብታስር ÷
፱ በልዋም ፡ ሰምቶ ፡ ዝም ፡ ቢላት ፡ ባይከለክላ
ትም ÷ ስእለትዋ ፡ ሁሉ ፡ ራስዋንም ፡ ያሰረች
በት ፡ መሐላ ፡ ሁሉ ፡ ይጸናል ። ባልዋ ፡ ግን ፡
፱ በሰማበት ፡ ቀን ፡ ከንቱ ፡ ቢያደርገው ÷ ስለ ፡ ስእ
ለትዋ ፡ ወይም ፡ ራስዋን ፡ ስላሰረችበት ፡ መሐላ ፡
ከአፍዋ ፡ የወጣው ፡ ነገር ፡ አይጸናም ፤ ባልዋ ፡
ከንቱ ፡ አድርጎታል ፡ እግዚአብሔርም ፡ ይቅር ፡
ይላታል ።
፲ ስእለትዋን ፡ ሁሉ ፡ ነፍስዋንም ፡ የሚያዋርደ
ውን ፡ መሐላ ፡ ሁሉ ፡ ባልዋ ፡ ያጸናዋል ÷ ባል
ዋም ፡ ከንቱ ፡ ያደርገዋል ። ባልዋ ፡ ግን ፡ በየ
፲፩ ዕለቱ ፡ ዝም ፡ ቢላት ÷ ስእለትዋን ፡ ሁሉ ፡ በእር
ስዋም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መሐላ ፡ ሁሉ ፡ አጽን
ቶታል ፡ በሰማበት ፡ ቀን ፡ ዝም ፡ ብሎአታልና ፡
፲፪ አጽንቶታል ። ከሰማው ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ከንቱ ፡
ቢያደርገው ፡ ኃጢአትዋን ፡ ይሸከማል ። እር
፲፫ ስዋ ፡ በብላቴንነትዋ ፡ ጊዜ ፡ በአባትዋ ፡ ቤት ፡
ሳለች ፡ በአባትና ፡ በልጂቱ ፡ መካከል ÷ ወይም ፡
በባልና ፡ በሚስት ፡ መካከል ፡ ይሆን ፤ ዘንድ ፡
እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ያዘዘው ፡ ሥርዓት ፡
ይህ ፡ ነው ።

ምዕራፍ ፡ ፴፩ ።

፩ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
፪ ተናገረው ፡ — ስለ ፡ አስራኤል ፡ ልጆች ፡ በቀል ፡
ምድያማውያንን ፡ ተበቀል ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡
ወደ ፡ ወገኖችህ ፡ ትከማቻለህ ። ሙሴም ፡ ሕዝ
፫ ቡን ፡ — ከእናንተ ፡ መካከል ፡ ሰዎች ፡ ሰጠናት ፡
ይሰለፉ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቀል ፡ ምድያ
ምን ፡ ይበቀሉ ፡ ዘንድ ፡ በምድያም ፡ ላይ ፡
፬ ይሂዱ ። ከእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ ሁሉ ፡ ከየነገዱ ፡
አንድ ፡ ሺህ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ስደዱ ፡
፭ ብሎ ፡ ተናገራቸው ። ከእስራኤልም ፡ አእላ
ፋት ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ÷ ከየነገዱ ፡ አንድ ፡
አንድ ፡ ሺህ ÷ ለጦርነት ፡ የተሰለፉ ፡ ሰዎች ፡
ተሰጡ ። ሙሴም ፡ ከየነገዱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡
፮ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ሰደደ ፤ እነርሱንና ፡ የካህኑን ፡
የአልዓዛርን ፡ ልጅ ፡ ፊንሐስን ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡
ሰደዳቸው ፤ የመቅደሱንም ፡ ዕቃ ፡ የሚነፋው
ንም ፡ መለከት ፡ በእጁ ፡ ሰጠው ። እግዚአብ
፯ ሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘ ፡ ከምድያም ፡ ጋር ፡
ተዋጉ ፤ ወንዶችንም ፡ ሁሉ ፡ ገደሉ ። ከተገ
፰ ደሉትም ፡ ጋር ፡ የምድያምን ፡ ነገሥታት ፡ ገደ
ሉአቸው ፡ አምስቱም ፡ የምድያም ፡ ነገሥታት ፡
ኢዊ ፡ ሮቆም ፡ ሱር ÷ ሑር ÷ ሬባ ፡ ነበሩ ። የቢ
ዖርንም ፡ ልጅ ፡ በለዓምን ፡ ደግሞ ፡ በሰይፍ ፡
ገደሉት ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ የምድያ
፱ ምን ፡ ሴቶችና ፡ ልጆቻቸውን ፡ ማረኩ ፤ እንስ
ሶቻቸውንና ፡ መንጎቻቸውንም ፡ ዕቃቸውንም ፡
ሁሉ ፡ በዘበዙ ። የተቀመጡባቸውን ፡ ከተሞ
፲ ቻቸውን ፡ ሁሉ ፡ ሰፈሮቻቸውንም ፡ ሁሉ ፡ በእ
ሳት ፡ አቃጠሉ ። የሰውንና ፡ የእንስሳን ፡ ምር
፲፩ ኮና ፡ ብዝበዛ ፡ ሁሉ ፡ ወሰዱ ። የማረኩአቸው
፲፪ ንም ፡ ሰዎች ፡ ምርኮውንና ፡ ብዝበዛውን ፡ ወደ ፡

ሙሴና ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ወደ ፡ አልዓዛር ፡ ወደ ፡
አስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ÷ በዮርዳኖስም ፡
አጠገብ ፡ በኢያሪኮ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በሞዓብ ፡
ሜዳ ፡ ወዳለው ፡ ሰፈር ፡ አመጡ ።
ሙሴና ፡ ካህኑ ፡ አልዓዛርም ፡ የማኅበሩም ፡
አለቆች ፡ ሁሉ ፡ ከሰፈሩ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ሊገና
ኙአቸው ፡ ወጡ ። ሙሴም ፡ ከዘመቻ ፡ በተመለ
ሱት ፡ በጭፍራ ፡ አለቆች ÷ በሻለቆችና ፡ በመቶ ፡
አለቆች ፡ ላይ ፡ ተቈጣ ። ሙሴም ፡ አላቸው ፡ —
በውኑ ፡ ሴቶችን ፡ ሁሉ ፡ አዳናችኋቸውን ?
እነሆ ÷ እነዚህ ፡ በፈጐር ፡ ምክንያት ፡ በበለዓም ፡
ምክር ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይበድሉ ፡ ዘንድ ፡
ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዕንቅፋት ፡ ሆኑ ፤ ስለዚ
ህም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ መቅሠ
ፍት ፡ ሆነ ። አሁን ፡ እንግዲህ ፡ ከልጆቹ ፡ ወን
ዱን ፡ ሁሉ ፡ ግደሉ ÷ ወንድንም ፡ በመኝታ ፡
የሚያውቁትን ፡ ሴቶች ፡ ሁሉ ፡ ግደሉ ። ወንድን ፡
የማያውቁትን ፡ ሴቶች ፡ ልጆችን ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡
ለራሳችሁ ፡ አድኑአቸው ። ከሰፈሩም ፡ ውጭ ፡
ሰባት ፡ ቀን ፡ ስፈሩ ፤ ሰውን ፡ የገደለ ፡ ሁሉ ፡
የተገደለውንም ፡ የዳሰሰ ፡ ሁሉ ÷ እናንተ ፡ የማ
ረከችኋቸውም ፡ በሦስተኛውና ፡ በሰባተኛው ፡
ቀን ፡ ሰውነታችሁን ፡ ንጹሕ ፡ አድርጉ ። ልብ
ስንም ÷ ከቁርበትም ፡ የተዘጋጀውን ፡ ሁሉ ÷
ከፍየልም ፡ ጠጉር ፡ ከእንጨትም ፡ የተሠራ
ውን ፡ ሁሉ ፡ ንጹሕ ፡ አድርጉ ።
ካህኑም ፡ አልዓዛር ፡ ከሰልፍ ፡ የመጡትን ፡
ሰዎች ፡ አላቸው ፡ — እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡
ያዘዘው ፡ የሕጉ ፡ ሥርዓት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ወርቁ
ንና ፡ ብሩን ÷ ናስንም ÷ ብረቱንም ÷ ቆርቆሮው
ንም ÷ እረሳንም ÷ በእሳት ፡ ለማለፍ ፡ የሚችለ
ውን ፡ ሁሉ ፡ በእሳት ፡ ታሳልፉታላችሁ ÷ ንጹ
ሕም ፡ ይሆናል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በማንጻት ፡ ውኃ ፡
ደግሞ ፡ ይጠራል ። በእሳትም ፡ ለማለፍ ፡ የማ
ይችለውን ፡ በውኃ ፡ ታሳልፉታላችሁ ። በሰባ
ተኛውም ፡ ቀን ፡ ልብሳችሁን ፡ እጠቡ ÷ ንጹ
ሕም ፡ ትሆናላችሁ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡
ሰፈሩ ፡ ትቀርባላችሁ ።
እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
ተናገረው ፡ — አንተና ፡ ካህኑ ፡ አልዓዛር ፡ የማ
ኅበሩም ፡ አባቶች ፡ አለቆች ፡ የተማረኩትን ፡
ሰውና ፡ እንስሳ ፡ ቍጠሩ ። ምርኮውንም ፡ በተ
ዋጉትና ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ በወጡት ÷ በማኅበ
ሩም ፡ ሁሉ ፡ መካከል ፡ አስተካክለህ ፡ ክፈል ።
ከእነዚያም ፡ ከተዋጉት ፡ ወደ ፡ ሰልፍም ፡ ከወ
ጡት ፡ ሰልፈኞች ፡ ዘንድ ÷ ከሰዎችም ፡ ከበሬ
ዎችም ፡ ከአህዮችም ፡ ከመንጎችም ፡ ከአም
ስት ፡ መቶ ፡ አንድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ግብር ፡
አውጣ ። ከድርሻቸው ፡ ወስደህ ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ለማንሣት ፡ ቍርባን ፡ ለካህኑ ፡ ለአልዓ
ዛር ፡ ስጠው ። ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ድርሻ ፡
ከሰዎች ፡ ከበሬዎችም ፡ ከአህዮችም ፡ ከመንጎ
ችም ፡ ከከብቶችም ፡ ሁሉ ፡ ከአምሳ ፡ አንድ ፡
ትወስዳለህ ÷ የእግዚአብሔርንም ፡ ማደሪያ ፡
አገልጋሉት ፡ ለሚጠብቁ ፡ ለሌዋውያን ፡ ትሰጣ
ለህ ። ሙሴና ፡ ካህኑ ፡ አልዓዛርም ፡ እግዚአ ፴፩
ብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረጉ ።
ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የወጡ ፡ ሰዎችም ፡ ከወሰዱት ፡ ፴፪
ብዝበዛ ፡ ያስቀሩት ፡ ምርኮ ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፤
ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ በጎች ÷
ሰባ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ በሬዎች ÷ ስድሳ ፡ አንድ ፡ ፴፫ ፴፬
ሺህ ፡ አህዮች ÷ ወንድ ፡ ከማያውቁ ፡ ሴቶችም ፡ ፴፭
ሠላሳ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ነፍስ ። በዘመቻም ፡ ለነበሩ ፡ ፴፮
ሰዎች ፡ ድርሻ ፡ የሆነ ፡ እኩሌታ ፡ ከበግ ፡ ሦስት ፡
መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰባት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡
በጎች ፡ ነበረ ÷ ከበጎችም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፴፯
ግብር ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ አምስት ፡ ነበረ ። በሬ ፴፰
ዎችም ፡ ሠላሳ ፡ ስድስት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡
ነበሩ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ግብር ፡ ሰባ ፡ ሁለት ፡
ነበረ ። አህዮቹም ፡ ሠላሳ ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ ፴፱
መቶ ፡ ነበሩ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ግብር ፡ ስድሳ ፡
አንድ ፡ ነበረ ። ሰዎቹም ፡ አሥራ ፡ ስድስት ፡ ፵
ሺህ ፡ ነበሩ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ግብር ፡ ሠላሳ ፡
ሁለት ፡ ነበረ ። እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እን ፵፩
ዳዘዘው ፡ ሙሴ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለማንሣት ፡
ቍርባን ፡ የሆነውን ፡ ግብር ፡ ለካህኑ ፡ ለአል
ዓዛር ፡ ሰጠው ።
ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እኩሌታም ÷ ወደ ፡ ፵፪
ሰልፍ ፡ ከወጡት ፡ ወንዶች ፡ ላይ ፡ ሙሴ ፡ የለ
የው ÷ የማኅበሩ ፡ ድርሻ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ፵፫
ሰባት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ በጎች ÷ ሠላሳ ፡ ፵፬
ስድስት ፡ ሺህ ፡ በሬዎች ÷ ሠላሳ ፡ ሺህ ፡ አም ፵፭
ስት ፡ መቶ ፡ አህዮች ÷ አሥራ ፡ ስድስት ፡ ሺህ ፡ ፵፮
ሰዎች ፡ ነበሩ ። ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ድርሻ ፡ ፵፯
ሙሴ ፡ ከሰውና ፡ ከእንስሳ ፡ ከአምሳ ፡ አንድ ፡
ወሰደ ÷ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ማደሪያ ፡ አገልጋሉት ፡ ለሚ
ጠብቁ ፡ ሌዋውያን ፡ ሰጠ ።
በሠራዊት ፡ አለላፋት ፡ ላይ ፡ የተሾሙት ፡ ፵፰
አለቆች ÷ ሻለቆችና ፡ የመቶ ፡ አለቆች ÷ ወደ ፡
ሙሴ ፡ ቀረቡ ÷ ሙሴንም ፡ — እኛ ፡ ባሪያዎችህ ፡ ፵፱
ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የወጡትን ፡ ከእጃችን ፡ በታች ፡
ያሉትን ፡ ቈጠርን ÷ ከእኛም ፡ አንድ ፡ አልጐ
ደለም ። ሰውም ፡ ሁሉ ፡ ካገኘው ፡ ከወርቅ ፡ ፶
ዕቃ ÷ ከእግር ፡ አልበም ÷ ከአምባርም ÷ ከቀለ
በትም ÷ ከጕትቻም ÷ ከድሪውም ፡ ለነፍሳችን ፡
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያስተሰርይልን ፡ ዘንድ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ መባ ፡ አምጥተናል ፡ አሉት ።
ሙሴና ፡ ካህኑ ፡ አልዓዛርም ፡ ወርቁንና ፡ በልዩ ፡ ፶፩
ልዩ ፡ የተሠራውን ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ከእጃቸው ፡
ተቀበሉ ። ሻለቆችም ፡ የመቶ ፡ አለቆችም ፡ ፶፪
ለእግዚአብሔር ፡ ለማንሣት ፡ ቍርባን ፡ ያቀረ
ቡት ፡ ወርቅ ፡ ሁሉ ፡ አሥራ ፡ ስድስት ፡ ሺህ ፡
ሰባት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ። ወደ ፡ ፶፫
ሰልፍ ፡ የወጡ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ከምርኮአቸው ፡
ለራሳቸው ፡ ወሰዱ ። ሙሴና ፡ ካህኑ ፡ አልዓዛ ፡ ፶፬
ርም ፡ ወርቁን ፡ ከሻለቆችና ፡ ከመቶ ፡ አለቆች ፡
ወስደው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለእስራኤል ፡

ልጆች ፡ መታሰቢያ ፡ ወደ ፡ መገናኛው ፡ ድን
ኳን ፡ አገቡት ።

ምዕራፍ ፡ ፴፪ ።

፩ የሮቤልና ፡ የጋድ ፡ ልጆችም ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡
እንስሶች ፡ ነበሩአቸው ፤ እነሆም ፡ የኢያዜር ፡
ምድርና ፡ የገለዓድ ፡ ምድር ፡ ለእንስሶች ፡ የተ
፪ መቸ ፡ ስፍራ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በዩ ፡ ጊዜ ፡ የጋ
ድና ፡ የሮቤል ፡ ልጆች ፡ መጥተው ፡ ሙሴንና ፡
ካህኑን ፡ አልዓዛርን ፡ የማኅበሩንም ፡ አለቆች ፡
፫-፴፫ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ተናገሩአቸው ፦ እግዚአብ
ሔር ፡ በእስራኤል ፡ ማኅበር ፡ ፊት ፡ የመታው ፡
ምድር ፡ አማሮት ፡ ዳዘን ፡ ኢያዜር ፡ ነምራ ፡
ሐሴበን ፡ ኤልያሊ ፡ ሰብማ ፡ ናባው ፡ ባያን ፡
ለእንስሶች ፡ የተመቸ ፡ ምድር ፡ ነው ፤ ለእኛም ፡
፬ ለባሪያዎችህ ፡ እንስሶች ፡ አሉን ። እኛስ ፡ በአ
ንተ ፡ ዘንድ ፡ ሞገስን ፡ አግኝተን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
ይህን ፡ ምድር ፡ ለባሪያዎችህ ፡ ርስት ፡ አድር
ገህ ፡ ስጠን ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስም ፡ ማዶ ፡ አታሻግ
ረን ።

፭ ሙሴም ፡ ለጋድና ፡ ለሮቤል ፡ ልጆች ፡ አላ
ቸው ፦ ወንድሞቻችሁ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ሲሄዱ ፡
፮ እናንተ ፡ በዚህ ፡ ትቀመጣላችሁን ? እግዚአብ
ሔር ፡ ወደሚሰጣቸው ፡ ምድር ፡ እንዳይሻገሩ ፡
የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ልብ ፡ ለምን ፡ ታደክማ
፯ ላችሁ ? ምድሪቱን ፡ ይሰልሉ ፡ ዘንድ ፡ ከቃዴስ ፡
በርኔ ፡ በሰደድኋቸው ፡ ጊዜ ፡ አባቶቻችሁ ፡ እን
፰ ዲህ ፡ አደረጉ ። ወደ ፡ ኤሽኮልም ፡ ሸለቆ ፡
በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ ምድሪቱንም ፡ በዩ ፡ ጊዜ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ሰጣቸው ፡ ምድር ፡ እንዳይ
ገቡ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ልብ ፡ አደከሙ ።
፱ በዚያም ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ነደደ ፥
፱-፲፱ እርሱም ፦ በእውነት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈጽ
መው ፡ ከተከተሉ ፡ ከእነዚህ ፡ ከቁጥዛዊው ፡ ከዮ
ፎኒ ፡ ልጅ ፡ ከኬብሮና ፡ ከካዊ ፡ ልጅ ፡ ከኢያሱ ፡
በቀር ፥ ከግብፅ ፡ የወጡት ፡ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡
ጀምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ እኔን ፡
ፈጽመው ፡ አልተከተሉምና ፡ ለአብርሃምና ፡
ለይስሐቅ ፡ ለያዕቆብም ፡ እሰጥ ፡ ዘንድ ፡ የማል
ሁበትን ፡ ምድር ፡ አያዩም ፡ ብሎ ፡ ማለ ። የእግ
፲፫ ዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ጸና ፥
በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ያደረገ ፡ ትው
ልድ ፡ ሁሉ ፡ እስኪጠፋ ፡ ድረስ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡
፲፬ በምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ አቅበዘበዛቸው ። እነ
ሆም ፥ የእግዚአብሔርን ፡ መዓት ፡ በእስራኤል ፡
ላይ ፡ አብዝታችሁ ፡ ትጨምሩ ፡ ዘንድ ፡ እናንተ ፡
የኃጢአተኞች ፡ ትውልድ ፡ በአባቶቻችሁ ፡
፲፭ ፋንታ ፡ ቆማችኋል ። እርሱን ፡ ከመከተል ፡ ብት
መለሱ ፡ እርሱ ፡ ሕዝቡን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ደግሞ ፡
ይተዋል ፤ ይህንንም ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ታጠፋላ
ችሁ ።

፲፮ ወደ ፡ እርሱም ፡ ቀርበው ፡ አሉት ፦ በዚህ ፡
ለእንስሶቻችን ፡ በረቶች ፡ ለልጆቻችንም ፡ ከተ
፲፯ ሞች ፡ እንሠራለን ፤ እኛ ፡ ግን ፡ ለጦርነት ፡ ተዘ
ጋጅተን ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ እስከናገባቸው ፡
ድረስ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ እንሄዳለን ፤
በዚህም ፡ ምድር ፡ ስላሉ ፡ ሰዎች ፡ ልጆቻችን ፡
በተመሸጉ ፡ ከተሞች ፡ ይቀመጣሉ ። የእስራ ፲፰
ኤል ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ርስታቸውን ፡ እስኪወርሱ ፡
ድረስ ፡ ወደ ፡ ቤቶቻችን ፡ እንመለስም ፡ ከዮር ፲፱
ዳኖስ ፡ ወዲህ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ርስታችን ፡
ደርሰናልና ፡ እኛ ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ወደዚያ ፡
ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ርስት ፡ አንወርስም ።

፳ ሙሴም ፡ አላቸው ፦ ይህንስ ፡ ነገር ፡ ብታደ
ርጉ ፥ ተዘጋጅታችሁም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡
ወደ ፡ ሰልፍ ፡ ብትሄዱ ፥ እርሱም ፡ ጠላቶቹን ፡ ፳፩
ከፊቱ ፡ እስከያሳድድ ፡ ድረስ ፡ ምድሪቱም ፡
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ድል ፡ እስከተሠራ ፡
ድረስ ፡ ከእናንተ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ጋሻ ፡ ጦሩን ፡
ይዞ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዮርዳኖስን ፡ ቢሻ
ገር ፥ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ትመለሳላችሁ ፤ በእግዚ ፲፱
አብሔርም ፡ ፊት ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ንጹ
ሕን ፡ ትሆናላችሁ ፤ ይህች ፡ ምድርም ፡ በእግ
ዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ርስት ፡ ትሆንላችኋለች ።
እናንተ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ባታደርጉ ፥ እነሆ ፥ ፳፫
እግዚአብሔርን ፡ ትበደላላችሁ ፤ ኃጢአታች
ሁም ፡ እንዳያገኛችሁ ፡ እወቁ ። ለልጆቻችሁ ፡ ፳፬
ከተሞች ፥ ለበጎቻችሁም ፡ በረቶች ፡ ሥሩ ፤
ከአፋችሁም ፡ የወጣውን ፡ ነገር ፡ አድርጉ ።

፳፭ የጋድና ፡ የሮቤልም ፡ ልጆች ፡ ሙሴን ፡ እን
ዲህ ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ፦ እኛ ፡ ባሪያዎችህ ፡
ጌታችን ፡ እንዳዘዘ ፡ እናደርጋለን ። ልጆቻችን ፥ ፳፮
ሚስቶቻችንም ፥ መንጎቻችንም ፥ እንስሶቻች
ንም ፡ ሁሉ ፡ በዚያ ፡ በገለዓድ ፡ ከተሞች ፡ ይሆ
ናሉ ፤ እኛ ፡ ባሪያዎችህ ፡ ግን ፡ ሁላችን ፡ ጋሻ ፡ ፳፯
ጦሩችንን ፡ ይዘን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡
ጌታችን ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ እንሄ
ዳለን ።

፳፰ ሙሴም ፡ ካህኑን ፡ አልዓዛርን ፡ የነዌንም ፡
ልጅ ፡ ኢያሱን ፡ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡
አለቆች ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ አዘዘ ። ሙሴም ፦ ፳፱
የጋድና ፡ የሮቤል ፡ ልጆች ፡ ሁላቸው ፡ ጋሻ ፡
ጦራቸውን ፡ ይዘው ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ በእግዚ
አብሔር ፡ ፊት ፡ ዮርዳኖስን ፡ ቢሻገሩ ፥ ምድሪ
ቱንም ፡ ድል ፡ ብትኑሙ ፥ የገለዓድን ፡ ምድር ፡
ርስት ፡ አድርጋችሁ ፡ ትሰጡአቸዋላችሁ ። ጋሻ ፡ ፴
ጦራቸውን ፡ ይዘው ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ባይሻ
ገሩ ፡ ግን ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ በእናንተ ፡ መካ
ከል ፡ ርስታቸውን ፡ ይወርሳሉ ፡ አላቸው ። የጋ ፴፩
ድና ፡ የሮቤልም ፡ ልጆች ፡ መልሰው ፦ እግዚ
አብሔር ፡ ለእኛ ፡ ለባሪያዎችህ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡
እንዲሁ ፡ እናደርጋለን ። ጋሻ ፡ ጦራችንን ፡ ፴፪
ይዘን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ከነዓን ፡
ምድር ፡ እንሻገራለን ፥ ከዮርዳኖስም ፡ ማዶ ፡
ከወዳሁ ፡ የወረስነው ፡ ርስት ፡ ይሆንልናል ፡
አሉት ።

፴፫ ሙሴም ፡ ለጋድና ፡ ለሮቤል ፡ ልጆች ፡ ለዮሴ
ፍም ፡ ልጅ ፡ ለምናሴ ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ የአ

ሞራውያንን ፡ ንጉሥ ፡ የሴዎንን ፡ ግዛት ፡ የባሳ
ንንም ፡ ንጉሥ ፡ የዐግን ፡ ግዛት ፥ ምድሪቱንና ፡
በዙሪያዋ ፡ ያሉትን ፡ ከተሞች ፡ ሰጣቸው ።
፴፬-፴፱ የጋድም ፡ ልጆች ፡ ዲቦንን ፥ አጣሮትን ፥ አሮዔ
ርን ፥ ዓጥሮትሾፋንን ፥ ኢያዜርን ፥ ዮግብሃን ፥
ቤትኒምራን ፤ ቤትሃራንን ፡ የተመሸጉ ፡ ከተ
ሞች ፡ አድርገው ፡ ሠሩ ፤ የበጎችን ፡ በረቶችንም ፡
ሠሩ ። የሮቤልም ፡ ልጆች ፡ ሐሴበንን ፥ ኤልያ
ሊን ፥ ቂርያታይምን ፥ ስማቸውም ፡ የተለወጠ
ውን ፡ ናባውን ፥ በአልሜዎንን ፥ ሴብማን ፡
ሠሩ ፤ አነዚህንም ፡ የሠሩአቸውን ፡ ከተሞች ፡
በሰሓ ፡ ስም ፡ ጠሩአቸው ። የምናሴም ፡ ልጅ ፡
የማኪር ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ገለዓድ ፡ ሄዱ ፥ ወሰ
ዱአትም ፥ በእርስዋም ፡ የነበሩትን ፡ አሞራው
ያንን ፡ አሳደዱ ። ሙሴም ፡ ለምናሴ ፡ ልጅ ፡
ለማኪር ፡ ገለዓድን ፡ ሰጠ ፤ በእርስዋም ፡ ተቀ
መጠ ። የምናሴም ፡ ልጅ ፡ ኢያዕር ፡ ሄዶ ፡ መን
ደሮችዋን ፡ ወሰደ ፥ የአኢያዕርም ፡ መንደሮች ፡
ብሎ ፡ ጠራቸው ። ኖባህም ፡ ሄዶ ፡ ቄናትንም ፡
መንደሮችዋንም ፡ ወሰደ ፥ በስሙም ፡ ኖባህ ፡
ብሎ ፡ ጠራቸው ።

ምዕራፍ ፡ ፴፫ ።

፩ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ጉዞ ፡ ከሙሴና ፡ ከአ
ሮን ፡ እጅ ፡ በታች ፡ በሠራዊታቸው ፡ ከግብፅ ፡
በወጡ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ነበረ ። ሙሴም ፡ በእ
ግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ እንደ ፡ ጉዞአቸው ፡ አወ
ጣጣቸውን ፡ ጻፈ ፤ እንደ ፡ አወጣጣቸውም ፡
ጉዞአቸው ፡ እንዲህ ፡ ነበረ ። በመጀመሪያው ፡
ወር ፡ ከወሩም ፡ በአሥራ ፡ አምስተኛው ፡ ቀን ፡
ከራምሴ ፡ ተጓዙ ፤ ከፋሲካ ፡ በኋላ ፡ በነጋው ፡
የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ግብፃውያን ፡ ሁሉ ፡ እያዩ ፡
ከፍ ፡ ባለች ፡ እጅ ፡ ወጡ ። በዚያም ፡ ጊዜ ፡
ግብፃውያን ፡ እግዚአብሔር ፡ የገደላቸውን ፡
በኵሮቻቸውን ፡ ይቀብሩ ፡ ነበር ፤ በአማልክቶ
ቻቸውም ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈረደበ
ቸው ።

የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከራምሴ ፡ ተጉዘው ፡
በሱኮት ፡ ሰፈሩ ። ከሱኮትም ፡ ተጉዘው ፡ በም
ድረ ፡ በዳ ፡ ዳርቻ ፡ ባለች ፡ በኤታም ፡ ሰፈሩ ።
ከኤታምም ፡ ተጉዘው ፡ በበአልዛፎን ፡ ፊት ፡
ወደ ፡ ነበረች ፡ ወደ ፡ ፈሀሒሮት ፡ ተመለሱ ፡
በሚግዶልም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሰፈሩ ። ከፈሀሒ
ሮትም ፡ ተጉዘው ፡ በባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡
ምድረ ፡ በዳ ፡ አለፉ ፥ በኤታምም ፡ በረዘ ፡ የሦ
ስት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ሄዱው ፡ በማራ ፡ ሰፈሩ ።
ከማራም ፡ ተጉዘው ፡ ወደ ፡ ኤሊም ፡ መጡ ፤
በኤሊምም ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ የውኃ ፡ ምንጮች ፡
ሰባ ፡ ዘንባባዎችም ፡ ነበሩ ። በዚያም ፡ ሰፈሩ ።
ከኤሊምም ፡ ተጉዘው ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡
ዳር ፡ ሰፈሩ ። ከኤርትራም ፡ ባሕር ፡ ተጉዘው ፡
በሲን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሰፈሩ ። ከሲን ፡ ምድረ ፡
በዳም ፡ ተጉዘው ፡ በራፋቃ ፡ ሰፈሩ ። ከራፋ
ቃም ፡ ተጉዘው ፡ በኤሉስ ፡ ሰፈሩ ። ከኤሉስም ፡
ተጉዘው ፡ በራፊዲም ፡ ሰፈሩ ፤ በዚያም ፡ ሕዝቡ ፡
የሚጠጣት ፡ ውኃ ፡ አልነበረም ። ከራፊዲምም ፡ ፲፫
ተጉዘው ፡ በሲና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሰፈሩ ። ከሲ ፲፬
ናም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ተጉዘው ፡ በምኖት ፡ መቃ
ብር ፡ ሰፈሩ ። ከምኖት ፡ መቃብርም ፡ ተጉዘው ፡ ፲፭
በሐጼሮት ፡ ሰፈሩ ። ከሐጼሮትም ፡ ተጉዘው ፡ ፲፮
በሪትማ ፡ ሰፈሩ ። ከሪትማም ፡ ተጉዘው ፡ በሬ ፲፯
ሞን ፡ ዘፋሬስ ፡ ሰፈሩ ። ከሬሞን ፡ ዘፋሬስም ፡
ተጉዘው ፡ በልብና ፡ ሰፈሩ ። ከልብናም ፡ ተጉ ፲፰
ዘው ፡ በረሳ ፡ ሰፈሩ ። ከረሳም ፡ ተጉዘው ፡ በቀ ፲፱
ሄላታ ፡ ሰፈሩ ። ከቀሄላታም ፡ ተጉዘው ፡ በሻ ፲፫
ፍር ፡ ተራራ ፡ ሰፈሩ ። ከሻፍር ፡ ተራራም ፡ ተጉ ፲፱
ዘው ፡ በሖራዳ ፡ ሰፈሩ ። ከሖራዳም ፡ ተጉዘው ፡ ፲፰
በመቅሄሎት ፡ ሰፈሩ ። ከመቅሄሎትም ፡ ተጉ ፲፯
ዘው ፡ በታሐት ፡ ሰፈሩ ። ከታሐትም ፡ ተጉዘው ፡ ፲፮
በታራ ፡ ሰፈሩ ። ከታራም ፡ ተጉዘው ፡ በሚ ፲፭
ትቃ ፡ ሰፈሩ ። ከሚትቃም ፡ ተጉዘው ፡ በሐሽ ፲፬
ሞና ፡ ሰፈሩ ። ከሐሽሞናም ፡ ተጉዘው ፡ በሞሴ ፡ ፲
ሮት ፡ ሰፈሩ ። ከሞሰሮትም ፡ ተጉዘው ፡ በብኔ ፡ ፱
ያዕቃን ፡ ሰፈሩ ። ከብኔያዕቃንም ፡ ተጉዘው ፡ ፰
በሖረሃጊድጋድ ፡ ሰፈሩ ። ከሖረሃጊድጋድም ፡ ፯
ተጉዘው ፡ በዮጥባት ፡ ሰፈሩ ። ከዮጥባትም ፡ ፮
ተጉዘው ፡ በዔብሮና ፡ ሰፈሩ ። ከዔብሮናም ፡ ፭
ተጉዘው ፡ በዓጽዮንጋብር ፡ ሰፈሩ ። ከዓጽዮ ፡ ፬
ንጋብርም ፡ ተጉዘው ፡ በጺን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡
ሰፈሩ ፤ ይህችም ፡ ቃዴስ ፡ ናት ። ከቃዴስም ፡ ፳
ተጉዘው ፡ በኤዶምያስ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡ በሰው ፡
በሖር ፡ ተራራ ፡ ሰፈሩ ።

ካህኑም ፡ አሮን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ፳፪
ወደ ፡ ሖር ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፥ በዚያም ፡ የእ
ስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከግብፅ ፡ ምድር ፡ ከወጡ ፡
በኋላ ፡ በአርባኛው ፡ ዓመት ፡ በአምስተኛው ፡
ወር ፡ ከወሩም ፡ በመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ ሞተ ።
፳፫ አሮንም ፡ በሖር ፡ ተራራ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ዕድ ፡
ሜው ፡ መቶ ፡ ሃያ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ነበረ ።
፳፬ በከነዓን ፡ ምድርም ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ተቀ
ምጦ ፡ የነበረው ፡ ከነዓናዊው ፡ የዓራድ ፡ ንጉሥ ፡
የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ መጡ ፡ ሰማ ።
፳፭ እነርሱም ፡ ከሖር ፡ ተራራ ፡ ተጉዘው ፡ በሴል
ሞና ፡ ሰፈሩ ። ከሴልሞናም ፡ ተጉዘው ፡ በፉ ፳፮
ኖን ፡ ሰፈሩ ። ከፉኖንም ፡ ተጉዘው ፡ በአቦት ፡
ሰፈሩ ። ከአቦትም ፡ ተጉዘው ፡ በሞዓብ ፡ ዳርቻ ፡ ፳፯
ባለው ፡ በጋይ ፡ ሰፈሩ ። ከጋይም ፡ ተጉዘው ፡
በዲቦንጋድ ፡ ሰፈሩ ። ከዲቦንጋድም ፡ ተጉዘው ፡ ፳፰
በዓልሞንዲብላታይም ፡ ሰፈሩ ። ከዓልሞንዲ ፡ ፳፱
ብላታይምም ፡ ተጉዘው ፡ በናባው ፡ ፊት ፡
ባሉት ፡ በዓብሪም ፡ ተራሮች ፡ ላይ ፡ ሰፈሩ ። ፴
ከዓብሪምም ፡ ተራሮች ፡ ተጉዘው ፡ በዮርዳኖስ ፡ ፴፩
አጠገብ ፡ በኢያሪኮ ፡ ፊት ፡ ባለው ፡ በሞዓብ ፡
ሜዳ ፡ ላይ ፡ ሰፈሩ ። በዮርዳኖስም ፡ አጠገብ ፡ ፴፪
በሞዓብ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ከቤትየሺሞት ፡ እስከ ፡
አቤልሰጢም ፡ ድረስ ፡ ሰፈሩ ።

፴፫ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ በዮርዳኖስ ፡ አጠ
ገብ ፡ በኢያሪኮ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በሞዓብ ፡ ሜዳ ፡

ዘፍ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፡ — ለእስራኤል ፡
ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ንገራቸው ፡ — ወደ ፡
ከነዓን ፡ ምድር ፡ ዮርዳኖስን ፡ በተሻገራችሁ ፡
ጊዜ ፡ የአገሩን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ከፊታችሁ ፡
ታሳድዳላችሁ ፥ የተቀረጹትንም ፡ ድንጋዮቻቸ
ውን ፡ ሁሉ ፡ ታጠፋላችሁ ፥ ቀልጠው ፡ የተሠ
ሩትንም ፡ ምስሎቻቸውን ፡ ሁሉ ፡ ታጠፋላችሁ ፥
በከረብታ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መስገጃዎቻቸውንም ፡
ታፈርሳላችሁ ፤ ምድሪቱንም ፡ ለእናንተ ፡ ርስት ፡
አድርጌ ፡ ሰጥቼአችኋለሁና ፡ ምድሪቱን ፡ ትወር
ሱአታላችሁ ፤ ትቀመጡበታላችሁም ። ምድ
ሪቱንም ፡ በየወገኖቻችሁ ፡ በዕጣ ፡ ትወርሳላ
ችሁ ፤ ለብዙዎች ፡ እንደ ፡ ብዛታቸው ፡ ለጥቂ
ቶቹም ፡ እንደ ፡ ጥቂትነታቸው ፡ መጠን ፡ ርስ
ትን ፡ ትሰጣላችሁ ፤ እያንዳንዱ ፡ ሁሉ ፡ ዕጣ ፡
እንደ ፡ ወደቀለት ፡ በዚያ ፡ ርስቱ ፡ ይሆናል ፤
በየአባቶቻችሁ ፡ ነገዶች ፡ ትወርሳላችሁ ። የአ
ገሩንም ፡ ሰዎች ፡ ከፊታችሁ ፡ ባታሳድዱ ፥ ያስ
ቀራችኋቸው ፡ ለዓይናችሁ ፡ እንደ ፡ እሾህ ፡ ለጎ
ናችሁም ፡ እንደሚወጋ ፡ ነገር ፡ ይሆኑባችኋል ፥
በምትቀመጡባትም ፡ ምድር ፡ ያስጨንቁአች
ኋል ። እኔም ፡ በእነርሱ ፡ አደርገው ፡ ዘንድ ፡
ያሰብሁትን ፡ በእናንተ ፡ አደርግባችኋለሁ ።

ምዕራፍ ፴፪ ።

፩ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
፪ ተናገረው ፡ — የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡
ብለህ ፡ እዘዛቸው ፡ — ወደ ፡ ከነዓን ፡ ምድር ፡
በገባችሁ ፡ ጊዜ ፥ ርስት ፡ ትሆናችሁ ፡ ዘንድ ፡
በዕጣ ፡ የምትደርሳችሁ ፡ ምድር ፥ በዳርቻዋ ፡
ያለች ፡ የከነዓን ፡ ምድር ፥ ይህ ፡ ናት ፤ የደቡቡ ፡
ወገን ፡ ከጺን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በኤዶምያስ ፡ በኩል ፡
ይሆናል ፤ የደቡቡም ፡ ዳርቻ ፡ ከጨው ፡ በሕር ፡
፫ ዳር ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ይጀምራል ፤ ዳር
ቻችሁም ፡ በአቅረቢም ፡ ዐቀበት ፡ በደቡብ ፡
በኩል ፡ ይዘራል ፡ ወደ ፡ ጺንም ፡ ያልፋል ፤
መውጫውም ፡ በቃዴስ ፡ በርኔ ፡ በደቡብ ፡
በኩል ፡ ይሆናል ፤ ወደ ፡ ሐጸርአዳር ፡ ይጐዳል ፤
፬ ወደ ፡ ዓጽሞንም ፡ ያልፋል ፤ ዳርቻውም ፡ ከዓ
ጽሞን ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ወንዝ ፡ ይዘራል ፥ መው
ጫውም ፡ በባሕሩ ፡ በኩል ፡ ይሆናል ።
፭ ለምዕራብም ፡ ዳርቻ ፡ ታላቁ ፡ በሕር ፡ ዳርቻ
ችሁ ፡ ይሆናል ፤ ይህ ፡ የምዕራብ ፡ ዳርቻችሁ ፡
ይሆናል ።
፮ የሰሜንም ፡ ዳርቻችሁ ፡ ይህ ፡ ይሆናል ፤ ከታ
ላቁ ፡ በሕር ፡ ወደ ፡ ሖር ፡ ተራራ ፡ ምልክት ፡
፯ ታመለክታላችሁ ፤ ከሖርም ፡ ተራራ ፡ ወደ ፡
ሐማት ፡ መግቢያ ፡ ምልክት ፡ ታመለክታላችሁ ፡
የዳርቻውም ፡ መውጫ ፡ በጽዳድ ፡ ይሆናል ፤
፰ ዳርቻውም ፡ ወደ ፡ ዚፍሮን ፡ ያልፋል ፡ እስከ ፡
ሐጸርዔኖንም ፡ ድረስ ፡ ይወጣል ፤ ይህ ፡ የሰ
ሜን ፡ ዳርቻችሁ ፡ ይሆናል ።
፱ የምሥራቁንም ፡ ዳርቻችሁን ፡ ከሐጸርዔኖን ፡
ወደ ፡ ሴፋማ ፡ ዓ ልክት ፡ ታመለክታላችሁ ፤
ዳርቻውም ፡ ከሴፋማ ፡ በዓይን ፡ ምሥራቅ ፡
ወዳለው ፡ ወደ ፡ ሪብላ ፡ ይወርዳል ፤ እስከ ፡ ኪኔ
ሬት ፡ የባሕር ፡ ወሽመጥ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡
ይደርሳል ፤ ዳርቻውም ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ይወ
ርዳል ፥ መውጫውም ፡ በጨው ፡ ባሕር ፡ ይሆ
ናል ። ምድራችሁ ፡ እንደ ፡ ዳርቻዋ ፡ በዙሪያዋ ፡
ይህች ፡ ናት ።
፲ ሙሴም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡
ብሎ ፡ አዘዛቸው ፡ — እግዚአብሔር ፡ ለዘጠኝ ፡
ነገድ ፡ ተኩል ፡ ይሰጡአቸው ፡ ዘንድ ፡ ያዘዘ ፡
በዕጣ ፡ የምትወርሱአት ፡ ምድር ፡ ይህች ፡ ናት ፤
የሮቤልም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ በየአባቶቻቸው ፡
፲፩ ቤት ፥ የጋድም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ በየአባቶቻ
ቸው ፡ ቤት ፥ የምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡
ርስታቸውን ፡ ወርሰዋል ። እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ነገ
፲፪ ድና ፡ የአንዱ ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ርስታቸውን ፡
በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በኢያሪኮ ፡ አንጻር ፡ በምሥ
ራቅ ፡ በኩል ፡ ወረሱ ።
፲፫ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
ተናገረው ፡ — ምድሪቱን ፡ ርስት ፡ አድርገው ፡
፲፬ የሚከፍሉላችሁ ፡ ሰዎች ፡ ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፤
ካህኑ ፡ አልዓዛርና ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ። ምድ
፲፭ ሪቱንም ፡ ርስት ፡ አድርገው ፡ ይከፍሉ ፡ ዘንድ ፡
ከየነገዱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡ ትወስዳላችሁ ።
የሰዎቹም ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡
፲፱ የዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ካሌብ ፥ ከስምዖን ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡
፳ የዓሚሁድ ፡ ልጅ ፡ ሰሚኤል ፥ ከብንያም ፡
፳፩ ነገድ ፡ የኪስሎን ፡ ልጅ ፡ ኤልዳድ ፥ ከዳን ፡
፳፪ ልጆች ፡ ነገድ ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡ የዮግሊ ፡ ልጅ ፡
ቡቂ ፥ ከዮሴፍም ፡ ልጆች ፡ ከምናሴ ፡ ልጆች ፡
፳፫ ነገድ ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡ የሱፊ ፡ ልጅ ፡ አኒኤል ፥
ከኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡ የሺ
፳፬ ፍጣን ፡ ልጅ ፡ ቀሙኤል ፥ ከዛብሎን ፡ ልጆች ፡
፳፭ ነገድ ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡ የፈርናክ ፡ ልጅ ፡ ኤሊሳ
ፌን ፥ ከይሳኮር ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡
፳፮ የሐዛ ፡ ልጅ ፡ ፈልጢኤል ፥ ከአሴር ፡ ልጆች ፡
፳፯ ነገድ ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡ የሴሌሚ ፡ ልጅ ፡ አሒ
ሁድ ፥ ከንፍታሌም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ አንድ ፡
፳፰ አለቃ ፡ የዓሚሁድ ፡ ልጅ ፡ ፈዳሄል ። እግዚአ
ብሔር ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡
ርስታቸውን ፡ ይከፍሉ ፡ ዘንድ ፡ ያዘዛቸው ፡ እን
ዚህ ፡ ናቸው ።

ምዕራፍ ፴፫ ።

፩ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ በዮርዳኖስ ፡ አጠ
ገብ ፡ በኢያሪኮ ፡ አንጻር ፡ በሞዓብ ፡ ሜዳ ፡ እን
ዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፡ — ሴዋውያን ፡ የሚቀመ
፪ ጡባቸውን ፡ ከተሞች ፡ ከርስታቸው ፡ ይሰጡ ፡
ዘንድ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እዘዛቸው ፡ በከ
ተሞቹም ፡ ዙሪያ ፡ ያለውን ፡ መሰምርያ ፡ ለሴዋ
ውያን ፡ ስጡ ። እነርሱም ፡ በከተሞቹ ፡ ውስጥ ፡
፫ ይቀመጣሉ ፤ መሰምርያቸውም ፡ ለከብቶቻቸው ፡
ለእንስሶቻቸውም ፡ ለእነርሱም ፡ ላለው ፡ ሁሉ ፡
ይሁን ። ለሴዋውያንም ፡ የምትሰጡት ፡ የከ
፬ ተማ ፡ መሰምርያ ፡ በከተማው ፡ ዙሪያ ፡ ከቅጥሩ ፡
ወደ ፡ ውጭ ፡ አንድ ፡ ሺህ ፡ ክንድ ፡ ይሁን ።
፭ ከከተማው ፡ ውጭ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ሁለት ፡
ሺህ ፡ ክንድ ፥ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡
ክንድ ፥ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ክንድ ፥
በሰሜንም ፡ በኩል ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ክንድ ፡ ትስ
ነዳላችሁ ፥ ከተማውም ፡ በመካከል ፡ ይሆናል ፤
ይህም ፡ የከተሞቹ ፡ መሰምርያ ፡ ይሆንላቸዋል ።
፮ ለሴዋውያንም ፡ የምትሰጡአቸው ፡ ስድስቱ ፡
የመማፀኛ ፡ ከተሞች ፡ ናቸው ፤ እነርሱም ፡ ነፍሰ ፡
ገዳይ ፡ ይሸሽባቸው ፡ ዘንድ ፡ የምትሰጡአቸው ፡
ናቸው ፤ ከእነዚህም ፡ ሴላ ፡ አርባ ፡ ሁለት ፡ ከተ
፯ ሞች ፡ ትሰጣላችሁ ። ለሴዋውያን ፡ የምትሰጡ
አቸው ፡ ከተሞች ፡ ሁሉ ፡ አርባ ፡ ስምንት ፡ ከተ
ሞች ፡ ይሆናሉ ፤ ከመሰምርያቸው ፡ ጋር ፡ ትሰ
ጡአቸዋላችሁ ። ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡
ለሴዋውያን ፡ የምትሰጡአቸውን ፡ ከተሞች ፡
እንዲሁ ፡ ስጡ ፤ ከብዙዎቹ ፡ ብዙ ፥ ከጥቂቶቹ ፡
ጥቂት ፡ ትወስዳላችሁ ፤ እያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ ወረ
ሱት ፡ እንደ ፡ ርስታቸው ፡ መጠን ፡ ከከተሞቻ
ቸው ፡ ለሴዋውያን ፡ ይሰጣሉ ።
፱ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
፲ ተናገረው ፡ — ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡
ብለህ ፡ ንገራቸው ፡ — ወደ ፡ ከነዓን ፡ ምድር ፡ ዮር
ዳኖስን ፡ በተሻገራችሁ ፡ ጊዜ ፥ በስሕተት ፡ ነፍስ ፡
፲፩ የገደለ ፡ ወደዚያ ፡ ይሸሽ ፡ ዘንድ ፡ የመማፀኛ ፡
ከተሞች ፡ እንዲሆኑላችሁ ፡ ከተሞችን ፡ ለእና
፲፪ ንተ ፡ ለዩ ። ነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡ በማኅበሩ ፡ ፊት ፡ ለፍ
ርድ ፡ እስኪቆም ፡ ድረስ ፡ እንዳይሞት ፥ ከተ
ሞቹ ፡ ከደም ፡ ተበቃዩ ፡ የመማፀኛ ፡ ከተሞች ፡
ይሁኑላችሁ ። የምትሰጡአቸውም ፡ ስድስቱ ፡
ከተሞች ፡ የመማፀኛ ፡ ከተሞች ፡ ይሁኑላችሁ ።
፲፫ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ሦስት ፡ ከተሞች ፡ ትሰጣላ
ችሁ ፥ በከነዓንም ፡ ምድር ፡ ሦስት ፡ ከተሞች ፡
ትሰጣላችሁ ፤ የመማፀኛ ፡ ከተሞች ፡ ይሆናሉ ።
፲፬ በስሕተት ፡ ነፍስ ፡ የገደለ ፡ ይሸሽበት ፡ ዘንድ ፡
እነዚህ ፡ ስድስት ፡ ከተሞች ፡ ለእስራኤል ፡
ልጆች ፡ በመካከላቸው ፡ ለሚቀመጡ ፡ እንግዶ
ችና ፡ መጻተኞች ፡ መማፀኛ ፡ ይሆናሉ ።
፲፭ በብረት ፡ መሣርያ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ቢመ
ታው ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ነው ፤ ነፍሰ ፡ ገዳዩም ፡
፲፮ ፈጽሞ ፡ ይገደል ። ሰውም ፡ በሚሞትበት ፡
በእጁ ፡ ባለው ፡ ድንጋይ ፡ ቢመታው ፡ የተመ
ታውም ፡ ቢሞት ፥ እርሱ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ነው ፤
፲፯ ነፍሰ ፡ ገዳዩም ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ። ሰውም ፡
በሚሞትበት ፡ በእጁ ፡ ባለው ፡ በእንጨት ፡
መሣርያ ፡ ቢመታው ፡ የተመታውም ፡ ቢሞት ፥
እርሱ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ነው ፤ ነፍሰ ፡ ገዳዩም ፡
፲፰ ፈጽሞ ፡ ይገደል ። ደም ፡ ተበቃዩ ፡ ራሱ ፡
ነፍሰ ፡ ገዳዩን ፡ ይገደል ፤ በገኘው ፡ ጊዜ ፡ ይግ
ደለው ። እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ በጥላቻ ፡ ቢደ
ፋው ፥ ወይም ፡ ሽምቆ ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ ቢጥል
፲፱ በት ፥ ወይም ፡ በጥላቻ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡
በእጁ ፡ ቢመታው ፥ የመታው ፡ ፈጽሞ ፡ ይገ

ደል ፤ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ነው ፤ ደም ፡ ተበቃዩ ፡ በገ
ኘው ፡ ጊዜ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩን ፡ ይግደለው ።
፳ ነገር ፡ ግን ፡ ያለ ፡ ጥላቻ ፡ ድንገት ፡ ቢደፋው ፥ ፳፪
ሳይሸምቅም ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ ቢጥልበት ፥
ወይም ፡ ሳያየው ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ሰው ፡ የሚ ፳፫
ሞትበትን ፡ ድንጋይ ፡ ቢጥልበት ፥ ጠላቱም ፡
ባይሆን ፥ ክፉም ፡ ያደርግበት ፡ ዘንድ ፡ ባይሻ ፥
ማኅበሩ ፡ በመቸውና ፡ በደም ፡ ተበቃዩ ፡ መካ ፳፬
ከል ፡ ፍርድን ፡ እንደዚሁ ፡ ይፍረድ ፤ ማኅበ ፳፭
ሩም ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩን ፡ ከደም ፡ ተበቃዩ ፡ እጅ ፡
ያድነዋል ፥ ማኅበሩም ፡ ወደ ፡ ሸሸበት ፡ ወደ ፡
መማፀኛው ፡ ከተማ ፡ ይመልሰዋል ፤ በቅዱስ ፡
ዘይትም ፡ የተቀባው ፡ ዋነኛው ፡ ካህን ፡ እስኪ
ሞት ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ይቀመጣል ። ነፍሰ ፡ ፳፮
ገዳዩ ፡ ግን ፡ ከሸሸበት ፡ ከመማፀኛው ፡ ከተማ ፡
ዳርቻ ፡ ቢወጣ ፥ ደም ፡ ተበቃዩም ፡ ከመማፀ ፳፯
ኛው ፡ ከተማ ፡ ዳርቻ ፡ ውጭ ፡ ቢያገኘው ፥ ደም ፡
ተበቃዩም ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩን ፡ ቢገድለው ፥ የደም ፡
ዕዳ ፡ አይሆንበትም ፤ ዋነኛው ፡ ካህን ፡ እስኪ ፳፰
ሞት ፡ ድረስ ፡ በመማፀኛው ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡
መቀመጥ ፡ ይገባው ፡ ነበርና ። ዋነኛው ፡ ካህን ፡
ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡ ወደ ፡ ርስቱ ፡
ምድር ፡ ይመለሳል ።
፳፱ እነዚህም ፡ ነገሮች ፡ ለልጅ ፡ ልጃችሁ ፡ በማደሪ ፳፱
ያችሁ ፡ ሁሉ ፡ ሥርዓትና ፡ ፍርድ ፡ ይሁኑላችሁ ።
ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ሁሉ ፡ በምስክሮች ፡ አፍ ፡ ይገደ ፳፩
ላል ፤ በአንድ ፡ ምስክር ፡ ግን ፡ ማናቸውንም ፡
ሰው ፡ መግደል ፡ አይገባም ። ሞት ፡ የተፈረደ ፳፪
በትን ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩንም ፡ ለማዳን ፡ የነፍስ ፡
ዋጋ ፡ አትቀበሉ ፤ እርሱ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ።
ዋነኛው ፡ ካህን ፡ ሳይሞት ፡ ወደ ፡ ምድሩ ፡ ይመ ፳፫
ለስ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ መማፀኛው ፡ ከተማ ፡ ከሸ
ሸው ፡ የነፍስ ፡ ዋጋ ፡ አትቀበሉ ። ደም ፡ ምድ ፳፬
ሪቱን ፡ ያረከሳታልና ፤ የምትኖሩበትን ፡ ምድር ፡
አታርክሱአት ፤ በደም ፡ አፍሰሹ ፡ ደም ፡ ካልሆነ ፡
በቀር ፡ ምድሪቱ ፡ ከፈሰሰበት ፡ ደም ፡ አትነጻም ።
እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካ ፳፭
ከል ፡ አድራለሁና ፤ የምትኖሩበትን ፡ በመካከል
ዋም ፡ የማድርበትን ፡ ምድር ፡ አታርክሱአት ።

ምዕራፍ ፴፮ ።

፩ ከዮሴፍ ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ የምናሴ ፡ ልጅ ፡
የማኪር ፡ ልጅ ፡ የገለዓድ ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ አለ
ቆች ፡ ቀረቡ ፥ በሙሴና ፡ በእስራኤልም ፡ ልጆች ፡
አለቆች ፡ ፊት ፡ ተናገሩ ፤ አሉም ፡ — ፪
ምድሪቱን ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ አድ
ርገህ ፡ በዕጣ ፡ ከፍለህ ፡ ትሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ አንተን ፡ ጌታችንን ፡ አዘዘህ ፤ እግ
ዚአብሔርም ፡ የወንድማችንን ፡ የሰለጰዳድን ፡
ርስት ፡ ለሴቶች ፡ ልጆቹ ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ፡ አን
ተን ፡ ጌታችንን ፡ አዘዘ ። ከሌላም ፡ ከእስራኤል ፡ ፫
ልጆች ፡ ነገድ ፡ ባል ፡ ቢያገቡ ፥ ርስታቸው ፡ ከአ
ባቶቻችን ፡ ርስት ፡ ይነቀላል ፥ እነርሱም ፡ ለሚ
ሆኑበት ፡ ለሌላው ፡ ነገድ ፡ ርስት ፡ ይጨመራል ፤

ዘዳ ፴፪ ፡ ፲ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ፡ ፳፬ ፡ ፳፭ ፡ ፳፮ ፡ ፳፯ ፡ ፳፰ ፡ ፳፱ ፡ ፴ ፡ ፴፩ ፡ ፴፪ ፡ ፴፫ ፡ ፴፬ ፡ ፴፭ ፡ ፴፮ ፡ ፴፯ ፡ ፴፰ ፡ ፴፱ ፡ ፵ ፡ ፵፩ ፡ ፵፪ ፡ ፵፫ ፡ ፵፬ ፡ ፵፭ ፡ ፵፮ ፡ ፵፯ ፡ ፵፰ ፡ ፵፱ ፡ ፶ ፡ ፶፩ ፡ ፶፪ ፡ ፶፫ ፡ ፶፬ ፡ ፶፭ ፡ ፶፮ ፡ ፶፯ ፡ ፶፰ ፡ ፶፱ ፡ ፷ ፡ ፷፩ ፡ ፷፪ ፡ ፷፫ ፡ ፷፬ ፡ ፷፭ ፡ ፷፮ ፡ ፷፯ ፡ ፷፰ ፡ ፷፱ ፡ ፸ ፡ ፸፩ ፡ ፸፪ ፡ ፸፫ ፡ ፸፬ ፡ ፸፭ ፡ ፸፮ ፡ ፸፯ ፡ ፸፰ ፡ ፸፱ ፡ ፹ ፡ ፹፩ ፡ ፹፪ ፡ ፹፫ ፡ ፹፬ ፡ ፹፭ ፡ ፹፮ ፡ ፹፯ ፡ ፹፰ ፡ ፹፱ ፡ ፺ ፡ ፺፩ ፡ ፺፪ ፡ ፺፫ ፡ ፺፬ ፡ ፺፭ ፡ ፺፮ ፡ ፺፯ ፡ ፺፰ ፡ ፺፱ ፡ ፻ ፡ ፻፩ ፡ ፻፪ ፡ ፻፫ ፡ ፻፬ ፡ ፻፭ ፡ ፻፮ ፡ ፻፯ ፡ ፻፰ ፡ ፻፱ ፡ ፻፲ ፡ ፻፲፩ ፡ ፻፲፪ ፡ ፻፲፫ ፡ ፻፲፬ ፡ ፻፲፭ ፡ ፻፲፮ ፡ ፻፲፯ ፡ ፻፲፰ ፡ ፻፲፱ ፡ ፻፳ ፡ ፻፳፩ ፡ ፻፳፪ ፡ ፻፳፫ ፡ ፻፳፬ ፡ ፻፳፭ ፡ ፻፳፮ ፡ ፻፳፯ ፡ ፻፳፰ ፡ ፻፳፱ ፡ ፻፴ ፡ ፻፴፩ ፡ ፻፴፪ ፡ ፻፴፫ ፡ ፻፴፬ ፡ ፻፴፭ ፡ ፻፴፮ ፡ ፻፴፯ ፡ ፻፴፰ ፡ ፻፴፱ ፡ ፻፵ ፡ ፻፵፩ ፡ ፻፵፪ ፡ ፻፵፫ ፡ ፻፵፬ ፡ ፻፵፭ ፡ ፻፵፮ ፡ ፻፵፯ ፡ ፻፵፰ ፡ ፻፵፱ ፡ ፻፶ ፡ ፻፶፩ ፡ ፻፶፪ ፡ ፻፶፫ ፡ ፻፶፬ ፡ ፻፶፭ ፡ ፻፶፮ ፡ ፻፶፯ ፡ ፻፶፰ ፡ ፻፶፱ ፡ ፻፷ ፡ ፻፷፩ ፡ ፻፷፪ ፡ ፻፷፫ ፡ ፻፷፬ ፡ ፻፷፭ ፡ ፻፷፮ ፡ ፻፷፯ ፡ ፻፷፰ ፡ ፻፷፱ ፡ ፻፸ ፡ ፻፸፩ ፡ ፻፸፪ ፡ ፻፸፫ ፡ ፻፸፬ ፡ ፻፸፭ ፡ ፻፸፮ ፡ ፻፸፯ ፡ ፻፸፰ ፡ ፻፸፱ ፡ ፻፹ ፡ ፻፹፩ ፡ ፻፹፪ ፡ ፻፹፫ ፡ ፻፹፬ ፡ ፻፹፭ ፡ ፻፹፮ ፡ ፻፹፯ ፡ ፻፹፰ ፡ ፻፹፱ ፡ ፻፺ ፡ ፻፺፩ ፡ ፻፺፪ ፡ ፻፺፫ ፡ ፻፺፬ ፡ ፻፺፭ ፡ ፻፺፮ ፡ ፻፺፯ ፡ ፻፺፰ ፡ ፻፺፱ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱